አካህን የመውደድ ማሊሰጥር

ፀሓፊ፡- ዑስማን ኑሪ ቶፕባሽ
Osman Nuri Topbash

ትርጉም፡ - ሐሰን ታጁ
Translated by Hassen Taju

አሳታሚ
አልበያን ሊሚትድ

አላህን የመውደድ ምስጢር

በዑስማን ኑሪ ቶኘባሽ

ትርጉም፡- አህመድ ሁሴን (አቡ ቢላል)

አርትኦት፡- ሐሰን ታጁ

አሳታሚ፡- አልበያን ሊሚትድ

ስልክ ቁጥር ፡- 0913 87 87 88 ወይም 0911 19 98 22

<u>አዲስ አበባ ኢትዮጵያ</u>

የአሳታሚው መብት በሕግ
የተጠበቀ ነው።

All rights are reserved

አንደኛ እትም ሕዳር 2003

AFKAD

Addis Ababa Ethiopia

First Edition Nov.2010

ማውጫ

ርእስ	ገጽ
መግቢያ	5
ምዕራፍ አንድ	
አላህን የመውደድ ምስጢር	6
ምዕራፍ ሁለት	
ስብእናው የተሟላ ሰው	12
ምዕራፍ ሶስት	
በአላህ መንገድ ላይ መጽናት	19
ምዕራፍ አራት	
ከሷሊሆች እና ከእውነተኞች ጋር መሆን	28
ምዕራፍ አምስት	
መልካም ሥራን በቅንነት (ኢኽላስ) መስራት	32
ምዕራፍ ስድስት	
አላህን መፍራትና እዝነቱንም ተስፋ ማድረግ	43
ምዕራፍ ሰባት	
ግድየለሽነት	56
ምዕራፍ ስምንት	
ወደ አላህ መቃረብ	60
ምዕራፍ ዘጠኝ	
ሪዝቅ (ሲሳይ)	**73**
ምዕራፍ አሥር	
ብርሃንና ጨለማ	85
ምዕራፍ አስራ አንድ	
ኢህሳን (ማሳመር) እና ሙራቀባህ	98

ርእስ	ገጽ
ምዕራፍ አሥራ ሁለት	
የሰውን ልጅ የሚመለከቱ እውነታዎች	113
ምዕራፍ አሥራ ሦስት	
ከራስ ይልቅ ሌሎችን ማስቀደም (አል-ኢዛር)	119
ምዕራፍ አሥራ አራት	
ኢስላም ለሰው ልጆች ሕይወት ይለግሳል	131
ምዕራፍ አሥራ አምስት	
የጸባይ ታላቅነትና ውስጥን ማጽዳት	141
ምዕራፍ አሥራ ስድስት	
አላህንና መልእክተኛውን (ሰ.ዐ.ወ.) መውደድ	150

መግቢያ

በአላህ ስም እጅግ በጣም ሩህሩህ በጣም አዛኝ በሆነው

አላህን መውደድ የእምነት አስኳል፣ የበጎ ስራዎች ሁሉ መሠረት እንደሆነ በቁርአንና በሐዲስ ተገልጿል። መልእክተኛውን መውደድ ደግሞ አላህን የመውደድ መገለጫ ነው። አላህ በቁርአኑ የአማኞችን ባህሪ ሲገልጽ፡-

﴿ وَٱلَّذِينَ ءَامَنُوٓاْ أَشَدُّ حُبًّا لِّلَّهِۗ ﴾ البقرة: ١٦٥

‹‹እነዚያ ያመኑት ለአላህ የበረታ ፍቅር አላቸው፡፡›› (አል በቀራና 165)
አላህን የመውደድ ዋነኛ ማሣያ ነቢዩን መውደድና መከተል መሆኑን አላህ እንዲህ ሲል ይነግረናል፡፡

﴿ قُلۡ إِن كُنتُمۡ تُحِبُّونَ ٱللَّهَ فَٱتَّبِعُونِي يُحۡبِبۡكُمُ ٱللَّهُ وَيَغۡفِرۡ لَكُمۡ ذُنُوبَكُمۡۚ وَٱللَّهُ غَفُورٞ رَّحِيمٞ ﴾

‹‹አላህን የምትወዱ እንደሆናችሁ ተከተሉኝ፣ አላህ ይወዳችኋልና›› በል፡፡ (አል ኢምራን 31)
ነቢዩ ሙሐመድ እርሳቸውን ከንብረቱ፣ ከቤተሰቦቹና ከራሱም በላይ ያልወደደ ኢማኑ ሙሉ እንዳልሆነ ተናግረዋል፡፡
የዚህ ፍቅር ሚስጥር መላ ሕይወትን ይቀይራል፡፡ አእምሮን ያስተካክላል፡፡ ቀልብን ንጹህና ቅን ያደርጋል፡፡ ነፍስያን ይገራል፡፡ ይህ ሲሆን የሰውየው ባህሪ ፍጹም ይለወጣል፡፡ ለአላህም ለፍጡራኑም የሚመች ስብእና ይኖረዋል፡፡ ሁሉን አፍቃሪ፣ ለሁሉም ቅን አሳቢ፣ የአላህ ቤተሰቦች ለሆኑት አዛኝና ጠቃሚ ይሆናል፡፡
እንዲህ ዓይነት ስብእናዎች ሲበዙ አለም በፍቅር እና መተሳሰብ ትደምቃለች፡፡ ወንድም በወንድሙ ላይ የሚጨክንበት ሂደት ያበቃል፡፡
ቱርካዊው አሊም ሸኽ ዑስማን ኑሪ ቶኑባሽ የአላህን ፍቅር ትርጉምና መገለጫዎች በተዋበ ብዕርና የገለጻ ስልታቸው በዚህ መጽሐፍ ውስጥ አብራርተውልናል፡፡ ለትምህርታቸው ተጠቃሚ ያደርገን ዘንድ አላህን እንለምናለን፡፡

ሐሰን ታጁ
ሕዳር 2003

ምዕራፍ አንድ

አላህን የመውደድ ምስጢር

በሰማያትና በምድር እንዲሁም በመካከላቸው ያሉ ፍጡራንን ሁሉ ካልነበሩበት ያስገኘው አላህ የሰው ልጅን ሲፈጥር ድንቅና ይህ ይቀረዋል የማይባለውን ችሎታውን ተጠቅሞ ነው፡፡ ይህንንም ሲያደርግ ለታላቅ ዓላማ ሲሆን ይኸውም እርሱን እንደሚገባው አድርጎ እንዲገዛው ነው፡፡ የሰው ልጅ ይህን የተጻፈለትን ግብ ሲከውን ግን አቅሙ በፈቀደው ያክል ፍቅርን ለብሶ ቢያደርገው ይበልጥለታል፡፡

የዚህ ዓለም የመፈጠር ዋነኛው ግብም ለሚያማምሩና አይንን አፍዝዘው ለሚያስቀሩ ልምላሜ የሞላባቸው ሜዳዎች፣ ሸለቆዎች፣ ተራሮችና ወንዛወንዞች ታስቦ አይደለም፡፡ ይህ ሁሉ የሆነው በዓለም ላይ ሰፍሮ ከዘመናት የጊዜ ማህጸን ውስጥ ዝርያዎቹን እያባዛና እየበዛ ለመጣውና በፈጣሪው ሞገስ ለተቸረው ለሰው ልጅ ተብሎ ነው፡፡

እንግዲህ የፍጥረት ሁሉ አስገኚ የሆነው አላህ ይህን አለም ሲፈጥረውም ሆነ ሲያስተናብረው በታላቅ ፍቅርና እዝነቱ በማካበብ ነው፡፡ ይህን ምስጢር መርምሮ ለማግኘት ሊቅነትን የማይጠይቅ ሲሆን፣ ጊንጥ የፈለፈለቻቸውን አምሳያዎቿን በጀርባዋ አዝላ መታየቷን ማስተዋል ብቻ በቂ ነው፡፡

ይህ በፍቅርና በመተዛዘን ስሌት ላይ የመሠረተ የፍጡራን ዝንባሌ ይበልጥ ጎልቶ የሚታየው በክቡሩ የሰው ልጅ ስብእናና ማህበራዊ ተራክቦ መሆኑ ይበልጥ ያስደንቃል፡፡ የሆነ ሆኖ የው ዘር በዚህች ዓለም በሚቆይባቸው ዘመናቱ ብዙ ፈተናዎችንና የመከራ ቀንበሮችን መሸከም ቢኖርበትም እንኳ እነዚህን ሁሉ አበሳዎች የፈጣሪውን ውዴታና ፍቅር በመሻት እስከተጋፈጣቸው ድረስ ፈተናውን ወድቋል አይባልም፡፡ ምክንያቱም የሚከፈለው ምንዳ ታላቅ የሆነ የፍቅር መገለጫ ሲሆን ተከትሎት የሚመጣው ዘውታሪ ፀጋም አማላይ ነውና፡፡ የሰው ልጅ ልቦና ሲፈጠር ጽንፍ አልባ የሆነ የፍቅር ማህደር እንዲሆን ተደርጎ ነው፡፡ ይህ ተፈጥሮው ከተሟላ ደረጃ ላይ የሚደርሰው ዝንባሌው አላህን

ወደማፍቀር ካዘመመ ነው፡፡ ይህን ሳያደርግ ቀርቶ ስሜቱንና ደመነፍሱን ተከትሎ ባፈተተው የሚነጉድ ከሆነ ግን ሕይወቱ ትርጉም አልባ ጉዞዋን አገባድዳ በሃዘን ታሳርጋለች፡፡ በሌላ አገላለጽ ሰው የዘራውን ነውና የሚያጭደው በአላህና መልእክተኛው (ሰ.ዐ.ወ.) ፍቅር ልቡ ያጌጠና ይህንኑም በሕይወት ዘመናቱ በተግባር ለመግለጽ ደፋ ቀና ያለ በልፋቱና በድካሙ ልክ መልካም ምንዳውን ማግኘቱ አይቀሬ ነው - በአላህ እዝነት፡፡

እርግጥ ነው ለሰማያትና ለምድር እንዲሁም ለተራሮች እንደሚከብድ በኃያሉ አላህ የተገለጸው አደራ (አማና) የሰው ልጅ ቢወድም ባይወድም ይሸከመው ዘንድ በጫንቃው ላይ ተጭኖበታል፡፡ ይህም በመሆኑ የሰው ነፍስ ጥንቱኑ ስትሰራ ለመልካምም ሆነ ለእኩይ ዝንባሌ ተገርታ ነው፡፡ ይህንንም በማስመልከት ኃያሉና ጥበበኛው አላህ በቁርዓኑ እንደሚከተለው ይናገራል፡-

﴿ وَٱلۡأَرۡضِ وَمَا طَحَىٰهَا ٦ وَنَفۡسٖ وَمَا سَوَّىٰهَا ٧ فَأَلۡهَمَهَا فُجُورَهَا وَتَقۡوَىٰهَا ٨ قَدۡ أَفۡلَحَ مَن زَكَّىٰهَا ٩ وَقَدۡ خَابَ مَن دَسَّىٰهَا ١٠ ﴾ الشمس: ٦ - ١٠

‹‹በነፍስም ባስተካከላትም አመጽዋንና ፍርሃቷንም ባሳወቃት አምላክ እምላለሁ፡፡ (ከሃጢአት) ያጠራት ሰው ፍላጎቱን በእርግጥ አገኘ፡፡ (በሃጢአት) የሸፈናትም ሰው በእውነት አፈረ›› (አሽ-ሸምስ ፡ 7-10)

በተጨማሪም አላህ እንዲህ ይላል፡-

﴿ فَأَمَّا مَن طَغَىٰ ٣٧ وَءَاثَرَ ٱلۡحَيَوٰةَ ٱلدُّنۡيَا ٣٨ فَإِنَّ ٱلۡجَحِيمَ هِيَ ٱلۡمَأۡوَىٰ ٣٩ وَأَمَّا مَنۡ خَافَ مَقَامَ رَبِّهِۦ وَنَهَى ٱلنَّفۡسَ عَنِ ٱلۡهَوَىٰ ٤٠ فَإِنَّ ٱلۡجَنَّةَ هِيَ ٱلۡمَأۡوَىٰ ٤١ ﴾ النازعات: ٣٧ - ٤١

‹‹የካደ ሰውማ ቅርቢቱንም ሕይወት የመረጠ ገሃነም እርሷ በእርግጥ መኖሪያው ናት፡፡ በጌታው ፊት መቆምን የፈራ ሰውማ ነፍሱንም ከዝንባሌዋ የከለከለ ገነት እርሷ በእርግጥ መኖሪያው ናት፡፡››

እንግዲህ ብርሃን በተሞላው ቁርዓን ውስጥ በተጠቀሱት በእነዚህ አንቀፆች አገላለጽ መሠረት የሰው ነፍስ በሁለት ተቃርኖዎች መካከል

ሆና በየጊዜው ከወዲያና ከወዲህ እየተላጋች የምትኖር ናት ማለት ነው፡፡ እነዚህን ሁለት የተቃርኖ ስሜቶች በሁለት ዋልታዎች ልንመስላቸው እንችላለን፡፡ የመልካምና የእኩይ ዋልታዎች ብለን፡፡ ከዚህ አገላለጽ አንደምታ የምንዋሰው ሃሳብ ቢኖር እኩይ ወደሆነው ዋልታ የምትሳብና በዚያው ተመችቷት ስትሰግር የኖረች ነፍስ እድለ ቢስ የምትሰኝ መሆኗን ነው፡፡ አዎን! እድለ ቢስና የሚታዘንላት ነፍስ፡፡ ይህችን ነፍስ የሚጋሩ የሰው ዘሮች ሁሉ የእኩያን ወደሆነው ዋልታ በዕውር ድንበሩ የሚጓዙ፣ ለራሳቸው ያላቸው ግምት የተጋነነ የሆነ፣ ለሚፈጽሙት እያንዳንዱ ድርጊታቸው ተጠያቂነት አለብን ብለው የማያስቡ ናቸው፡፡

ይህችን ነፍስ በስጋ ሸፍነው የሚንገላወዱት ፍጡራን የሰብአዊነታቸውን የክብር ካባ በገዛ ፈቃዳቸው በማውለቅ አሽቀንጥረው የጣሉ፣ ሕሊናቸውን የማያዳምጡና ለስጋዊ ስሜታቸው በማጎብደድ የተዋረዱ የሰው እንክርዳዶች ቢባሉ ሰብአዊነታቸውን ማንቋሸሽ አይሆንም፡፡

ነፍስን ከአጓጉል ዝንባሌዋና ድንበር ማለፏ ማቀብና መቆጣጠር ማለት ጭራሹኑ የተሰራችበት ድርና ማግ ከሚፈቅደው ተፈጥሮዋ እጅጉን በማራቅ የምናኔ ሕይወት እንድትገፋ ማድረግ ወይም ማሰቃየት ማለት አይደለም፡፡ ከዚያ ይልቅ ወደ ሃቁና ሞገስ ወደሚያሰጣት ዋልታ እንድትሳብ ማድረግ ነው፡፡ ይህን ሁኔታ አንድ የሃይማኖት ሊቅና ባለቅኔ እንደሚከተለው ይገልጹታል፡-

‹‹መርከቡ በተለመደው አኳኋን ከውሃው በላይ ሆኖ እስከተንሳፈፈ ድረስ ውሃው መርከቡን መሸከሙንና መንሳፈፉን ይቀጥላል፡፡ ሆኖም ግን ውሃው በመርከቡ ወለሎች ላይ እንደልብ መግባት ከቻለ መርከቡ ከመስጠም ሌላ እድል የለውም፡፡ በተመሳሳይ ሁኔታ የመርከቡን ሞተር በእንፋሎት እንዲንቀሳቀስ የሚያደርገው የታመቀ እሳት መሆኑ ይታወቃል፡፡ ይሁን እንጂ ይህ እሳት ከታመቀበት ቦታ አፈትልኮ ወደ ሌላው የመርከቡ አካላት ከተዛመተ መርከቡ በእሳት ከመንደድና አመድ ከመሆን አይድንም፡፡››

አንድ የአላህ አገልጋይ ባሪያ በየእለቱ በየሰዓታቱና ከዚያም ባነሱ የጊዜ ክፍልፋዮች የሚጠበቅበት ከእኩይ ምግባሮችና ከነፍስያውም እርኩስ

ዝንባሌ ለመራቅ ጥረት ማድረግ ነው፡፡ ይህን ለማድረግ እንደ አጋዥ መሣሪያና ድጋፍ ሆኖ የሚያገለግለው ለአላህ ያለው ፍቅርና አክብሮ (ፍርሃት) ነው፡፡

አላህ ለባሪያዎቹ ከዋላቸው መልካም የሆኑ ውለታዎች ውስጥ የእናት ፍቅር፣ የትዳር ጓደኛ ፍቅር፣የልጅ ፍቅር እንዲሁም ቁሳዊና መንፈሳዊ ፀጋ ዋና ዋናዎቹ ናቸው፡፡ ይሁን እንጂ እነዚህ ነገሮች ሁሉ የአንድን ሰው ልብ ሙሉ በሙሉ ሊቆጣጠሩትና ለአላህና ለመልእክተኛው (ሰ.ዐ.ወ.) የሚኖረውን ፍቅር ከልቡ ገፍተው ሊያስወጡት አይገባም፡፡ የኃይልና የንግስና ባለቤት የሆነው አላህ እንዲህ ይላል፡-

﴿ قُلْ إِن كَانَ ءَابَآؤُكُمْ وَأَبْنَآؤُكُمْ وَإِخْوَٰنُكُمْ وَأَزْوَٰجُكُمْ وَعَشِيرَتُكُمْ وَأَمْوَٰلٌ ٱقْتَرَفْتُمُوهَا وَتِجَٰرَةٌ تَخْشَوْنَ كَسَادَهَا وَمَسَٰكِنُ تَرْضَوْنَهَآ أَحَبَّ إِلَيْكُم مِّنَ ٱللَّهِ وَرَسُولِهِۦ وَجِهَادٍ فِى سَبِيلِهِۦ فَتَرَبَّصُوا۟ حَتَّىٰ يَأْتِىَ ٱللَّهُ بِأَمْرِهِۦ ۗ وَٱللَّهُ لَا يَهْدِى ٱلْقَوْمَ ٱلْفَٰسِقِينَ ﴿٢٤﴾ ﴾ التوبة: ٢٤

‹‹አባቶቻችሁና ወንዶች ልጆቻችሁ፣ ወንድሞቻችሁም፣ ሚስቶቻችሁም፣ ዘዶቻችሁም፣ የሰበሰባችኋቸው ሃብቶችም፣ መክሰሯን የምትፈሯት ንግድም፣ የምትወዷቸው መኖሪያዎችም ከእናንተ ዘንድ ከአላህና ከመልእክተኛው፣ በርሱ መንገድም ከመታገል ይበልጥ የተወደዱ እንደሆኑ አላህ ትእዛዙን እስከሚያመጣ ድረስ ተጠባበቁ በላቸው፡፡ አላህም አመፀኞች ሕዝቦችን አይመራም፡፡” (አት-ተውባህ ፡24)

ከዚህ የቁርዓን አንቀጽ የምንቀስመው ማስተዋል ሕሊናው ንቁ የሆነ ሰው በነፍስያው አፍራሽ ዝንባሌ ጎርፍ ተጠርጐ ሳይወሰድ በፊት የመፈጠሩን ግብ በሚገባ አጢኖ የአላህን ፍቅር ወደሚያስገኝለት ሌላኛው ዋልታ (ጠርዝ) መመለስ ያለበት መሆኑን ነው፡፡

አንድ ፍቅር ተቀባይነት የሚኖረው አቅጣጫው ወይም ግቡ ትክክለኛ ከሆነ ብቻ ነው፡፡ እንዲህ ዓይነቱ ፍቅር ደግሞ መጨረሻው በውድቀትና በሃዘን የሚደመደም አይደለም፡፡ ስለሆነም የሰው ልጅ ከውጥኑ ያማረና መጨረሻው የሰመረ የሆነውን የአላህን ፍቅር ዘር በልቡ ለም የሆነ ማሳ

ላይ ማሳረፍ አለበት፡፡ እንዲህ ዓይነት ባሪያዎቹን አላህ ሁልጊዜም የማይዘነጋ ለመሆኑ የሚከተለውንና በቁርአን ትልቅ ሥፍራ የተሰጠውን የነቢዩላህ ዩሱፍ (ዐ.ሰ.) ታሪክ በማስረጃነት ማየት ይኖርብናል፡፡

የአለማት ጌታ የሆነው አላህ በሰይጣን ጉትጐታ ተገፋፍተው እኩይ ድርጊት በፈጸሙባቸው ወንድሞቻቸው በግፍ ሲጣሉ ዩሱፍን (ዐ.ሰ.) አልተዋቸውም ነበር፡፡ እነሆም በዚያ በተጣሉበት የውሃ ጉድጓድ ውስጥ ሰዎች ውሃ ለመቅዳት መገለል እንዲያስገቡ አላህ አደረገ፡፡ ከዚያስ ውጤቱ ምን ሆነ? የሚያምርና ፍልቅልቅ ልጅ በውሃ ፈንታ አኮሌውን አንቆ ወደ መሬት ሲወጣ የተጠማው ሰው ጥሙን በመርሳት ፈዞ ቀረ፡፡ ይሁን እንጂ ግዴለሽ የሆነው ይህ የሲራራ ነጋዴና ባልደረቦቹ ያጋጠማቸውን በረከት ዓለማዊ ጐኑን እንጂ ከጀርባው ያለውን መንፈሳዊ ትሩፋት የሚያስተውሉበት ሁኔታ ላይ አልነበሩም፡፡ እናም እዚህ ግባ በማይባል መናኛ ፍራንክ ያንን መለኮታዊ ግርማ ያጠላበት ታዳጊ ልጅ ሸጠውት አረፉ፡፡

እነዚያ የሲራራ ነጋዴዎች የፈጣሪያቸውን ፍቅር ቀድሞም የተራቡ አልነበሩምና ይህን በምድረ በዳ ያጋጠማቸውን የተፈለቀቀ ሉል የመሰለ ልጅ ለጊዜው በአእምሯቸው ለተከሰተ አለማዊ ጥቅም አሳልፈው ሰጡት፡ ፡ ይህን ሲያደርጉም ወርቃማ የሆነውን መለኮታዊ ፍቅር እንደዘበት በሽርፍራፊ ሳንቲሞች መለወጣቸውን ልብ አላሉም፡፡

የአላህ ሃቀኛ ወዳጆች ባህሪ የእርሱን ውዴታ የሚያስገኙ ነገሮችን ለመፈጸም መጣደፍና ልባቸውንም በዚያ በሚያገኙት እርካታ መሙላት ነው፡፡ ከአላህና ከመልእክተኛው (ሰ.ዐ.ወ) ውጪ የሆኑ ነገሮችን ሲወዱ ደግሞ ገደብ በማበጀት ሲሆን ልባቸውን ሙሉ በሙሉ እንዲቆጣጠሯቸው አይፈቅዱም፡፡

ሌላው ለሁሉም ሰው ግልጽ ሊሆን የሚገባው ነገር የአላህን የውዴታ ውቂያኖስ ያለምንም ገደብ ለመቅዘፍ የፈለገ ሰው መልእክተኛውን ሙሐመድ (ሰ.ዐ.ወ.) ከልቡ መውደድ ይኖርበታል፡፡ እንዲሁም የሚወደውን ሰው ፈለግና የሕይወት ዘይቤ መከተሉ ከእርሱ የሚጠበቅ ነው፡፡ ስለሆነም አላህ ይህን አስመልክቶ እንደሚከተለው ይላል፡-

﴿ قُلۡ إِن كُنتُمۡ تُحِبُّونَ ٱللَّهَ فَٱتَّبِعُونِي يُحۡبِبۡكُمُ ٱللَّهُ وَيَغۡفِرۡ لَكُمۡ ذُنُوبَكُمۡۚ وَٱللَّهُ غَفُورٞ رَّحِيمٞ ٣١ ﴾ آل عمران: ٣١

“በላቸው፤ አላህን የምትወዱ እንደሆናችሁ ተከተሉኝ፡፡ አላህ ይወዳችኋልና፡፡ ኃጢአቶቻችሁንም ለእናንተ ይምራልና፡፡ አላህም መሐሪ አዛኝ ነው፡፡” (አሊ-ዒምራን፡ 31)

አላህ የሰውን ልጅ ሲፈጥረው የግንዛቤ አድማሱንና የማወቅ ችሎታውን ገድቦታል፡፡ ይሁን እንጂ መንፈሳዊ በሆኑ ጉዳዮች ምናቡን እስከፈለገው ድረስ መለጠጥ ይችላል፡፡ ይህም ማስተንተን (ተፈኩር) የሚባል ሲሆን በሰማያትና በምድር እንዲሁም በመካከላቸው ባሉ ነገሮች ላይ እንዳሻው መቅዘፍ ያስችለዋል፡፡ በአንድ ነገር ላይ ብቻ ይህን ምናቡን ሥራ ላይ ማዋል አይችልም፡፡ ይኸውም የአላህን አካል (ዛት) ምንነት ለማስተንተን አልተፈቀደለትም፡፡

ምዕራፍ ሁለት

ስብእናው የተሟላ ሰው

የሰውን ልጅ አላህ ሲፈጥረው በአቋሙም ሆነ በአስተሳሰቡ ባማረ ሁኔታ ነው፡፡ ይህንንም በቁርዓን እንዲህ በማለት ገልፆታል፡-

﴿ لَقَدْ خَلَقْنَا ٱلْإِنسَٰنَ فِىٓ أَحْسَنِ تَقْوِيمٍ ﴿٤﴾ ﴾ التين: ٤

"ሰውን በጣም በአማረ አቋም ላይ ፈጠርነው፡፡" (አት-ቲን፡4)

እንግዲህ ባለፈው ምዕራፍ ላይ በመጠኑ እንደተዳሰሰው የሰው ልጅ የስጋዊና መንፈሳዊ እንዲሁም የመልካምና የእኩይ ምግባራት ተቃርኖ (ፍጭት) የሚካሄድበት ፍጡር ነው፡፡ ሰው ፈጣሪው ያስቀመጠለትን ግብ ልጨብጥ ብሎ ከልቡ ከተነሣ ያንን ማድረግ የማይሳነው እንደመሆኑ የዝቅጠትን መንገድ ከመረጠ ደግሞ ከእንስሳት በባሰ ሁኔታ የደመነፍሱ ተገዥ ነው፡፡ አላህ እንዲህ ይላል፡-

﴿ أَفَرَءَيْتَ مَنِ ٱتَّخَذَ إِلَٰهَهُۥ هَوَىٰهُ وَأَضَلَّهُ ٱللَّهُ عَلَىٰ عِلْمٍ وَخَتَمَ عَلَىٰ سَمْعِهِۦ وَقَلْبِهِۦ وَجَعَلَ عَلَىٰ بَصَرِهِۦ غِشَٰوَةً فَمَن يَهْدِيهِ مِنۢ بَعْدِ ٱللَّهِ ۚ أَفَلَا تَذَكَّرُونَ ﴿٢٣﴾ ﴾ الجاثية: ٢٣

"ዝንባሌውን አምላኩ አድርጉ የያዘውን አላህም ከእውቀት ጋር ያጠመመውን በጆሮውና በልቡ ላይም ያተመበትን በዓይኑም ላይ ሽፋን ያደረገበትን ሰው አየህን! ታዲያ ከአላህ ኋላ የሚያቀናው ማን ነው? አትገሰጹምን?" (አል-ጃሲያህ፡ 23)

ስብእናውን በኢስላም አስተምህሮት ለመግራትና በሸሪዓ መርከብ ተሳፍሮ ለመቅዘፍ የመረጠን ሰው አላህ በአጽናፈ ዓለሙ ውስጥ ካሉ ፍጥረታት (ከመላእክትም ጭምር) በላይ ከፍ በማድረግ ያከብረዋል፡፡ የዚህ ዓለም ሕይወቱን፣ ሲሳዩንና ነገሩን ሁሉ ገር ያደርግለታል፡፡ ጥበብ በተሞላው መጽሐፍ በቁርዓን እንዲህ ተብሎ ተጽፎ እናገኛለን፡-

﴿ وَمَن يَتَّقِ ٱللَّهَ يَجۡعَل لَّهُۥ مَخۡرَجٗا ٢ وَيَرۡزُقۡهُ مِنۡ حَيۡثُ لَا يَحۡتَسِبُۚ وَمَن يَتَوَكَّلۡ عَلَى ٱللَّهِ فَهُوَ حَسۡبُهُۥٓۚ ٣ ﴾ الطلاق: ٢ - ٣

"...አላህንም የሚፈራ ሰው ለእርሱ መውጫን ያደርግለታል። ከማያስበውም በኩል ሲሳይን ይሰጠዋል። በአላህም ላይ የሚጠጋ ሰው እርሱ በቂው ነው። ....." (አል-ጠላቅ፡ 2-3)

﴿ وَلَوۡ أَنَّ أَهۡلَ ٱلۡقُرَىٰٓ ءَامَنُواْ وَٱتَّقَوۡاْ لَفَتَحۡنَا عَلَيۡهِم بَرَكَٰتٖ مِّنَ ٱلسَّمَآءِ وَٱلۡأَرۡضِ وَلَٰكِن كَذَّبُواْ فَأَخَذۡنَٰهُم بِمَا كَانُواْ يَكۡسِبُونَ ٩٦ ﴾ الأعراف: ٩٦

"የከተማዋ ሰዎች ባመኑና በተጠነቀቁ ኖሮ በእነርሱ ላይ ከሰማይም ከምድርም በረከቶችን በከፈትንላቸው ነበር።" (አል-አዕራፍ፡ 96)

ሙስሊም የሆነና በእምነት ልቡ የራሰ ማንም ሰው የዚህችን ዓለም ጠፊነትና ሁሉም ነገር መቅኖ የሌለው መሆኑን ከልቡ ያምናል። ስለሆነም በዚህች ዓለም ላይ ሲኖር እንደ እንግዳ ወይም መንገድ አቋራጭ ሆኖ ነው።

የአላህ መልእክተኛ (ሰ.ዐ.ወ.) እንደሚከተለው ማለታቸውን ኢብን ኡመር (ረ.ዐ.) አውርተዋል፡-

‹‹የአላህ መልእክተኛ ትከሻየን ያዝ በማድረግ ፡ ‹‹ በዚህች ዓለም ላይ ስትኖር እንደ እንግዳ ወይም መንገድ አቋራጭ ሁን፡፡›› አሉኝ። ሐዲሱን ቡኻሪ ዘግበውታል።

ስለሆነም የተሟላ ኢስላማዊ ስብዕና ያለው ሰው ይህችን ዓለም እንደዘላለማዊ ሀገር በመቁጠር ለሁልጊዜም ሊከትምባት አያስብም። እርግጥ ነው በሕይወት እስካለ ድረስ ለእለት ተእለት ኑሮው የሚያስፈልጉት ነገሮች ይኖራሉ። ለምግቡ፣ ለልብሱ፣ ለቤተሰቡ ቀለብና ለአንዳንድ ወጪዎቹ የሚሆነውን ነገር ለማግኘት በትጋት ይንቀሳቀሳል። በዚሁ ሰበብም ከሪዝቁ (ሲሳዩ) ጋር ይገናኛል። ይህን ማድረጉ ከቶም ዘላለማዊነትን አለመሻቱንና መንገድ አቋራጭ አለመሆኑን አያሳይም።

ከዚህም በተጨማሪ ቤተሰባዊ ግዴታዎቹን በመወጣት ለሚስቱ፣ ለልጆቹ፣ ለዘመዶቹና ለጐረቤቶቹ መልካም ሆኖ መገኘት ይጠበቅበታል፡፡

የጌታውን ሃቅ በተመለከተም የግዴታ ሰላቶቹንና ጾምን፣ ዘካውንና ሐጁን ሁሉንም አቅሙ በፈቀደለት ያክል ይፈጽማል፡፡ ቃል ኪዳኑን መጠበቅን በተመለከተስ ምን ለማለት ይቻላል? ይህ በማያጠራጥር ሁኔታ የአንድ አማኝ ሰው መገለጫ ባህሪ ሲሆን ለፈጣሪው፣ ለኃይማኖቱ ወይም ደግሞ ለሰዎች የገባውን ቃል ኪዳን ፈጽሞ አያጥፍም፡፡ መሃላውንም ይሞላል፡፡ ሰዎችን በምላሱም ሆነ በድርጉቱ አያስቀይምም፡፡ ፀባዩ ያማረና ከሰዎች ጋር ባለው ግንኙነትም ምግባረ ሰናይ መሆኑ በግልጽ ይንፀባረቃል፡፡

ይህን ጉዳይ አስመልክተው የአላህ መልእክተኛ (ሰ.ዐ.ወ.) እንደሚከተለው ብለዋል፡-

‹‹አትመቅኙ፣ ዋጋ አታሳቅሉ፣ በመካከላችሁ ጥል አይኑር፡፡ አንዱ ለሌላው ጀርባ አይስጥ (አትኮራረፉ)፣ ከፊሉ በከፊሉ ገበያ ጣልቃ አይግባ፡፡ እናንተ የአላህ ባሪያዎች ወንድማማቾች ሁኑ፡፡ ሙስሊም ለሙስሊም ወንድሙ ነውና አይበድለው፡፡ እርዳታውንም አያቋርጥበት፣ አይዋሸው፣ አይናቀው››

ይህን ካሉ በኋላ ወደልባቸው ሶስት ጊዜ በማመልከት፡- ‹‹አላህን መፍራት ከዚህ ነው›› አሉ፡፡ እንዲህ ሲሉም አከሉ፡- ‹‹አንድ ሙስሊም ወንድሙን መናቁ ብቻ ለወንጀለኝነት በቂ ነው፡፡ ሙስሊም የሌላውን ሙስሊም ደም ገንዘብና ክብር (መንካት) ክልክል ነው፡፡” ሐዲሱን አቡ ሁረይራ (ረ.ዐ) ያወሩት ሲሆን ሙስሊም ዘግበውታል፡፡

አቡ ዘር ጁንዱብ ኢብኑ ጁናዳ እና አብዱራህማን ሙዓዝ ኢብኑ ጀበል (ረ.ዐ) ባወሩትና ቲርሚዚ በዘገቡት ሌላ ሐዲስ የአላህ መልእክተኛ (ሰ.ዐ.ወ.) እንዲህ ብለዋል፡-

‹‹የትም ቦታ ብትሆን አላህን ፍራ፡፡ መጥፎ ሥራን በመልካም አስከትል- (ወንጀልህን) ታብስልሃለችና፡፡ ከሰዎች ጋር ያለህም ግንኙነት ግብረ ገባዊ ይሁን፡፡››

የአላህ ወዳጅ የሆነ ሰው ከሰዎች ጋር ባለው መስተጋብር ትእግስተኛ፣ ይቅር ባይና ሆደ ሰፊ መሆን ይጠበቅበታል፡፡ ሁልጊዜም ሰላምን የሚያራምድና በጎ አሳቢ መሆኑን አላህ በቁርዓን ሲገልጽ እንዲህ ይላል፡-

﴿ وَعِبَادُ ٱلرَّحۡمَٰنِ ٱلَّذِينَ يَمۡشُونَ عَلَى ٱلۡأَرۡضِ هَوۡنٗا وَإِذَا خَاطَبَهُمُ ٱلۡجَٰهِلُونَ قَالُواْ سَلَٰمٗا ٦٣ ﴾ الفرقان: ٦٣

‹‹የአር-ራህማንም ባሮች እነዚያ በምድር ላይ በዝግታ የሚሄዱት ባለጌዎችም (በክፉ) ባነጋገሩዋቸው ጊዜ ሰላም የሚሉት ናቸው፡፡›› (አል-ፉርቃን፡ 63)

ወደ አላህ የቀረበና በጧትም ሆነ በማታ እርሱን ለማስታወስ የሚሻ ሰው ሕይወቱ ሁሉ በቁርዓንና በነቢዩ (ሰ.ዐ.ወ.) መመሪያዎች ላይ የተመሠረተ መሆን አለበት፡፡ በዚህ ሂደት ላይ እያለ ከሰዎች በየጊዜው የሚደርስበትን ፈተናና በደል ታግሶ ያሳልፋል፡፡ ሌላው ቀርቶ ታላቅ የሚባልና ቁጭትን የሚያሳድር በደል ላደረሰበት ሰው እንኳን መልካም እንዲውል አላህ ይፈልጋል፡፡ ለዚህ አባባላችን እንደማስረጃ አድርገን የምናቀርበው የአቡበከርንና ሚሳጧህ የተባለውን ዘመዳቸውን ታሪክ ነው፡፡

አቡበከር (ረ.ዐ.) እጅግ ልበ ሩህሩህና ‘ሲዲቅ’ በሚል የማዕረግ ስም በሕዝበ ሙስሊሙ የሚታወቁ ደግና ፀባየ ለስላሳ ሰው ነበሩ፡፡ ኢስላምን ገና ከጧቱ ከመልእክተኛው (ሰ.ዐ.ወ.) አፍ እንደሰሙ ያለምንም ማቅማማት የተቀበሉት በመሆኑና በሌሎቹም በጎ ምግባሮቻቸው ሲዲቅ (እውነተኛው) የሚለውን፣ እንደመልካም ሽቶ እስከ ዓለም ፍጻሜ ትውልድን ሲያውድ የሚኖር ስም ተቀዳጅተዋል፡፡ አቡበከር (ረ.ዐ.) በቂ የሚባል ንብረት (ሃብት) ይዘው ኢስላምን ቢቀበሉም በየጊዜው ለኃይማኖታቸው ጉዳይ ወጪ ያደርጉት ስለነበር በመጨረሻ ላይ ልክ እንደተወዳጅ ጓደኛቸው ሙሐመድ ኢብኑ አብዱላህ (ሰ.ዐ.ወ.) ሁሉ ገንዘብና ሃብት አልነበራቸውም፡፡ እንደዚያም ሆኖ ካላቸው መጠነኛ ገቢ እየቀነሱ ይደጉሙት የነበር ሚስጧህ የሚባል ዘመድ ነበራቸው፡፡ ይህ

በእንዲህ እያለም ተወዳጅዋን ልጃቸውን (የነቢዩንም (ሰ.ዐ.ወ.) ባለቤት አኢሻን (ረ.ዐ.) መናፍቃን በዝሙት ሥራ ወንጅለዋት በነበረበት ጊዜ ይህ ሚስጧህ የተባለ ዘመዳቸው ያንን የሃሰት ወሬ (ኢፍክ) በማዛመቱ ሥራ ላይ ራሱን ማስጠመዱ ታወቀ። በኋላ ላይ አላህ የሚከተሉትን የቁርአን አንቀፆች በማውረድ አኢሻን (ረ.ዐ.) ከተወራባት የሃሰት ውንጀላ (ኢፍክ) ነፃ አደረጋት ።

﴿ إِنَّ ٱلَّذِينَ يَرۡمُونَ ٱلۡمُحۡصَنَٰتِ ٱلۡغَٰفِلَٰتِ ٱلۡمُؤۡمِنَٰتِ لُعِنُواْ فِي ٱلدُّنۡيَا وَٱلۡأٓخِرَةِ وَلَهُمۡ عَذَابٌ عَظِيمٞ ٢٣ يَوۡمَ تَشۡهَدُ عَلَيۡهِمۡ أَلۡسِنَتُهُمۡ وَأَيۡدِيهِمۡ وَأَرۡجُلُهُم بِمَا كَانُواْ يَعۡمَلُونَ ٢٤ ﴾ النور: ٢٣ - ٢٤

“እነዚያ ጥብቆቹን ከዝሙት ዘንጊዎች ምእመናት የሚሰድቡ በቅርቢቱም በመጨረሻይቱም ዓለም ተረገሙ። ለእነርሱም ታላቅ ቅጣት አላቸው። በእነርሱ ላይ ምላሶቻቸው እጆቻቸውና እግሮቻቸውም ይሰሩት በነበሩት ነገር በሚመሰክሩባቸው ቀን (ከባድ ቅጣት አላቸው)።“ (አን-ኑር 23-24)

﴿ إِنَّ ٱلَّذِينَ يُحِبُّونَ أَن تَشِيعَ ٱلۡفَٰحِشَةُ فِي ٱلَّذِينَ ءَامَنُواْ لَهُمۡ عَذَابٌ أَلِيمٞ فِي ٱلدُّنۡيَا وَٱلۡأٓخِرَةِۚ وَٱللَّهُ يَعۡلَمُ وَأَنتُمۡ لَا تَعۡلَمُونَ ١٩ ﴾ النور: ١٩

“እነዚያ በእነዚያ ባመኑት ሰዎች ውስጥ መጥፎ ወሬ እንድትስፋፋ የሚወዱ ለእነርሱ በቅርቢቱም በመጨረሻይቱም ዓለም አሳማሚ ቅጣት አላቸው። አላህም ያውቃል። እናንተ ግን አታውቁም።” (አን-ኑር፡ 19)

ይህ ከሆነ በኋላ አቡበከር (ረ.ዐ.) ለወሬኛውና የልጃቸውን ስም ላጠፋው ዘመዳቸው ለሚሰጧህ ከእንግዲህ ምንም ዓይነት እርዳታ ላያደርጉለት ማሉ። ይህን ሁኔታቸውን ያልወደደላቸው መሆኑን በሚከተለው የቁርዓን አንቀጽ በመግለጽ አላህ ገሰፃቸው፡-

﴿ وَلَا يَأۡتَلِ أُوْلُواْ ٱلۡفَضۡلِ مِنكُمۡ وَٱلسَّعَةِ أَن يُؤۡتُوٓاْ أُوْلِي ٱلۡقُرۡبَىٰ وَٱلۡمَسَٰكِينَ وَٱلۡمُهَٰجِرِينَ فِي سَبِيلِ ٱللَّهِۖ وَلۡيَعۡفُواْ وَلۡيَصۡفَحُوٓاْۗ أَلَا تُحِبُّونَ أَن يَغۡفِرَ ٱللَّهُ لَكُمۡۗ وَٱللَّهُ غَفُورٞ رَّحِيمٌ ٢٢ ﴾ النور: ٢٢

"ከእናንተም የችሮታና የክብረት ባቤቶች የሆኑት ለቅርብ ዘመዶችና ለድሆች በአላህም መንገድ ለተሰደዱ ሰዎች ላይሰጡ አይማሉ፡ ፡ ይቅርታም ያድርጉ፡፡ ጥፋተኞቹን ይለፉም፡፡ አላህ ለእናንተ ሊምር አትወዱምን? አላህም መሐሪ አዛኝ ነው፡፡" (አን-ኑር፡22)

ከዚህ ጉዳይ ጋር የሚሄደው ሌላው የቁርዓን አንቀጽ የሚከተለው ነው፡-

﴿ وَلَا تَجۡعَلُواْ ٱللَّهَ عُرۡضَةٗ لِّأَيۡمَٰنِكُمۡ أَن تَبَرُّواْ وَتَتَّقُواْ وَتُصۡلِحُواْ بَيۡنَ ٱلنَّاسِۗ وَٱللَّهُ سَمِيعٌ عَلِيمٞ ٢٢٤ ﴾ البقرة: ٢٢٤

"መልካም እንዳትሠሩ፣ አላህንም እንዳትፈሩ፣ በሰዎችም መካከል እንዳታስታርቁ አላህን ለመሐሎቻችሁ ግርዶ አታድርጉ፡፡ አላህም ሰሚ አዋቂ ነው፡፡" (አል-በቀራህ፡224)

አቡበከር (ረ.ዐ.) ከአላህ የወረደላቸውን ተግሳጽ ተከትሎ "አላህ እንዲምረኝ እከጅላለሁ" በማለት ለሚስጧህ የሚሰጡትን ድጐማ ቀጥለዋል፡፡ ምእመናን በእለት ተእለት የሕይወት ሂደት አፍራሽ የሆኑና የእነርሱን ቅስም የሚሰብሩ ንግግሮችን ከባለጌ ሰዎች ሊሰሙ ይችላሉ፡፡ በዚህ ጊዜ ማድረግ ያለባቸውን ወይም መውሰድ የሚገባቸውን እርምጃ አላህ በመለኮታዊ ንግግሩ ሲጠቁም እንዲህ ይላል፡-

﴿ وَسَارِعُوٓاْ إِلَىٰ مَغۡفِرَةٖ مِّن رَّبِّكُمۡ وَجَنَّةٍ عَرۡضُهَا ٱلسَّمَٰوَٰتُ وَٱلۡأَرۡضُ أُعِدَّتۡ لِلۡمُتَّقِينَ ١٣٣ ٱلَّذِينَ يُنفِقُونَ فِي ٱلسَّرَّآءِ وَٱلضَّرَّآءِ وَٱلۡكَٰظِمِينَ ٱلۡغَيۡظَ وَٱلۡعَافِينَ عَنِ ٱلنَّاسِۗ وَٱللَّهُ يُحِبُّ ٱلۡمُحۡسِنِينَ ١٣٤ ﴾ آل عمران: ١٣٣ - ١٣٤

"ከጌታችሁ ወደሆነችም ምህረትና ስፋቷ እንደ ሰማያትና ምድር ወደ ሆነች ገነት አላህን ለሚፈሩ የተዘጋጀች ስትሆን ተቻኮሉ፡፡ ለእነዚያ በድሎትም ሆነ በችግር ለሚለግሱት፣ ቁጭትንም ገቺዎች፣ ከሰዎችም

ይቅርታ አድራጊዎች ለሆኑት (ተደግሳለች)። አላህም በጐ ሠሪዎችን ይወዳል።” (አሊዒምራን ፡134)

ይህ የቁርዓን አንቀጽ የያዘውን መልእክት በተግባር ላይ ካዋሉት ሰለፍ ደጋግ የአላህ ባሪያዎች መካከል ጃዕፈር አስ-ሲዲቅ አንዱ ሲሆን ባሪያው በልብሱ ላይ የደፋበትን ምግብ በይቅርታ አልፎታል። ከዚያ በኋላም በእንክብካቤና በመልካም ሁኔታ ነበር የያዘው። አል-ሃሰን አል- በስሪ ደግሞ ያሟቸውን ሰዎች ይቅርታ ያደረጉላቸው ሲሆን ይህን መጥፎ ፀባይ እንዲያርሙ ለማድረግ በማሰብ ስጦታ ልከውላቸዋል።

ስብእናው በኢስላም መርሆዎች የተገራ ሰው አላህን መገዛትና መልካም ሥራዎችን መሥራት የጧት የማታ ተግባሩ ነው። ተስቢህ (ሱብሃነሏህ) ማለት ደግሞ እንደትንፋሹ ሁሉ ሁልጊዜም ከአፉ የሚወጣ ቃል ነው። ሰዎች እርሱን ሲያዩ የመጪውን ዓለም (አኺራን) አይቀሬነት ያስታውሳሉ። ከእርሱ ጋር የተቀማመጡ ከንቱ ንግግርንና እብለትን ሳይሆን ውስጥን የሚቀይሩ ቃላትን ተምረው ይነሳሉ። በአጠቃላይ የእርሱ ማንነት የታጠረው በእውነት፣ በቁምነገር፣ በመልካም ንግግር፣ በበጐ ምግባርና ወደ አላህ በሚያቃርቡ ነገሮች ነው። ለዚህም ነው ኃያሉ አላህ እንዲህ ዓይነት ሰዎች በሁለቱም ዓለማት ለስኬት የሚበቃ ሕይወት እንደሚኖሩ የሚናገረው። እነዚህ ሰዎች በቅርቢቱ ዓለም የአላህ ወዳጆችና ባለሟሎች ሲሆኑ በመጪው ዓለም ደግሞ ፍርሃትም ሆነ ሐዘን የለባቸውም። አላህ እንዲህ ይላል፡-

﴿أَلَآ إِنَّ أَوۡلِيَآءَ ٱللَّهِ لَا خَوۡفٌ عَلَيۡهِمۡ وَلَا هُمۡ يَحۡزَنُونَ ٦٢﴾ يونس: ٦٢

“ንቁ! የአላህ ወዳጆች በእነርሱ ላይ ፍርሃት የለባቸውም፤ እነርሱም አያዝኑም።” (ዩኑስ፡62)

ምዕራፍ ሶስት

በአላህ መንገድ ላይ መጽናት

በአላህ መንገድ ላይ መጽናት ወይም ቀጥ ማለት (በአረብኛው እስቲቃማህ) የሚል ትርጓሜን ይሟል፡፡ አንድ የአላህ ባሪያ የፈጣሪውን ባሕሪያት፣ የመፈጠሩን ግብ፣ እና ኢስላም ከእርሱ የሚፈልግበትንም ሊጫወታቸው የሚችላቸውን ሚናዎች ለይቶ ካወቀ በኋላ ቀጣዩ ተግባሩ ኢባዳ ነው፡፡ ከዚያ በኋላስ? አላህ በቁርዓን፡-

﴿ فَٱسۡتَقِمۡ كَمَآ أُمِرۡتَ وَمَن تَابَ مَعَكَ وَلَا تَطۡغَوۡاْۚ إِنَّهُۥ بِمَا تَعۡمَلُونَ بَصِيرٞ ١١٢ ﴾

“እንደታዘዝከውም ቀጥ በል፡፡ ከአንተ ጋር ያመኑትም (ቀጥ ይበሉ) ወሰንንም አትለፉ፡፡ እርሱ የምትሰሩትን ተመልካች ነውና፡፡” (ሁድ፡112)

በማለት እንዳዘዘው ቀጥ ማለት ነው የሚጠበቅበት፡፡ ይህም ታላቅ የሆነ ትእዛዝ ሲሆን ነቢዩ (ሰ.ዐ.ወ) “ሱራ አል-ሁድ አሸበተችኝ›› በማለት እንዲናገሩ አስገድዷቸዋል፡፡ አንድ ሰው የመጪውን ዓለም በሚመለከት ማመን ባለበትና ከስሜት ሕዋሳት በራቁ (ገይብ) ነገሮች ሁሉ ካመነ በኋላ ቀሪው ተግባር በዚያ ላይ መጽናት ነው፡፡ ሆኖም ግን ይህ ጽናት አላህ የሚፈልገውና መለኮታዊውን መስፈርት ያሟላ ሊሆን ግድ ይላል፡፡

አቡ አምር ሱፍያን ኢብን አብደላህ (ረ.ዐ.) እንዲህ ሲል አውግቷል፡- ነቢዩን (ሰ.ዐ.ወ.) ፡- “አንቱ የአላህ መልእክተኛ ሆይ! ስለ ኢስላም ከእርስዎ ሌላ ማንንም መጠየቅ የማያስፈልገኝ የሆነ አንድ ነገር ይንገሩኝ፤” አልኳቸው፡፡ እርሳቸውም፡- “በአላህ አምኛለሁ በል፡፡ ከዚያም ቀጥ በል፡፡” አሉኝ፡፡ ሐዲሱን ሙስሊም ዘግበውታል፡፡ “እንደታዘዝከውም ቀጥ በል…” የሚለው በሱራ ሁድ፡ ቁጥር 112 ላይ የተጠቀሰው ቁርዓናዊ ትዕዛዝ እውነትም በነቢዩ (ሰ.ዐ.ወ.) ጫንቃ ላይ ታላቅ የሆነን ሸክም ያሳረፈ ነው ማለት ይቻላል፡፡ በዚህም የተነሳ ጥቁር ሆኖ ዞማ የነበረው የነቢዩ ፀጉር ከዚህ ሱራ መውረድ በኋላ አልፎ አልፎ ሽበት

ወረር ሊያደርገው በቅቷል። የቁርዓን ተንታኞች ይህን የቁርዓን አንቀጽ እንደሚከተለው አብራርተውታል፡-

“አንተ ነቢዩ ሆይ! በቁርዓን ላይ የተጠቀሱትን የሞራልና የሥነምግባር ደንቦች በመከተል አኳያ አርአያ ሆኖ መገኘት ይጠበቅብሃል። ይህን በማድረግህም የሚደርስብህ አንዳች ችግር አይኖርም። መናፍቃንንና ከሃዲያንንም አትፍራ። የእነርሱን ጉዳይ ለአላህ ተወው። በግልህ ወይም በተከታዩችህ ጉዳይ ላይ ቀናውን ጐዳና ከመከተል በመለስ ከሃቁ ዘንበል እንዳትል። ቀናውን መንገድ ይዘህ ስትጓዝ የሚገጥምህ ፈተና ከባድ ቢሆንም እንኳን ለአፍታም ቢሆን የጥመትን ጐዳና እንዳትመርጥ። ጌታህ በማንኛውም ጉዳይህ ረዳትህ ነው።››

ይህን ጉዳይ አስመልክተው ኢብን አባስ (ረ.ዐ.) ሲናገሩ “በዚህ ምዕራፍ ላይ ከታዘዙት የበለጠ የነቢዩን (ሰ.ዐ.ወ.) ጫንቃ ያጐበጠ አንዳችም መለኮታዊ ትዕዛዝ የለም” ብለዋል።

በሌላ በኩል ደግሞ በሱራ ሁድ ምዕራፍ 112 ላይ “እንደታዘዝከውም ቀጥ በል” የተባሉት ነቢዩ ብቻ አልነበሩም። በዚያ ሱራ ላይ ከነቢዩ (ሰ.ዐ.ወ.) ትዕዛዝ ቀጥሎ “ ....ከአንተ ጋር ያመኑትም ቀጥ ይበሉ...” የሚል ተጠቅሶ ይገኛል። በመሆኑም ጉዳዩ እርሳቸውን ብቻ ሳይሆን የሃቅ መንገድ የሆነውን ኢስላምን ተቀብለን አማኞች ሆነናል የሚሉትን ክቡራን ባልደረቦቻቸውን ሁሉ የሚመለከት ነው ማለት ይሆናል። የእርሳቸውን ጽናትና መልእክቱን ከማድረስ አኳያ ያላቸውን ብቃትማ ኃያሉ አላህ በሚከተለው አኳኋን ሲመሰክርላቸው እናነባለን፡-

﴿ إِنَّكَ لَمِنَ ٱلْمُرْسَلِينَ ﴿٣﴾ عَلَىٰ صِرَٰطٍ مُّسْتَقِيمٍ ﴿٤﴾ ﴾ يس: ٣ - ٤

“አንተ በእርግጥ ከመልእክተኞቹ ነህ። በቀጥታው መንገድ ላይ ነህ።” (ያሲን፡3-4)

ስለዚህ ከአላህ ጋር ለመቃረብ ቀናውን መንገድ ተከትሎ መልካም ነገር ከመስራት ውጪ ሌላ ምንም መንገድ የለም። ይህንንም መንገድ

የሚከተሉት በአላህ የተመረጡ ብቻ ሲሆኑ እነርሱም ነቢያት፣ ሰማዕታት (ሹሃዳዕ)፣ እንዲሁም የአላህ ደጋግ ባሪያዎች ናቸው፡፡ ጋያሉ አላህ እንዲህ ይላል፡-

﴿ وَإِنَّكَ لَتَهۡدِيٓ إِلَىٰ صِرَٰطٖ مُّسۡتَقِيمٖ ٥٢ صِرَٰطِ ٱللَّهِ ٱلَّذِي لَهُۥ مَا فِي ٱلسَّمَٰوَٰتِ وَمَا فِي ٱلۡأَرۡضِۗ أَلَآ إِلَى ٱللَّهِ تَصِيرُ ٱلۡأُمُورُ ٥٣ ﴾ الشورى: ٥٢ - ٥٣

“ወደዚያ በሰማያትና በምድር ያለው ሁሉ የእርሱ ወደሆነው አላህ መንገድ (ትመራለህ)፡፡ ንቁ! ነገሮች ሁሉ ወደ አላህ ይመለሳሉ፡፡” (አሹ-ሹራ፡53)

﴿ إِنَّ ٱللَّهَ رَبِّي وَرَبُّكُمۡ فَٱعۡبُدُوهُۚ هَٰذَا صِرَٰطٞ مُّسۡتَقِيمٞ ٥١ ﴾ آل عمران: ٥١

“አላህ ጌታየና ጌታችሁ ነው፡፡ ስለዚህ ተገዙት፡፡ ይህ ቀጥተኛው መንገድ ነው (አላቸው)፡፡” (አሊ ዒምራን፡51)

﴿ وَمَن يَعۡتَصِم بِٱللَّهِ فَقَدۡ هُدِيَ إِلَىٰ صِرَٰطٖ مُّسۡتَقِيمٖ ١٠١ ﴾ آل عمران: ١٠١

“...በአላህም የሚጠበቅ ሰው ወደ ቀጥተኛው መንገድ በእርግጥ ተመራ፡፡” (አሊ-ዒምራን፡ 101)

ቀናው ጐዳና በይበልጥ በሱራ አል-አንዓም በሚከተለው ሁኔታ ተገልጿል፡-

﴿ ۞ قُلۡ تَعَالَوۡاْ أَتۡلُ مَا حَرَّمَ رَبُّكُمۡ عَلَيۡكُمۡۖ أَلَّا تُشۡرِكُواْ بِهِۦ شَيۡـٔٗاۖ وَبِٱلۡوَٰلِدَيۡنِ إِحۡسَٰنٗاۖ وَلَا تَقۡتُلُوٓاْ أَوۡلَٰدَكُم مِّنۡ إِمۡلَٰقٖۖ نَّحۡنُ نَرۡزُقُكُمۡ وَإِيَّاهُمۡۖ وَلَا تَقۡرَبُواْ ٱلۡفَوَٰحِشَ مَا ظَهَرَ مِنۡهَا وَمَا بَطَنَۖ وَلَا تَقۡتُلُواْ ٱلنَّفۡسَ ٱلَّتِي حَرَّمَ ٱللَّهُ إِلَّا بِٱلۡحَقِّۚ ذَٰلِكُمۡ وَصَّىٰكُم بِهِۦ لَعَلَّكُمۡ تَعۡقِلُونَ ١٥١ وَلَا تَقۡرَبُواْ مَالَ ٱلۡيَتِيمِ إِلَّا بِٱلَّتِي هِيَ أَحۡسَنُ حَتَّىٰ يَبۡلُغَ أَشُدَّهُۥۖ وَأَوۡفُواْ ٱلۡكَيۡلَ وَٱلۡمِيزَانَ بِٱلۡقِسۡطِۖ لَا نُكَلِّفُ نَفۡسًا إِلَّا وُسۡعَهَاۖ وَإِذَا قُلۡتُمۡ فَٱعۡدِلُواْ وَلَوۡ كَانَ ذَا قُرۡبَىٰۖ وَبِعَهۡدِ ٱللَّهِ أَوۡفُواْۚ ذَٰلِكُمۡ وَصَّىٰكُم بِهِۦ لَعَلَّكُمۡ تَذَكَّرُونَ

﴿١٥٢﴾ وَأَنَّ هَٰذَا صِرَٰطِي مُسۡتَقِيمٗا فَٱتَّبِعُوهُۖ وَلَا تَتَّبِعُواْ ٱلسُّبُلَ فَتَفَرَّقَ بِكُمۡ عَن سَبِيلِهِۦۚ
ذَٰلِكُمۡ وَصَّىٰكُم بِهِۦ لَعَلَّكُمۡ تَتَّقُونَ ﴿١٥٣﴾ ﴾ الأنعام: ١٥١ - ١٥٣

"ኑ ጌታችሁ በእናንተ ላይ እርም ያደረገውን ነገር (በእርሱም ያዘዛችሁን) ላንብብላችሁ በላቸው፡፡ በእርሱ (በአላህ) ምንንም ነገር አታጋሩ፣ ለወላጆችም በጎን ሥራ (ሥሩ)፣ ልጆቻችሁንም በድህነት (ፍራቻ) አትግደሉ፡፡ እኛ እናንተንም እነርሱንም እንመግባችኋለንና፡፡ መጥፎ ሥራዎችንም ከርሷ የተገለጸውንም የደበቀውንም ሁሉ አትቅረቡ፡፡ ያችንም አላህ እርም ያደረጋትን ነፍስ በሕግ ቢሆን እንጂ አትግደሉ፤ ይኻችሁ ታውቁ ዘንድ (አላህ) በርሱ አዘዛችሁ፡፡ የየቲምንም ገንዘብ ብርታቱን (አካለ መጠን) እስኪደርስ ድረስ በዚያች እርሷ መልካም በሆነች ሁኔታ እንጅ አትቅረቡ፡፡ ስፍርንና ሚዛንንም በትክክሉ ምሉ፡፡ ነፍስን ችሎታዋን እንጂ አናስገድድም፤ በተናገራችሁም ጊዜ በዘመዶቻችሁ ላይ ቢሆንም እንኳን (እውነቱን በመናገር) አስተካክሉ፡፡ በአላህም ቃል ኪዳን ምሉ ይኻችሁ ትገሰጹ ዘንድ በርሱ አዘዛችሁ፡፡ ይህም ቀጥተኛ ሲሆን መንገዴ ነው፡፡ ተከተሉትም፡፡ (የጥምመት) መንገዶችንም አትከተሉ፡፡ ከ(ቀጥተኛው) መንገድ እናንተን ይለያዩዋችኋልና፡፡ ይኻችሁ ትጠነቀቁ ዘንድ በርሱ አዘዛችሁ፡፡" (አል-አንአም ፡ 151-153)

የሰው ልጅ ቀናውን ጐዳና በትክክል አይመራም፤ ለዓለማት ጌታ ለአላህ ያለው ፍቅር ለሌሎች ነገሮች ካለው ፍቅር የበለጠ ሆኖ እስካልተገኘ ድረስ፡፡ ይህንንም ለማድረግ የአላህን ታላቅነት ማወቅ የሚገባውን ያህል ማወቅ ይኖርበታል፡፡ ምክንያቱም ሰዎች አላህን ማወቅ የሚገባቸውን ያክል ካላወቁት እንደሚገባው አድርገው ሊገዙት አይችሉምና፡፡ እንዲሁም ከሰይጣን ወጥመድና ከሚያሳድረውም አፍራሽ ተጽዕኖ ለመጠንቀቅ የአላህን ብቸኛ የኃይል ባለቤት መሆን ማወቁ ጠቃሚ ነው፡፡

የአላህ መልእክተኛ (ሰ.ዐ.ወ.) አላህን በማወቅና እርሱንም በመፍራት ታላቅ ተምሳሌትን ለተከታዮቻቸው ትተውልን አልፈዋል፡፡ አንድ አማኝ የቱንም ያህል አላህን የሚፈራ ቢሆን የሚያከናውናቸውን የአምልኮ

ተግባራት በእርሳቸው መንገድ እስካልፈጸመ ድረስ ፈጽሞ ተቀባይነት የለውም፡፡ አላህ በቁርዓኑ እንዲህ ይላል፡-

﴿ لَّقَدۡ كَانَ لَكُمۡ فِي رَسُولِ ٱللَّهِ أُسۡوَةٌ حَسَنَةٞ لِّمَن كَانَ يَرۡجُواْ ٱللَّهَ وَٱلۡيَوۡمَ ٱلۡأٓخِرَ وَذَكَرَ ٱللَّهَ كَثِيرٗا ٢١ ﴾ الأحزاب: ٢١

"ለእናንተ አላህንና የመጨረሻውን ቀን የሚከጅል ለሆነ ሰው አላህንም በብዙ ለሚያወሳ በአላህ መልእክተኛ መልካም መከተል አላችሁ፡፡" (አል-አሕዛብ 21)

የአላህ መልእክተኛ (ሰ.ዐ.ወ.) የሕይወት ፈለግ ለማንኛውም ሙስሊም በቂ ተምሳሌትነት ያለው፣ ለሁሉም የሕይወት ዘርፍ ተስማሚ የሆነም ነው፡፡ በእርግጥም እርሳቸው ይህችን ዓለም ያሳለፉት እንደ መልካም አባወራ፣ ጥሩ የትዳር አጋር፣ተወዳጅ አባት፣ ተስማሚ ጐረቤት፣ እንከን የማይወጣለት ባልደረባ፣ ቅን መሪ ወዘተ... በመሆን ነው፡፡ ስለዚህም በሁሉም እንቅስቃሴዎቻቸው ያሳዩት የነበረው ፈለጋቸው መለኮታዊ ሞገስ የተቸረው ለመሆኑ በቂ ማስረጃዎችን ማቅረብ ይቻላል፡፡ አላህ እንዲህ ይላል፡-

﴿ وَمَآ ءَاتَىٰكُمُ ٱلرَّسُولُ فَخُذُوهُ ﴾ الحشر: ٧

"...መልእክተኛው የሰጣችሁን (ማንኛውም) ነገር ያዙት ፡፡..." (አል-ሐሽር፡ 7)

﴿ قُلۡ إِن كُنتُمۡ تُحِبُّونَ ٱللَّهَ فَٱتَّبِعُونِي يُحۡبِبۡكُمُ ٱللَّهُ وَيَغۡفِرۡ لَكُمۡ ذُنُوبَكُمۡۚ وَٱللَّهُ غَفُورٞ رَّحِيمٞ ٣١ ﴾ آل عمران: ٣١

"በላቸው፡ አላህን የምትወዱ እንደሆናችሁ ተከተሉኝ አላህ ይወዳችኋልና፡፡ ኃጢአቶቻችሁንም ለእናንተ ይምራልና....." (አሊ.ዒምራን፡31)

﴿ لَّقَدۡ كَانَ لَكُمۡ فِي رَسُولِ ٱللَّهِ أُسۡوَةٌ حَسَنَةٞ لِّمَن كَانَ يَرۡجُواْ ٱللَّهَ وَٱلۡيَوۡمَ ٱلۡأٓخِرَ وَذَكَرَ ٱللَّهَ كَثِيرٗا ٢١ ﴾ الأحزاب: ٢١

"ለእናንተ አላህንና የመጨረሻውን ቀን የሚከጅል ለሆነ ሰው አላህንም በብዙ ለሚያወሳ በአላህ መልእክተኛ መልካም መከተል አላችሁ፡፡" (አል-አሕዛብ፡21)

﴿ فَلَا وَرَبِّكَ لَا يُؤۡمِنُونَ حَتَّىٰ يُحَكِّمُوكَ فِيمَا شَجَرَ بَيۡنَهُمۡ ثُمَّ لَا يَجِدُواْ فِيٓ أَنفُسِهِمۡ حَرَجٗا مِّمَّا قَضَيۡتَ وَيُسَلِّمُواْ تَسۡلِيمٗا ٦٥ ﴾ النساء: ٦٥

"በጌታህ (በራሴ) እምላለሁ በመካከላቸው በተከራከሩበት ፍርድ እስከሚያስፈርዱህ፤ ከዚያም ከፈረድከው ነገር በነፍሶቻቸው ውስጥ ጭንቀትን እስከማያገኙ፣ ፍጹም መታዘዝንም እስከሚታዘዙ ድረስ አያምኑም፡፡" (አል-ኒሳእ፡65)

እናም የነቢዩን (ሰ.ዐ.ወ.) መንገድ ትተን ወደ ሌሎች ጐዳናዎች የምንገባ ከሆነ ባዝነን ከመቅረት በስተቀር የምናገኘው ፋይዳ አይኖርም፡፡ ከእርሳቸው ትዕዛዝ ውጪ የሆኑ ነገሮችን መፈጸምም ቢድዓ (ፈጠራ) ነው የሚሆነው፡፡ አዲስ የተፈጠረ ነገር ደግሞ ተቀባይነት የለውም፡፡ ይህን ጉዳይ አጽንኦት ሰጥተው ነቢዩም (ሰ.ዐ.ወ.) እንደሚከተለው በማለት ይናገራሉ፡-

"ማንም (ሰው) በዚህ ጉዳያችን ላይ (በኢስላም) ከእርሱ ያልሆነ አዲስ ነገር ካመጣ (አዲሱ ነገር) ውድቅ ነው፡፡"

የው ልጅ በታሪኩ ብዙ የድንቁርና ዘመናትን አሳልፏል፡፡ በእነዚህ ጊዜያት ከተወሰኑ የአላህ ባሪያዎችና ወዳጆች በስተቀር አብዛኛው የሰው ዘር ለዝንባሌውና ለቁሳዊ ፍላጎቱ ሲያድር ኖሯል፡፡ እነዚያ የአላህ ምርጥ ባሪያዎችና ወዳጆቹ በየተፈጠሩበት ማኅበረሰብ ውስጥ በአርአያነት ሲታዩ የሚከተሉትን ኃላፊነቶች በጫንቃቸው ላይ በማሳረፍ ነው፡-

1. የአላህን አንቀጾች ለሕዝቦቻቸው በማንበብ በሥራ ላይ እንዲውሉ ያደርጋሉ፡፡

2. መጽሓፍንና የኃይማኖት ሕግጋትን ለሕዝቡ ያብራራሉ፣ ሌሎች መንፈሳዊ ጥበባትንም ያስተምራሉ፡፡
3. ሰዎች የፈጣሪያቸውን ሕግጋት ጠብቀው እንዲጸኑ (እስቲቃማህ እንዲኖራቸው) ያበረታታሉ፤ ይህንንም ራሳቸው በሥራ በማዋል ያሳያሉ፡፡

በዚሁ መንገድ ከአባታችን አደም (ዐ.ሰ.) የጀመረው የመለኮታዊ አገዛዝ ሕግ በተሟላና ባማረ ሁኔታ በነቢዩ ሙሐመድ (ሰ.ዐ.ወ.) እስኪደመደም ድረስ ቀጥሏል፡፡

እንግዲህ መልካም ነገሮችን (አመለ ሷሊህ) ለመፈጸም ሁለት ቅድመ ሁኔታዎችን ታሳቢ ማድረግ ተገቢ ነው፡፡

1. የአላህን ትዕዛዛት በአክብሮትና በመተናነስ መፈጸም፡፡
2. የአላህን ውዴታ በመሻትና ለእርሱ ብሎ ለሰው ልጆችም ሆነ ለሌሎች ፍጡራን ደግነትና ርህራሄን ማሳየት እንዲሁም ቸር መሆን፡፡

በሌላ አገላለጽ ቅኑን መንገድ መመራት ማለት ሌላ ሳይሆን አላህንና መልእክተኛውን ከልብ መውደድ፣የእነርሱን ትእዛዛት አቅም በፈቀደ መጠን መፈጸምና ክልከላዎችን ግን ሙሉ በሙሉ ማክበር፣ የነቢዩን (ሰ.ዐ.ወ.) የሕይወት ፊለግ መከተል ማለት ነው፡፡

ከቀናው ጐዳና መዘንበልና ለአላህ ብሎ መልካም ሥራዎችን አለመፈጸም ከሃቅ ማፈንገጥ ነው፡፡ ይህም ከአላህ ፊት ሥራን ዋጋ ያሳጣል፡፡

ይህን በመሰለው ቀናነት ውስጣቸው ከተሞላ የኢስላም የበኩር ልጆች መካከል ሁለተኛው ኸሊፋና አል-ፋሩቅ በመባል የሚታወቁት ኡመር ኢብን አል ኸጣብ (ረ.ዐ.) ይገኙበታል፡፡ የኸሊፋነቱን መንበር ሲቆናጠጡ እንዲህ ብለው ነበር፡-

“ሰዎች ሆይ! ከአላህ መንገድ ባፈነግጥና ወደ ስህተት ብዘነበል ምንድን ነው የምታደርጉት?” በዚህ ጊዜ አንድ በድዊን ተነሳና እንዲህ አላቸው፡-

“ኸሊፋችን ሆይ! ይህን ጉዳይ በተመለከተ ምንም አይጨነቁ፡፡ ቀናውን መንገድ ስተው ጥመትን ከመረጡ በሰይፋችን እናስተካክልዎታለን፡፡”

ይህን በመሰለው መልስ ኡመር (ረ.ዐ.) በመደሰታቸው እንዲህ አሉ፡-

“ጌታዬ ሆይ! ምስጋና የሚገባው ላንተ ነው፡፡ ቀናውን ጐዳና ትቼ የጥመትን መንገድ ብከተል የሚያስተካክለኝ ኡማ (ሕዝብ) በመስጠት ባርከኸኛልና!”

የአላህ መልእክተኛ (ሰ.ዐ.ወ.) ከተከታዮቻቸው መካከል በልባቸው ውስጥ የንፍቅና በሽታ ያለባቸውን ሰዎች ሙስሊሙ ኡማ ይጠነቀቃቸው ዘንድ ለሁዘይፋ ኢብን አል-የማን (ረ.ዐ.) በምስጢር አሳውቀውት ነበር፡፡ ይህን የሰሙት ኡመር (ረ.ዐ.) አንድ እለት ሁዘይፋን እንደሚከተለው በማለት ጠየቁት ፡-

“ሁዘይፋ ሆይ! አንዳች ዓይነት የመናፍቅነት ምልክት በእኔ ላይ ካለ ለአላህ ብለህ ንገረኝ!” ሁዘይፋም (ረ.ዐ.) እንዲህ አለ፡- “የምእመናን አዛዥ ሆይ! ምንም አይነት የሙናፊቅነት ምልክት እንደማይታይብዎት ላረጋግጥልዎት እችላለሁ፡፡”

አል-ሀሰን አል በስሪ ጣውስ ለተባለውና የሐዲስም መምህር ለነበረው ደቀመዝሙራቸው እንዲህ ብለውታል፡-

“ጣውስ ሆይ! ሐዲስን በማስተማርህ ኩራት የሚሰማህ ከሆነ ማስተማሩን ብትተወው ይሻላል፡፡”

ኢማም አል-ገዛሊ ሶስት መቶ የሚሆኑ ተማሪዎቻቸውን በሚያስተምሩበት ጊዜ ከውስጣቸው በተፈጠረው ሃሳብ በጣም ይጨነቁ ነበር፡፡ እናም እንዲህ አሉ፡-

“እነዚህን ተማሪዎች በማስተማሬ የአላህን ውዴታ ነው የፈለግኩት ወይስ የግል ዝናዬን በመካብ ፍቅር ወድቄያለሁ?”
ይህን ካሉ በኋላ አል-ገዛሊ ማስተማራቸውን አቁመውና ሃብታቸውን ሁሉ ለድሆች አከፋፍለው ከሰዎች በመገለል ተቀመጡ፡፡ ያንን

በማድረጋቸውም ይህ ወሰንህ የማይባል የአእምሮ ስክነትን፤ እንዲሁም የተለየ ስብእናን የተላበሰ ገዛሊ ለመሆን ቻሉ፡፡ ከዚያ በኋላ ትተውት የነበረውን የማስተማር ሥራቸውን እንደገና ቀጠሉ፡፡
ሱልጣን ያቩዝ ሳሊም የተባለው የኦቶማን ቱርክ ገዢ ከግብጽ ዘመቻው እንደተመለሰ በኢስታንቡል ከተማ ሕዝቡ በታላቅ አድናቆቱ ሊቀበለው ተሰብስቦ እየተጠባበቀው እንደሆነ ሰማ፡፡ በዚህ ጊዜ ሱልጣኑ ምንም እንኳን ወደ ከተማዋ የተቃረበ ቢሆንም ካሚላ በሚባለው ኮረብታ ግርጌ ሰራዊቱ እንዲያርፍ በማድረግ እዚያው ቆየ፡፡ ያንን ያደረገው ነፍሱ ኩራትንና ማን አለብኝነትን እንዲላበስ ከውስጥ ይጮተጮተው ስለነበር ነው፡፡ ከዚያም ሃሰን ኻን ለተባለው አማካሪው እንዲህ አለው፡-
“እስኪመሽና ሰው ሁሉ ወደየቤቱ ገብቶ እስኪከተት ድረስ እዚሁ እንቆይ፡፡ ከዚያም ወደ ኢስታንቡላችን እንገባለን፡፡ ሰዎች እንዲያጨበጭቡልንና ለምስጋና ተከማችተው እንዲጠብቁን ካደረግን የድሉ ኩራት ልባችንን አሳብጦ መቀመቅ ያወርደናል ብዬ እሰጋለሁ፡፡››
ይህን ካለ በኋላ ሱልጣኑ ከነሰራዊቱ በምስጢር ወደ ከተማው በመግባት የሰውን ግርግርና ጭብጨባ ሊያመልጥ ችሏል፡፡ ከዚህ ሁሉ የምንማረው በሁሉም ጉዳዮቻችን አላህ ከማይወዳቸው መጥፎ ሐሳቦች ልባችንን ማጽዳት አስፈላጊ መሆኑን ነው፡፡
ልባችን (ቀልባችን) የአላህን ውዴታ በመሻት የምንፈጽማቸውን ተግባራት ብቻ ማውጠንጠን ይኖርበታል፡፡ አላህ በቁርዓን የሚነግረንም ይህንኑ ነው፡-

﴿ يَوْمَ لَا يَنفَعُ مَالٌ وَلَا بَنُونَ ﴿٨٨﴾ إِلَّا مَنْ أَتَى ٱللَّهَ بِقَلْبٍ سَلِيمٍ ﴿٨٩﴾ ﴾ الشعراء: ٨٨ - ٨٩

“ገንዘብም፣ ልጆችም በማይጠቅሙበት ቀን፣ ወደ አላህ በንጹህ ልብ የመጣ ሰው ቢሆን እንጅ፡፡” (ሹዐራ፡88-89)
መልእክተኛውም (ሰ.ዐ.ወ) ከዚሁ ጋር የሚቀራረብ አባባላቸውን እንደሚከተለው ያስቀምጣሉ፡-
“በእውነቱ አላህ የሚያየው መልካችሁን ወይም ገንዘባችሁን ሳይሆን ልባችሁንና ሥራችሁን ነው፡፡›› (ሶሂህ ሙስሊም)

ምዕራፍ አራት

ከሷሊሆች እና ከእውነተኞች ጋር መሆን

አነስ ኢብኑ ማሊክ (ረ.ዐ.) ባወሩት ሐዲስ ነቢዩ (ሰ.ዐ.ወ.) እንዲህ ብለዋል፡-

“በምድር ላይ በህብረት ሆነው አላህን የሚያወሱ (ዚክር የሚያደርጉ) ሰዎችን የሚያስሱ መላእክት አሉ፡፡ የሚፈልጉትን እንዳገኙም ያንን ቦታ ያካብቡና እንዲህ ይላሉ፡-

“ጌታችን ሆይ! እነዚህ ሰዎች (ባሪያዎችህ) ያንተን መጽሐፍ እያነበቡ የዚህንም ሆነ የመጪውን ዓለም ሁኔታቸውን እንድታሳምርላቸው ይጠይቃሉ፡፡”

በዚህ ጊዜ ኃያሉ አላህ እንዲህ ይላል፡-

“እናንተ ምስክሮቼ ናችሁ፤ ሁሉንም ምሬያቸዋለሁ፡፡” መላእክቱም ይላሉ፡-

“ጌታችን ሆይ ! እገሌና እገሌ እዚህ ስብስብ ውስጥ የገቡት በአጋጣሚ እንጅ አስበውበት አይደለም፡፡››

አላህም፡- “ከሷሊሆችና እውነተኞች ጋር አብረው ያሉ ሁሉ እድለቢሶች አይደሉም፡፡” በማለት ይመልስላቸዋል፡፡

ከዚህ በላይ በቀረበው ሐዲስ ውስጥ የተጠቀሰው መልእክት ከደጋግና ቅን የአላህ ባሪያዎች ጋር መሆን ትሩፋት እንደሚያስገኝ የምስራች ይናገራል፡፡ የሰው ልጅ ልብ (ቀልብ) በተፈጥሮው ከአካባቢዋ (አቀማመጧ) ጋር የመመሳሰል ባሕሪ አላት፡፡ ይህም ሁኔታ የሚያሳየው የሰው ቀልብ ለመልካምም ሆነ ለእኩይ ሁኔታዎች ተጋላጭ መሆኗን ነው፡፡ የሰው ልጅ ልብ (ቀልብ) ትክክለኛ የሆነውን ኃይማኖታዊ እውቀት የማታገኝ ከሆነና ቁጥጥርም ካልተደረገባት ታላቅ የሆነ አደጋ ይደቀንባታል፡፡

ከአላህ ደጋግ ባሪያዎችና ከእውነተኞች ጋር መሆን፣ ከእነርሱም ጋር መቀማመጥ የአንድን ሰው መንፈሳዊ ጥንካሬ ያሳድጋል፡፡ ይህም ይበልጥ የሚሳካው ሰዎቹ እርስበርሳቸው ለአላህ ብለው የሚዋደዱና በዓለማዊ ጥቅም ያልተሳሰሩ ከሆነ ነው፡፡

በነቢዩ (ሰ.ዐ.ወ.) ዙሪያ ይሰባሰቡ የነበሩት የኢስላም የበኩር ልጆች ለዚህ አባባል ጥሩ ማሳያዎች ሆነው ያገለግላሉ፡፡ ተዝቆ የማያልቀውንና ከመለኮታዊ የእውቀት ማእድ እየተጨለፈ የሚመጣውን የነቢዩን (ሰ.ዐ.ወ.) ንግግር ፍጹም በሆነ አንክሮ ነበር የሚከታተሉት፡፡ ይህንን ጉዳይ አስመልክቶ አንድ ባልደረባቸው ሲገልጽ እንዲህ ይላል፡-

"የነቢዩን (ሰ.ዐ.ወ.) ንግግር ስናዳምጥ በከፍተኛ ጥንቃቄ ከመሆኑ የተነሣ በአንዳችን ራስ ላይ ወፍ የተቀመጠችና ትንሽ ብንንቀሳቀስ የምትበር እስኪመስለን ድረስ እንመሰጣለን፡፡"

በምድረ በዳ ላይ ክፉኛ በፀሐይ የደረቀ ተክል ከሰማይ ካፊያ ሲወርድ እንደሚለመልም ሁሉ የአላህ መልእክተኛ (ሰ.ዐ.ወ.) ያፈሱት የነበረው ጣፋጭ ንግግር የተከታዮቻቸውን ልብ ያረሰርሰው ነበር፡፡ ይህም ጥበብንና እዝነትን ያጣመረ ኩትኮታ (ተርቢያ) ዓለም ከዚያ በፊት አይቶት የማያውቀውንና አምሳያ ያልተገኘለትን ምርጥ ትውልድ አስገኘ፡፡ ሴትን ልጅ ከነነፍሷ የሚቀብረውና ሌሎች ዓረመኔያዊ ድርጊቶችን የሚፈጽመው መሐይም ማሕበረሰብ በአስደናቂ ሁኔታ ተለወጠ፡፡ በምድረበዳው ለዘመናት ተንሰራፍቶ የነበረው ጃሂሊያም (የድንቁርና ሥርዓት) ተንኮታኮተ፡፡ በዘመነ ድንቁርና (ጃሂሊያ) የኖሩ ሰዎችም የአውሬትና አረመኔያዊ ድርጊታቸውን አራግፈው በመጣል አልቃሾች፣ ትሁታን ፣ከራሳቸው ይልቅ ለሌሎች የሚያስቡ፣ መልካም ሰዎች ሆኑ፡፡

ከዚያ በኋላ በየትኛውም የምድር ጫፍ ቢሄዱ የነቢዩን (ሰ.ዐ.ወ.) አርአያነት የሚያራምዱ ሆኑ፡፡ የሰው ልጅ ስብዕና የመጨረሻውን የምጥቀት ጫፍ ተቆናጠጠ፡፡ ይህንኑ ሰብዓዊ ምጥቀት ያስተዋለው የዓለማቱ ጌታ ለዚያ ምርጥ ትውልድ የሚከተለውን ውዳሴ ችሮታል፡-

﴿ وَٱلسَّٰبِقُونَ ٱلۡأَوَّلُونَ مِنَ ٱلۡمُهَٰجِرِينَ وَٱلۡأَنصَارِ وَٱلَّذِينَ ٱتَّبَعُوهُم بِإِحۡسَٰنٖ رَّضِيَ ٱللَّهُ عَنۡهُمۡ وَرَضُواْ عَنۡهُ وَأَعَدَّ لَهُمۡ جَنَّٰتٖ تَجۡرِي تَحۡتَهَا ٱلۡأَنۡهَٰرُ خَٰلِدِينَ فِيهَآ أَبَدٗاۚ ذَٰلِكَ ٱلۡفَوۡزُ ٱلۡعَظِيمُ ١٠٠ ﴾ التوبة: ١٠٠

"ከስደተኞቹ ከረዳቶቹም ሲሆኑ የመጀመሪያዎቹ ቀዳሚዎችና እነዚያም በበጐ ሥራ የተከተሏቸው አላህ ከእነርሱ ወዷል፡፡ ከርሱም ወደዋል፡፡ በሥሮቻቸው ወንዞች የሚፈሱባቸውን ገነቶች በውስጣቸው ዘለዓለም ነዋሪዎች ሲሆኑ ለእነርሱ አዘጋጅቶላቸዋል፡፡ ይህ ታላቅ እድል ነው፡፡ " (አት-ተውባህ፡ 100)

ቁጥራቸው የበዛ የነቢዩ ተከታዮች በዙሪያቸው በመሰባሰብ ከእርሳቸው ንግግር፣ ድርጊትና እንቅስቃሴ በየጊዜው ትምህርት ይቀስሙ ነበር፡፡ ሙስሊሞች ይህን የመሰሉ በነቢዩ (ሰ.ዐ.ወ.) ዙሪያ የሚደረጉ መሰባሰቦች የጀነት ጨፌዎች መሆናቸውን ከተወዳጁ መሪያቸው (ሰ.ዐ.ወ.) አፍ ሰምተው ስለነበር ሁሌም ሊያገኟቸው ይረባረቡ ነበር፡፡ ይህን ያደርጉ የነበረው ቀልብን በብርሃን ማስጌጥና ፀባይን (አኽላቅን) ማሳመር የሚቻለው በዚያ መንገድ ብቻ መሆኑንም በሚገባ ያምኑ ስለነበር ነው፡፡

አንድ አማኝ የሆነ ሰው በመንፈሳዊ ጥንካሬው ላይ አሉታዊ ተጽእኖ እንዳያርፍበት ከፈለገ ግዴለሽና ኃጢአተኛ ከሆኑ ሰዎች ጋር ያለውን ቁርኝት ማጥፋት ይጠበቅበታል፡፡ ምክንያቱም እንደዚህ አይነት ሰዎች ከበዙበት አካባቢ የሚገኘው ነፋስ ቀፋፊና አመጽ የተሞላበት ነውና፡፡

ሸይኽ ኡበይዱላህ የተባሉ ሰው ባልደረቦቻቸውን ሲመክሩ " ከኃጢአተኞች ጋር መሆን የመንፈስ ጭንቀትን፣ ሃዘንን እና የልብ አለመረጋጋትን ያመጣል" ብለዋል፡፡

ከነቢዩ (ሰ.ዐ.ወ.) የሕይወት ተሞክሮ የምንቀስመው ሌላ ትምህርት አለ፡፡ አንድ ቀን በአረፋትና በሙዝደሊፋ መካከል በሚገኝ ሙሃሲር የተባለ ሸለቆ ነቢዩ (ሰ.ዐ.ወ.) ፈጠን ፈጠን እያሉ መራመድ ጀመሩ፡፡ በዚህ ድርጊታቸው የተደነቁት ባልደረቦቻቸው "የአላህ መልእክተኛ ሆይ! በድንገት ለምንድን ነው ጥለውን የገሰገሱት?" ተብለው ሲጠየቁ እንዲህ

በማለት መልስ ሰጡ፡- “አምባገነኑን አብረሃንና ሰራዊቱን አላህ ዶግ አመድ ያደረጋቸው በዚህ ቦታ ላይ ነው፡፡”

በሌላ አጋጣሚም ነብዩ (ሰ.ዐ.ወ.) ከተቡክ ዘመቻ ሲመለሱ ባልደረቦቻቸው በጣም በመዳከማቸው እረፍት ለማድረግ ፈለጉ፡፡ ስለሆነም በአንድ ወቅት ሰሙድ የሚባሉት አመጸኛ ሕዝቦች ከትመውበት ከነበረው ቦታ ላይ ሲደርሱ እረፍት ለመውሰድ ቆም አሉ፡፡ በዚህ ጊዜ ነብዩ (ሰ.ዐ.ወ.) እንዲህ አሉ፡- “ ኃያሉ አላህ የሰሙድን ሕዝቦች ያወደማቸው በዚህ ቦታ ላይ ነው፡፡ ስለሆነም ምንም ዓይነት ጠብታ ውሃ ከዚህ አትቅዱ፡፡ እርግማናቸው (ጦሳቸው) እንዳይነካችሁ፡፡”

ሆኖም ግን ተከታዮቻቸው፡- “የአላህ መልእክተኛ ሆይ! እኛ በዚህ ውሃ ዱቄታችንን አቡክተናል፡፡ እንዲሁም የውሃ ኮሮጆዎቻችንንም ሞልተናል፡፡” አሏቸው፡፡ በዚህን ጊዜ ነብዩ (ሰ.ዐ.ወ.) ሊጡን ለግመሎቻቸው እንዲያበሏቸውና ውሃውን ግን እንዲደፉት አዘዟቸው፡፡ (ቡኻሪ፡ ኪታቡል አንቢያ፡ 17)

አቡ በከር (ረ.ዐ.) ነብዩን (ሰ.ዐ.ወ.) በጣም ይወዷቸው ነበር፡፡ ለነብዩ (ሰ.ዐ.ወ.) የነበራቸው ፍቅር እርሳቸው ባጠገባቸው እያሉ እንኳን ግለቱ የሚበርድ አልነበረም፡፡ ለአንድ ዘመቻ መልእክተኛው (ሰ.ዐ.ወ.) የገንዘብ መዋጮ ባስፈለጋቸው ጊዜ አቡበከር (ረ.ዐ.) ያላቸውን ገንዘብ በሙሉ አምጥተው አስረከቡ፡፡ ነብዩም (ሰ.ዐ.ወ.) በዚህ አድራጐታቸው ልባቸው ተነካ፡፡ ይህ የሁለቱ ሰዎች ጓደኝነትና ፍቅር ከሞላ ጐደል የእድሜ ልክ ነበር ማለት ይቻላል፡፡ የአላህ መልእክተኛ (ሰ.ዐ.ወ.) ለአቡበከር ያላቸውን አምሳያ የሌለው ፍቅር ሲገልጹ “ ከአላህ ሌላ ወዳጅ (ኸሊል) የምይዝ ቢሆን ኖሮ አቡበከርን ወዳጅ አድርጌ እይዘው ነበር፡፡” ብለዋል፡፡ ለመሞት ጥቂት ጊዜያት ብቻ ቀርቷቸው በነበረበት ጊዜም “የመስጊዱ በሮች በሙሉ ከአቡበከር በር በስተቀር ይዘጉ” በማለት ለእርሳቸው ያላቸውን ክብር ገልፀዋል፡፡

ምዕራፍ አምስት

መልካም ሥራን በቅንነት (ኢኽላስ) መስራት

ኢኽላስ ማለት መልካም ሥራን የአላህን ውዴታ ብቻ በመሻት መሥራት ሲሆን ፍሬውም ኢህሳን ነው፡፡ ስለ ኢህሳን ጂብሪል ነብዩን (ሰ.ዐ.ወ.) በአንድ ረዥም ሐዲስ ላይ ጠይቋቸው ነበር፡፡ “….ስለ ኢህሳን ንገረኝ” አላቸው፡፡ “ አላህን እንደምታየው አድርገህ ልትገዛው ነው፡፡ አንተ ባታየው እርሱ ያይሃልና፡፡” አሉት፡፡

አላህ ኢኽላስን አስመልክቶ የተለያዩ የቁርዓን አንቀጾችን ያወረደ ሲሆን የሚከተሉት ጥቂቶቹ ናቸው፡-

﴿ وَمَآ أُمِرُوٓاْ إِلَّا لِيَعۡبُدُواْ ٱللَّهَ مُخۡلِصِينَ لَهُ ٱلدِّينَ حُنَفَآءَ وَيُقِيمُواْ ٱلصَّلَوٰةَ وَيُؤۡتُواْ ٱلزَّكَوٰةَۚ وَذَٰلِكَ دِينُ ٱلۡقَيِّمَةِ ٥ ﴾ البينة: ٥

“አላህን ኃይማኖትን ለእርሱ ብቻ አጥሪዎቹ ቀጥተኞች ሆነው ሊገዙት፣ ሶላትንም አስተካክለው ሊሰግዱ፣ ዘካንም ሊሰጡ እንጂ ያልታዘዙ ሲሆን (ተለያዩ)፡፡ ይህም የቀጥተኛይቱ (ኃይማኖት) ድንጋጌ ነው፡፡” (አል-በይናህ፡5)

﴿ لَن يَنَالَ ٱللَّهَ لُحُومُهَا وَلَا دِمَآؤُهَا وَلَٰكِن يَنَالُهُ ٱلتَّقۡوَىٰ مِنكُمۡۚ ﴾ الحج: ٣٧

“አላህን ሥጋዎቿም ደሞቿም ፈጽሞ አይደርሰውም ግን ከእናንተ የሆነ ፍራቻ ይደርሰዋል፡፡…..” (አል-ሐጅ፡ 37)

﴿ قُلۡ إِن تُخۡفُواْ مَا فِي صُدُورِكُمۡ أَوۡ تُبۡدُوهُ يَعۡلَمۡهُ ٱللَّهُۗ ﴾ آل عمران: ٢٩

“በደረቶቻችሁ ውስጥ ያለውን ነገር ብትደብቁ ወይም ብትገልጹት አላህ ያውቀዋል (በል)፡፡ (አሊ-ዒምራን፡29)

አምር ኢብን ለይጥ የኩራሳን ጦር አዛዥ ነበር፡፡ ከሞተ በኋላ አንድ አላህን የሚፈራ ሰው በሕልሙ አይቶት የሚከተለውን ጥያቄ አቀረበለት፡
፡

“አላህ ያደረገልህ አቀባበል እንዴት ነው?”

“ሁሉንም ኃጢአቶቼን ምሮኛል”

“እንዴት ሊምርህ ቻለ?”

አምር እንዲህ በማለት መልስ ሰጠ፡፡

“አንድ እለት በሆነ ትልቅ ዳገት ላይ ወጥቼ ሰራዊቴን ቁልቁል እመለከት ነበር፡፡ ጥንካሬአቸውና የቁጥራቸው መብዛት ታላቅ የሆነ እርካታ እንዲሰማኝ አደረገኝ፡፡ ከዚያም ለራሴ እንዲህ አልኩ፡- “ነብዩ (ሰ.ዐ.ወ.) በተዋጉባቸው የጦር አውዶች ተገኝቼ ቢሆን ኖሮ በዚያ ቀውጢ ሰአታቸው ይህን በመሰለ ሰራዊቴ እየተረዳሁ ጠላታቸውን ድባቅ እመታላቸው ነበር፡፡” ይህን የመሰለ እድሜ ልኬን አብሮኝ የኖረ ምኞት ነበረኝ፡፡ በዚህ ኢክላስ ባለው አስተሳሰቤና ፍላጐቴ ምክንያት ኃያሉ አላህ ኃጢአቶቼን ምሮ ለታላቅ ሽልማት አብቅቶኛል፡፡”

ይህ አጋጣሚ ንያን (እሳቤን) ለአላህ ብሎ ማጥራትና ሥራንም በፍጹም ቅንነት (ኢክላስ) መከወን ከአላህ ዘንድ ምን ያህል ታላቅ ደረጃ እንዳለው ያሳያል፡፡ ይህን አስመልክቶ ነብዩ (ሰ.ዐ.ወ.) የሚከተለውን መናገራቸውን ኡመር ኢብን አል ኸጣብ (ረ.ዐ.) አስተላልፈዋል፡-

“የአንድ ሰው ተግባር የሚለካው በቁርጠኛ ፍላጐቱ (በንያው) ነው፡፡ ማንኛውም ሰው እንደ ሃሳቡ (ንያው) ያገኛል፡፡ ስደቱ አላህንና ነብዩን ለማስደሰት ዓላማ ከሆነ ስደቱ ወደ አላህና መልእክተኛው ነው፤ የተሰደደው ዓለማዊ ጥቅም ለማግኘት ወይም ሴት ለማግባት ከሆነ ስደቱ ለተሰደደበት ነገር ነው፡፡”

ስለሆነም አንድን ሥራ ከመስራታችን በፊት ሃሳባችንን (ንያችንን) ቆም ብለን መመርመር አለብን፡፡ በምንሰራው ሥራ ለማስደሰት ያሰብነው ከአላህ ሌላ የሆነን አካል ከሆነ ያንን ነገር አቁመን ተውበት በማድረግ

አላህን የሚያስደስተውን ነገር ብቻ መፈጸም ይኖርብናል፡፡ ይህም ኢኽላስ (ፍጹም ተነሳሽነት) ተብሎ ሊገለጽ ይችላል፡፡ በዚህ ትንታኔ መሠረት ሥራ ልክ እንደ አካል ሲሆን እሳቤ (ንያ) ደግሞ እንደ ነፍስ (ሩህ) ሊቆጠር ይችላል፡፡ ስለሆነም ነፍስ ከታመመች አካልም አብሮ ይታመማል ማለት ነው፡፡

በዚህ ስሌት መሠረት ሶላት፣ ጾም፣ ሰደቃም ሆነ ማንኛውም የአምልኮት ተግባር በጥሩ እሳቤ (ንያ) የማይከወን ከሆነ ከአላህ ዘንድ ተቀባይነት የሌለው ብቻ ሳይሆን ሰሪውንም ያስጠይቃል፡፡ ምክንያቱም በሚፈጽመው አምልኮ አላህን ብቻ ለማስደሰት ከማለም ይልቅ ከእርሱ ውጭ የሆነን አካል ለማስደሰት አልሟልና፡፡ ይህም ሽርክ (ማጋራት) የተባለውን ኃጢአት ከመፈጸም ያስፈርጃል፡፡ ስለሆነም ይህን ዓይነት ድርጊት የሚፈጽሙ ሰዎች የሚተርፋቸው ነገር ድካም ብቻ ነው ማለት ነው፡፡ በሌላ በኩል አንድ ሰው አላህን ለማስደሰት በመሻት ሌላው ቀርቶ አነስተኛ የሚባሉ ነገሮችን ቢፈጽም እንኳን ምንዳ ማግኘቱ አይቀርም፡፡

የሰው ልጅ በተወሰነ መልኩም ቢሆን ከሌሎች እንስሳት ጋራ የሚጋራው ደመ ነፍሱን (ዝንባሌውን) የመከተል አዝማሚይ ይታይበታል፡፡ ሰው በመሠረቱ ከእነዚህ እንስሳት የሚለየው ይህን ዝንባሌውን በቁጥጥሩ ስር ለማድረግ የሚያስችለው አቅም የተቸረ በመሆኑ ነው፡፡ ይህም ሁኔታው የአደምን ዘር በሌሎች ፍጡራንና በራሷም በተፈጥሮ ላይ እንዲሰለጥን በአላህ በራሱ የተሰጠው ደረጃ መሆኑን ያሳያል፡፡ እንግዲህ የሰው ልጅ ይህን ስልጣን በእጁ እንዲይዝ ሲደረግ በሌላ በኩል ደግሞ ዓለማዊ ጉዳዮቹን ለአብነት ያክል መተኛት፣ መብላት መጠጣት ማግባትና ልጆችን መውለድን በተመለከተ ሁሉን ለአላህ ፈቃድ ማስገዛት የግድ ይሆንበታል፡፡ እነዚህንና ሌሎችንም ድርጉቶቹን ሲከውን ከፈጣሪው ምንዳ ሊያስገኙለት በሚያስችለው መልኩ መሆን ይኖርበታል፡፡

አማኝ የሆነ ሰው ምንጊዜም ልቦናውን ከራስ ወዳድነት ማንጻትና የአላህን ውዴታ መሻት ይጠበቅበታል፡፡ ኒያን የማጥራት (ኢኽላስ) መጨረሻው ኢህሳን ነው ብለናል፡፡ ኢህሳን ማለት አንድ ሰው ማንኛውንም ነገር አላህን እንደሚያየው አድርጎ መስራት ማለት ሲሆን

እኔ ባላየውም እርሱ ያየኛል ብሎ ማሰብን ያመላክታል። አላህ እንዲህ ይላል፡-

﴿ إِنَّآ أَنزَلۡنَآ إِلَيۡكَ ٱلۡكِتَٰبَ بِٱلۡحَقِّ فَٱعۡبُدِ ٱللَّهَ مُخۡلِصٗا لَّهُ ٱلدِّينَ ٢ أَلَا لِلَّهِ ٱلدِّينُ ٱلۡخَالِصُۚ ٣ ﴾ الزمر: ٢ - ٣

"እኛ ወደ አንተ መጽሐፉን በእውነት አወረድነው አላህንም ኃይማኖትን ለእርሱ ብቻ ያጠራህ ሆነህ ተገዛው። ንቁ! ፍጹም ጥሩ የሆነው ኃይማኖት የአላህ ብቻ ነው።...." (አዝ-ዙመር፡

﴿ قُلۡ إِنِّيٓ أُمِرۡتُ أَنۡ أَعۡبُدَ ٱللَّهَ مُخۡلِصٗا لَّهُ ٱلدِّينَ ١١ ﴾ الزمر: ١١

"እኔ አላህን ኃይማኖትን ለእርሱ ያጠራሁ ሆኜ እንድገዛው ታዘዝኩ በል፡፡" (አዝ-ዙመር፡11)

ኢብሊስ (ሰይጣን) ከመለኮታዊ ባለሟልነቱ ሲባረር እንዲህ ብሎ ነበር፡-

﴿ قَالَ رَبِّ بِمَآ أَغۡوَيۡتَنِي لَأُزَيِّنَنَّ لَهُمۡ فِي ٱلۡأَرۡضِ وَلَأُغۡوِيَنَّهُمۡ أَجۡمَعِينَ ٣٩ إِلَّا عِبَادَكَ مِنۡهُمُ ٱلۡمُخۡلَصِينَ ٤٠ ﴾ الحجر: ٣٩ - ٤٠

"(ኢብሊስ) አለ፡- ጌታዬ ሆይ! እኔን በማጥመምህ ይሁንብኝ፡፡ ለእነርሱ በምድር ላይ (ኃጢአትን) እሸልምላቸዋለሁ፡፡ ሁሉንም አጠማቸውማለሁ፡ ፡ ከእነርሱ ፍጹሞቹ ባሮችህ ብቻ ሲቀሩ፡፡" (አል-ሒጅር፡ 39-40)

በዚህ አንቀጽ አላህ በግልጽ የሚነግረን ቅንነትን (ኢኽላስ) በተላበሱ ባሮቹ ላይ ኢብሊስ ምንም ዓይነት ሥልጣን የሌለው መሆኑን ነው፡፡ ከእነርሱ ውጭ የሆኑ ሌሎች ሙስሊሞችና ሌሎች ሕዝቦች ግን በታላቅ አደጋ ላይ ናቸው፡፡

ፍጹም ምዕመናን በሆኑት ባሮቹ ላይ ኢብሊስ ሥልጣን የሌለው መሆኑን አላህ ሲናገር እንዲህ ይላል፡-

﴿ قَالَ هَٰذَا صِرَٰطٌ عَلَيَّ مُسۡتَقِيمٌ ٤١ إِنَّ عِبَادِي لَيۡسَ لَكَ عَلَيۡهِمۡ سُلۡطَٰنٌ إِلَّا مَنِ ٱتَّبَعَكَ مِنَ ٱلۡغَاوِينَ ٤٢ ﴾ الحجر: ٤١ - ٤٢

“ (አላህም) አለ፡- ይህ በእኔ ላይ (መጠበቁ የተገባ) ቀጥተኛ መንገድ ነው፡፡ እነሆ ባሮቼ በእነርሱ ላይ ላንተ ሥልጣን የለህም፡፡ ከጠማሞቹ የተከተለህ ሰው ብቻ ሲቀር፡፡” (አል-ሒጅር፡41-42)

በሱራ አል ኢስራእ አንቀጽ 65 ላይ ይህ ሃቅ እንዲህ ተገልጾ እናገኘዋለን፡-

﴿ إِنَّ عِبَادِي لَيۡسَ لَكَ عَلَيۡهِمۡ سُلۡطَٰنٌۚ وَكَفَىٰ بِرَبِّكَ وَكِيلٗا ٦٥ ﴾ الإسراء: ٦٥

“ባሮቼ በእነርሱ ላይ ፈጽሞ ለአንተ ስልጣን የለህም፡፡ መጠጊያም በጌታህ በቃ፡፡” (አል-ኢስራእ፡65)

አንድ ወጣት የንጉሱን ልጅ በር በማንኳኳት እንደሚወዳት ነገራት፡፡ እርሷም አንድ ሺህ ዲርሃም ወስዶ ከአጠገቧ ዘወር እንዲል ነገረችው፡፡ ይህ ወጣት ተስፋ ባለመቁረጥ ወደ ልጅቷ ቤት እንደገና መጣ፡፡ አሁንም አንድ ሺህ ዲርሃም ወስዶ ዘወር እንዲልና እንዳይረብሻት ነገረችው፡፡ እንዲህ እንዲህ እያለ በመጨረሻ ከእርሷ አጠገብ ላለመድረስ አስር ሺህ ብር እንዲከፈለው ተስማማ፡፡ ይሁን እንጂ የንጉሱ ልጅ ዋነኛ ፍላጐት ልጁ በትክክል ይወዳትና አይወዳት እንደሆነ ለመፈተን ነበር፡፡ “አንተ ግን ምን ዓይነት ፍቅር ቢሆን ነው ከእኔ ይልቅ ገንዘብን እንድትመርጥ ያደረገህ?“ ካለች በኋላ “ከእኔ ይልቅ ሌላን ነገር አስበልጦ የወደደን ሰው በምን እንደምቀጣው ታቃለህ?” በማለት ጠየቀችው፡፡ ከዚያም ወታደሮቿን በማዘዝ ለእርሷ ፍቅር ታማኝ ያልሆነውን ያንን ወጣት እንዲገድሉት አደረገች፡፡

ይህን ታሪክ ያዳመጠ አንድ ሙስሊም መንፈሳዊ ሰው ህሊናውን ሳተና ወደቀ፡፡ ከዚያም ሲነቃ ለጓደኞቹ እንዲህ አላቸው፡- “ተመልከቱ፣ የሃሰት ፍቅር በዚህ ዓለም ላይ የሚያስከፍለውን እዳ፡፡ አላህን እንወደዋለን

እያሉ ሆኖም ግን በማይረባ ነገር የእርሱን ውዴታ የሚቀይሩ ሰዎች በመጪው ዓለም ከሚገጥማቸው ቅጣት ጋር አነጻጽሩት፡፡”

ከሁሉም በላይ በማንኛውም አምልኮት ውስጥ እንደ ፍጹምነት (ኢኽላስ) ውድ የሆነ ነገር የለም፡፡ ይህንንም ሁኔታ አላህ በቁርአን ሲገልፀው እንዲህ ይላል፡-

﴿ إِنَّكُمۡ لَذَآئِقُواْ ٱلۡعَذَابِ ٱلۡأَلِيمِ ٣٨ وَمَا تُجۡزَوۡنَ إِلَّا مَا كُنتُمۡ تَعۡمَلُونَ ٣٩ إِلَّا عِبَادَ ٱللَّهِ ٱلۡمُخۡلَصِينَ ٤٠ أُوْلَٰٓئِكَ لَهُمۡ رِزۡقٞ مَّعۡلُومٞ ٤١ فَوَٰكِهُۖ وَهُم مُّكۡرَمُونَ ٤٢ ﴾ الصافات: ٣٨ - ٤٢

“እናንተ አሳማሚውን ቅጣት በእርግጥ ቀማሾች ናችሁ፡፡ ትሰሩትም የነበራችሁትን እንጂ ሌላን አትመነዱም፡፡ ግን ምርጥ የሆኑት የአላህ ባሮች (ቅጣትን አይቀምሱም)፡፡ እነዚያ ለእነርሱ የታወቀ ሲሳይ አላቸው፡፡ ፍራፍሬዎች (አሏቸው) እነርሱም የተከበሩ ናቸው፡፡” (አስ-ሷፋት፡ 38-42)

﴿ يَٰٓأَيُّهَا ٱلَّذِينَ ءَامَنُواْ عَلَيۡكُمۡ أَنفُسَكُمۡۖ لَا يَضُرُّكُم مَّن ضَلَّ إِذَا ٱهۡتَدَيۡتُمۡۚ إِلَى ٱللَّهِ مَرۡجِعُكُمۡ جَمِيعٗا فَيُنَبِّئُكُم بِمَا كُنتُمۡ تَعۡمَلُونَ ١٠٥ ﴾ المائدة: ١٠٥

“እናንተ ያመናችሁ ሆይ! ነፍሶቻችሁን (ከእሳት) ያዙ (ጠብቁ)፡፡ በተመራችሁ ጊዜ የተሳሳተ ሰው አይጐዳችሁም፡፡ የሁላችሁም መመለሻ ወደ አላህ ብቻ ነው፡፡ ትሰሩትም የነበራችሁትን ሁሉ ይነግራችኋል፡፡” (አል-ማኢዳህ፡105)

ፍጹምነት (ኢኽላስ) ከአላህ ጋር ምንንም ማንንም ተጋሪ ከማድረግ ይጠብቀናል፡፡ እንዲሁም አላህን በማምለክ ሂደት ላይ አለማዊ ጥቅማጥቅሞችን ታሳቢ በማድረግ ከመንቀሳቀስ ይታደገናል፡፡ ስለሆነም ፍጹምነትን የተላበሱ ስራዎች መጥፎ ሐሳቦችን (ንያዎች) የሚደመስሱ እንደመሆናቸው ከደምና ፈርስ መካከል ተጨምቆ እንደወጣ ወተት የተጣሩ ናቸው፡-

﴿ وَإِنَّ لَكُمْ فِي ٱلْأَنْعَٰمِ لَعِبْرَةً ۖ نُّسْقِيكُم مِّمَّا فِي بُطُونِهِۦ مِنۢ بَيْنِ فَرْثٍ وَدَمٍ لَّبَنًا خَالِصًا سَآئِغًا لِّلشَّٰرِبِينَ ﴿٦٦﴾ ﴾ النحل: ٦٦

"ለእናንተም በግመል፣በከብት፣ በፍየል በእርግጥ ትምህርት አለላችሁ፡፡ በሆዶቹ ውስጥ ካለው ከፈርስና ከደም መካከል ጥሩ ወተትን ለጠጪዎች ጣፋጭ ሲሆን እናጠጣችኋለን፡፡" (አን-ነሕል፡66)

ከላይ የቀረበውን የቁርአን አንቀጽ አስመልክተው የቁርአን ተንታኞች ሲናገሩ ወተት ከደምና ፈርስ መካከል ተጨምቆ እንደሚወጣ ሁሉ ኢኽላስ ደግሞ ከአላህ ሌላ የሆኑ ጥቅማጥቅሞችን ለማግኘት ብሎ ሥራን ከመሥራት ይጠብቃል (ያጠራል)፡፡

የአላህ ነብይ የነበሩት ሙሣ (ዐ.ሰ.) ከነገደ እስራኤል ሰባ የሚሆኑ አማኞችን እንዲመርጡ አላህ አዘዛቸው፡፡ እርሳቸውም ይህን ትእዛዝ ለሕዝባቸው ሲገልጹ ሶስት ሰዎች በራሳቸው ፈቃድ አላህን ፈሪና ጥሩ ንያ እንዳላቸው በመቁጠር ከሕዝቡ ተነጥለው ወጡ፡፡ በዚህ ጊዜ ለነብዩ ሙሣ (ዐ.ሰ.) ወህይ የወረደላቸው ሲሆን የወህዩ መልእክት "እነዚያ ሶስት ሰዎች ከሕዝቡ ሁሉ ከእኔ የራቁ ናቸው፡፡ ምክንያቱም ራሳቸውን እንደ ቅዱስና እውነተኛ ቆጥረዋልና!›› የሚል ነበር፡፡

ነብዩ ዒሣ (ዐ.ሰ.) በበኩላቸው ፍጹማዊነትን (ኢኽላስ) የተላበሰ መልካም ሥራ ምን እንደሆነ ተጠይቀው፡- "ምንም እይነት ዓለማዊ ጥቅምን ሳይጠብቁ ለአላህ ብሎ መሥራት ነው" በማለት መልሰዋል፡፡

ለመሆኑ የኢኽላስ ታላቁ ጠላት ምንድን ነው! መናፍቅነት፣ ልታይ ልታይ ባይነት፣ አላህን ከማስደሰት ይልቅ መልካም ሥራን በመሥራት ዓለማዊ ጥቅምን መሻት ናቸው፡፡ ከአላህ ሌላ የሆነ አካል እንዲወድልን፣ እንዲያይልን ወይም እንዲያመሰግነን በመሻት የምንሰራ ከሆነ ይህ ድብቅ የሆነ ማጋራት (ሽርክ) ነው፡፡ ከዚህ በታች በሚቀርበው ሐዲስ የምንገነዘበው ቁምነገር የመናፍቅነትና የእዩልኝ ባይነት (ሪያእ) አስከፊ ውጤት ምን እንደሆነ ነው፡፡

ከአቡ ሁረይራ በተወራውና ሙስሊም በዘገቡት ሐዲስ የአላህ መልእክተኛ (ሰ.ዐ.ወ.) እንዲህ ብለዋል፡- “ሶስት ዓይነት ሰዎች በፍርዱ ቀን ከሰው ሁሉ በፊት አላህ የእነርሱን ጉዳይ ይፈርዳል፡፡ የመጀመሪያው ሰማእት (ሸሂድ) በመሆን የተገደለ ሲሆን አላህ ፊት እንዲቆም ይደረግና አላህ የዋለለትን ፀጋ አንድ በአንድ ይቆጥርለታል፡፡ እርሱም እነዚያን ፀጋዎች ሁሉ ማጣጣሙን ይናዘዛል፡፡ ከዚያም አላህ እንዲህ ይለዋል፡፡ “የዋልኩልህን ፀጋዎች ለመክፈል ለእኔ ብለህ ምን አድርገሃል?” እርሱም ይላል፡- “እስክገደል ድረስ በአንተ መንገድ ላይ ተዋግቻለሁ፡፡” አላህም ይላል፡- “ዋሸህ፡፡ የተዋጋኸው በሰዎች ዘንድ ጀግና፣ ጦረኛ እንድትሰኝ ነበር፡፡ ይህንንም ተብለሃል፡፡ ከዚያም መላእክቶች ይታዘዙና በፊት ለፊቱ እየጐተቱ ወደ ጀሃነም ወስደው ይጥሉታል፡፡

ከዚያም የእውቀት ባለቤት (ዓሊም) የሆነና ይህንኑ እውቀቱን ለሰዎች የሚያደርስ እንዲሁም ቁርአንንም የሚያነብ ሰው ከአላህ ፊት እንዲቀርብ ይደረጋል፡፡ ከዚያም አላህ የዋለለትን ፀጋዎች ሁሉ እየቆጠረ ይዘረዝርለታል፡፡ እርሱም እነዚያን ፀጋዎች ሁሉ ማጣጣሙን ይመሰክራል፡፡ አላህም እንዲህ ይለዋል፡- “የዋልኩልህን ፀጋዎች ለመክፈል ለእኔ ብለህ ምን ፈጽመሃል?” እርሱም እንዲህ ይላል፡- “እኔ የአንተን ውዴታ በመሻት እውቀትን ተምሬ ለሰዎች አድርሻለሁ፡፡ ቁርአንንም ቀርቸላቸዋለሁ፡፡›› አላህም ይላል፡- “ዋሸህ፤ እውቀትን የተማርከው ሰዎች አዋቂ እንዲሉህ አስበህ ነበር፡፡ ቁርአንንም ታነብላቸው የነበረው እርሱ እኮ ድምጹ የሚያምር ቃሪእ ነው እንዲሉህ ነበር፡፡ ያንንም ተብለሃል፡፡ ስለዚህ ዛሬ ከእኔ ዘንድ ምንም ምንዳ የለህም፡ ፡” ይህን ካለው በኋላ መላእክት ይታዘዙና እየጐተቱ ወስደው ጀሃነም ውስጥ ይጥሉታል፡፡

ከዚያም ሃብታም የሆነ ሰው ከአላህ ፊት እንዲቀርብ ይደረጋል፡፡ አላህም የዋለለትን ፀጋዎች አንድ በአንድ እየዘረዘረ ይቆጥርለታል፡፡ እርሱም እነዚያን ፀጋዎች ማጣጣሙን ያለእብለት ይናዘዛል፡፡ አላህም “የዋልኩልህን ፀጋዎች ለመክፈል ለእኔ ብለህ ምን ፈጽመሃል?” በማለት ይጠይቀዋል፡፡

ሰውየውም ይላል፡- “አንተ እንዳወጣ በምትፈልገው አኳኋን ገንዘቤን ወጪ ሳደርግ ቆይቻለሁ፡፡”

አላህም ይላል፡- “ዋሽህ፡፡ አንተ ገንዘብህን ታወጣ የነበረው ሰዎች ቸር ነው እንዲሉህ ነበር፡፡ ያንንም ተብለሃል፡፡” ከዚያም መላእክት ይታዘዙና እየጎተቱ ወደ ጀሃነም ወስደው ይጥሉታል፡፡

በኢስላም የተወሰኑ መልካም ሥራዎች ትልቅ ግምት የሚሰጣቸውና አድናቆትም የሚቸራቸው ናቸው፡፡ ከእነዚህ ውስጥ በአላህ መንገድ ላይ የእርሱን ውዴታ በመሻት መጋደል፣ ኢስላማዊ እውቀትን መማርና ሰዎችን ማስተማር እንዲሁም ለድሆች ምጽዋት (ሰደቃ) ማድረግና በአላህ መንገድ ላይ ለሚያስፈልጉ ነገሮች ሁሉ ገንዘብን ማውጣት ይገኙበታል፡፡ ይሁን እንጂ ከዚህ ሐዲስ እንደምንማረው እነዚህ ነገሮች ከአላህ ዘንድ ተቀባይነት የሚኖራቸው ኢኽላስ ሲኖር ነው፡፡

እምነት የሚገለጸው በአንደበት ብቻ ሳይሆን በተግባርም ጭምር መሆን ይኖርበታል፡፡ አማኝ ወንድና አማኝ ሴት የአላህን ትእዛዛት በሙሉ ልባቸው የሚቀበሉ ሲሆን ክልከላዎቹንም እንዲሁ ይጠነቀቃሉ፡፡ ከሁሉም ነገር በላይ አላህን ያስቀድማሉ፡፡ ዓለማዊ ጥቅሞችን ከአላህ አስበልጠው የሚወዱት መናፍቃን ብቻ ናቸው፡፡ እነርሱ በእርግጥም ኢስላምን ለሚፈጽሙት ተንኮል ሽፋን በማድረግ ምእመናንን ያታልሉበታል፡፡ እነዚህ ሰዎች ከንቱ ስሜታቸውን እንደ አምላካቸው አድርገው ይቆጥሩታል፡፡ ይህን የመሰሉ ሰዎችን አስመልክቶ ኃያሉ አላህ በቁርአን ሲናገር እንዲህ ብሏል፡-

﴿ أَفَرَءَيْتَ مَنِ ٱتَّخَذَ إِلَٰهَهُۥ هَوَىٰهُ وَأَضَلَّهُ ٱللَّهُ عَلَىٰ عِلْمٍ وَخَتَمَ عَلَىٰ سَمْعِهِۦ وَقَلْبِهِۦ وَجَعَلَ عَلَىٰ بَصَرِهِۦ غِشَٰوَةً فَمَن يَهْدِيهِ مِنۢ بَعْدِ ٱللَّهِ ۚ أَفَلَا تَذَكَّرُونَ ﴿٢٣﴾ ﴾ الجاثية: ٢٣

“ዝንባሌውን አምላኩ አድርጉ የያዘውን አላህም ከእውቀት ጋር ያጠመመውን፣ በጆሮውና በልቡ ላይም ያተመበትን በዓይኑም ላይ ሽፋን ያደረገበትን ሰው አየህን? ታዲያ ከአላህ ኋላ የሚያቀናው ማን ነው? አትገሰጹምን?“ (አል-ጃሲያህ፡23)

አላህ በዚህ የቁርአን አንቀጽ የሰጠን ተግሳጽ እርሱን በመገዛት ሂደት ላይ ከንቱ ምኞትን (ፍላጐትን) መከተል እንደማይገባን ነው፡፡ ለአላህ ወዳጆች ሥራን ማጥራት (ኢኽላስ) ጥልቅ ትርጉምን የያዘ ጉዳይ ነው፡፡

ጥራት (ኢኽላስ) ያለው ጥቂት መልካም ሥራ ኢኽላስ ከሚጐድለው ፣ የተግበሰበሰና ብዛት ካለው መልካም ሥራ ይበልጣል፡፡ ነብዩ (ሰ.ዐ.ወ.) “ሥራን አጥራ (ኢኽላስ ይኑርህ) ጥቂቱ ይበቃሃልና!›› በማለት ተናግረዋል፡፡ አቡ ሁረይራ (ረ.ዐ.) ባወሩትና ሙስሊም በዘገቡት ሐዲስ የአላህ መልትክተኛ (ሰ.ዐ.ወ.) እንዲህ ብለዋል፡-

“አላህ አካላችሁንም ሆነ የሰውነት አቋማችሁን አይመለከትም (ግድ የለውም)፡፡ የሚመለከተው ልባችሁንና ሥራዎቻችሁን ነው፡፡”

የሚከተለው የቁርአን አንቀጽ የሚያሳየን አላህ የሰውን ልጅ የፈጠረው መልካም ይሰራ እንደሆነ ለመፈተን መሆኑን ብቻ ነው፡-

﴿ ٱلَّذِى خَلَقَ ٱلْمَوْتَ وَٱلْحَيَوٰةَ لِيَبْلُوَكُمْ أَيُّكُمْ أَحْسَنُ عَمَلًا ۚ وَهُوَ ٱلْعَزِيزُ ٱلْغَفُورُ ﴿٢﴾ ﴾ الملك: ٢

“ያ የትኛችሁ ሥራው ይበልጥ ያማረ መሆኑን ሊሞክራችሁ ሞትንና ሕይወትን የፈጠረ ነው፡፡ እርሱም አሸናፊ መሃሪው ነው፡፡” (አል-ሙልክ፡2)

አላህ የሰውን ልጅ መልካም ሥራ ኢኽላስ ያለው መሆኑንና አለመሆኑን የሚፈተሽበት የተለያዩ መንገዶች አሉት፡፡ አንዳንድ ጊዜ ሰዎች በእምነታቸውና በመልካም ሥራቸው የተነሣ ግፍንና ስቃይን እንዲቀምሱ ያደርጋቸዋል፡፡ የማይናወጹና በሃቅ ላይ የሚፀኑ ከሆኑ ለእርሱ ታማኝና ፍጹም ታዛዥ (ኢኽላስ ያላቸው) መሆኑ ይረጋገጣል፡፡

﴿ أَحَسِبَ ٱلنَّاسُ أَن يُتْرَكُوٓا۟ أَن يَقُولُوٓا۟ ءَامَنَّا وَهُمْ لَا يُفْتَنُونَ ﴿٢﴾ وَلَقَدْ فَتَنَّا ٱلَّذِينَ مِن قَبْلِهِمْ ۖ فَلَيَعْلَمَنَّ ٱللَّهُ ٱلَّذِينَ صَدَقُوا۟ وَلَيَعْلَمَنَّ ٱلْكَٰذِبِينَ ﴿٣﴾ ﴾ العنكبوت: ٢ - ٣

“ሰዎች አምነናል በማለታቸው ብቻ እነርሱ ሳይፈተኑ የሚትተው መሆናቸውን ጠረጠሩን? እነዚያንም እውነት የተናገሩትን

በእርግጥ ፈትነናል፡፡ እነዚያንም እውነት የተናገሩትን አላህ በእርግጥ ያውቃል፡፡ ውሸታሞቹንም ያውቃል፡፡" (አል-ዐንከቡት፡2-3)

ይሁን እንጂ ይዩልኝንና ይስሙልኝን በመፍራት ከመልካም ሥራ መታቀብ አይኖርብንም፡፡ እንደዚያ ካደረግን ሥራን ለአላህ የማጥራትን (የኢኽላስን) ምንነት ወይም ትርጓሜ በሚገባ አልተገነዘብንም ማለት ነው፡፡ አንዳንድ ጊዜ ሰይጣን ኢኽላስ እንደሌለን በመጐትጐት መልካም ሥራዎችን እንዳንሰራ ሊያደርገን ይችላል፡፡ አንዳንድ ጊዜ በምንሰራው መልካም ሥራ ሳይቀር ቁርጠኛ ሃሳብ (ኢኽላስ) እንደሌለን እንዲሰማን ሊያደርግም ይችላል፡፡ በዚህ ጊዜ ማድረግ ያለብን መልካም ሥራዎችን ከመሥራት መታቀብ ሳይሆን ቁርጠኛ እሳቤያችንን (ንያችንን) ማስተካከል በቻ ነው፡፡ ሥራን አጥርቶ መሥራት እንዲህ በቀላሉ የሚገኝ ስኬት እንዳልሆነም ልብ ልንል ግድ ነው፡፡ በዚህ መንገድ (ሥራን በማጥራት ላይ) ብዙ መሰናክሎች ተኑረዋል፡፡ ከሁሉም በላይ ከነፍሳችን ጋር መፋለምን ይጠይቀናል፡፡ እርሷን የሚጋልባት ወይም የሚሸፍናት ደግሞ ከፍላጐት (ሸህዋ) ነው፡፡ ከዚህ ሁሉ በኋላ ነው ሥራችንን እያጠራን ሄደን የኢኽላስን ተራራ ጫፉን የምንቆናጠጠው፡፡ እስከዚያው ድረስ ግን ደረጃ በደረጃ መጓዛችንን መቀጠል ይኖርብናል፡፡ ይህን ስናደርግ ግን ከራሳችን ጥረትና ትጋት በተጨማሪ የአላህን እገዛ መጠየቅ ይኖርብናል፡፡

ምዕራፍ ስድስት

አላህን መፍራትና እዝነቱንም ተስፋ ማድረግ

﴿ أَتُهۡلِكُنَا بِمَا فَعَلَ ٱلسُّفَهَآءُ مِنَّآۖ ﴾ الأعراف: ١٥٥

‹‹.... ጌታዬ ሆይ! ...ከእኛ ቂሎቹ በሰሩት ነገር ታጠፋናለህን? ›› (አል-አዕራፍ ፡ 155)

የአንድ አማኝ ሰው ሕይወት ምንጊዜም ቢሆን አላህን በመፍራትና እዝነቱንም ተስፋ በማድረግ (በመከጀል) መካከል ሚዛኗን ጠብቃ መጓዝ ይኖርባታል፡፡ አላህን መፍራት ብቻውን ተስፋ ካልታከለበት ጨለምተኛና ተስፋ ቆራጭ ያደርጋል፡፡ አላህን ተስፋ ማድረግ ሲበዛም፣ ፍርሃቱ ካልታከለበት ከሥራ በማዘናጋት በተጋነነ ምኞት ውስጥ ለጥፋት ይዳርጋል፡፡ በሌላው ጠርዝ ያለው ደግሞ አላህን መፍራትና ለአኼራ (መጪው ዓለም) ስንቅን መያዝ ሳይኖር በባዶና ተምኔታዊ እሳቤ የአላህን ምህረት ለማግኘት የሚሞከርበት ጥግ ነው፡፡ ስለሆነም እነዚህ ሁለቱ ማለትም አቢይ ተስፋና ተምኔት በአማኝ ሕይወት ላይ አፍራሽ መልእክትን ያዘሉና የማይበጁ መሆናቸው ሊሰመርበት ይገባል፡፡

በዚህም ምክንያት አንድ ጥንቃቄ ያልተለየው አማኝ ሰው በሁለቱ ጽንፎች መካከል የሆነና ሚዛናዊ መንገድን ይይዛል ማለት ነው፡፡ አላህ እንዲህ ይላል፡-

﴿ تَتَجَافَىٰ جُنُوبُهُمۡ عَنِ ٱلۡمَضَاجِعِ يَدۡعُونَ رَبَّهُمۡ خَوۡفٗا وَطَمَعٗا وَمِمَّا رَزَقۡنَٰهُمۡ يُنفِقُونَ ١٦ ﴾ السجدة: ١٦

‹‹ጌታቸውንም በመፍራትና በመከጀል የሚጠሩት ሆነው ጎኖቻቸው ከመጋደሚያ ሥፍራዎች ይራራቃሉ፡፡ ከሰጠናቸውም (ፀጋ) ይለግሳሉ፡፡ ›› (አስ-ሰጅዳ፡ 16)

ይህም ማለት አንድ አማኝ የአላህን ቁጣና ቅጣቱን ለተስፋ መቁረጥ ደረጃ እስኪያደርሰው ድረስ መፍራት የሌለበት ሲሆን በሌላ በኩል ደግሞ ከተጣሉበት ግዴታዎችና ከሚጠበቅበት ኃላፊነት እስኪያዘናጋው ድረስ በምህረቱ አይታለልም ማለት ነው፡፡

አልፎ አልፎ የሚመጡና ያልተለመዱ የሆኑ ክስተቶች በሰው ልጅ ሕይወት ላይ አደጋን የሚደቅኑ መከራዎች በመሆን (ለምሳሌ በ1999 በቱርክ እንደደረሰው ዓይነት ርዕደ መሬት) ይህንን ሚዛን ሲያዛቡት ይታያሉ፡፡

ስለሆነም አንድ አማኝ ‹‹ጀነት የሚገባው አንድ ሰው ብቻ ነው!›› ቢባል እንኳ ‹‹ያ ሰው እኔ ልሆን አልችልም?›› ብሎ ራሱን የሚጠይቅ መሆን አለበት፡፡ በሌላ በኩል ‹‹ጀሃነም የሚገባው አንድ ሰው ብቻ ነው! ›› ሲባል ቢሰማም እንዲሁ ‹‹ያ ሰው እኔ እሆን እንዴ?›› ብሎ ራሱን የሚጠይቅ ሊሆን ይገባዋል፡፡ ይህ የሚያሳየው አማኝ ሰው አላህን በመፍራትና የእርሱንም እዝነት ተስፋ በማድረግ ሕይወቱን መግፋት ያለበት መሆኑን ነው፡፡

ኃያሉ አላህ ሰዎች ወደ ሕሊናቸው እንዲመለሱና ቀናውን መንገድ እንዲከተሉ ለማድረግ በተለያዩ ጊዜያቶች ታላላቅ የሚባሉ ሰብአዊና ቁሳዊ ውድመቶችን የሚያስከትሉ የተፈጥሮ አደጋዎችን ያመጣል፡፡ እነዚህ አደጋዎች የሚከሰቱት እንዲሁ በአጋጣሚ ነው ብሎ ማሰብ ቂልነት እንጂ ሌላ ስም ሊሰጠው አይችልም፡፡ በሺዎች የሚቆጠሩ ሰዎች እየሞቱ፣ ቤት አልባ እየሆኑና እየተፈናቀሉ እያየን ፤ ይህ ትርጉም አልባ የሆነ ክስተት ነው ብሎ ማሰብ በእውነቱ የአእምሮን የምናብ ኃይል ማምከን ነው፡፡ ሰው የተፈጠረው እንዲያስብ፣ እንዲመራመር፣ እንዲያስተነትንና ነገሮችን እንዲመዝን ተደርጎ ነው፡፡ የተፈጥሮ አደጋዎች እዚህም እዚያም በድንገትና ያለምንም እቅድ የሚደርሱ ከሆነና ሰዎችም ዝም ብለው ያለ መለኮታዊ ትእዛዝ የሚያልቁ ከሆነ ይህ ዓለምና የሚተዳደርበት ሥርአት እንዴት ትርጉም ሊኖረው ይችላል? እነዚህ የተፈጥሮ አደጋዎች የኃያሉን ፈጣሪያችንን ወሰን አልባ ስልጣንና የሻውን የሚያደርግ ጌታ መሆኑን አያሳዩምን?

ዛሬ ጀንበር በሰረቀችና በገባች ቁጥር የምናስተውለው እውነታ በመላው አለም በርእደ መሬት፣ በጎርፍ፣ በመሬት መንሸራተትና በሌላም ተፈጥሮአዊ አደጋዎች ብዙ ሰዎች እያለቁ መሆኑን ነው፡፡ ይህም በሃቅ በተላኩት ነቢይ (ሰ.ዐ.ወ.) አንደበት ከብዙ ምእተ አመታት በፊት የፍርዱ ቀን መቃረቡን የሚያሳዩ ምልክቶች እንደሆኑ የተነገረንን ያስታውሰናል፡፡ እናም አንድን ተፈጥሮአዊ መቅሰፍት ስናይ ከቁሳዊነትና ከፍልስፍና በተዋስነው የተንሸዋረረ መነጽር እየቃኘን ለነገሮች ያልሆነ ትርጉም መስጠት የለብንም፡፡ ከዚያ ይልቅ ከዚያ ክስተት ጀርባ ያጠላውን መለኮታዊ ግሳጼና የተቃጣውን የእርምት እርምጃ ነው ማስተዋል ያለብን፡፡ ይህንንም ቢሆን የልቦናና የማስተዋል ባለቤቶች እንጂ ማንም አይገነዘበውም፡፡

ይህን አጽናፈ ዓለም በአርምሞ ለማስተዋል ከታደልን ከጥቃቅኗ ነገር ጀምሮ ልኬቱ እስከማይታወቀው ግዙፍ አካል ድረስ ያለው ሁሉ የመለኮታዊውን የማስተናበር ሕግ ተከትሎ እንደሚጓዝ እንገነዘባለን፡፡ ይህም ከእኛ እይታና ግንዛቤ ውጪ የሆኑትን ክስተቶችና በስሜት ሕዋሳቶቻችን ልንገነዘባቸው የምንችላቸውን ጭምር ያጠቃልላል፡፡ አናም ሁሉም ነገር ጥንቱኑ በታቀደለት ሁኔታ እየተከናወነ እንደሚገኝ ማወቅ ልባምነት ነው፡፡

ይህን ሁሉ ተዓምራዊ ክስተት ላይ ላዩን ለመቀበል አሻፈረን የሚሉ ሰዎች ለስሜታቸው ያደሩ ሰዎች መሆናቸው ቢታወቅም ውስጣቸው ግን ብዙውን ነገር ይቀበላል፤ ያምናልም፡፡ ሁሉም ነገር በመለኮታዊው መዘውር ውስጥ ገብቶ እየተሽከረከረ መሆኑን ለማስተባበል በቂ አቅም ሲያንሳቸው የሚታየውም ለዚሁ ነው፡፡ እናም መለኮታዊውን ሥርዓትና ይህ አጽናፈ ዓለም የሚተዳደርበትን ደንብ “ተፈጥሮ” በሚል ከንቱ ስያሜ ይጠሩታል፡፡

ይህ ዓለም የተፈጠረው በበቂ ምክንያትና በውስጥም ያሉት ነገሮች ሁሉ በምክንያትና ውጤት የተሳሰሩ መሆናቸውን ማመን ብልህነት ነው፡፡ እርግጥ ነው መለኮታዊው መሻት አንዳችን ነገር ያለ ምክንያትና ውጤት እንዲገኝ ቢፈቅድ ከዚህ ሁነት በስተጀርባ ያለውን መንፈሳዊ ጥበብ

ሊፈላፈልና ሊያውቅ የሚገዳደር ማንም አይኖርም፡፡ ስለሆነም የእውቀት ባለቤቶች ምን ጊዜም ሰበብን ሳይሆን ሰበብን ያስገኘውን ፈጣሪ ነው የሚያስቡት፡፡ በሌላ በኩል ያሉትና የፈጣሪን መኖር የማይቀበሉት ወገኖች ደግሞ ለእያንዳንዱ ክስተት ተጨባጭ (ቁሳዊ) የሆነ ትንታኔን ለማግኘት በክስተቶች ዙሪያ ይባዝናሉ፡፡ እናም የመሬት መንቀጥቀጥ የሚከሰተው በራሷ በምድር ውስጥ የሚፈጠር የሚንጥ ኃይል ሲኖር ነው በማለት የጉዳዩን መንፈሳዊ ጎን ይክዳሉ፡፡

አላህ በየዘመናቱ ከመለኮታዊው ደንብ በማፈንገጥ ባፈተተው የሕይወት ዘይቤ ለሚነጉዱ ሥርዓትን ለማስተማር ተፈጥሮአዊ የሆኑና የተለመዱ ክስተቶችን በአርጩሜነት ይጠቀማል፡፡ በዚሁ አሰራሩም አንጻር እሳትንና ውሃን እንዲሁም ነፋስን የመሳሰሉ ለሰው ልጅም ሆነ ለሌሎች ፍጥረታት ጠቃሚ የሆኑ ነገሮችን ወደ መቅሰፍትነት ይቀይራቸዋል፡፡

አላህ እውነተኛ የሆኑ ባሮቹን በዚህ ዓለም ላይ የተለያዩ ፈተናዎችን በማምጣት የጽናት ደረጃቸውን ይገመግማል፡፡ ይህንንም በቁርዓን አንደሚከተለው አስቀምጦታል፡-

﴿ وَلَنَبۡلُوَنَّكُم بِشَيۡءٖ مِّنَ ٱلۡخَوۡفِ وَٱلۡجُوعِ وَنَقۡصٖ مِّنَ ٱلۡأَمۡوَٰلِ وَٱلۡأَنفُسِ وَٱلثَّمَرَٰتِۗ وَبَشِّرِ ٱلصَّٰبِرِينَ ١٥٥ ﴾ البقرة: ١٥٥

‹‹ከፍርሃትም፣ ከረሃብም፣ በጥቂት ነገር ከገንዘቦችና ከነፍሶችም፣ ከፍራፍሬዎችም በመቀነስ በእርግጥ እንሞክራችኋለን፡፡ ታጋሾችንም (በገነት) አብስር፡፡ (አል-በቀራህ፡ 155)

ሌላው ቀርቶ ነቢያት እንኳ ኃጢአት የማይፈጽሙ ከመሆናቸው ጋር ብዙ መከራና ፈተናዎች ይደርሱባቸው ነበር፡፡ ለአብነት ያክል በነቢዩ አዩብ (ዐ.ሰ.) ላይ የደረሰውን ስናስብ በጣም የሚስብ የጽናት ተምሳሌት ሆነው እናገኛቸዋለን፡፡ አላህ አዩብን (ዐ.ሰ.) በመጀመሪያ የፈተናቸው ሃብታቸውን በሙሉ በማጥፋት ነበር፡፡ የበግ መንጋቸውን ጎርፍ ጠራርጐ የወሰደባቸው ሲሆን አዝመራቸውን ደግሞ ነፋስ ከጥቅም ውጭ አደረገባቸው፡፡ ከዚያ በኋላ ደግሞ ልጆቻቸው ሁሉ በመሬት መንቀጥቀጥ አለቁ፡፡ ከዚህ ሁሉ የፈተና ውርጅብኝ በኋላ ደግሞ ራሳቸው አዩብ

(ዐ.ሰ.) በጽኑ ደዌ ቢያዙም በአላህ ላይ የነበራቸው እምነት ቅንጣት አልተነካም ነበር፡፡ ያደረሰባቸውን መከራ እያነሱ አልወቀሱትም፡፡ ከዚያ ይልቅ ሁለንተናቸውን ለእርሱ ፈቃድ ማስገዛታቸውን ቀጠሉ፡፡

ይህ ሁሉ ከሆነ ከብዙ ዓመታት በኋላ አዩብ (ዐ.ሰ.) ባሳዩት ጽናትና የማይናወጽ እምነት የተነሣ ኃያሉ አላህ ከበሽታቸውና ከደረሰባቸውም መከራ ይገላገሉ ዘንድ ፈቃዱ ሆነ፡፡ ልጆቻቸውንም ቀድሞ ከነበሩት የበለጡ በማድረግ ተካላቸው፡፡

ከዚህ ተምሳሌት የምንቀስመው ትምህርት በአንዳንድ መቅሰፍቶች ህፃናት ሊሞቱ ይችላሉ፡፡ ከወላጆቻቸው ትዕግስት (ሰብር) ይጠበቃል ማለት ነው፡፡ እንዲሁም ሃቀኛና አላህን በመፍራት የሚታወቁ ሰዎችም ይሞቱ ይሆናል፡፡ ለእነርሱ ደግሞ ለሃጢአታቸው መርገፍ ሰበብ ሊሆናቸው ይችላል፡፡ ይህን ጉዳይ አስመልክተው የአላህ መልእክተኛ (ሰ.ዐ.ወ.) እንዲህ ብለዋል፡-

‹‹አላህ የባሪያውን ደረጃ ከፍ ለማድረግ ጥንቱኑ ይወስንለታል፡፡ ሆኖም ግን ባሪያው በመልካም ሥራዎቹ እዚያ ደረጃ መድረስ አልቻለም፡ ፡ በዚህ ጊዜ አላህ የተወሰኑ መከራዎችንና ፈተናዎችን ይልክበታል፡፡ ከዚያም በማስከተል እነዚያን ፈተናዎቹን የሚሸከምበት ትዕግስት ያጎናጽፈዋል፡፡ ያንን የወሰነለትን ደረጃም ያገኛል፡፡›› (ሙስነድ አቡ ያዕላ፣ሶሂህ ኢብን ሂባን)

ነቢዩ ሙሣ (ዐ.ሰ.) ከአላህ ጋር ለመነጋገር በሲናይ ምድረበዳ ወደ አንድ ተራራ እየወጡ ሳሉ አንድ ሰው ያጋጥማቸዋል፡፡ ሰውየውም ሙሳን (ዐ.ሰ.) እንዲህ አላቸው፡-

‹‹አንተ ከአላህ ጋር የምትነጋገረው (ከሊሙሏህ) ሆይ! ወደ ተራራው ስትወጣ አላህን እንድትለምንልኝ የምሻው ነገር አለኝ፡፡››

‹‹ጉዳይህ ምንድን ነው? ንገረኝና አላህን እለምንልሃለሁ፡፡›› አሉት፡፡

‹‹የአላህ መልእክተኛ ሆይ! ይህ በእኔና በአላህ መካከል ያለ ምስጢር ነው፡፡››

ሙሣ (ዐ.ሰ.) ይህን ከሰሙ በኋላ ጉዟቸውን ቀጥለው ከተራራው ጫፍ ላይ ሰረሱ፡፡ ከዚያም ከአላህ ጋር ሲነጋገሩ ሰውየው የጠየቀውን ነገር እንዲሰጠው አላህን ለመኑለት፡፡ አላህም የሰውየው ልመና መልስ ማግኘቱን ነገራቸው፡፡ ከተራራው ላይ ሲወርዱ ነቢዩ ሙሣ (ዐ.ሰ.) ሰውየውን ካገኙበት ቦታ ሲደርሱ ቆሙ፡፡ ይህንን ያደረጉት ጥያቄው መልስ ማግኘቱን ሊያበስሩት ስለፈለጉ ነበር፡፡ ይሁን እንጂ በዚያ ቦታ ያዩት የዱር አራዊት የገድሉትን የሰውየውን የተቦጫጨቀ በድን ነበር፡፡ በዚህ ክስተት ግራ የተጋቡት ሙሣ (ዐ.ሰ.) ጌታቸውን እንዲህ በማለት ጠየቁ፡-

‹‹ጌታዬ ሆይ! ይህ ምስጢር ምንድን ነው? የሰውየው ልመናስ እንዴት ነው?

አላህም አላቸው፡- “ሙሣ ሆይ !ይህ ባሪያዬ በመልካም ድርጊቶቹ ሊደርስበት የማይችለውን መንፈሳዊ ደረጃ እሰጠው ዘንድ ጠየቀኝ፡፡ እኔም ይህን መከራ እንዲጋፈጥ ላኩበት፡፡ ከዚያም እርሱ የጠየቀኝን ደረጃ እንዲጎናፀፍ አበቃሁት፡፡”

አንድ ጊዜ ነቢዩ (ሰ.ዐ.ወ.) እንዲህ አሉ፡-

“አላህ ባሪያውን በሆነ መከራ ከፈተነው ወይ ኃጢአቱን ያነጻለታል፡፡ አሊያም ደግሞ ደረጃውን ከፍ ያደርግለታል፡፡” (ሙስነድ አህመድ)

ስለሆነም የአላህ ወሰን አልባ ኃይል መገለጫ የሆኑ ተፈጥሮአዊ መቅሰፍቶች ተስፋ ሊያስቆርጡን እንደማይገባ ሁሉ፤ የደግነቱና የርህራሄው ስፋት ደግሞ ራሳችንን እንደ መልካም ሰዎች በመቁጠር የልብ ልብ እንዲሰማን ሊያደርጉን አይገባም፡፡

በአጽናፈ ዓለሙ ውስጥ ያሉ ተፈጥሮአዊ ልማዶችና የተለያዩ እንደ ርዕደ መሬት፣ የቋያ እሳት፣ ጦርነት፣ ቸነፈር፣ ድርቅ ያሉ ክስተቶች፣ በሌላ በኩል ደግሞ የአላህ እዝነትና ፀጋዎች የሚከሰቱት በባሮቹ የመንፈሳዊነት ደረጃ እንደየሁኔታው እየታዩ ነው፡፡ ብዙ ባሮቹ በቀጥተኛው መንገድ ላይ ከሆኑ ዝናብና በረከት ከሰማይ እንደልብ

እየተንቧቧ በቀያቸው ደስታንና ተስፋን ይዘራል። ሆኖም ግን አብዛኞቹ ለስጋቸው ያደሩና ምድራዊ ደስታን ብቻ የሚያሳድዱ ከሆኑ ጎርፍ፣ ድርቅ፣ ርዕደ መሬትና ሌላም አደጋ አይቀሬ እጣቸው ይሆናል።

በሌላ አገላለጽ ተፈጥሮአዊ መቅሰፍቶች የሚከሰቱት በሰዎች ልብ ውስጥ መንፈሳዊ መናወጽ ሲደርስና የእምነት ድህነት ሲንሰራፋ ነው።

﴿ إِنَّ ٱللَّهَ لَا يُغَيِّرُ مَا بِقَوۡمٍ حَتَّىٰ يُغَيِّرُواْ مَا بِأَنفُسِهِمۡۗ ﴾ الرعد: ١١

"አላህ በሕዝቦች ዘንድ ያለውን ፀጋ በነፍሶቻቸው ያለውን (ሁኔታ) እስከሚለውጡ ድረስ አይለውጥም..." (አር-ረዕድ፡ 11)

በምድር ላይ የሚፈጠረው መከራና የሰው ልጆች ሥቃይ በሰዎች በራሳቸው ኃጢአት ምክንያት መሆኑን አላህ እንዲህ በማለት ይገልጽልናል፡-

﴿ فَكُلًّا أَخَذۡنَا بِذَنۢبِهِۦۖ فَمِنۡهُم مَّنۡ أَرۡسَلۡنَا عَلَيۡهِ حَاصِبٗا وَمِنۡهُم مَّنۡ أَخَذَتۡهُ ٱلصَّيۡحَةُ وَمِنۡهُم مَّنۡ خَسَفۡنَا بِهِ ٱلۡأَرۡضَ وَمِنۡهُم مَّنۡ أَغۡرَقۡنَاۚ وَمَا كَانَ ٱللَّهُ لِيَظۡلِمَهُمۡ وَلَٰكِن كَانُوٓاْ أَنفُسَهُمۡ يَظۡلِمُونَ ٤٠ ﴾ العنكبوت: ٤٠

"ሁሉንም በኃጢአቱ ያዝነው። ከእነርሱም ውስጥ ጠጠርን ያዘለ ነፋስን የላክንበት አለ። ከእነርሱም ውስጥ ጩኸት የያዘችው አለ። ከእነርሱም ውስጥ ያሰጠምነው አለ። አላህም የሚበድላቸው አልነበረም። ግን ነፍሶቻቸውን የሚበድሉ ነበሩ።" (አል-ዐንከቡት፡ 40)

﴿ ظَهَرَ ٱلۡفَسَادُ فِي ٱلۡبَرِّ وَٱلۡبَحۡرِ بِمَا كَسَبَتۡ أَيۡدِي ٱلنَّاسِ لِيُذِيقَهُم بَعۡضَ ٱلَّذِي عَمِلُواْ لَعَلَّهُمۡ يَرۡجِعُونَ ٤١ ﴾ الروم: ٤١

"የሰዎች እጆች በሰሩት ኃጢአት ምክንያት የዚያን የሰሩትን ከፊሉን ያቀምሳቸው ዘንድ መከራው በየብስና በባሕር ተገለጠ (ተሰራጨ)። እነርሱ ሊመለሱ ይከጀላልና።" (አር-ሩም፡ 41)

አላህ የሰውን ልጆች በሰራነው ኃጢአትና በአጠቃላይ በእያንዳንዷ ድርጊታችን ቢተሳሰበን ኖሮ አንድም ሰው በምድር ላይ እንደማይተርፍ ሲገልጽ እንዲህ ይላል፡-

﴿ وَلَوۡ يُؤَاخِذُ ٱللَّهُ ٱلنَّاسَ بِظُلۡمِهِم مَّا تَرَكَ عَلَيۡهَا مِن دَآبَّةٖ وَلَٰكِن يُؤَخِّرُهُمۡ إِلَىٰٓ أَجَلٖ مُّسَمّٗىۖ فَإِذَا جَآءَ أَجَلُهُمۡ لَا يَسۡتَـٔۡخِرُونَ سَاعَةٗۖ وَلَا يَسۡتَقۡدِمُونَ ٦١ ﴾ النحل: ٦١

"አላህም ሰዎችን በበደላቸው በያዛቸው ኖሮ በእርሷ (በምድር) ላይ ከተንቀሳቃሽ ምንንም ባልተወ ነበር፡፡ ግን እስከተወሰነ ጊዜ ድረስ ያቆያቸዋል፡፡ ጊዜያቸውም በመጣ ወቅት አንዲትን ሰአት አይቆዩም፣ አይቀድሙምም፡፡" (አን-ነሕል ፡ 61)

በሌላ በኩል ደግሞ አላህ የሰዎች ልቦችና መንፈሳቸውም እርሱን በማምለክ የሚያተኩሩ ከሆነና ሰዎች መለኮታዊውን ሕግና ደንብ ካከበሩ በረከቱን ሁሉ ከያቅጣጫው እንደሚለቅ ሲገልጽ እንዲህ ይላል፡-

﴿ وَلَوۡ أَنَّ أَهۡلَ ٱلۡقُرَىٰٓ ءَامَنُواْ وَٱتَّقَوۡاْ لَفَتَحۡنَا عَلَيۡهِم بَرَكَٰتٖ مِّنَ ٱلسَّمَآءِ وَٱلۡأَرۡضِ وَلَٰكِن كَذَّبُواْ فَأَخَذۡنَٰهُم بِمَا كَانُواْ يَكۡسِبُونَ ٩٦ ﴾ الأعراف: ٩٦

"የከተማዋም ሰዎች ባመኑና በተጠነቀቁ ኖሮ በእነርሱ ላይ ከሰማይም ከምድርም በረከቶችን በከፈትንላቸው ነበር፡፡ ግን አስተባበሉ፤ ይሰሩት በነበሩትም ኃጢአት ያዝናቸው፡፡" (አል-አዕራፍ፡ 96)

ስለሆነም በግልጽ ማስተዋል የምንችለው የአመጻን መንገድ የመረጡና ከመለኮታዊው አገዛዝ የሚያፈገፍጉ ሕዝቦች በራሳቸው ላይ የቅጣትን በር የሚከፍቱ መሆናቸውን ነው፡፡ ይህንንም የሰው ልጅ ድርጊት ሁሉ ልቅም አድርጎ የሚያውቅና ምንም ነገር የማይሰወርበት መሆኑን አላህ ሲናገር እንዲህ ይላል፡-

﴿ ۞ وَعِندَهُۥ مَفَاتِحُ ٱلۡغَيۡبِ لَا يَعۡلَمُهَآ إِلَّا هُوَۚ وَيَعۡلَمُ مَا فِي ٱلۡبَرِّ وَٱلۡبَحۡرِۚ وَمَا تَسۡقُطُ مِن وَرَقَةٍ إِلَّا يَعۡلَمُهَا وَلَا حَبَّةٖ فِي ظُلُمَٰتِ ٱلۡأَرۡضِ وَلَا رَطۡبٖ وَلَا يَابِسٍ إِلَّا فِي كِتَٰبٖ مُّبِينٖ ٥٩ ﴾ الأنعام: ٥٩

“የሩቅ ነገርም መክፈቻዎች እርሱ ዘንድ ናቸው፡፡ ከእርሱ በቀር ማንም አያውቃቸውም፡፡ በየብስም በባሕር ያለውንም ሁሉ ያውቃል፡፡ ከቅጠልም አንዲትም አትረግፍም የሚያውቃት ቢሆን እንጅ፡፡ ከቅጣትም በመሬት ጨለማዎች ውስጥ የለም ከእርጥብም ከደረቅም አንድም የለም ግልጽ በኾነው መጽሐፍ ውስጥ (የተመዘገበ) ቢሆን እንጅ፡፡” (አል-አንዐም፡ 59)

ይህ ሁሉ ሲሆንና ሲባል ግን እርግጥ ነው ሕንፃዎች የተሰሩባቸው መሬቶች ባለመጽናታቸው ትክክለኛና ጥራት ያላቸውን ግብአቶች ባለመጠቀማቸውና በመሣሰሉት ሰው ሰራሽ ችግሮች አደጋዎች አያጋጥሙም እያልን አይደለም፡፡ ይህ የሚካድ ነገር አይደለምና፡፡ በሌላ በኩል ደግሞ የሰዎች መንፈሳዊ አቋም በመዝቀጡና ከትክክለኛው መንገድ በመራቃቸው ምክንያት ርእደ መሬትና ሌሎች መቅሰፍቶችንም መካድ አይቻልም፡፡

ሌላውና ትኩረት ሊያገኝ የሚገባው ጉዳይ ለወደፊቱ ሊከሰቱ ይችላሉ ተብለው ከሚገመቱ ተፈጥሯዊ ውድመቶች አንፃር የጥንቃቄ እርምጃ መውሰድ የሚገባ መሆኑ ነው፡፡ ሆኖም ግን ጥንቃቄዎች ከተደረጉ በኋላ ለሚደርሱ ውድመቶች ሰዎች ሁኔታውን ወደ አላህ ማስጠጋት አለባቸው፡፡ አንድ ጊዜ ኡመር (ረ.ዐ.) ሊወድቅ ባዘመመ ግድግዳ አጠገብ ሲደርሱ ፈጠን ብለው በመራመድ ቦታውን አለፉት፡፡ በዚህ ጊዜ ባልደረቦቻቸው “የምእመናን አዛዥ ሆይ! አላህ ከወሰነብዎት ጉዳይ (ከቀደር) ማምለጥዎ ነውን?” በማለት ጠየቋቸው፡፡ ኡመርም (ረ.ዐ.) በዚህን ጊዜ እንዲህ በማለት መለሱ “ከአንዱ የአላህ ውሳኔ (ቀደር) ወደ ሌላው የአላህ ውሳኔ (ቀደር) ነው የምሸሸው፡፡”

ቁሳዊያንና ኃይማኖት የለሽ ሕዝቦች የተፈጥሮ አደጋዎችን ለመከላከል የሰው ልጅ በሚወስዳቸው ቅድመ ጥንቃቄዎች ላይ የተጋነነ እምነት ያሳድራሉ፡፡ ይህም በመሆኑ አንድ ውድመት ከተከሰተ በኋላ “ህንፃው ጠንካራ ቢሆን ኖሮ ይህ የመሬት ነውጥ ይህን ሁሉ ሕዝብ ባልጨረሰ ነበር” ይላሉ፡፡ ሆኖም ግን ነገሮችን ወደ መለኮታዊው ውሳኔ ቢያስጠጉ ኖሮ ውድመቱ አይቀሬ ከሆነ የተለያዩ ቅድመ ጥንቃቄዎች ቢኖሩም ፈጽሞ ሊያስቀሩት እንደማይችሉ መገንዘብ በቻሉ ነበር፡፡

ለምሳሌ በ7.4 ፋንታ 11.4 ሬክተር ስኬል ኃይል ያለው ርዕደ መሬት ተከሰተ እንበል፡፡ ለዚህ ጥሩ ማሳያ የምትሆነን የጃፓን ከተማ ነች፡፡ በዚያች ከተማ ህንፃዎች የተገነቡት ይህን ርዕደ መሬት እንዲቋቋሙ፣ የሚያስችላቸው ዘመናዊ አሰራርን ተከትለው ነበር፡፡ ይሁን እንጂ ርእደቱ እንደተከሰተ ወዲያው የጋዝ ቧንቧዎች ፈንድተው በተፈጠረው የእሳት ነበልባል እየተጠበሱ ያለቁት ሰዎች ብቻ ስድስት ሺህ ሆኗል፡፡ ለሃያ ሰከንዶች ብቻ የቆየው ነውጥ የከተማዋ ነዋሪዎች ለአመታት ያካበቷቸውን ውድ ሃብቶቻቸውን ዶግ አመድ ለማድረግ በቂ ነበር፡፡

እኛ የአላህ ባሮች እስከሆንን ድረስ ሊከሰቱ ከሚችሉ ውድመቶች ራሳችንን ለመከላከል አስፈላጊ እርምጃዎችን መውሰድ ግዴታችን ነው፡፡ ይሁንና እነዚህ እርምጃዎች በራሳቸው እጣ ፈንታችንን ከመወሰን አንፃር ወሳኝ ናቸው ማለት አይደለም፡፡ እርምጃዎችና ጥንቃቄዎች ፋይዳ የሚኖራቸው እኛ ራሳችንን ከመለኮታዊው ደንብ ጋር አስማምተን መጓዝ ከቻልን ብቻ ነው፡፡ ከዚህ በተቃራኒ የሚደረጉ ጥንቃቄዎች የሰሙድ ሕዝቦች ለአድ ሕዝቦች ውድመት ካሳዩት የተንሻፈፈ ግንዛቤ የተለዩ አይሆኑም፡፡

የሰሙድ ሕዝቦች ለአድ ሕዝቦች ውድመት ተጠያቂ ያደረጉት የአመፃ ሕይወት መግፋታቸውንና ፈጣሪያቸውን በመገዳደራቸው ቁጣውን ማትረፋቸውን ሳይሆን የቤቶቻቸውን ጥንካሬ አልባነት ነበር፡፡ እናም እንዲህ አሉ፡- “የአድ ሕዝቦች የጠፉት ቤቶቻቸውን እንደ እኛ ከጠንካራ አለቶች ጠርበው በማነጽ ፋንታ በለሰለሰ መሬት ላይ በመስራታቸው ነበር፡፡ ሆኖም ግን እኛ ቤቶቻችንን ጠንካራ አለቶችን እየፈለፈልን አንፀናል፡፡ ስለሆነም ለማንኛውም የተፈጥሮ አደጋ ተጋላጮች አይደለንም፡፡”

እርግጥ ነው ሰሙዶች እንዳሉትም ቤቶቻቸውን እጅግ በሚያስደንቅ ጥበብና ብቃት ከዓለቶች እየፈለፈሉ አንፀዋል፡፡

የሆነ ሆኖ የሰሙዶች ጠንካራ ህንፃዎች ከውድመት አላዳኗቸውም፡፡ ምክንያቱም የውድመቱ ሰበብ የቤቶቹ ብቃት ማነስ ሳይሆን የሰዎቹ ጠማማውን መንገድ መምረጥና የአመጻ የሕይወት ዘይቤ ነበርና፡፡

ስለሆነም እጅግ አሰቃቂ በሆነ ከመሬት ስር የወጣ ድምጽ (ጩኸት) ሰበብ በሕንጻዎቻቸው ውስጥ እንዳሉ ሞተው አነጉ፡፡ አላህ በቁርአን እንዲህ ይላል፡-

﴿ وَأَخَذَ ٱلَّذِينَ ظَلَمُواْ ٱلصَّيۡحَةُ فَأَصۡبَحُواْ فِي دِيَٰرِهِمۡ جَٰثِمِينَ ٦٧ كَأَن لَّمۡ يَغۡنَوۡاْ فِيهَآۗ أَلَآ إِنَّ ثَمُودَاْ كَفَرُواْ رَبَّهُمۡۗ أَلَا بُعۡدٗا لِّثَمُودَ ٦٨ ﴾ هود: ٦٧ - ٦٨

"እነዚያንም የበደሉትን ጩኸት ያዛቸው በቤቶቻቸውም ውስጥ የተንበረከኩ ሆነው ሞተው አነጉ፡፡ በእርሷ ውስጥ እንዳልኖሩባት ሆኑ፡፡ ንቁ! ሰሙዶች ጌታቸውን በእርግጥ ካዱ፡፡ ንቁ! ለሰሙዶች ከአላህ እዝነት መራቅ ተገባቸው፡፡" (ሁድ፡67-68)

ታላላቅና ጠንካራ ሕንጻዎችን መገንባት በራሱ ከተፈጥሮ አደጋዎች አያድንም፡፡ የአላህን ቁጣ ጐትተው የሚያመጡት አመጻ፣ ክፋት፣ ውለታ ቢስነት፣ ሸፍጥ፣ የኃጢአት ኑሮና ከአላህ ሌላ የሆኑ አማልክትን መገዛት ናቸው፡፡ ስለሆነም የሰዎች የሞራል ርክሰት በየብስም ሆነ በባህር ሲገለጽና ምድር በኃጢአት ስትቀረና አንዱን ጥፋት ተከትሎ ሌላው ይመጣል፡፡ የኃይልና የንግሥና ባለቤት የሆነው አላህ ይህን ጉዳይ በቁርዓን ሳያወሳ አላለፈም፡-

﴿ ظَهَرَ ٱلۡفَسَادُ فِي ٱلۡبَرِّ وَٱلۡبَحۡرِ بِمَا كَسَبَتۡ أَيۡدِي ٱلنَّاسِ لِيُذِيقَهُم بَعۡضَ ٱلَّذِي عَمِلُواْ لَعَلَّهُمۡ يَرۡجِعُونَ ٤١ ﴾ الروم: ٤١

"የሰዎች እጆች በሠሩት ሀጢአት ምክንያት የዚያን የሰሩትን ከፊሉን ያቀምሳቸው ዘንድ መከራው በየብስና በባሕር ተገለጠ (ተሰራጨ)፡፡ እነርሱ ሊመለሱ ይከጀላልና፡፡" (አር-ሩም፡41)

ቀደም ሲል በቀረቡት የቁርአን አንቀጾች ላይ የተጠቀሰው የአላህ ቅጣት ከፊሉ ብቻ ነው፡፡ ዋናውና ዘላለማዊው ቅጣት ግን በመጪው ዓለም የሚጠብቃቸው ነው፡፡ በተጨማሪም ማንኛውም ምድራዊ ቅጣት በጊዜው በሕይወት ለሚገኙ ሌሎች ሕዝቦችና ወደፊት ለሚመጡ ትውልዶችም የታለመ ማስጠንቀቂያ መሆኑን ከአንቀጾቹ መገንዘብ አያዳግትም፡፡ ስለሆነም የአላህን ቁጣ መምጣት ሁሉም ሰው እንዲፈራና ወደ እርሱም

በተውበት (ንስሃ) ተመልሶ መጠጊያ አድርጐ እንዲይዘው ነው የሚመከረው፡፡ አላህ እንዲህ ይላል፡-

﴿ وَمَا كَانَ ٱللَّهُ لِيُعَذِّبَهُمۡ وَأَنتَ فِيهِمۡۚ وَمَا كَانَ ٱللَّهُ مُعَذِّبَهُمۡ وَهُمۡ يَسۡتَغۡفِرُونَ ٣٣ ﴾ الأنفال: ٣٣

“አላህም አንተ በውስጣቸው እያለህ በተፈጥሮ አደጋ የሚቀጣቸው አይደለም፡፡ አላህም እነርሱ ምሕረትን የሚለምኑ ሲሆኑ የሚቀጣቸው አይደለም፡፡” (አል-አንፋል፡33)

ከአላህ ጋር የሚኖርን ግንኙነት ከሁሉም በላይ የሚያሳምረው ሶላት መስገድና ይህንንም በማድረግ ላይ መታገስ ነው፡፡ በእርግጥ ሰላት አላህን በማይፈሩ ሰዎች ላይ ገር አይደለችም፡፡

﴿ يَٰٓأَيُّهَا ٱلَّذِينَ ءَامَنُواْ ٱسۡتَعِينُواْ بِٱلصَّبۡرِ وَٱلصَّلَوٰةِۚ إِنَّ ٱللَّهَ مَعَ ٱلصَّٰبِرِينَ ١٥٣ ﴾ البقرة: ١٥٣

“እናንተ ያመናችሁ ሆይ! በመታገስና በሶላት ተረዱ፡፡ አላህ (በእርዳታው) ከታጋሾች ጋር ነውና፡፡” (አል-በቀራህ ፡153)

አንድ ዓይነት የተፈጥሮ አደጋ ከደረሰና በሺዎች የሚቆጠሩ ሰዎች ካለቁ በኋላ በሕይወት የሚገኙ ሰዎች አንደገና የተፈጠሩ ያህል የመኖርን እድል አግኝተዋል ማለት ይቻላል፡፡ ስለዚህም እነዚህ ሰዎች እድለኞች ናቸውና ይህንን አጋጣሚ ተጠቅመው የበለጠ ወደ አላህ መቅረብና ውዴታውን ማግኘት ይጠበቅባቸዋል፡፡ ምክንያቱም ይህን ሳያደርጉ ቀርተው ከሞቱ በኋላ “ ጌታችን ሆይ ! ወደ ምድር ዓለም መልሰንና አንተን እንደሚገባህ አድርገን እንገዛሃለን” ቢሉ ይቅርታን ሊያገኙ አይችሉምና፡፡ ይህን የመሰለው አስፈሪ መቅሰፍት ከተኛንበት ሊያነቃን ይገባል፡፡ ከዚያም ሕይወታችንን እንደገና እንድናስተካክልና ስለአይቀሬው ሞትም ደጋግመን እያሰብን በመልካም ሥራ እንድንሰነቅ እድል ይከፍትልናል፡፡

ከዚህ በታች የሚቀርበው የቁርዓን አንቀጽ ነቢዩ ሙሣ (ዐ.ሰ.) በሲናይ ተራራ ላይ እያሉ የምድር ነውጽ በተከሰተ ጊዜ ያደረጉትን ዱዓ (ልመና) የያዘ ሲሆን ለእኛ የሚሆን ጠቃሚ ትምህርት በውስጡ አካቷል፡-

﴿ وَٱخۡتَارَ مُوسَىٰ قَوۡمَهُۥ سَبۡعِينَ رَجُلٗا لِّمِيقَٰتِنَاۖ فَلَمَّآ أَخَذَتۡهُمُ ٱلرَّجۡفَةُ قَالَ رَبِّ لَوۡ شِئۡتَ أَهۡلَكۡتَهُم مِّن قَبۡلُ وَإِيَّٰيَۖ أَتُهۡلِكُنَا بِمَا فَعَلَ ٱلسُّفَهَآءُ مِنَّآۖ إِنۡ هِيَ إِلَّا فِتۡنَتُكَ تُضِلُّ بِهَا مَن تَشَآءُ وَتَهۡدِي مَن تَشَآءُۖ أَنتَ وَلِيُّنَا فَٱغۡفِرۡ لَنَا وَٱرۡحَمۡنَاۖ وَأَنتَ خَيۡرُ ٱلۡغَٰفِرِينَ ١٥٥ ﴾ الأعراف: ١٥٥

“ሙሳም ከሕዝቦቹ ውስጥ ለቀጠሮዎች ሰባት ሰዎች መረጠ፡፡ ብርቱ የምድር እንቅጥቃጤ በያዘቻቸው ጊዜ ሙሳ አለ፡- “ጌታዬ ሆይ! በሻህ ኖሮ ከአሁን በፊት ባጠፋሃቸው ነበር፡፡ እኔንም (ባጠፋኸኝ ነበር)፡፡ ከእኛ ቂሎቹ በሰሩት ነገር ታጠፋናለህን? እርሷ (ፈተናይቱ) ያንተ ፈተና እንጂ ሌላ አይደለችም፡፡ በእርሷ የምትሻውን ታሳስታለህ፡፡ የምትሻውንም ታቀናለህ፡፡ አንተ ረዳታችን ነህና፡፡ ለእኛ ምህረት አድርግልን፡፡ እዘንልንም፤ አንተም ከመሐሪዎች ሁሉ በላጭ ነህ፡፡” (አል-አዕራፍ፡155)

ከዚህ አገላለጽ የምናስተውለው ነገር ሌላው ቀርቶ ነቢያትም ቢሆኑ እንኳን ከፈተና የማያመልጡና ልቦቻቸውም እጅግ አስፈሪ የሆኑ መከራዎችን እንደሚጋፈጡ ነው፡፡ ከዚህ ፈተና መጨረሻ ላይም እነርሱ ምንጊዜም በተስፋና በፍርሃት መካከል ሆነው ሕዝባቸውን መምራታቸውን እንደሚቀጥሉ እንገነዘባለን፡፡ ሁላችንም ብንሆን በፀጋ ላይም ሆንን በመከራችን ሰዓት አላህን እየፈራንና እዝነቱንም ተስፋ እያደረግን መንገዝ ያለብን መሆኑ ግልጽ ነው፡፡

ምዕራፍ ሰባት

ግድየለሽነት

አንድ ሰው በምድረበዳ እየተጓዘ እያለ ሳያስበው ከአንድ አደገኛ አውሬ ጋር ይገናኛል፡፡ ይህ ሰው ምንም ያክል በፍጥነት ቢሮጥ ከዚህ አይምሬ የሆነ የዱር አውሬ ሊያመልጥ እንደማይችል አመነ፡፡ ሆኖም ግን ተስፋ ቆርጦ ሞትን ከመጠባበቅ በደመነፍስ ከአቅራቢያው ከሚገኝ ጉድጓድ ውስጥ ዘሎ ገባ፡፡ ወደ ጉድጓዱ ውስጥ እየገባ እያለ በጉድጓዱ ግድግዳዎች ላይ የበቀሉ ቁጥቋጦዎችን በማግኘቱ የሞት ሞቱን ሙጭጭ አድርጐ በመያዝ ወደ አዘቅት ከመውረድ ይድናል፡፡ ሆኖም ግን በዚያው ቅጽበት ቁልቁል ሲመለከት እጅግ መርዛማ የሆኑ እባቦችና ዘንዶዎችን ሊበሉት ሲርመሰመሱ ያያል፡፡ ሽቅብ ሲመለከት ደግሞ ነጭና ጥቁር መልክ ያላቸው አይጦች በእጁ ጨምድዶ የያዛቸውን ቁጥቋጦዎች ሥራቸውን በጥርሳቸው እየገዘገዙ እንደሆነ አስተዋለ፡፡ በዚህ ጊዜ ፍርሃት አንዘፍዝፎ ከሞላ ጐደል ህሊናውን ሊያስተው ቀረበ፡፡ በዚህ ሁኔታ ውስጥ እያለ ጥቂት ጊዜ እንደቆየ በጉድጓዱ አንድ ጥግ ላይ ማር የሞላበት ቀፎ አስተዋለ፡፡ ከዚያም ለራሱ እንዲህ አለ፡- “እንደምንም ብዬ ከዚህ ማር መቅመስ አለብኝ፡፡ ምክንያቱም ሌላ ጊዜ ይህን የመሠለ እድል ላላገኝ እችላለሁና፡፡”

ሰውየው ይህን ካለ በኋላ ምንም እንኳን ያን በመሰለ አደጋና አጣብቂኝ ውስጥ ቢሆንም ያጋጠመውን ነገር ለጊዜው በመርሳት ማሩን በመላሱ ላይ ብቻ ተማረከ፡፡ የማሩ ጥፍጥና ያጋጠመውን ታላቅ አደጋና ያንዣበበበትን የሞት ጥላ እንዳይመለከት አይኑን ያወረው ሲሆን ሕሊናውንም ጋርዶታል፡፡ እናም ሰውየው እንደምንም ብሎ ከጉድጓዱ በመውጣት ነፍሱን በማትረፍ ፋንታ ማሩን መላሱን የቀጠለ ሲሆን በተመሳሳይ ሰዓት እነዚያ አይጦች ቁጥቋጦዎችን ቆርጠው በመጨረሳቸው ወደ ጉድጓዱ ወድቆ አርፏል፡፡

በዚህ ተምሳሌታዊ ትረካ ጉድጓዱ የሚወክለው የዚህችን ዓለም ኑሮና በውስጧ የያዘቻቸውን መከራዎች ሲሆን እባቦቹና ዘንዶዎቹ ደግሞ

መጥፎ ባሕሪያቶችን (ሥራዎችን) ነው፡፡ ማሩ የሚወክለው ለጊዜያዊና ጠፊ ጥቅም መስገብገበን ነው፡፡ ነጭና ጥቁር የተባሉት ሁለት አይጦች በሰው ልጅ ሕይወት ላይ የሚያልፉ የሆኑት ቀንና ሌሊት ናቸው፡፡ ተጓዥ ሰው ደግሞ ግዴለሽ (ጋፊል) የሆነና ለመጪው ዓለም (የፍርዱ ቀን) ምንም ዝግጅት የማያደርግ ሰው ነው፡፡ አይጦቹ የቁጥቋጦዎቹን ሥሮች በሹል ጥርሳቸው ቀረጣጥፈው ሲጨርሷቸው ቁጥቋጦዎቹ ስለተነቀሉ ሰውየውን ወደ ጉድጓዱ አዘቅት ከመውረድ የሚጠብቀው ነገር ሊኖር አይችልም፡፡ እናም ወድቆ የእባቦችና ዘንዶዎች ሲሳይ ሆነ፡፡

በዚህ ትረካ በግርድፉ ለማሳየት የተሞከረው የሰው ልጅ ወደዚህች ዓለም የተላከው ለታላቅ ዓላማ ቢሆንም፤ እርሱ ግን ኃላፊ በሆነው ሥጋዊ ፍላጎቱ የሚሸነፍ መሆኑን ነው፡፡

እንግዲህ የሰው ልጅ ሲባል ከመጪው ዓለም ታላላቅ አደጋዎች ለመዳን ከፈለገ ከመጥፎ ምግባራት ራሱን ማንጻት፣ ጊዜውንም በአግባቡ መጠቀም ይኖርበታል፡፡ በምድር ገጽ ላይ የሚገኙ ሁሉም ፍጥረታት በተፈጥሮ የተነደፈላቸውን የአኗኗር ዘይቤ ተከትለው በመጓዝ ብቻ ደስታን የሚያጋኙ ይመስላሉ፡፡ የሰው ልጅ ግን የእነዚያ ሁሉ ፍጡራን የበላይ ቢሆንም የቀልብ ደስታ የሚያገኘው የአላህን ሕግ አክብሮ መጓዝ ሲችል ነው፡፡ ከአላህ ህግ (ሸሪዓ) ውጭ ያለ ሕይወት የድንቁርና (ጃሂሊያ) ሕይወት ሲሆን ይህም የስቃይና የመከራ ሕይወት ነው፡፡ ይህን የመሰለ የሕይወት ዘይቤን የሚከተል ሰውም ግድየለሽ (ጋፊል) ይባላል፡፡ የሰው ልጅ የተፈጠረበትን ዓላማ፣ አሁን የሚገኝበትን ሁኔታ፣ በሕይወት የመገኘቱን ምስጢርና ከዚህ ሁሉ ጀርባ ያለውን ጥበብ አለማስተዋሉ ከንቱነት ነው፡፡ በእርግጥ አንድ ብልህ ወይም አስተዋይ ሰው የሰው ልጅ ካልነበረበት (ኢምንት ከሆነ ነገር) ወደዚህች ዓለም የመምጣቱንና ከተወሰነ ፈተና በኋላም የመሞቱን ጥበብ ለማወቅ አለመፈለጉ ያስደንቃል፡፡

ሰው ሆኖ የመፈጠርን እውነተኛ ዓላማ አንዲሁም የሕይወትንና የሞትን ምንነት ለማወቅ የመጀመሪያው እርምጃ ግዴለሽነትን ማስወገድ ነው፡፡ ይህንንም ለማድረግ የሚቻለው እውነተኛ በሆነ ምክንያታዊነትና

በመንፈሳዊነት ማስተንተን በጐለበተ ልቦና (ቀልብ) ነው፡፡ ተፈጥሯዊ የሆኑ እንደ ቸልተኝነት፣ ስግብግብነት፣ ኩራት፣ የተጋነነ ተስፋ፣ ቅናት፣ አባካኝነትና ንዴት የመሳሰሉት የሰው ልጅ ዝንባሌዎች የግዴለሽነት (ገፍላ) መገለጫዎች ናቸው፡፡

እነዚህ ባህሪያት የሰውን ልጅ ጠፍንገው በመያዝ በራሳቸው እሽክርክሪት ውስጥ የሚያዞሩት ከሆነ ታላቅ ጥፋት ላይ ወድቋል ማለት ነው፡፡ የሰው ልጅ በእነዚህ ባሕሪያትና በነፍስያው (ego) አንድ ጊዜ ከተቀየደ የሐቅን መንገድ ለመያዝ ከቶም አይቻለውም፡፡ ከዚያ በኋላ ሕሊናው የጨለመ፣ ክብሩ የተዋረደና ፈጣሪውንም የሚስተባብል ሆኖ ያርፈዋል፡፡

ይህን በመሰለ ሁኔታ ውስጥ የሚገኙ ሰዎች አላህ የሚጠብቃቸውን አሣር በሚከተሉት የቁርአን አንቀጾች ይገልጻል፡-

﴿ فَوَيۡلٞ لِّلۡقَٰسِيَةِ قُلُوبُهُم مِّن ذِكۡرِ ٱللَّهِۚ أُوْلَٰٓئِكَ فِي ضَلَٰلٖ مُّبِينٖ ٢٢ ﴾ الزمر: ٢٢

“.....ልቦቻቸውም አላህን ከማውሳት ለደረቁ ሰዎች ወዮላቸው፡፡ እነዚያ በግልጽ መሳሳት ውስጥ ናቸው፡፡” (አዝ-ዙመር፡22)

﴿ وَمَن كَانَ فِي هَٰذِهِۦٓ أَعۡمَىٰ فَهُوَ فِي ٱلۡأٓخِرَةِ أَعۡمَىٰ وَأَضَلُّ سَبِيلٗا ٧٢ ﴾ الإسراء: ٧٢

“በዚህች ዓለም (ልበ) እውር የሆነ ሰው እርሱ በመጨረሻይቱም (ዓለም) ይበልጥ እውር ነዉ፡፡ መንገድንም በጣም የተሳሳተ ነው፡፡” (አል-ኢስራእ ፡72)

﴿ أَفَرَءَيۡتَ مَنِ ٱتَّخَذَ إِلَٰهَهُۥ هَوَىٰهُ وَأَضَلَّهُ ٱللَّهُ عَلَىٰ عِلۡمٖ وَخَتَمَ عَلَىٰ سَمۡعِهِۦ وَقَلۡبِهِۦ وَجَعَلَ عَلَىٰ بَصَرِهِۦ غِشَٰوَةٗ فَمَن يَهۡدِيهِ مِنۢ بَعۡدِ ٱللَّهِۚ أَفَلَا تَذَكَّرُونَ ٢٣ ﴾ الجاثية: ٢٣

“ዝንባሌውን አምላኩ አድርጐ የያዘውን፣ አላህም ከእውቀት ጋር ያጠመመውን፣ በጆሮውና በልቡ ላይም ያተመበትን በዓይኑም ላይ ሽፋን ያደረገበትን ሰው አየህን? ታዲያ ከአላህ ኋላ የሚያቀናው ማን ነው? አትገሰጹምን?” (አል-ጃሲያህ፡23)

በአንድ ሰው ልብ ውስጥ የሞራል ይዞታ ሲዳከምና ሲያሽቆለቁል መንፈሳዊ ለሆኑ ነገሮች የሚሰጠው ክብርና ግንዛቤም የዚያኑ ያክል ይዳከማል፡፡ እንዲህ አይነቱ ሰው ደግሞ በአምልኮት ላይ ጽናት (ኢስቲቃማህ) አይኖረውም፡፡ በኃጢአት አረንቋ ውስጥ የተዘፈቀ ሰው በዚያው ሁኔታው እስከቀጠለ ድረስ የሕሊናው ዓይን ስለሚታወር ያለበትን ሁኔታ አይገነዘብም፡፡ ግዴለሽ የሆኑና በነፍስያቸው (ego) ጣጣ የተዋጡ ሰዎች በኃጢአታቸው ምክንያት የሚደርስባቸውን አፍራሽ ሁኔታ እንዳያስተውሉ አይናቸው የሚታወር ሲሆን ጆሮአቸውም ይደነቁራል፡፡ ጣቱ የቆሰለ ሰው ምንም ነገር ሳይሰማውና ሳይጸየፍ ምግቡን እየቆረሰ ሊመገብ ቢችል እንኳ ከእርሱ ጋር አብረው በማእድ የታደሙ ሰዎች የእርሱን ቁስል እያዩ ምግቡ ሊያስጠላቸው ይችላል፡፡ በተመሳሳይ ሁኔታ ሕይወታቸውን በዘፈቀደ የሚመሩ ሰዎች እንዳሉ አይሰማቸውም፡፡ ለእነርሱ ስሜትና መረን ለለቀቀ ራስ ወዳድነታቸው እስከተስማማ ድረስ ሌላው የፈለገውን ቢሆን አይገዳቸውም ፡፡ እነርሱ በእርግጥም አንድ የጦር ሰው ሰውነቱን በጡሩሩ (የብረት ልብሱ) ውስጥ እንደሚደብቀው ሁሉ በኃጢአት ማቅ ተጀቡነው ያሻቸውን ማድረግ ያስደስታቸዋል፡፡ እነዚህ ሰዎች ለሃቅና መለኮታዊ ለሆኑ ግሳጼዎች ጆሮ ዳባ ልበስ ያሉ እውሮች፣ ደንቆሮዎችና ዲዳዎች ናቸው፡፡

አቡ ያዕላ ሸዳድ ኢብን አውስ (ረ.ዐ.) ባወሩትና ቲርሚዚ በዘገቡት ሐዲስ የአላህ መልእክተኛ (ሰ.ዐ.ወ.) እንዲህ ብለዋል፡-

“አዋቂና ብልህ ሰው ማለት ሥጋዊ ፍላጐቱንና ስሜታዊ ዝንባሌውን ተቆጣጥሮ ከሞት በኋላ ላለው ሕይወቱ የሰራ ሰው ነው፡፡ ሞኝ፣ ተላላና ደካማ ሰው ማለት ደግሞ ራሱን (ወደ ተከለከሉና አጥፊ ወደሆኑ እኩይ ምግባራት በምትመራው ነፍሱ) ስሜታዊ ዝንባሌ ቁጥጥር ሥር አውሎ የዝንባሌው ተከታይ በመሆን (ምህረትና ፀጋውን ያላንዳች ጥረት) በባዶ ምኞት ከአላህ (ምህረት) የሚጠብቅ ሰው ነው፡፡”

ምዕራፍ ስምንት

ወደ አላህ መቃረብ

አንድ የአላህ ባሪያ ከኃጢአት ርቆ የእውነትን መንገድ ሲይዝ አላህ ይበልጥ ወደ እርሱ እየቀረበ እንደሚመጣ ይታወቃል። ይህም በተከታዩ ሐዲሰል ቁድስ ይበልጥ ተገልጿል፡-

ከአነስ (ረ.ዐ.) በተወራው መሠረት ነብዩ (ሰ.ዐ.ወ.) አላህ እንዲህ ብሏል አሉ፡- " አንድ አገልጋዬ (ባሪያዬ) አንድ ስንዝር ወደእኔ ሲቀርብ እኔ አንድ ክንድ ወደርሱ እቀርባለሁ። አንድ ክንድ ሲቀርበኝም አንድ እርምጃ እቀርበዋለሁ። እየተራመደ ወደኔ ሲመጣም እኔ እየሮጥኩ ወደርሱ እመጣለሁ።"

ይህም በመሆኑ ወደ አላህ ለመቃረብ የሚፈልግ ሰው የሚከተሉትን ሁኔታዎች በሚገባ ማጤንና መተግበር ይጠበቅበታል፡-

1.ተውባ ማድረግ

የኃጢአትን ጥንስስ በልብ ላይ ከሚጥሉ ነገሮች መካከል የድንቁርና (ጃሂሊያ) ተግባራት፣ የወሲብ ፍላጐት፣ ኩራት፣ ንዴት (ብስጭት)፣ ጥለቻ፣ ከንቱ ምኞት፣ ቅናት፣ ጋጠወጥነትና አባካኝነት ጥቂቶቹ ናቸው፡ ፡ እነዚህና መሰል ባህሪያት አንድ ሰው ከፈጣሪው ጋር የሚኖረውን ዝምድና (መቃረብ) እጅጉን የሚጐዱና ከእርሱም የሚያርቁ ናቸው። አንድ ሰው የራሱን አቋም በየጊዜው የሚመረምርና እርምጃውንም ከፈጣሪው ፍላጐት ጋር እያስተካከለ የሚጓዝ ካልሆነ በሰራቸው መጥፎ ድርጊቶች ሳይረበሽና መንፈሱም ሳይታወክ አይቀርም። ፈጣሪው በውስጡ ያስቀመጠው ሕሊናው ድምጹን እያሰማ ልቡን ያውከዋል። በዚህ ጊዜ ዝናብ እንዳረገዘ ዳመና ሃዘንና ፀፀት የከበደው መንፈሱ እዝነ ልቦናውን በመቀስቀስ እንባው ከዓይኑ እንዲንከባለልና ወደፈጣሪውም የእርቅ መንገድን እንዲፈልግ ያደርገዋል። ይህ በሃዘንና በፀፀት ተነሳስቶ በእንባ እየታጀበ የሚቀርብ መቃተት ተውባ (ንስሃ) ተብሎ ይጠራል። ሞት ሳይወስደው በፊት በፈቃዱ ወደ ፈጣሪው የሚመለስበትና

የኃጢአት ሥርየት የሚጠይቅበት ሂደት ነው- ተውባ፡፡ በሌላ አገላለጽ ተውባ (ንስሃ) ማለት በሰውና በፈጣሪው መካከል ደንቃራ በመሆን ግንኙነታቸውን ያውክ የነበረውን የኃጢአት ጋሬጣ በፀፀት ማስወገድ (ማጽዳት) ነው፡፡

የሰው ልጅ ወደ ፈጣሪው መቃረቢያ ከሚያደርጋቸው መንገዶች ተውባ የመጀመሪያው የሆነበት ምክንያት ኃጢአት የልብን ኃይልና ኃጢአትን የመቃወም ብቃቷን፣ እንዲሁም የህሊናን ድምጽ ስለሚያደክም ነው፡፡ ይህንም ሁኔታ ጥላሸት በተቀባ መስታወት መልክን ከመመልከት ጋር ማመሳሰል ይቻላል፡፡ በዚያ ቆሻሻ መስተዋት ትክክለኛውን ገጽታችንን እናይ ዘንድ ልናጸዳውና ጭጋጉን ልናስወግድለት ግድ ነው፡፡ በተመሳሳይ ሁኔታ ከኃጢአት በመወገድ ተውባ አድርጐ ወደ አላህ መመለስ ልብን የጋረዳትን ጽልመት የመወልወል ያህል ይቆጠራል፡፡

አላህ እንዲህ ይላል፡-

﴿ ثُمَّ تَابَ عَلَيۡهِمۡ لِيَتُوبُوٓاْۚ إِنَّ ٱللَّهَ هُوَ ٱلتَّوَّابُ ٱلرَّحِيمُ ١١٨ ﴾ التوبة: ١١٨

“...ከዚያም ይጸጸቱ ዘንድ ወደ ፀፀት መራቸው፡፡ አላህ እርሱ ፀፀትን ተቀባይ አዛኝ ነውና፡፡” (አት-ተውባህ፡118)

﴿ يَٰٓأَيُّهَا ٱلَّذِينَ ءَامَنُوٓاْ إِن تَتَّقُواْ ٱللَّهَ يَجۡعَل لَّكُمۡ فُرۡقَانٗا وَيُكَفِّرۡ عَنكُمۡ سَيِّـَٔاتِكُمۡ وَيَغۡفِرۡ لَكُمۡۗ وَٱللَّهُ ذُو ٱلۡفَضۡلِ ٱلۡعَظِيمِ ٢٩ ﴾ الأنفال: ٢٩

“እናንተ ያመናችሁ ሆይ! አላህን ብትፈሩ የእውነት መለያን ብርሃን ያደርግላችኋል፡፡ ክፉ ሥራዎቻችሁንም ከእናንተ ላይ ያብስላችኋል፡፡ አላህም ይምራችኋል፤ አላህም የታላቅ ችሮታ ባለቤት ነዉ፡፡” (አል-አንፋል፡29)

2. **ዙህድ** ፡-

ዙህድ ማለት ዓለማዊና ብልጭልጭ የሆኑ ነገሮችን ለማግኘት ከመስገብገብ ልቦናን ነጻ ማድረግ ሲሆን ይህም አለመሥራንና ልመናን አያበረታታም፡፡ ከዚያ ይልቅ በአላህ መተማመን እንዳለብን፣

ገንዘባችንንም አላህ ለሚወደው ነገር መስዋእት ማድረግን ወዘተ... የሚያጠቃልል ጽንሰ ሐሳብ ነዉ፡፡

ይህን አባባል ይበልጥ የሚያብራራልንን ተከታዩን ሐዲስ ኢብን ማጃህና ሌሎችም የዘገቡት ሲሆን አቡ አባስ ሳህል ኢብን ሳዕድ አስ-ሳኢዲይ (ረ.ዐ.) እንዲህ ብለዋል፡-

“ አንድ ሰው ወደ ነብዩ (ሰ.ዐ.ወ.) መጣና “የአላህ መልእክተኛ ሆይ! ብሰራው አላህና ሰዎች የሚወዱልኝን ሥራ ይጠቁሙኝ” አለ፡፡ እርሳቸውም “ አለማዊነትን ናቅ (ዛሂድ ሁን)፣ አላህ ይወድሃል፡፡ በሰዎች እጅ ያለን ነገር ትኩረት አትስጥ፣ ያፈቅሩሐል፡፡” አሉት፡፡

እንግዲህ ከሐዲሱ የምንቀስመው ትምህርት ዙህድ ማለት ለዓለማዊነት መስገብገብን ማቆም እንጂ ሥራን (ከስብን) ትቶ ለልመና እጆችን መዘርጋት አለመሆኑን ነው፡፡ ሰው ትንፋሽ አጥቶና መከራውን በልቶ አድሜ ልኩን የሰበሰበውን ሃብት ሳይበላው ጥሎት እንደሚሄድ ሁሌም እናያለን፡፡ እናም ሺህ ዓመታትን የምንኖር ይመስል ታላላቅ ሕንጻዎችን እየገነባን፣ የመቶ አመት እቅድ እየነደፍን ሕይወታችንን የምንገፋ ከሆነ ይህ ከዙህድ ጋር በቀጥታ የሚቃረን ድርጊት ነው፡፡ ምክንያቱም ያንን ሁሉ ገንዘብ እኛ ገና ለወደፊቱ ይጠቅመናል ብለን ስንከምር እዚሁ አፍንጫችን ሥር ስንት የቲሞች፣ ችግረኞችና አረጋውያን በረሃብ አለንጋ ይገረፋሉ፡፡ በሃቅ የተላኩት ነብዩ (ሰ.ዐ.ወ.) የሚከተለውን መናገራቸውን ኢብን ዑመር (ረ.ዐ.) እንዲህ በማለት ተናግረዋል፡-

የአላህ መልእክተኛ (ሰ.ዐ.ወ.) ትከሻዬን ያዝ በማድረግ፡- ‹‹በዚህች ዓለም ላይ (ስትኖር) እንደ እንግዳ ወይም መንገድ አቋራጭ ሁን” አሉኝ፡፡

ኢብን ኡመር (ረ.ዐ.) በበኩላቸው እንዲህ ይሉ ነበር፡፡

“ካመሸህ ንጋትን አትጠብቅ፡፡ ካነጋህ ደግሞ እስከ ምሽት (እኖራለሁ ብለህ) አትጠብቅ፡፡ ከጤንነትህ ለሕመምህ፣ ከሕይወትህ ደግሞ ለሞትህ አዘጋጅ፡፡››

3. ተወኩል (በአላህ መመካት)

ተወኩል (በአላህ መመካት) ማለት አንድ የአላህ ባሪያ ሁለንተናውን ለአላህ ፍጹም ተገዢ በማድረግ የእርሱን ጥበቃና እንክብካቤ መሻቱ ማለት ነው፡፡ ተወኩልን የሚመለከቱና ኃያሉ አላህ በክቡር ቃሉ ከተናገራቸው የቁርዓን አንቀጾች ውስጥ የሚከተሉት ይገኙበታል፡፡

﴿ وَلَمَّا رَءَا ٱلۡمُؤۡمِنُونَ ٱلۡأَحۡزَابَ قَالُواْ هَٰذَا مَا وَعَدَنَا ٱللَّهُ وَرَسُولُهُۥ وَصَدَقَ ٱللَّهُ وَرَسُولُهُۥۚ وَمَا زَادَهُمۡ إِلَّآ إِيمَٰنٗا وَتَسۡلِيمٗا ٢٢ ﴾ الأحزاب: ٢٢

"አማኞቹም አሕዛብን ባዩ ጊዜ ይህ አላህና መልእክተኛው የቀጠሩን ነው፡፡ አላህና መልእክተኛውም እውነትን ተናገሩ (የተናገሩት እውነት መሆኑ ተገለጠ) አሉ፡፡ (ይህ) እምነትንና መታዘዝንም እንጂ ሌላን አልጨመረላቸውም፡፡" (አል-አሕዛብ፡22)

﴿ ٱلَّذِينَ قَالَ لَهُمُ ٱلنَّاسُ إِنَّ ٱلنَّاسَ قَدۡ جَمَعُواْ لَكُمۡ فَٱخۡشَوۡهُمۡ فَزَادَهُمۡ إِيمَٰنٗا وَقَالُواْ حَسۡبُنَا ٱللَّهُ وَنِعۡمَ ٱلۡوَكِيلُ ١٧٣ ﴾ آل عمران: ١٧٣

"እነዚያ ሰዎቹ ለእነርሱ፡- ሰዎች ለእናንተ (ጦርን) አከማችተዋልና ፍሯቸው ያሉዋቸውና (ይህም) እምነትን የጨመረላቸው፣ በቂያችንም አላህ ነው፤ ምን ያምርም መጠጊያ ያሉ ናቸው ...." (አሊ-ዒምራን ፡ 173)

﴿ وَتَوَكَّلۡ عَلَى ٱلۡحَيِّ ٱلَّذِي لَا يَمُوتُ ﴾ الفرقان: ٥٨

"በዚያ በማይሞተው፣ ሕያው አምላክ ላይ ተመካ ....."

﴿ وَعَلَى ٱللَّهِ فَلۡيَتَوَكَّلِ ٱلۡمُؤۡمِنُونَ ١٦٠ ﴾ آل عمران: ١٦٠

".....ምእመናን በአላህ ብቻ ይመካሉ፡፡" (አሊ-ዒምራን፡160)

"...ቁርጥ ሐሳብም ባደረግህ ጊዜ በአላህ ላይ ተመካ፡፡ ..."

﴿ وَمَن يَتَوَكَّلۡ عَلَى ٱللَّهِ فَهُوَ حَسۡبُهُۥٓۚ ﴾ الطلاق: ٣

"...በአላህም የሚመካ ሰው እርሱ በቂው ነው፡፡..."(አጥ-ጦላቅ፡3)

﴿ إِنَّمَا ٱلۡمُؤۡمِنُونَ ٱلَّذِينَ إِذَا ذُكِرَ ٱللَّهُ وَجِلَتۡ قُلُوبُهُمۡ وَإِذَا تُلِيَتۡ عَلَيۡهِمۡ ءَايَٰتُهُۥ زَادَتۡهُمۡ إِيمَٰنٗا وَعَلَىٰ رَبِّهِمۡ يَتَوَكَّلُونَ ٢ ﴾ الأنفال: ٢

"ፍጹም ምእመናን እነዚያ አላህ በተወሳ ጊዜ ልቦቻቸው የሚፈሩት፣ በእነርሱም ላይ አንቀጾቻችን በተነበቡ ጊዜ እምነትን የሚጨምሩላቸው፣ በጌታቸውም ብቻ የሚመኩት ናቸው፡፡" (አል-አንፋል፡2)

የአንድ ሰው ልብ አላህን በመውደድ ከረካ እርሱን ብቻ የሚከጅልና ነገሩን ሁሉ ወደ እርሱ ብቻ የሚያስጠጋ ይሆናል፡፡ አላህ ነብዩ ሙሣን (ዐ.ሰ.) በእጃቸው ስለያዟት በትር ምንነት ከጠየቃቸው በኋላ "ጣላት" በማለት አዘዛቸው፡፡ ይህም ተዓምራዊ የሆነ ክስተትን (የበትሯን ወደ እባብነት መለወጥ) ስላስከተለ ለሙሣ (ዐ.ሰ.) ታላቅ የሆነ በራስ የመተማመን መንፈስን ፈጠረላቸው፡፡ ምክንያቱም ሊጋፈጡት የተነሱት ኃያልና ጨካኝ የሆነ ባለጋራ (ፈርዖን) ከፊት ለፊታቸው ይጠብቃቸው ነበርና፡፡ አላህ በሱራ አል-ማኢዳህ እንዲህ በማለት ይናገራል፡-

﴿ وَعَلَى ٱللَّهِ فَتَوَكَّلُوٓاْ إِن كُنتُم مُّؤۡمِنِينَ ٢٣ ﴾ المائدة: ٢٣

"...ምእመናንም እንደሆናችሁ በአላህ ላይ ተመኩ፡፡" (ማኢዳህ፡ 23)

ተወኩል ማለት ለሰነፎች፣ ለዋልጌዎችና ሥራን ጠልተው፣ አስባብን ንቀው ለሚንገላወዱ አውደልዳዮች የሚመች ቃል አይደለም፡፡ እንዲያውም ተወኩል ከዚህ ዓይነት እሳቤ በተቃራኒ የሚቆም ምርጥ የተውሂድ ክፍል ነው፡፡ ለምሳሌ የነብዩ ኢብራሂምን (ዐ.ሰ.) ተወኩል (በአላህ መመካት) ካየን ያ በጣም ምርጥ የሆነ የተወኩል ተምሳሌት

ሲሆን እሳትን ድል የነሱበትና የክብር አክሊል የደፉበት ክስተት ሆኖ በመንፈሳዊው ዓለም ተመዝግቦ አልፏል፡፡

የአላህ መልእክተኛም (ሰ.ዐ.ወ.)

“ሐስቡነላ ሁ ወኒዕመልወኪል” (አላህ በቂያችን ነው፡፡ መመኪያነቱ ምን ያምር!) ነብዩ ኢብራሂም (ዐ.ሰ.) ወደ እሳት ሲወረወሩ ያሉት ቃል ሲሆን ነብዩ ሙሐመድም (ሰ.ዐ.ወ.) “ሰዎች ጦር አከማችተውላችኋልና ፍሯቸው” ሲባሉ ሁኔታው ይበልጥ ኢማን (እምነት) ጨምሮላቸው ይህንኑ ቃል “ሐስቡነላ ሁ ወኒዕመል ወኪል›› ብለዋል፡፡ በማለት ኢብን አባስ (ረ.ዐ.) አስተላልፈዋል፡፡

በሌላ አቡ ሁረይራ (ረ.ዐ.) ባስተላለፉትና ሙስሊም በዘገቡት ሌላ ሐዲስ የአላህ መልእክተኛ (ሰ.ዐ.ወ.) እንደሚከተለው ብለዋል፡-

“ልቦቻቸው እንደ አሞራ ልብ የሆኑ (እንደ አእዋፍ ልቦቻቸው የረቀቁ ወይም ልቦቻቸው በአላህ ፍርሃት የለሰለሱና በማንኛውም ጉዳያቸው በአላህ ላይ ብቻ ተወኩል የሚያደርጉ) ብዙ ሕዝቦች ጀነት ይገባሉ፡፡” ብለዋል፡፡

የአላህ መልእክተኛ (ሰ.ዐ.ወ.) እንዲህም ብለዋል፡-

“በአላህ እውነተኛና ተገቢ የሆነ ተወኩልን (መመካትን) የምትመኩ ብትሆኑ ኖሮ ማለዳ ባዶ ሆዱን ወጥቶ ማታ ሲመለስ ሆዱን ሞልቶና ጠግቦ ለሚመለሰው አሞራ ሲሣይ እንደሰጠ ሁሉ ለእናንተም በሰጣችሁ ነበር፡፡”

ሐዲሱን ኡመር (ረ.ዐ.) ያስተላለፉት ሲሆን ቲርሚዚ “ሀሰን” ነው ብለዋል፡፡

4- ዚክር (አላህን ማስታወስ)

ኃያሉ አላህ ዚክርን (እርሱን ማስታወስን) አስመልክቶ እንደሚከተለው ይላል፡-

﴿ فَٱذۡكُرُونِيٓ أَذۡكُرۡكُمۡ وَٱشۡكُرُواْ لِي وَلَا تَكۡفُرُونِ ١٥٢ ﴾ البقرة: ١٥٢

“አስታውሱኝ አስታውሳችኋለሁና ፤ አመስግኑኝም፣ አትካዱኝም፡ ፡” (አል-በቀራህ፡ 152)

﴿ يَٰٓأَيُّهَا ٱلَّذِينَ ءَامَنُواْ ٱذۡكُرُواْ ٱللَّهَ ذِكۡرٗا كَثِيرٗا ٤١ وَسَبِّحُوهُ بُكۡرَةٗ وَأَصِيلًا ٤٢ ﴾ الأحزاب: ٤١ - ٤٢

“እናንተ ያመናችሁ ሆይ! አላህን ብዙ ማውሳትን አውሱት፡፡ በቀኑ መጀመሪያም መጨረሻም አጥሩት፡፡” (አል-አሕዛብ ፡41-42)

﴿ وَٱلذَّٰكِرِينَ ٱللَّهَ كَثِيرٗا وَٱلذَّٰكِرَٰتِ أَعَدَّ ٱللَّهُ لَهُم مَّغۡفِرَةٗ وَأَجۡرًا عَظِيمٗا ٣٥ ﴾ الأحزاب: ٣٥

“...አላህን በብዙ አውሺዎች ወንዶችና አውሺዎች ሴቶችም አላህ ለእነርሱ ምሕረትንና ታላቅን ምንዳ አዘጋጅቶላቸዋል፡፡” (አል-አህዛብ፡ 35)

﴿ إِنَّ ٱلَّذِينَ عِندَ رَبِّكَ لَا يَسۡتَكۡبِرُونَ عَنۡ عِبَادَتِهِۦ وَيُسَبِّحُونَهُۥ وَلَهُۥ يَسۡجُدُونَ ٢٠٦ ﴾ الأعراف: ٢٠٦

“እነዚያ እጌታህ ዘንድ ያሉት (መላእክት) እርሱን ከመገዛት አይኮሩም፤ ያወድሱታልም፡፡ ለእርሱም ብቻ ይሰግዳሉ፡፡” (አል-አዕራፍ፡ 206)

አላህን ማውሳት (ዚክር) የአላህን ውዴታ የሚያስገኝና እርሱን ወደ መፍራትና እንዲሁም ወደ መጠንቀቅ (ተቅዋ) የሚያሰጠጋ ብቸኛ መንገድ ነው፡፡ ስለ ዚክር ስናወሳ ማወቅ ያለብን ሶላት፣ ዘካ (ሰደቃ)፣ ጾምም ሆነ ሐጅ እንዲሁም ሌሎች የአምልኮ ተግባራት ከዚክር (አላህን ከማስታወስ) ይቆጠራሉ፡፡ አላህ እንዲህ ይላል፡-

﴿ ٱلَّذِينَ ءَامَنُواْ وَتَطۡمَئِنُّ قُلُوبُهُم بِذِكۡرِ ٱللَّهِۗ أَلَا بِذِكۡرِ ٱللَّهِ تَطۡمَئِنُّ ٱلۡقُلُوبُ ٢٨ ﴾

“(እነርሱም) እነዚያ ያመኑ፣ ልቦቻቸውም አላህን በማውሳት የሚረኩ ናቸው። ንቁ! አላህን በማውሳት ልቦች ይረካሉ።” (አር-ረዕድ፡28)

የአላህ መልእክተኛ (ሰ.ዐ.ወ.) የሚከተለውን መናገራቸውን አቡ ሁረይራ አስተላልፈዋል፡-

“አንድን አማኝ ካለበት ዓለማዊ ጭንቀት የገላገለ ሰው አላህ ከፍርዱ ቀን ጭንቅ ይገላግለዋል። የተቸገረን ሰው የረዳ አላህ በዚህም ሆነ በተከታዩ ዓለም ችግሩን ያቃልልለታል። የአንድን ሙስሊም ነውር የሸፈነ አላህ በቅርቢቱ ሕይወት (አዱንያም)፣ በአኼራም የእርሱን ነውር ይሸፍንለታል። እውቀትን ለመፈለግ ጉዞ የጀመረ አላህ ወደ ጀነት የሚወስደውን መንገድ ያገራለታል። ሰዎች ከአላህ ቤቶች በአንዱ ተሰብስበው የአላህን መጽሐፍ በሚያነቡበት (በጋራ ጥናት በሚያደርጉበት) ወቅት በእነርሱ ላይ እርጋታ ይሰፍናል። የአላህ እዝነትም ይከብባቸዋል። መላእክትም ያጅቧቸዋል። አላህም ለእርሱ ቅርብ በሆኑ ክፍሎች (መላእክት ዘንድ) ያወሳቸዋል። ሥራው (ወደ ኋላ) የሚጐትተው ዘሩ ወደፊት አያስቀድመውም።” (ሙስሊም የዘገቡት ሐዲስ)

5- ሶብር (ትዕግስት)

ሶብር (ትዕግስት) ብለን የምንጠራው አንድ ሰው ለአላህ ፈቃድና ውሳኔ ራሱን የሚያስገዛበትን አጠቃላይ ሁኔታ ነው። ይህም ይበልጥ የሚስተዋለው ሰውየውን በሚያጋጥሙት የተለያዩና የማያስደስቱ አለፍ ሲልም የሚፈታተኑ ክስተቶች ጊዜ ነው። አንድ ሰው ሶብር (ትዕግስት) አደረገ የሚባለው አላህ ጥንቱኑ (በቀደር) የወሰናቸው ነገሮች በእርሱ ላይ ሲከሰቱ ውስጣዊውም ሆነ ውጫዊው ባሕሪው ሳይቀየር እንዳመጣጣቸው ማስተናገድ ሲችልና በሁሉም ሁኔታ አላህን ሲያመሰግን ነው። ትዕግስትን የሚጠይቅ ክስተት ሲያጋጥመን ይቅርባይነትን፣ ጨዋነትን፣ ትህትናን፣ ቁጥብነትን፣ ባለው ሁኔታ መርካትን፣ እዝነትን፣ ርህራሄነና መቻልን የመሳሰሉ ባሕሪያትን ማንፀባረቅ ይጠበቅብናል። አላህ በቁርዓን እንዲህ በማለት ያዝዘናል፡-

﴿ وَٱتَّبِعۡ مَا يُوحَىٰٓ إِلَيۡكَ وَٱصۡبِرۡ حَتَّىٰ يَحۡكُمَ ٱللَّهُۚ وَهُوَ خَيۡرُ ٱلۡحَٰكِمِينَ ١٠٩ ﴾

“ወዳንተም የሚወረደውን ነገር ተከተል፡፡ አላህም እስከሚፈርድ ድረስ ታገሥ፡፡ እርሱ ከፈራጆች ሁሉ በላጭ ነው፡፡” (ዩኑስ፡ 109)

﴿ يَٰٓأَيُّهَا ٱلَّذِينَ ءَامَنُواْ ٱصۡبِرُواْ وَصَابِرُواْ وَرَابِطُواْ وَٱتَّقُواْ ٱللَّهَ لَعَلَّكُمۡ تُفۡلِحُونَ ٢٠٠ ﴾ آل عمران: ٢٠٠

“እናንተ ያመናችሁ ሆይ! ታገሱ። ትእግስታችሁም (ከጠላቶቻችሁ ጽናት) የላቀ ይሁን። (ሕልውናችሁን) በንቃት ጠብቁም። አላህንም ፍሩ -ትድኑ ዘንድ።”(አሊ-ዒምራን፡ 200)

﴿ وَلَنَبۡلُوَنَّكُم بِشَيۡءٖ مِّنَ ٱلۡخَوۡفِ وَٱلۡجُوعِ وَنَقۡصٖ مِّنَ ٱلۡأَمۡوَٰلِ وَٱلۡأَنفُسِ وَٱلثَّمَرَٰتِۗ وَبَشِّرِ ٱلصَّٰبِرِينَ ١٥٥ ﴾ البقرة: ١٥٥

“ከፍርሃትና ከረሃብም በጥቂት ነገር ከገንዘቦችና ከነፍሶችም፣ ከፍራፍሬዎችም በመቀነስ በእርግጥ እንሞክራችኋለን፡፡ ታጋሾችንም (በገነት) አብስር፡፡” (አል-በቀራህ፡ 155)

﴿ إِنَّمَا يُوَفَّى ٱلصَّٰبِرُونَ أَجۡرَهُم بِغَيۡرِ حِسَابٖ ١٠ ﴾ الزمر: ١٠

“...ታጋሾቹ ምንዳቸውን የሚስሰጡት ያለገደብ ነው፡፡” (አዝ-ዙመ፡10)

﴿ وَلَمَن صَبَرَ وَغَفَرَ إِنَّ ذَٰلِكَ لَمِنۡ عَزۡمِ ٱلۡأُمُورِ ٤٣ ﴾ الشورى: ٤٣

“የታገሰና ምህረት ያደረገም ሰው ይህ ከምሮቹ (ተፈላጊዎቹ) ነገሮች ነው፡፡” (አስ-ሹራ፡43)

አላህ ትዕግስትን አስመልክቶ በብዙ ቦታዎች ላይ በቁርአን መናገሩ ወደ አላህ ከሚያቃርቡን ነገሮች ዋነኛው መሆኑን እንድናውቅ ያደርገናል፡፡ አላህ በተጨማሪም እንዲህ ይላል፡-

﴿ يَٰٓأَيُّهَا ٱلَّذِينَ ءَامَنُواْ ٱسۡتَعِينُواْ بِٱلصَّبۡرِ وَٱلصَّلَوٰةِۚ إِنَّ ٱللَّهَ مَعَ ٱلصَّٰبِرِينَ ١٥٣ ﴾

"እናንተ ያመናችሁ ሆይ፡ በመታገስና በሶላት ተረዱ፤ አላህ ከታጋሾች ጋር ነውና፡፡" (አል-በቀራህ፡153)

ትእግስት በቁርአን ሰፊ ሽፋን የተሰጠው ሲሆን የአላህ መልእክተኛም (ሰ.ዐ.ወ.) ብዙ ሃዲሶችን ተናግረዋል፡፡ ሱሃይብ ኢብን ሲሃን (ረ.ዐ.) ያስተላለፈውንና ሙስሊም የዘገቡትን የሚከተለውን ሐዲስ አቅርበን ርዕሱን እንዘጋዋለን፡-

"ሙእሚን (አማኝ) ሰው ነገሩ ሁሉ አስደናቂ ነው፡፡ ሁሉም ነገር ለርሱ በጎ ይሆንለታል፡፡ ይህ ደግሞ ማንም የማያገኘውና ለአማኝ ሰው ብቻ የተሰጠ ጸጋ ነው፡፡ ጥሩ ነገር ካጋጠመው አላህን ያመሰግንና ጥሩ ይሆንለታል፡፡ መጥፎ ነገር ሲያጋጥመውም ይታገሥና ጥሩ ይሆንለታል።"

6-ሙራቀባህ

ሙራቀባህ ማለት በግልጽም ሆነ በስውር የምናደርገውን ሁሉ አላህ የሚያይ መሆኑን በመገንዘብ ራስን በሕግጋቱ ቁጥጥር ሥር ማዋል ማለት ነው፡፡ ሃያሉ አላህ እንዲህ ብሏል፡-

﴿ وَتَقَلُّبَكَ فِي ٱلسَّٰجِدِينَ ٢١٩ ﴾ الشعراء: ٢١٩

"በዚያ ለሶላት በምትቆም ጊዜ በሚያይህ በሰጋጆች ውስጥ መዘዋወርህንም (በሚያየው ጌታህ ላይ ተጠጋ)" (አሽ-ሹዐራ፡ 219)

﴿ وَهُوَ مَعَكُمۡ أَيۡنَ مَا كُنتُمۡۚ وَٱللَّهُ بِمَا تَعۡمَلُونَ بَصِيرٞ ٤ ﴾ الحديد: ٤

"እርሱም የትም ብትሆኑ ከእናንተ ጋር ነው...." (አል-ሐዲድ ፡4)

"አላህ በምድርም በሰማይም ምንም ነገር በርሱ ላይ አይሰወርም፡፡" (አሊ-ዒምራን፡14)

“(አላህ) የዓይኖችን ክህደት፣ ልቦችም የሚደብቁትን ሁሉ ያውቃል፡፡” (አል-ሙእሚን፡19)

በዚህ አጽናፈ አለም ውስጥ ከአላህ በስተቀር ሁሉም ጠፊ ነው፡፡ ከመሞትና በመቀስቀስ የሚቀር የለም፡፡ ሕይወትና ሞት፣ መኖርና አለመኖር የየእለት ሁነቶች ናቸው፡፡ በእያንዳንዷ ቅጽበት በሺዎች የሚቆጠሩ ሕዋሳት በሰውነታችን ውስጥ ይሞታሉ፡፡ በሺዎች የሚቆጠሩ ደግሞ ይፈጠራሉ፡፡ በሺዎች የሚቆጠሩ ሕጻናት ይወለዳሉ፣ በሺዎች የሚቆጠሩት ደግሞ ይሞታሉ፡፡ በሌላ በኩል ቁጥር ስፍር የሌላቸው ሰዎች በስሜታቸው ማእበል እየተናጡ አላህን የሚያስቆጣ ነገር ይፈጽማሉ፤ የዚያኑ ያክል የሚሆኑ ሰዎች ደግሞ ወደርሱ በሚያቃርቧቸው መልካም ተግባራት፣ በዱዓ (ልመና) እና በመማፀን ተጠምደው ይገኛሉ፡፡ ያም ቢሆን ቀብር ሁሉንም ሕይወት ያለውን ፍጡር ሁሉ ይጠብቀዋል፡፡

አላህን መጠንቀቅና የምንሰራውን ሁሉ የሚያውቅ መሆኑን ማመን ታላቅ የሆነ የኢማን (እምነት) ደረጃ ሲሆን “ሙራቀባህ” በመባል ይታወቃል፡፡ የአላህ መልእክተኛ ሙራቀባህን አስመልክተው የተናገሩትን አቡ ዘርና ሙአዝ ኢብን ጀበል (አላህ የሁሉንም ሥራ ይውደድላቸውና) ያስተላለፉ ሲሆን ቲርሚዚ ሐዲሱን ዘግበውታል፡፡

“ባለህበት ቦታ ሁሉ አላህን ፍራ፡፡ ክፉ ሰርተህ ከሆነ ወዲያውኑ መልካም ሥራ አስከትልበት፣ ያብሰዋልና፡፡ በመልካም ሥነምባር ከሰዎች ጋር ኑር፡፡”

አቡ ሁረይራ (ረ.ዐ.) ባስተላለፉት ሌላ ሐዲስ የአላህ መልእክተኛ (ሰ.ዐ.ወ.) እንዲህ ብለዋል፡-

“ኃያሉ አላህ ይቀናል፡፡ አላህ የሚቀናው አንድ ሰው እርሱ እርም (ውጉዝ) ያደረገውን ነገር ሲፈጽም ነው፡፡” (ቡኻሪና ሙስሊም የዘገቡት)

7- ሞትን ማስታወስ

ሞት ያለአንተ ፈቃድና ውዴታ ከምትወዳቸው ቤተሰቦችህና ባለቤትህ በግድ መንጭቆ እንደሚወስድህ አስታውስ። ስለሆነም ለሥጋህ ማደሩን ወደ ጐን አድርግና ተዘጋጅተህ ጠብቀው። ይህም በእምነት (ኢማን) ላይ የተመሠረተ ማሰላሰልንና የሕሊና ንቃትን ይጠይቃል። የዚህ ዓለም ከንቱ ምኞቶች፣ ኃላፊና ጠፊ የሆኑ የቁም ቅዠቶችና የማይጨበጡ ተስፋዎች ልክ በመቃብሮች ላይ እንደረገፉ የዛፍ ቅጠሎች ናቸው። እያንዳንዱ የመቃብር ቦታና በላዩ ላይ ለምልክት የተተከለበት ድንጋይ በዝምታቸው ድባብ ቢዋጡም ብዙ ብዙ ነገር ይነግሩናል።

መቃብሮች በከተሞች ውስጥ፣ በመንገድ ዳርና ሰዎች በቀላሉ ሊደርሱባቸው በሚችሉባቸው ቦታዎች የሚዘጋጁት ለዚህ ተብሎ ነው። በእነዚያ የመቃብር ሥፍራዎች በኩል የሚያልፍ ሰው ሁሉ ሞትን በተደጋጋሚ ያስታውሳል።

እርግጥ ነው የሞትን አስፈሪ ገጽታ ቃላት ተሰሳስበው የመግለጽ አቅም አይኖራቸውም ይሆናል። የሆነ ሆኖ የሁላችንም የመጨረሻ እጣ ፈንታ እርሱ መሆኑና ኃይላችንና ሩጫችንን ሁሉ እንደሚገታው ለአፍታ መዘንጋት የለብንም። ሞት በሚመጣበት ጊዜ ለዚህ ዓለም ሰዎች (ለቋሚዎቹ) የሚተርፋቸው እንባና ሃዘን ብቻ ነው።

እናም የሰው ልጅ ስጋዊ ስሜቱን ማሳደዱን በፈቃደኝነቱ ቢተውና ወደ አላህ ቢመለስ አላህን በእርግጠኝነት አዛኝና ሩህሩህ ሆኖ ያገኘዋል። የልእልና ባለቤት የሆነው አላህ በክቡር ቃሉ እንዲህ ይላል፡-

﴿ أَوَمَن كَانَ مَيۡتٗا فَأَحۡيَيۡنَٰهُ وَجَعَلۡنَا لَهُۥ نُورٗا يَمۡشِي بِهِۦ فِي ٱلنَّاسِ كَمَن مَّثَلُهُۥ فِي ٱلظُّلُمَٰتِ لَيۡسَ بِخَارِجٖ مِّنۡهَاۚ كَذَٰلِكَ زُيِّنَ لِلۡكَٰفِرِينَ مَا كَانُواْ يَعۡمَلُونَ ١٢٢ ﴾

الأنعام: ١٢٢

“ሙት የነበረና ሕያው ያደረግነው፣ ለእርሱም በሰዎች መካከል በእርሱ የሚሄድበትን ብርሃን ያደረግንለት ሰው በጨለማዎች ውስጥ

ከእርሷ የማይወጣ ሆኖ እንዳለ ሰው ብጤ ነውን? እንደዚሁ ለከሃዲያን ይሰሩት የነበሩት ነገር ተጌጠላቸው፡፡" (አል-አንዐም፡122)

ይህች ዓለም የማትጨበጥና እንደ ጤዛ ጧት ታይታ ረፋድ ላይ የምትረግፍ ስትሆን ሃገር ማለት መጪው ዓለም (አኼራ) ነው፡፡ ሞት ደግሞ በአንድ ሰው ላይ ቂያማን (የፍርዱን ቀን) ለብቻው የሚያቆምበት ክስተት ነው፡፡ ስለሆነም ከጥልቅ እንቅልፋችን እንንቃ፡፡ ማንም ቢሆን ከሞት መላአክት ጋር መገናኘቱን ሊያስወግድ ከቶ አይቻለው፡፡ ወዴት ተሂዶ ማምለጥ ይቻላል? ስለሆነም የሰው ልጅ የአላህን እዝነትና ርህራሄ መላበስና ለመጪው ነገር ሁሉ ተዘጋጅቶ መጠበቅ ግድ ይሆንበታል፡፡ አላህ እንዲህ ይላል፡-

﴿ فَفِرُّوٓاْ إِلَى ٱللَّهِۖ إِنِّي لَكُم مِّنۡهُ نَذِيرٞ مُّبِينٞ ٥٠ ﴾ الذاريات: ٥٠

"ወደ አላህም ሽሹ ፤ እኔ ለእናንተ ከእርሱ ግልጽ አስጠንቃቂ ነኝና (በላቸው)፡፡" (አዝ-ዛሪያት፡50)

አንድ ሰው ለሥጋዊ ስሜቱ በማደር የዚህች ዓለም ኮንትራቱን ጨርሶ ወደዚያ ጉድጓድ ከገባ ጥልቅና ድቅድቅ ጨለማን እንጂ ሌላ የሚያገኘው ነገር አየኖርም፡፡ ይህን ጽልመትና በዚያ የሚጠብቀውን አስፈሪ ትእይንት ከሌላ ከምንም አይነት ነገር ጋር ማነጻጸር አይቻልም፡፡

ምዕራፍ ዘጠኝ

ሪዝቅ (ሲሳይ)

አቡ ሃዚም የተባሉ የእውቀት ባለቤት ሪዝቅን (ሲሳይን) አስመልክተው እዲህ ይላሉ ፡- “ይህን ዓለም ስዳስሰው ከሁለት ነገር ውጪ ምንም አላገኘሁበትም፡፡ የመጀመሪያው የራሴን ሪዝቅ ሲሆን ሁለተኛው ደግሞ የሌላን ሰው ሪዝቅ ነው፡፡ እኔ ነፋስን እየጋለብኩ አብሬው ብከንፍም እንኳ የእኔ ሪዝቅ የትም እንደማይሄድ አመንኩ፡፡ የሌላን ሰው ሪዝቅ ለመውሰድ ከነፋስ ጋር ብከንፍ እንኳ ፈጽሞ ልይዘው (ልደርስበት) እንደማልችልም ተገነዘብኩ፡፡››

ማጣት፣ ድህነት፣ የገቢ ምንጭ አለማግኘት፣ የተጣበበ ኑሮ የሰውን ልጅ ሕይወት ከሚያጨናንቁትና ታላቅ ፍርሃት ከሚያጭሩ ምክንያቶች ዋነኞቹ ከሆኑ ቆይተዋል፡፡ የሰው ልጅ በእናቱ ማህፀን ውስጥ መፈጠር ከጀመረበት ጊዜ ጀምሮ እስኪሞት ድረስ ሪዝቅ አይቋረጥም፡፡ እንዲያውም የአላህ መልእክተኛ (ሰ.ዐ.ወ.) የሰው ልጅ ሪዝቅ (ማለትም እድሜ ልኩን የሚያገኘው) በአላህ አስቀድሞ የተወሰነ መሆኑን በቀጣዩ ሐዲስ ተናግረዋል፡-

“በእርግጥ የእያንዳንዳችሁ መሠረተ አካል በእናታችሁ ሆድ (ማህፀን) ውስጥ ለአርባ ቀን በዘር መልክ ይሰበሰባል፡፡ ለተመሳሳይ ቀናትም የረጋ ደም ይሆናል፡፡ ቀጥሎም በተመሳሳይ ቀናት (የታኘከ የሚመስል) ሥጋ ይሆናል፡፡ ከዚያ ከኋላ መልአክ ወደርሱ ይላክና ሩህ (ነፍስ) ይዘራበታል፡ ፡ መልአኩም አራት ነገሮችን እንዲጽፍ ይታዘዛል፡፡ የእለት ጉርሱን፣ እድሜውን፣ ሥራውንና ከሃዲ ወይም አማኝ መሆኑን፡፡ ...”

እዚህ ላይ የእለት ጉርስ የሚለው አገላለጽ ሪዝቅ (ሲሳይ) ማለት እንደሆነ ልብ ይሏል፡፡

ሌላው አስደናቂ ነገር የሰው ልጅ ሪዝቅ (ሲሳይ) ብቻ ሳይሆን የማንኛውም ሕይወት ያለው ፍጡር ሪዝቅ ሁሉ በመጀመሪያ ሳይፈጠር በፊት የተወሰነ ወሆኑ ነው፡፡ ከዚያ ከተወሰነለት ከፍ ወይም ዝቅ

አይልም፡፡ ኃያሉ ፈጣሪያችን አላህ ለእያንዳንዱ ፍጡር ሲሳዩን የሚያቀርበው እርሱ መሆኑንና ሁሉም የእርሱ ጥገኛ እንደሆነ ሲገልጽ እንዲህ ይላል፡-

﴿ وَمَا مِن دَآبَّةٖ فِي ٱلۡأَرۡضِ إِلَّا عَلَى ٱللَّهِ رِزۡقُهَا وَيَعۡلَمُ مُسۡتَقَرَّهَا وَمُسۡتَوۡدَعَهَاۚ كُلّٞ فِي كِتَٰبٖ مُّبِينٖ ٦ ﴾ هود: ٦

"በምድርም ላይ ምንም ተንቀሳቃሽ የለችም ምግቧ በአላህ ላይ ያለ ቢሆን እንጂ፡፡ ማረፊያዋንም መርጊያዋንም ያውቃል፡፡ ሁሉም ግልጽ በሆነው መጽሐፍ ውስጥ ነው፡፡"(ሁድ፡6)

እንግዲህ አላህ ለእያንዳንዱ ፍጡር የየራሱን ድርሻ የሆነውን ሲሳዩን ቢለግሰውም በተሰጣቸው ሪዝቅ (ሲሳይ) የሚረኩና የሚያመሰግኑት የእርሱ ወዳጆች ብቻ ናቸው፡፡ በቀጣዩ የቁርአን አንቀጽ አላህ የራሳቸውን ምግብ መሸከምና ከቦታ ቦታ ማድረስ የማይችሉ ደካማና ስንኩላን የሆኑ ፍጡራንን ሳይቀር እንደሚመግብ ሲገልጽ እንዲህ ይላል፡-

﴿ وَكَأَيِّن مِّن دَآبَّةٖ لَّا تَحۡمِلُ رِزۡقَهَا ٱللَّهُ يَرۡزُقُهَا وَإِيَّاكُمۡۚ وَهُوَ ٱلسَّمِيعُ ٱلۡعَلِيمُ ٦٠ ﴾ العنكبوت: ٦٠

"ከተንቀሳቃሽም ምግቧን ለመሸከም የማትችለው ብዙ ናት፡፡ አላህ ይመግባታል፡፡ እናንተንም (ይመግባል)፡፡ እርሱ ሰሚው አዋቂው ነውና፡፡" (አል-ዐንከቡት፡60)

በዚህ ዓለም ላይ የሰው ልጆች ሪዝቅ የተለያየ (ለአንዱ ብዙ ለሌላው ትንሽ) መሆኑ በራሱ ከጀርባው ታላቅ ጥበብን ያዘለ መሆኑን ማወቅ ይጠቅማል፡፡ አንዱ ሃብታም ሌላው ድሃ መሆኑ ሰዎች እርስ በርስ እንዲከፋፈሉና እንዲጋጩ ሳይሆን ስምምነት እንዲኖራቸው አድርጓል፡፡ ቁርአን የሚያስተምረን ሁሉም የዚህ ዓለም ሃብት የአላህ እንደሆነና ለሰዎች የተከፋፈለውም በመለኮታዊ ጥበብ ተቀምሮ መሆኑን ነው፡፡ ይህም የሲሳይ ድልድል የሰው ልጅ ሳይፈጠር በፊት የአላህን ውሳኔ (ቀደርን) መሠረት ያደረገ ነው፡፡

ስለሆነም የሰው ልጆች በሚያገኙት ጉርሳቸው (ሲሳያቸው) መጠን መለያየታቸው በአላህ ውሳኔና ለእርሱ በሚበጃቸው መልኩ እንደሆነ አማኞች ማመን አለባቸው፡፡ የዚህን ዓለም ሕይወት መምራትና ማስተናበር ለሰው ልጆች ለራሳቸው የተተወ ቢሆን ኖሮ ብዙ መከራና ችግር በተከሰተና ስርአት አልበኝነትና ራስ ወዳድነትም በነገሰ ነበር፡፡

አላህ በቁርአኑ እንዲህ ይላል፡-

﴿ أَهُمۡ يَقۡسِمُونَ رَحۡمَتَ رَبِّكَۚ نَحۡنُ قَسَمۡنَا بَيۡنَهُم مَّعِيشَتَهُمۡ فِي ٱلۡحَيَوٰةِ ٱلدُّنۡيَاۚ وَرَفَعۡنَا بَعۡضَهُمۡ فَوۡقَ بَعۡضٖ دَرَجَٰتٖ لِّيَتَّخِذَ بَعۡضُهُم بَعۡضٗا سُخۡرِيّٗاۗ وَرَحۡمَتُ رَبِّكَ خَيۡرٞ مِّمَّا يَجۡمَعُونَ ٣٢ ﴾ الزخرف: ٣٢

“እነርሱ የጌታህ ችሮታ ያከፋፍላሉን? እኛ በቅርቡቱ ሕይወት ኑሯቸውን በመካከላቸው አከፋፍለናል፡፡ ከፊላቸውም ከፊሉን ሰራተኛ አድርጎ ይይዝ ዘንድ ከፊላቸውን ከከፊሉ በላይ በደረጃዎች (በሃብት) አበለጥን፡፡ የጌታህም ፀጋ (ገነት) ከሚሰበሰቡት (በሃብት) በላጭ ናት፡፡” (አዝ-ዙኽሩፍ፡ 32)

በሌላ የቁርአነ አንቀጽ ኃያሉ አላህ እንዲህ ይላል፡-

﴿ قُل لَّوۡ أَنتُمۡ تَمۡلِكُونَ خَزَآئِنَ رَحۡمَةِ رَبِّيٓ إِذٗا لَّأَمۡسَكۡتُمۡ خَشۡيَةَ ٱلۡإِنفَاقِۚ وَكَانَ ٱلۡإِنسَٰنُ قَتُورٗا ١٠٠ ﴾ الإسراء: ١٠٠

“እናንተ የጌታዬን የችሮታ መጋዘኖች ብትይዙ ኖሮ ያን ጊዜ ስትመጸውቱ እንዳታልቅ በመፍራት በነፈጋችሁ ነበር፡፡ ሰውም በጣም ንፉግ ነው፡፡“ (አል-ኢስራእ፡100)

ለፍጡራኑ የእለት ሲሳያቸውን መስጠት የአላህ ሉአላዊነት መገለጫ ዋና ምልክት ነው፡፡ በእያንዳንዱ እለት በማንኛውም ሰአት በሰማይ ለሚበርሩ፣ በምድር ለሚጓዙና በባህርም ውስጥ ለሚዋኙ ፍጡራን የማእድ ጠረጴዛ እንደተዘጋጀላቸው ነው፡፡ ከዚህም በተጨማሪ አንዱ የሚመገበውን ሌላው ስለማይፈልገው የምግብ አቅርቦት ስርአቱ በመልካም ስሌት ላይ የተደላደለ እንዲሆን አስችሏል፡፡

የሰው ልጆች ምን እንመገብ ይሆን? ብለው ከልክ በላይ እንዳይጨነቁ ለማረጋጋት አላህ የሚከተለውን የቁርአን አንቀጽ አውርዷል፡-

﴿ وَلَا تَقۡتُلُوٓاْ أَوۡلَٰدَكُمۡ خَشۡيَةَ إِمۡلَٰقٖۖ نَّحۡنُ نَرۡزُقُهُمۡ وَإِيَّاكُمۡۚ إِنَّ قَتۡلَهُمۡ كَانَ خِطۡـٔٗا كَبِيرٗا ٣١ ﴾ الإسراء: ٣١

"ልጆቻችሁንም ድህነትን በመፍራት አትግደሉ፡፡ እኛ እንመግባቸዋለን፡፡ እናንተንም (እንመግባለን)፡፡ እነርሱን መግደል ታላቅ ኃጢአት ነውና፡፡"(አል-ኢስራእ፡31)

አላህን መገዛትና ሶላትን መስገድ ሪዝቅ (ሲሳይ) ለማግኘት ሰበብ እንደሚሆን አላህ ሲገልጽ እንዲህ ይላል፡-

﴿ وَأۡمُرۡ أَهۡلَكَ بِٱلصَّلَوٰةِ وَٱصۡطَبِرۡ عَلَيۡهَاۖ لَا نَسۡـَٔلُكَ رِزۡقٗاۖ نَّحۡنُ نَرۡزُقُكَۗ وَٱلۡعَٰقِبَةُ لِلتَّقۡوَىٰ ١٣٢ ﴾ طه: ١٣٢

"ቤተሰብህን በስግደት እዘዝ፤ በርሷም ላይ ዘወትር፡፡ ሲሳይን አንጠይቅህም፡፡ እኛ እንሰጥሃለን፡፡ መልካሚቱ ፍጻሜም ለጥንቁቆቹ ናት፡፡" (ጣሃ፡132)

የአላህ መልእክተኛ (ሰ.ዐ.ወ.) ሪዝቅን (ሲሳይን) አስመልክተው እንዲህ ብለዋል፡-

"ከእናንተ አንዳችሁ በደረጃ (በሃብት) የሚበልጠውን ካየ ከእርሱ የሚያንሰውን ደግሞ ይመልከት፡፡ ይህን ማድረጋችሁ አላህ የሰጣችሁን ፀጋ አሳንሳችሁ እንዳታዩ ይረዳችኋልና፡፡" (ቡኻሪ፣ሙስሊምና ቲርሚዚ)

ስለሆነም በሕይወት ስንኖር ደስታ የምናገኘው ጥበበኛ የሆነው አላህ የሰጠን ሪዝቅ (ሲሳይ) ለእኛ የሚበጀንና የተሻለ ነው ብለን ስናምን ነው፡፡ በዚህ አለም ላይ ላዩን ሲታዩ ለእኛ መጥፎ የሚመስሉ፣ ውጤታቸው ግን መልካም የሆኑ ነገሮች አሉ፡፡ ለምሳሌ አንድ ሰው በድህነት ኖሮ ጀነት ሊገባ ይችላል፡፡ በሌላ በኩል ደግሞ መልካም መስለው የሚታዩ ነገሮች መጨረሻቸው ለእኛ የማይጠቅም እንዲያውም አጥፊያችን ይሆናሉ፡፡ ለምሳሌ ሃብትን አንድ ሰው ተሰጥቶ አላህ ለሚፈልገው ጉዳይ

ሳይሆን ለራሱ ስሜትና ለማይረቡ ነገሮች ወጪ የሚያደርገው ከሆነ ይህ ታላቅ ጥፋት ነው። አላህ እንዲህ ይላል፡-

﴿ وَلَا تَمُدَّنَّ عَيۡنَيۡكَ إِلَىٰ مَا مَتَّعۡنَا بِهِۦٓ أَزۡوَٰجٗا مِّنۡهُمۡ زَهۡرَةَ ٱلۡحَيَوٰةِ ٱلدُّنۡيَا لِنَفۡتِنَهُمۡ فِيهِۚ وَرِزۡقُ رَبِّكَ خَيۡرٞ وَأَبۡقَىٰ ١٣١ ﴾ طه: ١٣١

"አይናችሁንም በእነርሱ (ከሰዎቹ) ክፍሎችን በእርሱ ልንፈትናቸው ወደ አጣቀምንበት ወደ ቅርቢቱ ሕይወት ጌጦች አትዘርጋ። የጌታህ ሲሳይም በጣም በላጭ ዘውታሪም ነው።" (ጣሃ፡131)

አላህ በተጨማሪም እንዲህ ይላል፡-

﴿ كُلُواْ مِن طَيِّبَٰتِ مَا رَزَقۡنَٰكُمۡ وَلَا تَطۡغَوۡاْ فِيهِ فَيَحِلَّ عَلَيۡكُمۡ غَضَبِيۖ وَمَن يَحۡلِلۡ عَلَيۡهِ غَضَبِي فَقَدۡ هَوَىٰ ٨١ ﴾ طه: ٨١

"ከሰጠናችሁ ሲሳይ ከመልካሙ ብሉ። በእርሱም ወሰንን አትለፉ። ቁጣዬ በእናንተ ላይ ይወርድባችኋልና። በእርሱም ላይ ቁጣዬ የሚወርድበት ሰው ይጠፋል።" (ጣሃ፡81)

አላህ ነገሮችን በልክ እንደሚያወርድና በይበልጥም ደግሞ ሲሳይን ሲለግስ የባሮቹን ሁኔታ፣ ባህሪ፣ የገንዘብ አጠቃቀም ብልሃትን ወዘተ... ታሳቢ አድርጎ መሆኑን እንዲህ በማለት ይገልጻል።

﴿ وَلَوۡ بَسَطَ ٱللَّهُ ٱلرِّزۡقَ لِعِبَادِهِۦ لَبَغَوۡاْ فِي ٱلۡأَرۡضِ وَلَٰكِن يُنَزِّلُ بِقَدَرٖ مَّا يَشَآءُۚ إِنَّهُۥ بِعِبَادِهِۦ خَبِيرُۢ بَصِيرٞ ٢٧ ﴾ الشورى: ٢٧

"አላህ ለባሮቹ (ሁሉ) ሲሳይን በዘረጋ ኖሮ በምድር ውስጥ (ሁሉም) ወሰን ባለፉ ነበር። ግን የሚሻውን በልክ ያወርዳል። እርሱ በባሮቹ ውስጥ አዋቂ ተመልካች ነውና።" (አሹ-ሹራ፡27)

የሰው ልጅ ሪዝቁ ተወስኖ የተቀመጠው ከመፈጠሩ በፊት እንደመሆኑ ለአላህ ፈቃድ ራሱን በማስገዛት በቀደር የማመንን ጣፋጭ ለዛ ሊያጣጥም ይችላል። የሚከተለው አባባል በሐዲስ አል-ቁድስ ተጠቅሶ እናገኘዋለን፡-

አላህ የሰዎችን ሪዝቅ (ሲሳይ) የማያከፋፍሉ ለሆኑ መላእክት እንዲህ በማለት ያዛቸዋል፡-

“በመጪው ዓለም ጉዳይ ላይ ብቻ ተመስጦ ለምታገኙት ባሪያዬ የሰማይንና የምድርን በረከቶች ስጡት፡፡ ባሪያዬ ሲሳዩን ለማግኘት ቀናውን ጉዳና እየተከተለ ካገኛችሁት ለእርሱ መልካም በመሆን መንገዱ እንዲገራለት አድርጉ፡፡” (ነዋዲር አል-ኡሱል)

ይህ ሐዲስ በግልጽ እንደሚያሳየው አንድ የአላህ ባሪያ አላህን በመግዛት ላይ ትኩረቱን ሲያደርግ፣ የእርሱን ትእዛዛት ሲያከበርና የእርሱን ውዴታ በመሻት ሁለንተሃውን ሲያስገዛና ሐቀኛ የአላህ ወዳጅ በመሆን ተቅዋ ያለው ይሆናል፡፡ ለእንዲህ አይነቱ ሰው ደግሞ ከሰማይም ሆነ ከምድር የአላህ በረከቶች ይከፈቱለታል፡፡ አላህ በቁርአን እንዲህ ይላል፡-

﴿ وَمَن يَتَّقِ ٱللَّهَ يَجۡعَل لَّهُۥ مَخۡرَجٗا ۝٢ وَيَرۡزُقۡهُ مِنۡ حَيۡثُ لَا يَحۡتَسِبُۚ وَمَن يَتَوَكَّلۡ عَلَى ٱللَّهِ فَهُوَ حَسۡبُهُۥٓۚ إِنَّ ٱللَّهَ بَٰلِغُ أَمۡرِهِۦۚ قَدۡ جَعَلَ ٱللَّهُ لِكُلِّ شَيۡءٖ قَدۡرٗا ۝٣ ﴾ الطلاق: ٢ - ٣

“….አላህንም የሚፈራ ሰው ለእርሱ መውጫን ያደርግለታል፡፡ ከማያስበውም በኩል ሲሳይን ይሰጠዋል፡፡ በአላህም ላይ የሚጠጋ ሰው እርሱ በቂው ነው፡፡ አላህ ፈቃዱን አድራሽ ነው….” (አጥ-ጦላቅ፡2-3)

ኡመር (ረ.ዐ.) ባወሩትና ቲርሚዚ የ ”ሐሰን” ደረጃ በሰጡት ሐዲስ የአላህ መልእክተኛ (ሰ.ዐ.ወ.) እንደሚከተለው ብለዋል፡-

“እውነተኛና ተገቢው የሆነ ተወኩል (መመካት) በአላህ ላይ ቢኖራችሁ ማለዳ ባዶ ሆዱን ወጥቶ ማታ ሲመለስ ሆዱን ሞልቶና ጠግቦ ለሚመለሰው አሞራ ሲሣይ እንደሰጠ ሁሉ ለእናንተም በሰጣችሁ ነበር፡፡”

በፍጥረተ ዓለሙ ውስጥ ልክ እንደ ጉንዳን ለክረምት ወራት ምግባቸውን የሚያስቀምጡ ነፍሳት ጥቂት ናቸው፡፡ አብዛኛዎቹ ለከፋ የክረምት ወቅት እንኳ ቅድመ ዝግጅት በማድረግ ምግባቸውን አያከማቹም፡፡ እንዲያም ሆኖ በህልውና የሚያቆያቸውን ጥንካሬ በማግኘት ለፀደይ ወራት መዝለቅ አይሳናቸውም፡፡ ብቃትና አስተማማኝነት ባለው

መለኮታዊ አገዛዝ ሥር ፍጡራን እንዴት የእለት ጉርሳቸውን አያገኙም ተብሎ ይታሰባል? ይሁን እንጂ ስንፍና፣ ስግብግብነት፣ ቅናት፣ ልጆች እንዳይወለዱ መፈለግ ወዘተ...ለሪዝቃችን (ሲሳያችን) መጥበብ ተጠያቂ የሆኑ ጋሬጣዎች ናቸው፡፡

እንግዲህ ኢስላም የሚያስተምረን እያንዳንዱ ሰው የእለት ጉርስ (ሪዝቅ) አስቀድሞ የተወሰነ ሲሆን አይጨምርም አይቀንስም፡፡ የሰው ልጅ ከተፈጠረባት ቅጽበት ጀምሮ የሚተነፍሳት አየርና የሚጐርሳት እያንዳንዷ ጉርሻ በልክ ተወስና የተቀመጠች ናት፡፡ ይሁን እንጂ ይህንን የእለት ጉርስን ለማግኘት ተግቶ መንቀሳቀስ በአማኞች ላይ ግዴታ የሆነ ተግባር ነው፡፡ ስለሆነም አላህን መታዘዝና ለሪዝቃችን (ሲሳያችን) መንቀሳቀስ ግዴታችን ነው ማለት ነው፡፡ ይህ ማለት በሌላ አባባል በቀደር የተጻፈልን ሪዝቃችንና እርሱን ለማግኘት የምናደርገው ጥረት በጽኑ የተሳሰሩ ናቸው ማለት ነው፡፡ አንድ የቱርኮች አባባል አለ፡- “በቂ የሆነ ጥረት ሳታደርግ በሃሰት በቀደር አታመካኝ” ይላል፡፡ ኃያሉ አላህ ነጻ ፈቃድ ሰጥቶናል፡፡ የሥራ ፈጠራ፣ ኃላፊነትን መሸከም፣ የመምረጥ ነጻነትና ማስተዋልን የመሳሰሉ ብቃቶችን አላብሶናል፡፡ እነዚህን ነገሮች ችላ ማለትና ለድህነት እንዲሁም ለተረጂነት መዳረግ በእውነቱ በአላህ ላይ እንደማመጽ ነው የሚቆጠረው፡፡

ራሳችንን ከአደጋ መጠበቅ በተፈጥሮ የምንወርሰው ነገር ነው፡፡ ለምሳሌ፡- ስንታመም ወደ ሃኪም ዘንድ መሄድ፣ አደገኛ የሆነ እሳት ወይም ርእደ መሬት ሲያጋጥመን ከዚያ ሥፍራ መሸሽ ከዚህ ተፈጥሮአዊ ባህሪያችን የወረስነው ነው፡፡ በሌላ በኩል ሪዝቃችንን ወዲያና ወዲህ ተሯሩጠን መፈለግ ከአደጋ ሚጠብቀን መለኮታዊ ትእዛዝ ነው፡፡ ይህን ማድረጋችን ከቶም በቀደር ከማመናችን ጋር ፈጽሞ የሚጋጭ አይደለም፡፡ ከአስባብ ጋር የመጋጨትን ሕግ መጣስ በራሱ በአላህ ላይ እንደማመጽ የሚቆጠር ሲሆን ይህም ታላቅ የሆነ ኃጢአት ነው፡፡ አላህ በቁርአኑ እንዲህ ይላል፡-

﴿ وَأَن لَّيْسَ لِلْإِنسَٰنِ إِلَّا مَا سَعَىٰ ﴿٣٩﴾ ﴾ النجم: ٣٩

"ለሰውም ሁሉ የሰራው እንጂ ሌላ የለውም፡፡" (አን-ነጅም፡ 39)

ታላቁ መልእክተኛ ሙሐመድ ኢብን አብዱላህም (ሰ.ዐ.ወ.) እንዲህ ብለዋል፡-

"አንድ ሰው ከሰዎች ከመለመን ገመድ ይዞ ወደ ጫካ በመሄድ በእንጨት ሰብስቦ እየሸጠ ቢተዳደር ይሻለዋል፡፡ ሰዎች የሚፈልገውን ቢሰጡትም ቢነፍጉትም፡፡" (ቡኻሪ የዘገቡት)

ኢብን አል ፊራሲ እንዳስተላለፉት አንድ እለት አባታቸው ነብዩን (ሰ.ዐ.ወ.) እንዲህ በማለት ጠየቋቸው፡- "የአላህ መልክተኛ ሆይ! የሚያስፈልገኝን ነገር ከሰዎች መጠየቅ እችላለሁን?" ነብዩም (ሰ.ዐ.ወ.) እንዲህ በማለት መልስ ሰጧቸው፡- "ማንንም አትጠይቅ! ይሁን እንጂ መጠየቅህ ግድ ከሆነ ምእመናንን ጠይቅ፡፡" (ነሳኢ፣ አቡ ዳውድና ኢብን ማጃህ)

ከዚህ በተጨማሪ ደግሞ ኃያሉ አላህ አንዱን ፍጡር ለሌላው ጉርስ የማግኛ ሰበብ አድርጐ ነው የፈጠረው፡፡ ይህም በመሆኑ ድሆችን መንከባከብ፣ የእነርሱን ፍላጐት ማሟላትና አላህ በለገሰን ነገር የእነርሱን ችግር መቅረፍ እንደ ታላቅ መልካም ሥራና ጽድቅ ይቆጠርልናል፡፡ ጂብሪል (ዐ.ሰ.) የሚከተለውን መናገሩ ተወስቷል፡-

"እኔ ከዚህ ዓለም ሕዝብ መካከል ብሆን ኖሮ ሶስት ነገሮችን ከሁሉም በላይ እወድ ነበር፡፡ መንገድ የጠፋቸው ሰዎችን ማመላከት፣ አላህን በድህነት ላይ ሆኖ የሚያመልክን ሰው፣ እንዲሁም በድህነት ላይ ሆነው ብዙ ልጆችን የሚያሳድጉ ሰዎችን መርዳት፡፡"

የተፈቀዱ (ሃላል) ምግቦች

በአላህ የምናምን ሰዎች ሁሉ የትኩረት ማዕከል መሆን ያለበት ሌላው ነጥብ የምናገኘው ሲሳይ (ምግብ) የተፈቀደ (ሃላል) ከሆነ ምንጭ የተገኘ ከመሆኑ ላይ ነው፡፡ አንድን ሰው ቀናውን መንገድ ተከትሎ እንዲጓዝ ትልቅ አትስተዋጽኦ የሚያደርግለት የሚመገበው ሲሳይ ሃላል መሆኑ ነው፡፡ ሃላል (የተፈቀደን) ምግብ መመገብ ለሕይወት ብርሃን፣ ለልብ

ደስታን፣ ለአምልኮት (ኢባዳ) ለዛን ያላብሳል። የተስተካከለችና አላህን የምትፈራ ቀልብ (ልብ) እንድትኖረንም ወሳኝ ነው። በሌላ በኩል ደግሞ ሃራም የሆነ ምግብ ሕይወትን የሚያበላሽ መርዝ ሲሆን ለቀልብም ጨለማን ያላብሳል። በዚህ ዓለም ላይ የሚታየው የዘቀጠ ስርዓትና በመጪውም ዓለም የሚያጋጥመው ውርደት የዚሁ ህገወጥ (ሃራም) የሆነ ሲሳይ አስፈሪ ውጤት እንጂ ሌላ አይደለም።

ሃላል (የተፈቀደ) ገቢና ምግብ ከአላህ ዘንድ ለመቃረብ ሰበብ የሚሆኑ ሲሆን በተቃራኒ ሃራም (ህገወጥ) ከሆነ ገቢ የተገኘ ገንዘብና ምግብ ለታላቅ ፀፀትና መከራ የሚዳርግ የእሳት ጉርስ ነው። የአንድ ሰው ቀልብ በአላህ ፈንታ በገንዘብና በልጆች ፍቅር ሲሞላ መጨረሻው ሃዘንና ተስፋ መቁረጥ ነው።

አላህ በቁርአን እንዲህ ይላል፡-

﴿ يَٰٓأَيُّهَا ٱلنَّاسُ أَنتُمُ ٱلۡفُقَرَآءُ إِلَى ٱللَّهِۖ وَٱللَّهُ هُوَ ٱلۡغَنِيُّ ٱلۡحَمِيدُ ١٥ ﴾ فاطر: ١٥

“እናንተ ሰዎች ሆይ! እናንተ (ሁልጊዜ) ወደ አላህ ከጃዮች ናችሁ። አላህም እርሱ ተብቃቂው ምስጉኑ ነው።” (ፋጢር፡15)

ኡመር ኢብን አል-ኸጣብ (ረ.ዐ.) የሚከተለውን ዱዓ ያደርጉ ነበር፡-

“አላህ ሆይ! ለጋስ ለሆኑት ሰዎቻችን ሲሳያቸውን አስፋላቸው። ከእኛ ውስጥ የተቸገሩትን ይረዱበታልና።”

በሌላ በኩል ግን በሃራም የተገኘ ገንዘብ ዘካም ሆነ ሰደቃ ሊወጣበት አይችልም። ምንጩ ሃላል (የተፈቀደ) አይደለምና። ሃራም የሆነ ምግብ በዚህም ሆነ በመጪው ዓለም የመከራ ምንጭ ነው። ሃላል የሆነ ጉርስ ለልብ መልካም ሲሆን ጥበብንና የአላህን ፍራቻ (ተቅዋ) ለማቀጣጠል ያግዛል። እንዲሁም መላውን አካል ለአላህ ፍራቻ ያዘጋጃል።

እንክርዳድን በጥሩ ማሳ ላይ ዘርቶ መልካም የሆነን የስንዴ ዘለላ ማጨድ እንደማይቻል ሁሉ ከሃራም ምንጮች የተገኘ ምግብን እየተመገቡ መንፈሳዊ ምልዓትን ማምጣት አይቻልም።

በዚህና በሌሎችም ምክንያቶች አማኝ ሰው ለመኖር የሚያስፈልጉትን ነገሮች ማሟላት ያለበት ሃላል (ሕጋዊ) ከሆኑ ምንጮች ነው፡፡ ሃላል የሆነ ምግብን የሚመገብ ሕዝብ ቀናውን መንገድ ለመያዝ የተገራ ነው፡፡ ሃላል ጉርስ መለኮታዊውን ጥበብ ለመቅሰምና በልቡም ተቅዋን ለመሰነቅ ወሳኝ ነው፡፡ ሰዎች ሃላል ነገርን ሲመገቡ ከዚህ ዓለም የመንፈስ እስራት ነጻ ይሆናሉ፡፡ በብርሃን ወደተሞላው የአላህ ህግ ፊታቸውን ያዞራሉ፡፡

ሌላውና ታላቅ አትኩሮትን የሚሻው በሃላል (የተፈቀዱ) በሆኑና ሃራም (ሕገወጥ) በሆኑ ነገሮች መካከል ግራጫ ቀለም ያለው የሃሳብ መስመር መኖሩ ነው፡፡ ይህም አጠራጣሪ (ሹብሃት) በመባል የሚታወቅ ሲሆን እውነተኛ ምእመናን ከዚህ ሁኔታ እንዲርቁ ይመከራሉ፡፡ የአላህ መልእክተኛ (ሰ.ዐ.ወ.) ይህን አስመልክተው እንዲህ ይላሉ፡-

“ያ እርሱ ሃላል የሆነው ግልጽ ነው፡፡ ያም እርሱ ሐራም የሆነው ግልጽ ነው፡፡ በሁለቱ መካከልም ብዙ ሰዎች የማያውቋቸው አሻሚ የሆኑ ነገሮች አሉ፡፡ (ስለዚህ) አሻሚ የሆኑ ነገሮችን ያስወገደ እርሱ ከሃይማኖቱና ከክብሩ አኳያ ራሱን ያጠራ ነው፡፡ አሻሚ ከሆኑ ነገሮች ላይ የወደቀ ሰው ግን እርሱ በሐራም ውስጥ ተዘፍቋል፡፡ ምሳሌውም በክልክል መስክ ዙሪያ (ከብቶችን) እንዳሰማራ እረኛ ነው፡፡ ንቁ! ማንኛውም ንጉሥ ክልል አለው፡፡ ንቁ! በአካላችን ውስጥ አንዲት ሙዳ (ቁራጭ) ሥጋ አለች፡፡ እርሷ ከቀናች (ከተስተካከለች) መላው አካል የቀና ይሆናል፡፡ እርሷ ከተበላሸች መላው አካልም ይበላሻል፡፡ ንቁ! ይህች ሙዳ (ቁራጭ) ሥጋ ልብ ናት፡፡” ሐዲሱን ኑእማን ኢብን በሽር ያስተላለፉት ሲሆን ቡኻሪና ሙስሊም ዘግበውታል፡፡

በዚህ ዓለም ላይ ስንኖር ያሉብን ወጪዎች ለራሳችንና ለቤተሰባችን መተዳደሪያ የሚበቃ ከሆነ ለሌሎች አስፈላጊ ጉዳዮች ማውጣታችንን በማቆም ብክነትን ማስወገድ ይኖርብናል፡፡ በዚህ ዓለም ላይ ያለ ሃብትና ፀጋ ውስን ነው፡፡ ያንንም የሰጠን አላህ ሲሆን በፍርዱ ቀንም የሰጠንን ፀጋ ይተሳሰበናል፡፡ አሁን እንዳሉት የካፒታሊስቱ ዓለም ማኅበረሰቦች ሃብታችንን በብልግናና በዘፈቀደ የምናባክን ከሆነ የወደፊቶቹን

ትውልዶች እጣ ፈንታ አደጋ ላይ እንጥላለን፡፡ ከሁሉም የአላህ ፍጥረታት መካከል የሰው ልጅ ብቻ ነው ባገኘው ነገር በቀላሉ የማይረካው፡፡ የዱር አራዊትን ብንመለከት ለምሳሌ የሚያድኑት ረሃባቸውን ለማስታገስ ነው፡፡ አንድ ጊዜ ከረኩ በኋላ ግን ዝም ብለው እያሳደዱ መግደላቸውን አይቀጥሉም፡፡ በተቃራኒው ግን የሰው ልጆች ፍላጎት መገቻ የለውም፡፡ ስለሆነም የሰው ልጅ ገደብ ከሌለው ፍላጐቱ ለመገታት ከፈለገ አባካኝነትን ማስወገድ አለበት፡፡ ምክንያቱም አላህ ለሰው ልጅ የወሰነለት ሪዝቅ (ሲሳይ) አይጨምርም አይቀንስምና፡፡ አላህ እንዲህ ይላል፡-

﴿ وَإِن مِّن شَيْءٍ إِلَّا عِندَنَا خَزَآئِنُهُۥ وَمَا نُنَزِّلُهُۥٓ إِلَّا بِقَدَرٍ مَّعْلُومٍ ﴿٢١﴾ ﴾ الحجر: ٢١

“መጋዘኖቹም (መክፈቻቸው) እኛ ዘንድ ያልሆነ ምንም ነገር የለም፡፡ በታወቀ ልኬታ እንጂ አናወርደውም፡፡” (አል-ሒጅር፡21)

የሰውን ልጅ ፍላጎት ገደብ የለሽነት አስመልክቶ የአላህ መልእክተኛ (ሰ.ዐ.ወ.) እንደሚከተለው ብለዋል፡-

“የአደም ልጅ አንድ ሸለቆ ሙሉ ወርቅ ቢኖረው ሌሎች ሁለት ሸለቆዎች እንዲኖሩት ይሻል፡፡ አፉን የሚሞላው አፈር ብቻ ነው፡፡ ተጸጽቶ ወደርሱ የተመለሰውን (ተውበት ያደረገውን) ሰው አላህ ፀፀቱን ይቀበላል፡፡” (ቡኻሪና ሙስሊም)

በተፈቀደና ንጹህ በሆነ (ሃላል) የገቢ ምንጭ መወሰን ለአንድ አማኝ ሰው ግዴታው መሆኑን ለማስገንዘብ ተከታዩ ሐዲስ ሊጠቀስ ይበቃል፡፡ ይህውም አቡ ሁረይራ ባስተላለፉትና ሙስሊም በዘገቡት ሐዲስ ነብዩ (ሰ.ዐ.ወ.) እንዲህ ማለታቸው ተጠቅሷል፡-

“ያ ታላቁ አላህ ጥሩ (ጦይብ) በመሆኑ ጥሩን በስተቀር አይቀደልም፡፡ ሃያሉ ጌታ እንዲህ ብሏል፡- (እናንተ መልእክተኞች ሆይ! ከተፈቀዱት ምግቦች ብሉ፤ በጎ ሥራም ሥሩ...) እንዲሁም፡- እናንተ ያመናችሁ ሆይ! ከእነዚያ ከሰጠናችሁ ጣፋጮች ብሉ .... በማለት መልእክተኞቹን በአዘዛቸው ነገሮች ምእመናንንም አዟል” አሉን፡፡

አያይዘውም አንድ በረጅም ጉዞ ላይ ያለ፣ ፀጉሩ የተንጨባረረ፣ በአቧራ የተበላሸና እጁን ወደ ሰማይ ዘርግቶ ጌታዬ ሆይ! ጌታዬ ሆይ! የሚል ሰውዬን ጉዳይ አነሱብን፡፡ ቀጥለውም ምግቡ ሐራም፣ የሚጠጣው ሐራም፣ የሚለብሰው ሐራም፣ የተገነባው በሐራም፤ እንዴት ፀሎቱ (ዱዓው) ተቀባይነት ያገኛል?” ሲሉ ተናገሩ፡፡

ምዕራፍ አሥር

ብርሃንና ጨለማ

ኃያሉ አላህ የሰውን ልጅ የማወቅና የመገንዘብ ክህሎት እንዲኖረው አድርጐ የፈጠረው እነዚህን ችሎታዎቹን ተጠቅሞ ሃቁን በማነጻፀር እንዲረዳ አስቦ ነው፡፡ እናም የአንድን ነገር ጥሩነት የምናውቀው ከመጥፎ ነገር ጋር ማለትም፣ ቆንጆን ከአስቀያሚ፣ ትክክለኛን ከስህተት፣ ብርሃንን ደግሞ ከጽልመት ጋር በማነጻጸር ነው፡፡ ስለዚህም የሰው ልጅ ግንዛቤ የተመሰረተው ነገሮችንና ጽንሰ ሐሳቦችን እየለያዩና እያወዳደሩ በማነፃፀር ነው ማለት ያስኬዳል፡፡ በዚሁ አገላለጽ መሠረት በአላህ የማመንን (የኢማንን) ውበት የምናውቀው የክህደትን አስቀያሚነት በሚገባ ስንገነዘብ ነው፡፡

ቁርአን የሰውን ልጅ ከጨለማ የክህደት ማጥ በማውጣት ወደ ብርሃናማው የእምነት ሕይወት ይመራል፡፡ አላህ ለሰው ልጆች በሁለት መንገዶች ራሱን እንደገለጸ ማስተዋል ይቻላል፡፡ አንደኛው በዚህ አጽናፈ ዓለም ውስጥ በፈጠራቸው ሥፍር ቁጥር የሌላቸው ድንቃድንቅ ፍጡራን አማካኝነት ሲሆን ሌላኛው ደግሞ በቁርአን ውስጥ በገለጻቸው የእውነትና የእምነት ተዓምራት ነው፡፡ ሁለቱ የተለያዩና አላህ የራሱን ሕልውና ያሳየባቸው መገለጫዎች ለየብቻቸው በመቆም ስለታላቅነቱ በበቂ ሁኔታ ማወጅ ቢችሉም አንዱ ሌላውን ማሟላት (መግለጽ) መቻሉ ግን እውነት ነው፡፡ ይህ አጽናፈ ዓለም የአላህን ታላቅነት በሚያውጁና በሚገልጹ ሥፍር ቁጥር የሌላቸው መለኮታዊ ምስጢራት የተሞላ ነው፡፡ የሰው ልጅ ራሱ የሁለቱ መገለጫዎችን ባሕሪያት በውስጡ አዋህዶ ይዟል፡፡

የሰው ልጅ በተፈጥሮው ወደ መልካምም ሆነ ወደ መጥፎ ነገር የማዘንበል ባህሪ ይታይበታል፡፡ ይህም የሆነው በውስጡ በሰረፀው የብርሃንና ጨለማ ጥንተ ተፈጥሮ ምክንያት ነው፡፡ በሰው ልጅ ጫንቃ ላይ የተጣለው ታላቅ ኃላፊነት ያ በነፍሱ ውስጥ አድብቶ የተቀመጠ ጽልመት ብርሃኑን እንዳያዳፍንበት መጠንቀቅ ሆኖ እናገኘዋለን፡፡ ይህ

በጽልመት የተመሰለ የሰው ልጆች የድንቁርና ሕይወት እንዳይንሰራፋ በነፍስ ወከፍ ብቻ ሳይሆን በማኅበረሰብና ዓለምአቀፋዊ ሁኔታ ጭምር መታገል እንዳለብን ያስተምረናል። እንዲህ ይላል፡-

﴿ أَفَلَمۡ يَسِيرُواْ فِي ٱلۡأَرۡضِ فَتَكُونَ لَهُمۡ قُلُوبٞ يَعۡقِلُونَ بِهَآ أَوۡ ءَاذَانٞ يَسۡمَعُونَ بِهَاۖ فَإِنَّهَا لَا تَعۡمَى ٱلۡأَبۡصَٰرُ وَلَٰكِن تَعۡمَى ٱلۡقُلُوبُ ٱلَّتِي فِي ٱلصُّدُورِ ٤٦ ﴾ الحج: ٤٦

"ለእነርሱም በእነርሱ የሚያውቁባቸው ልቦች ወይም በእነርሱ የሚሰሙባቸው ጆሮዎች ይኖሯቸው ዘንድ በምድር ላይ አይሄዱምን? እነሆ ዓይኖች አይታወሩም፣ ግን እነዚያ በደረቶች ውስጥ ያሉት ልቦች ይታወራሉ።" (አል-ሐጅ፡46)

በእምነት ብርሃን እየተመሩ ቁርአንን መመርመር ለሚታክታቸው ግዴለሽ ልቦች ቁርአን የሚከተለውን መልእክት ያስተላልፋል፡-

﴿ أَفَلَا يَتَدَبَّرُونَ ٱلۡقُرۡءَانَ أَمۡ عَلَىٰ قُلُوبٍ أَقۡفَالُهَآ ٢٤ ﴾ محمد: ٢٤

"ቁርአንንም አያስተነትኑምን? በእውነቱ ልቦቻቸው ተቆልፈዋልን?" (መሐመድ፡24)

ሰዎች ልባቸውን አቅንተውና መንፈሳቸውንም አነሳስተው የቁርአንን ገጾች እያገላበጡ ቢያነቡ፣ እንዲሁም በአጽናፈ ዓለሙ ውስጥ ያሉትን የአላህ ተዓምራት ቢመረምሩ ታላቅ የሆነን ሃቅ ይገነዘባሉ። ኃያሉ አላህ እንዲህ ይላል፡-

﴿ سَنُرِيهِمۡ ءَايَٰتِنَا فِي ٱلۡأٓفَاقِ وَفِيٓ أَنفُسِهِمۡ حَتَّىٰ يَتَبَيَّنَ لَهُمۡ أَنَّهُ ٱلۡحَقُّۗ أَوَلَمۡ يَكۡفِ بِرَبِّكَ أَنَّهُۥ عَلَىٰ كُلِّ شَيۡءٖ شَهِيدٌ ٥٣ أَلَآ إِنَّهُمۡ فِي مِرۡيَةٖ مِّن لِّقَآءِ رَبِّهِمۡۗ أَلَآ إِنَّهُۥ بِكُلِّ شَيۡءٖ مُّحِيطُۢ ٥٤ ﴾ فصلت: ٥٣ - ٥٤

"እርሱም (ቁርአን) እውነት መሆኑ ለእነርሱ እስከሚገለጽላቸው ድረስ በአጽናፎቹ ውስጥና በነፍሳቸው ውስጥ ያሉት ተዓምራቶቻችን በእርግጥ እናሳያቸዋለን። ጌታህም እርሱ በነገሩ ሁሉ ላይ አዋቂ መሆኑ

አይበቃቸውምን? ንቁ! እነርሱም ከጌታቸው መገናኘት በመጠራጠር ውስጥ ናቸው፡፡ ንቁ! እርሱ በነገሩ ሁሉ ከባቢ ነው፡፡" (ፉሲለት 53-54)

የሰው ልጅ ለእምነት ጆሮ ዳባ ልበስ ማለቱንና ፈጣሪውን ለመታዘዝ አለመፈለጉን አላህ ሲተች እንዲህ ይላል፡-

﴿ يَٰٓأَيُّهَا ٱلۡإِنسَٰنُ مَا غَرَّكَ بِرَبِّكَ ٱلۡكَرِيمِ ٦ ٱلَّذِي خَلَقَكَ فَسَوَّىٰكَ فَعَدَلَكَ ٧ فِيٓ أَيِّ صُورَةٖ مَّا شَآءَ رَكَّبَكَ ٨ ﴾ الانفطار: ٦ - ٨

"አንተ ሰው ሆይ! በቸሩ ጌታህ ምን አታለለህ? በዚያ በፈጠረህ፣ አካለ ሙሉም ባደረገህ፣ ባስተካከለህም፤ በማንኛውም ባሻው ቅርጽ በገጣጠመህ (ጌታህ ምን አታለለህ)" (አል-ኢንፊጣር፡ 6-8)

አላህ የሚሻው እኛ የሰው ልጆች ሁላችን፣ በሁሉም የሕይወታችን ዘርፍ መለኮታዊውን ሕግ እየተገበርን ከዚያ በምናገኘው ብርሃን እንድንመራ ነው፡፡ የሰው ልጅ መጥፎ ምግባራትና ራሱ የፈጠራቸው ድንቁርና፣ ስንፍና፣ አምባገነንነትና ክህደና ሌሎች ወንጀሎች ስብዕናውን በማጉደፍ የግልና የማህበራዊ ሕይወቱን አመሰቃቅለውበታል፡፡ በሌላ በኩል ቁርአን የሚያበረታታው ከዚህ ተቃራኒ የሆኑ ባህሪያትን ሲሆን እነርሱም እውቀትን መሻት፣ ጠንክሮ መስራት፣ ፍትህን ማስፋፋት፣ በመጪው ዓለም ማመን ወዘተ..ናቸው፡፡

አላህ የሰውን ልጅ ከፈጠረው በኋላ ያለ መመሪያ ብርሃን አልተወውም፡፡ ለሰው ልጅ ከተሰጡት ታላላቅ ስጦታዎች መካከል አንዱ ቁርአንና የነብዩም (ሰ.ዐ.ወ.) ሱና ነው፡፡ ታሪክ የሚያሳየን የጃሂልያ (የዘመነ ድንቁርና) የጨለማ የአናኗር ሥርአት ድል የተነሳውና ድባቅ የተመታው በቁርአንና በነብዩም (ሰ.ዐ.ወ.) የሱና ብርሃን ነው፡፡ አላህ እንዲህ ይላል፡-

﴿ فَـَٔامِنُواْ بِٱللَّهِ وَرَسُولِهِۦ وَٱلنُّورِ ٱلَّذِيٓ أَنزَلۡنَاۚ وَٱللَّهُ بِمَا تَعۡمَلُونَ خَبِيرٞ ٨ ﴾ التغابن: ٨

"በአላህና በመልእክተኛውም በዚያ ባወረድነው ብርሃን እመኑ፡፡ አላህም በምትሰሩት ሁሉ ውስጥ አዋቂ ነው፡፡" (አት-ተጋቡን፡8)

እነዚያ ሕይወታቸውን በቁርአን ብርሃን ለመምራት ያልወሰኑ ሰዎች በጨለማ ውስጥ መዳከርን መርጠዋል ማለት ነው፡፡ ስለሆነም እኛ ነፍሳችንንና ቤተሰቦቻችንን ከጨለማ ሕይወት ልንጠብቅ ግዴታ አለብን፡፡ አላህ እንዲህ ይላል፡-

﴿ يَٰٓأَيُّهَا ٱلَّذِينَ ءَامَنُواْ قُوٓاْ أَنفُسَكُمۡ وَأَهۡلِيكُمۡ نَارٗا وَقُودُهَا ٱلنَّاسُ وَٱلۡحِجَارَةُ عَلَيۡهَا مَلَٰٓئِكَةٌ غِلَاظٞ شِدَادٞ لَّا يَعۡصُونَ ٱللَّهَ مَآ أَمَرَهُمۡ وَيَفۡعَلُونَ مَا يُؤۡمَرُونَ ٦ ﴾ التحريم: ٦

"እናንተ ያመናችሁ ሆይ! ነፍሶቻችሁንና ቤተሰቦቻችሁን መቀጣጠያዋ ሰዎችና ድንጋዮች ከሆነች እሳት ጠብቁ፡፡ በእርሷ ላይ ጨካኛች ኃይለኞች የሆኑ መላእክት አሉ፡፡ አላህን ያዘዛቸውን ነገር (በመጣስ) አያምጹም፡፡ የሚታዘዙትንም ሁሉ ይሰራሉ፡፡"(አት-ተሕሪም፡6)

በቁርአንና በነብዩ (ሰ.ዐ.ወ.) ሱና ብርሃን እየተመራን ሕይወታችንን ለመምራት የመጀመሪያው እርምጃ ልጆቻችንን ማስተማር ነው፡፡ ከዚህም በተጨማሪ የኢስላምን ማእዘናትና የእምነትን (ኢማን) መሠረቶች እንዲይዙ መጣር ይኖርብናል፡፡ ይህ የትምህርት አሰጣጥ ስልት ምናልባትም በቤተሰብ አባላት ብቻ መሰጠቱ ስኬታማ ላያደርገው ይችላል፡፡ ስለሆነም የእውቀት ባለቤቶችን እገዛ ማግኘት ያስፈልጋል፡፡

ኢስላምን ለአዲሱ ትውልድ ከሥረ መሠረቱ ጀምሮ ማስተማር የሰውን ልጅ ስብዕና ከማነጽ አንጻር ታላቅ ሚና ይኖረዋል፡፡ ይህን ሁኔታ ምርጥ የሆነን የሰብል ዘር ለም በሆነ መሬት ላይ ከመጣል ጋር ልናመሳስለው እንችላለን፡፡ ዘሩ በቅሎ ፍሬ ሲያፈራ የሚያምርና በቁርአናዊ የሕይወት ዘይቤ የሚመራ ትውልድ እናገኛለን ማለት ነው፡፡ ይህን ጉዳይ አስመልክተው የአላህ መልእክተኛ (ሰ.ዐ.ወ.) እንደተናገሩት ልጆቻችን ሶላት እንዲሰግዱ ማበረታታት ያለብን ገና የሰባት ዓመት ልጅ እያሉ ጀምሮ መሆን አለበት፡፡ ይህ አባባል የሚያሳየን መንፈሳዊ ኩትኮታ ለልጆች መቅረብ ያለበት ገና በለጋ እድሜ ላይ እያሉ መሆኑን ነው፡፡ ልባዊ የሆነው ምክርና መንፈሳዊ ኩትኮታ (ተርቢያ) በልጆቻችን

ጭንቅላት ላይ በትክክል ካረፈ በድንጋይ ላይ ፊደላትን የመቅረጽ ያህል እድሜ ልክ የሚጠፋ አይደለም፡፡

አቡ በከር ወራቅ የተባለ አላህን የሚፈራ ሰው ልጁን ቁርዓንና መንፈሳዊ ትምህርቶች ወደሚሰጥበት ት/ቤት ላከው፡፡ ልጁ ከእለታት በአንዱ ቀን ፊቱ ተቀያይሮና በጣም አዝኖ ከት/ቤት ተመለሰ፡፡ በዚህ ጊዜ አቡ በከር ልጁን ምን እንዳጋጠመው ጠየቀው፡፡ ልጁም እንዲህ በማለት መለሰ "አባቴ ሆይ! ዛሬ በትምህርት ቤታችን የሚከተለውን የቁርአን አንቀጽ ተማርን፡-

﴿ فَكَيۡفَ تَتَّقُونَ إِن كَفَرۡتُمۡ يَوۡمٗا يَجۡعَلُ ٱلۡوِلۡدَٰنَ شِيبًا ١٧ ﴾ المزمل: ١٧

"ብትክዱ ልጆችን ሸበቶዎች የሚያደርገውን ቀን (ቅጣት) እንዴት ትጠበቃላችሁ" (ሙዘሚል፡17)

ይህን አባባል ሳሰላስለው በውስጤ ታላቅ ድንጋጤን ስለፈጠረብኝ ፍርሃት አንቀጠቀጠኝ፡፡" ልጁ ይህን ከተናገረ በኋላ ጥቂት ጊዜ ቆይቶ ሞተ፡፡ አቡበከር የልጁን መቃብር በየጊዜው እየሄደ ይጐበኛል፡፡ ከዚያም እንዲህ እያለ ለራሱ ያለቅሳል፡-"የአላህን ቃል ለረዥም ጊዜ ሳነበው ቆይቻለሁ፡፡ ሆኖም ግን ይህ አንቀጽ የያዘውን ማስጠንቀቂያ ልብ ብየው አላውቅም፡፡ ምን ዓይነት የማልረባ ሰው ነበርኩ!፡፡ ልጄ ግን የዚህን አንቀጽ ትርጉም በሚገባ ተረድቶት ነበር፡፡"

በእርግጥ ቁርአን ለሚያነበው ሰው እንደታላቅ ውቂያኖስ ውስጡን መርምሮ መጨረስ የማይቻል የአላህ አደራ ነው፡፡ ስለሆነም ቁርአንን ማንበብ ከኢባዳ ዓይነቶች ሁሉ ምርጡ ነውና ሁላችንም በሶላታችንም ላይ ይሁን በሌላ ጊዜ በተመስጦ ማንበብ ይኖርብናል፡፡

ቁርአንን ስናነብ እንደ ቀላል መቁጠር የለብንም፡፡ ትኩረት ሰጥቶ ማንበብ ያስፈልጋል፡-

﴿ أَوۡ زِدۡ عَلَيۡهِ وَرَتِّلِ ٱلۡقُرۡءَانَ تَرۡتِيلًا ٤ ﴾ المزمل: ٤

“ወይም በርሱ ላይ ጨምር፡፡ ቁርአንንም በዝግታ ማንበብን አንብብ” (አል-ሙዘሚል፡4)

ቁርአን በሚቀራበት ጊዜ በጽሞና እንድናዳምጥ አላህ እንዲህ በማለት ያዘናል፡-

﴿ وَإِذَا قُرِئَ ٱلْقُرْءَانُ فَٱسْتَمِعُوا۟ لَهُۥ وَأَنصِتُوا۟ لَعَلَّكُمْ تُرْحَمُونَ ﴿٢٠٤﴾ ﴾ الأعراف: ٢٠٤

“ቁርአንም በተነበበ ጊዜ እርሱን አዳምጡ፡ ፀጥም በሉ፤ ይታዘንላችኋልና፡፡” (አል-አዕራፍ፡204)

ቁርአን ሲነበብ ፀጥ ብሎ ማዳመጥ በውስጡ የያዘውን መልእክት ለመገንዘብ ያግዛል፡፡ መገንዘቡ ደግሞ የእውቀት ባለቤት ያደርጋል፡፡ እውቀት ያለውን ሰው ደግሞ አላህ ያዝንለታል፡፡ የአላህ መልእክተኛም (ሰ.ዐ.ወ.) በዚህ ረገድ ታላቅ የሆነ ተምሳሌትን ትተውልናል፡፡ አብደላህ ኢብን መስዑድ (ረ.ዐ.) ቁርአን እንዲቀራላቸው ይጠይቁትና ከዚያም በታላቅ አክብሮትና መንፈሳዊ ጉጉት ሲያዳምጡ ከቆዩ በኋላ አይኖቻቸው በእንባ ይሞላሉ፡፡

በተመሳሳይ ሁኔታ ልጆቻቸው ቁርዓንን በሚያምር ድምጽና የአነባበብ ስልት ሲያነቡላቸው የሚያዳምጡ ወላጆች የታላቅ እደብ ባለቤቶች ናቸው፡፡ ወላጆችን መውደድና ማክበር ጠንካራ የሆነ ተፈጥሮአዊ ዝንባሌ መሆኑ ይታወቃል፡፡ ይሁን እንጂ ከዚህ የበለጠ ጠንካራ የሆነው ፍቅር ወላጆቹ ለልጆቻቸው ያላቸው ፍቅር ነው፡፡ ይህ ወላጃዊ ዝምድና ሁሉንም የፍቅር ዓይነቶች የመቆጣጠርና የበላይ የመሆን ኃይል አለው፡፡ እንደዚያም ቢሆን ቁርዓን የሚያስጠነቅቀን ለልጆቻችን ልናደርግላቸው የሚገባንን ወላጃዊ ግዴታ ችላ እንዳንል ነው፡፡ ወላጆች ልጆቻቸውን ኢስላማዊ ትምህርቶችን በማስተማር የሚኮተኩቷቸው ከሆነ ከአላህ የሆነ በረከት ያገኛሉ፡፡ ያን ሳያደርጉ ቀርተው እንዲሁ እንዲያድጉ ከለቀቋቸው ግን ለእነርሱም ሆነ ለማኅበረሰቡ የመከራ ምንጭ ይሆናሉ፡፡

ወላጆች ልጆቻቸውን በቁርአን አስተምህሮት በሚገባ ካነጿቸው የሚገጥማቸውን ሽልማት ነብዩ (ሰ.ዐ.ወ.) ሲናገሩ እንዲህ ብለዋል፡-

"ቁርአንን በሚገባ የሚያነቡ ልጆች ያሏቸው ወላጆች በፍርዱ ቀን የኑር (ብርሃን) አክሊል ይደፋሉ፡፡ የኑር ካባም ይደርባሉ፡፡›› (አቡ ዳውድ፣ አህመድ አል-ሃኪም)

ብዙ ወላጆች እንዲህ ዓይነት ልጆች እንዲኖራቸው ይመኛሉ፡፡ ይህም የተለመደና በእያንዳንዱ ወላጅ ተፈጥሮ ውስጥ ያለ ነገር ነው፡፡ ሆኖም ግን ወላጆች ይህን ነገር ለማድረግ ሲነሱ ሊያስከፍል የሚችለውን መስዋእትነትም ጠንቅቀው መገንዘብ ይኖረባቸዋል፡፡ ይህን ማድረጋቸው የአላህን ፈቃድ መፈጸማቸው እንደሆነና ለዚህም ታላቅ ጥረታቸው ተገቢውን ምንዳ ከዓለማት ጌታ አላህ ያገኛሉ፡፡ አንድ ሰው በያዘው ነገር ላይ ከልቡ ከጣረ ቤተሰቡን ለመቀለብ የሚያደርገው ልፋት እንኳ ምንዳ የሚያስገኝለት መሆኑ ታላቅ የምሥራች ነው፡፡ በተጨማሪም የተወሰኑ ኃጢአቶቹ ይራገፉለታል፡፡ ሕፃናት በጀሃነምና በወላጆቻቸው መካከል የሚጋርዱ የሆኑ ጋሻዎች ናቸው፡፡ ልጆቻችን አላህ ለእኛ የሰጠን በጣም ውድ የሆኑ ሃብቶቻችን ናቸው፡፡ ስለሆነም ከሁሉም ዓይነት፣ በተለይም ደግሞ ከመንፈሳዊ አደጋ ልንጠብቃቸው ግዴታ አለብን፡፡

ይሁን እንጂ ልጆቻችንን ከተለያዩ አደጋዎች ልንጠብቃቸው የምንችለው እንዴት ነው? ለምሳሌ ምርጥ የተባለ ምግብን በመመገብና ያን ስናደግር በሚያሳዩን ጥሩ የምግብ ፍላጐት (አፒታይት) ነው? ከሁሉም በላይ መልካም የሆነ ምግብ መንፈሳዊ የሆነው አላህን የመፍራት ምግብ ነው፡፡ ይህ መንፈሳዊ ምግብ አላህንና መልእክተኛውን (ሰ.ዐ.ወ.) ከሁሉም በላይ መውደድን በልባቸው ውስጥ እንዲያሰርጹ ያደርጋቸዋል፡፡ እንደዚያ ካደረጉ ደግሞ ኃይማኖታዊ ግዴታዎቻቸውን በታማኝነትና በደስታ ይፈጽማሉ፡፡ ካልሆነም ግን ሶላታቸውን በዘፈቀደና እርካታ ሳይሰማቸው ይሰግዳሉ፡፡

ብዙ ሙስሊሞች ለልጆቻቸው ኢስላማዊና በቁርዓን ላይ የተመሠረቱ መንፈሳዊ ስልጠናዎችን የማይሰጡ መሆኑ ያሳዝናል፡፡ እነዚህ ሰዎች

ይህን ሲያደርጉ ልጆቻቸውን በቀጥታ ከመለኮታዊው ብርሃን እየለያዩዋቸው እንደሆነ አይገነዘቡም፡፡ ይህም በወደፊቱ ትውልድና በልጆቻችን ላይ ያጠላ መንፈሳዊ ጽልመት መሆኑ ግልጽ ነው፡፡

ለልጆቻችን የትዳር አጋር በመምረጡ ዙሪያ ላይም ከፍተኛ ጥንቃቄ ልናደርግ ይገባናል፡፡ የመጀመሪያውና ትኩረት ልንሰጠው የሚገባን ሙሽራ ሆኖ ወይም ሆና የምትመጣው የልጃችን ተጓዳኝ ለአላህ ያላት ቀረቤታና በቁርዓን አስተምህሮት የታነፀች መሆኗ ነው፡፡ ለዚህ ዋነኛ ጉዳይ ትኩረት የማይቸሩ ተጋቢዎች ትዳራቸው መሠረቱ አላህን በመፍራት ላይ የታነፀ አይደለምና ፈጥነውም ሆነ ዘግይተው ለፍቺ መዳረጋቸው አይቀሬ ነው፡፡ በአጭር አነጋገር ልጆቻችንን በዘመናችን ያለንበትን ማኅበረሰብ ካጥለቀለቀው ብክለት (ፈሳድ) የመጠበቅ አደራ አለብን፡፡ ከእነዚህ መጥፎና እኩይ የሚባሉ ምግባራት መካከል ወደ ቤት አምሽቶ መግባት፣ ጊዜንና ገንዘብን ያለአግባብ ማባከን፣ ፀያፍና ምግባረ ብልሹ ፊልሞችን ማየት፣ ዝሙት፣ ስርቆት፣ አደንዛዥ እጽ፣ ግብረሰዶማዊነት፣ ቁማር፣ አስካሪ መጠጥ ወዘተ.. ይገኙበታል፡፡

ሁኔታው ይህን የሚመስል ከሆነ በልጆቻችን እጣ ፈንታ ላይ የተደቀነው አደጋ እጅግ ከባድ መሆኑን ያሳያል፡፡ አላህም በቁርዓን የሚያዘን ቤተሰቦቻችንን ወደ ጀሃነም እሳት ከሚወረውረው ከእንዲህ ዓይነቱ አደጋ እንድንጠብቅ ነው፡-

﴿ يَٰٓأَيُّهَا ٱلَّذِينَ ءَامَنُواْ قُوٓاْ أَنفُسَكُمۡ وَأَهۡلِيكُمۡ نَارٗا وَقُودُهَا ٱلنَّاسُ وَٱلۡحِجَارَةُ عَلَيۡهَا مَلَٰٓئِكَةٌ غِلَاظٞ شِدَادٞ لَّا يَعۡصُونَ ٱللَّهَ مَآ أَمَرَهُمۡ وَيَفۡعَلُونَ مَا يُؤۡمَرُونَ ٦ ﴾ التحريم: ٦

“እናንተ ይመናችሁ ሆይ! ነፍሶቻችሁንና ቤተሰቦቻችሁን መቀጣጠያዋ ሰዎችና ድንጋዮች ከሆነች እሳት ጠብቁ፡፡ በእርሷ ላይ ጨካኞች፣ ኃይለኞች የሆኑ መላእክት አሉ፡፡ አላህን ያዘዛቸውን ነገር (በመጣስ) አያምጹም፤ የሚታዘዙትንም ሁሉ ይሰራሉ፡፡” (አት-ተሕሪም፡ 6)

ከዚህም በተጨማሪ የሕዝቦች ችግሮች ሁሉ መፍትሄ የሚያገኙት ኢስላም በሚያስተምረው የሞራል ሥርአት መሆኑ መታወቅ አለበት፡፡ አላህ እንዲህ ይላል፡-

﴿ يَٰٓأَيُّهَا ٱلنَّاسُ قَدۡ جَآءَتۡكُم مَّوۡعِظَةٞ مِّن رَّبِّكُمۡ وَشِفَآءٞ لِّمَا فِي ٱلصُّدُورِ وَهُدٗى وَرَحۡمَةٞ لِّلۡمُؤۡمِنِينَ ٥٧ ﴾ يونس: ٥٧

"እናንተ ሰዎች ሆይ! ከጌታችሁ ግሳጼ በደረቶች ውስጥም ላለው (የመጠራጠር በሽታ) መድሃኒት ለምእመናንም ብርሃንና እዝነት በእርግጥ መጣላችሁ፡፡" (ዩኑስ ፡57)

ሥርአት አልበኝነትን፣ ወንጀልንና ሌሎችንም ፀያፍ የሆኑ ድርጊቶች ለማስወገድ ብቸኛው መፍትሄ የኢስላምን ሕግጋት (ሸሪአን) ማስፈን ነው፡፡ እነዚህ ሁሉ ወንጀሎች የሚፈፀሙት ራሳቸውን በማይገቱና የነፍሳቸውን ዝንባሌ በማይቆጣጠሩ ሰዎች ነው፡፡ ራስ ወዳድነትና ለቁሳዊ ሃብት መስገብገብም የሚገቱት በኢስላም ነው፡፡ ምክንያቱም የኢስላም መርሆዎች የሚያጠነጥኑት ከግል ጉዳዮች ይልቅ የማኅበረሰቡን ችግሮችና ፍላጐቶች በመጋራት ዙሪያ ነውና፡፡ እንደሚታወቀው ቁሳዊነት የሚንሰራፋው ለሐይማኖታዊ እሴቶች ዋጋ በማይሰጥ ማኅበረሰብ ውስጥ ነው፡፡ ምክንያቱም ቁሳዊነት ሕብረተተሰብን አስማምቶና አደላድሎ የመምራት ብቃት የለውም፡፡ በዛሬው ጊዜ ብዙ ከሃዲያን የሆኑ ሰዎች የአስተሳሰባቸውን አድማስ እንዴት እንደሚጠቀሙበትና የስሜት ሕዋሳቶቻቸውንም እንዴት መገልገል እንዳለባቸው አያውቁም፡፡ ለኃይማኖታዊ እሳቤዎች ግድ የሌላቸው በመሆኑ በሕልውና የመገኘታቸውን ሁኔታም ሊያስተባብሉ ይቃጣቸዋል፡፡ ይህን የመሰሉ ሰዎችን ቁርዓን እንዲህ በማለት በጽኑ ይተቻቸዋል፡፡ እንዲህ ይላል፡-

﴿ أَوَلَمۡ يَرَ ٱلۡإِنسَٰنُ أَنَّا خَلَقۡنَٰهُ مِن نُّطۡفَةٖ فَإِذَا هُوَ خَصِيمٞ مُّبِينٞ ٧٧ ﴾ يس: ٧٧

“ሰውየው እኛ ከፍትወት ጠብታ የፈጠርነው መሆናችንን አላወቀምን? ወዲያውም እርሱ (ትንሣኤን በመካድ) ግልጽ ተከራካሪ ይሆናልን? “ (ያሲን፡77)

﴿ يَٰٓأَيُّهَا ٱلۡإِنسَٰنُ مَا غَرَّكَ بِرَبِّكَ ٱلۡكَرِيمِ ٦ ٱلَّذِي خَلَقَكَ فَسَوَّىٰكَ فَعَدَلَكَ ٧ فِيٓ أَيِّ صُورَةٖ مَّا شَآءَ رَكَّبَكَ ٨ ﴾ الانفطار: ٦ - ٨

“አንተ ሰው ሆይ! በቸሩ ጌታህ ምን አታለለህ? በዚያ በፈጠረህ በማንኛውም በሻው ቅርጽ በገጣጠመህ (ጌታህ ምን አታለለህ)?” (አል-እንፊጣር፡6፡8)

ኢስላም ይዟቸው የመጣውን እውነታዎች ከሃዲያን አይቀበሉም፡፡ ምነው ቢባል ልባቸው ሞቷልና፡፡ እናም አንድ አማኝ የሆነ ሰው ወደ ኢስላም ሲጠራቸው እንዲህ ይሉታል፡- “እኛ የምንኖረው ሳይንስና ቴክኖሎጂ በዘመነበት፣ እንዲሁም ምክንያታዊነት በሰፈነበት ዘመን ነው፡፡ አንተ እየጠራኸን ያለኸው የጥንተ ዘመን ሰዎች የቀመሩት ወደ ኾነ ተረት ነው፡፡ ይህም ሌላ ሳይሆን የጥንቆላ ውጤት (ድግምት) ነው፡፡››

ቁርአን ይህንና ይህን የመሰለ መደዴ አነጋገር ለሚጠቀሙ እምነት አልባዎች የሚሆን መልስ አዘጋጅቷል፡-

﴿ يَعۡلَمُونَ ظَٰهِرٗا مِّنَ ٱلۡحَيَوٰةِ ٱلدُّنۡيَا وَهُمۡ عَنِ ٱلۡأٓخِرَةِ هُمۡ غَٰفِلُونَ ٧ أَوَلَمۡ يَتَفَكَّرُواْ فِيٓ أَنفُسِهِمۚ مَّا خَلَقَ ٱللَّهُ ٱلسَّمَٰوَٰتِ وَٱلۡأَرۡضَ وَمَا بَيۡنَهُمَآ إِلَّا بِٱلۡحَقِّ وَأَجَلٖ مُّسَمّٗىۗ وَإِنَّ كَثِيرٗا مِّنَ ٱلنَّاسِ بِلِقَآئِ رَبِّهِمۡ لَكَٰفِرُونَ ٨ ﴾ الروم: ٧ - ٨

“ከቅርቢቱ ሕይወት ግልጹን ብቻ ያውቃሉ፡፡ እነርሱም ከኋለኛይቱ ዓለም እነርሱ ዘንጊዎች ናቸው፡፡ በነፍሶቻቸው (ሁኔታ) አያስተውሉምን? ሰማያትንና ምድርን በመካከላቸው ያለውንም ሁሉ አላህ በእውነትና በተወሰነ ጊዜ እንጂ አልፈጠራቸውም፡፡ ከሰዎቹም ብዙዎቹ በጌታቸው መገናኘት ከሐዲዎች ናቸው፡፡” (አል-ሩም፡7-8)

እኛ ለልጆቻችን ልናወርሳቸው ከምንችላቸው እሴቶች በጣም ጠቃሚ የሆነው ለቀጣዩ ዓለም ሕይወታቸው መድህን የሚያስገኝላቸውና ሰይጣንን የሚያሸንፉበት የሆነን ትምህርት ነው፡፡ ይህን ተግባራዊ ለማድረግም ወደ ኢስላማዊ ትምህርት ቤቶች ልንልካቸው ይገባል፡፡ እንዳለመታደል ሆኖ በአሁኑ ጊዜ በዓለም ዙሪያ የሚገኙ ብዙ ኢስላማዊ ት/ቤቶች በቂ ትኩረት ባለማግኘታቸው ምክንያት ከሚዘገብት አፋፍ ላይ ይገኛሉ፡፡ ብዙ ወላጆች ለልጆቻቸው ት/ቤቶችን ሲመርጡ አነስተኛ ገንዘብ ወደሚያስከፍለው ተቋም መላክን ይሻሉ፡፡ ሆኖም ግን ያ ት/ቤት ኢስላማዊ እሴቶችን ለልጆቻቸው ማስተማር አለማስተማሩ ጉዳያቸው አይደለም፡፡ ጥቂት የሚባሉ ወላጆች ብቻ ልጆቻቸውን ወደ ኢስላማዊ ተቋማት ይልካሉ፡፡

ልጆቻችንን በኢስላማዊ ት/ቤቶች ውስጥ አስገብተን ማስተማር እስካልቻልንና በኢስላም መርሆዎች እስካላነጽናቸው ድረስ ከዘመኑ ማኅበራማዊ ደዌ ይተርፋሉ ብሎ ማሰብ አጉል ምኞት ነው፡፡ ቁርአን መጪውን ትውልድ በትክክል የመቅረጽ አቅም አለው፡፡ ያለፉትን ትውልዶች የመቅረጽ አቅም እንደነበረው ሁሉ፡፡ የዚህ ሁሉ ውጥንቅጡ የወጣ ዓለም ችግሮች ብቸኛ የመፍትሄ ምንጭ ቁርአን ነው፡፡

﴿ وَنُنَزِّلُ مِنَ ٱلۡقُرۡءَانِ مَا هُوَ شِفَآءٞ وَرَحۡمَةٞ لِّلۡمُؤۡمِنِينَۙ وَلَا يَزِيدُ ٱلظَّٰلِمِينَ إِلَّا خَسَارٗا ٨٢ ﴾ الإسراء: ٨٢

“ከቁርአንም ለምእመናን መድሃኒትና እዝነት የሆነን እናወርዳለን፡፡ በዳዮችንም ኪሳራን እንጂ ሌላ አይጨምርላቸውም፡፡” (አል-ኢስራእ፡82)

በሌላ የቁርአን አንቀጽ እንዲህ በማለት ይገልጻል፡-

﴿ فَـَٔامِنُواْ بِٱللَّهِ وَرَسُولِهِۦ وَٱلنُّورِ ٱلَّذِيٓ أَنزَلۡنَاۚ وَٱللَّهُ بِمَا تَعۡمَلُونَ خَبِيرٞ ٨ ﴾ التغابن: ٨

“በአላህና በመልእክተኛው፣ በዚያም ባወረድነው ብርሃን እመኑ፡፡ አላህም በምትሰሩት ሁሉ ውስጠ ዓዋቂ ነው (በላቸው)፡፡”(አት-ተጋቡን፡8)

ስለሆነም እኛ ሁልጊዜም ቢሆን ትኩረት ማድረግ ያለብን ለዓለማዊ ጉዳዮቻችን ብቻ ሳይሆን ለልጆቻችን እጣ ፈንታ ጭምር ሊሆን ይገባል፡፡ ታሪክ በእማኝነት እንደሚነግረን የአላህ መልእክተኞች በየጊዜው ያመጧቸውን መልእክቶች ተቀብለው ቀናውን መንገድ የተከተሉ ሕዝቦች የቅርቢቱን ዓለም (ዱኒያንም) ሆነ የመጪውን ዓለም የስኬት ልጓም ጨብጠዋል፡፡ አላህም ከእነርሱ ወዶ ሥራቸውን ተቀብሏቸዋል፡፡

የአላህ መልእክተኛ (ሰ.ዐ.ወ.) እንደተናገሩትም ከእርሳቸው ኡማ (ሕዝብ) ውስጥ የተወሰኑትን ቁርአን በደረጃዎች ከፍ የሚያደርግ ሲሆን የተወሰኑትን ደግሞ ቁርአንን ባለመቀበላቸው (በመጣላቸው) ያጠፋቸዋል፡ ፡ (ሙስሊም፣ ኢብን ማጃህ)

﴿ وَقَالَ ٱلرَّسُولُ يَٰرَبِّ إِنَّ قَوۡمِي ٱتَّخَذُواْ هَٰذَا ٱلۡقُرۡءَانَ مَهۡجُورٗا ٣٠ ﴾ الفرقان: ٣٠

“መልእክተኛውም፡- ጌታዬ ሆይ! ሕዝቦች ይህንን ቁርአን የተተወ ነገር አድርገው ያዙት አለ፡፡” (አል-ፉርቃን፡30)

የአዛኙ አምላክ ችሮታ የሆነችው ይህች ዓለም በሚያምሩና ጣፋጭ በሆኑ የምግብ ዓይነቶች እንደተሞላ ጠረጴዛ ማለት ናት፡፡ እኛ ወደዚህ ዓለም የተላክነው (የተፈጠርነው) እንዚህን ጣፋጭ የሆኑ ምግቦችና መጠጦች እያጣጣምን ለመኖርና ለመራባት አይደለም፡፡ እኛ የተፈጠርንበትን ዋነኛ ግብ (አላህን መገዛትን) ዘንግተን ስንባዝን ከኖርን በመጪው ዓለም ያለጥርጥር ታላቅ አደጋ እንደሚጠብቀን ማወቅ አለብን፡፡

የአላህ እዝነቶች ከሚገለጹባቸው ሁኔታዎች አንዱ በዚያ በጣፋጭ ምግቦች በተሞላ ጠረጴዛ ዙሪያ ተሰይመው እንዲቋደሱ የተፈቀደላቸው አማኞች ብቻ አለመሆናቸው ነው፡፡ ከሃዲያንና መናፍቃንም እንብርታቸው እስኪያብጥ ድረስ ቢመገቡ አላህ ደንታው አይደለም፡፡ ይሁን እንጂ ሁሉም ሰው ከዚህ ፀጋ የሚጠየቅበት ጊዜ ሩቅ አይደለም፡፡

በፍርዱ ቀን የሰው ልጅ “መሸሻው የት ነው” (አል-ቂያማህ፡10) ከማለቱ በፊት ለዚያ ቀን እንዲዘጋጅ ይፈለጋል፡፡ ከሃዲያን “ሰቀር” በተባለው

የጀሃነም አዘቅት ውስጥ ሆነው ዋይታና ጥርስ ማፋጨትን ሲያሰሙ ምእመናን እንዲህ በማለት ይጠይቋቸዋል፡-

﴿ مَا سَلَكَكُمْ فِي سَقَرَ ﴿٤٢﴾ قَالُوا لَمْ نَكُ مِنَ الْمُصَلِّينَ ﴿٤٣﴾ وَلَمْ نَكُ نُطْعِمُ الْمِسْكِينَ ﴿٤٤﴾
وَكُنَّا نَخُوضُ مَعَ الْخَائِضِينَ ﴿٤٥﴾ وَكُنَّا نُكَذِّبُ بِيَوْمِ الدِّينِ ﴿٤٦﴾ حَتَّىٰ أَتَانَا الْيَقِينُ ﴿٤٧﴾ ﴾
المدثر: ٤٢ - ٤٧

“በሰቀር ውስጥ ምን አገባችሁ? (እነርሱም) ይላሉ፡- ከሰጋጆቹ አልነበርንም፡፡ ለድሆችም የምናበላ አልነበርንም፡፡ ከዘባራቂዎቹም ጋር እንዘባርቅ ነበርን፡፡ በፍርዱ ቀንም እናስተባብል ነበር፡፡ እርግጠኛው (ሞት) እስኪመጣን ድረስ፡፡” (አል-ሙደሲር፡ 42-47)

ምዕራፍ አስራ አንድ

ኢህሳን (ማሳመር) እና ሙራቀባህ

ኢህሳን የሚለውን የአረብኛ ቃል ነብዩ (ሰ.ዐ.ወ.) "አላህን እንደምታየው አድርገህ መገዛት ማለት ነው፡፡ አንተ ባታየውም እርሱ ያይሃልና" በማለት ተርጉመውታል፡፡ ሙራቀባህ የሚለውም ስያሜ ከኢህሳን ጋር ዝምድና ያለው ሲሆን በግልጽም ሆነ በስውር የምናደርገውን ሁሉ አላህ የሚያይ መሆኑን በመገንዘብ ራስን በሕግጋቱ ሥር ማዋል የሚልን ትርጓሜ ይሟል፡፡

ጋያሉ አላህ ኢህሳንንና ሙራቀባህን አስመልክቶ በቁርአን እንዲህ ይላል፡-

﴿ ٱلَّذِى يَرَىٰكَ حِينَ تَقُومُ ﴿٢١٨﴾ وَتَقَلُّبَكَ فِى ٱلسَّٰجِدِينَ ﴿٢١٩﴾ ﴾ الشعراء: ٢١٦ - ٢١٩

በዚያ ለሶላት በምትቆም ጊዜ በሚያይህ በሰጋጆች ውስጥ መዘዋወርህንም (በሚያየው ጌታህ ላይ ተጠጋ)" (አስ-ሹዐራ፡219)

﴿ وَلَقَدْ خَلَقْنَا ٱلْإِنسَٰنَ وَنَعْلَمُ مَا تُوَسْوِسُ بِهِۦ نَفْسُهُۥ ۖ وَنَحْنُ أَقْرَبُ إِلَيْهِ مِنْ حَبْلِ ٱلْوَرِيدِ ﴿١٦﴾ ﴾ ق: ١٦

"ሰውንም ነፍሱ (በሐሳቡ) የምታጫውተውን የምናውቅ ስንሆን ፈጠርነው፡፡ እኛም ከደም ጋኑ ጅማት ይበልጥ ወደርሱ ቅርብ ነን፡፡" (ቃፍ፡ 16)

﴿ وَهُوَ مَعَكُمْ أَيْنَ مَا كُنتُمْ ۚ ﴿٤﴾ ﴾ الحديد: ٤

"...እርሱም የትም ብትሆኑ ከእናንተ ጋር ነው..."(አል-ሐዲድ፡4)

በእውነቱ በሃቅ አላህን የሚፈራ ሰው ማለት የአል-ኢህሳንን እውነተኛ ትርጓሜ የተረዳና ይህንንም በሕይወቱ ላይ ተግባራዊ የሚያደርግ ነው፡፡ የትም ሥፍራ ቢሆን በየትኛውም ጊዜ የሚሰራውንና ሁኔታውን የሚከታተለው መለኮታዊ ጥላ ከእርሱ እንደማይለይ አንድ ሰው

እርግጠኛ ከሆነ ምንም ዓይነት ኃጢአት እያወቀ አይፈጽምም፡፡ አላህ እንዲህ ይላል፡-

﴿ إِنَّ ٱللَّهَ لَا يَخۡفَىٰ عَلَيۡهِ شَيۡءٞ فِي ٱلۡأَرۡضِ وَلَا فِي ٱلسَّمَآءِ ٥ ﴾ آل عمران: ٥

“አላህ በምድርም በሰማይም ምንም ነገር በእርሱ ላይ አይሰወርም፡፡” (አሊ-ዒምራን፡5)

ብዙውን ጊዜ ሰዎች በእለት ተእለት ኑሯቸው ኃጢአት ከመፈፀም የሚቆጠቡት ሌሎች ሰዎች እንዳያዩዋቸውና ውርደት እንዳያገኛቸው በመፍራት ነው፡፡ ታዲያ እንዲህ ዓይነቱ ሰው ሁሉን ቻይ የሆነው አላህን ለመፍራትና የሚሰራውንና የሚያደርጋትን እያንዳንዷን ድርጊት እርሱ እንደሚመለከተው ለማወቅ ይቀርባል? ፈጽሞ እዚያ ደረጃ አይደርስም፡፡ ይህን ካደረገ የአል-ኢህሳንን ደረጃ ተቀዳጅቷል ማለት ነው። አላህ እንዲህ ይላል፡-

﴿ يَعۡلَمُ خَآئِنَةَ ٱلۡأَعۡيُنِ وَمَا تُخۡفِي ٱلصُّدُورُ ١٩ ﴾ غافر: ١٩

“(አላህ) የአይኖችን ክዳት፣ ልቦችም የሚደብቁትን ሁሉ ያውቃል፡፡” (አል-ሙእሚን፡19)

ሆኖም ግን የነብዩ (ሰ.ዐ.ወ.) ባልደረቦች በኖሩበት ዘመን ይህ ተግባራዊ ሆኗል፡፡

በአንድ ምሽት ላይ ኸሊፋው ኡመር ኢብን አልኸጣብ (ረ.ዐ.) በመዲና ጐዳናዎች ላይ ዘወትር እንደሚያደርጉት የሕዝባቸውን ደህንነት በመከታተል ሥራ ተጠምደው ነበር፡፡ በዚያው ቅጽበት በአንዲት ልጃገረድና በእናቷ መካከል የሚደረግ የቃላት ልውውጥ ጆሮአቸው ውስጥ ገባ፡፡ እናት ለልጅዋ እንዲህ ትላት ነበር፡-

“ልጄ ሆይ! ወተቱ ውስጥ ውሃ ጨምሪበትና ነገ እንሸጠዋለን፡፡”

ልጅ ደግሞ እንዲህ በማለት መለሰች፡-

“እናቴ ሆይ! ኸሊፋችን በወተት ውስጥ ውሃ እንዳንጨምር አልከለከሉምን?”

“ልጄ ሆይ! አሁን ኸሊፋው የምንሰራውን ነገር እንዴት ሊመለከቱ ይችላሉ?”

ያቺ አላህን የምትፈራ ልጅ በእናቷ ሃሳብ አልተስማማችም፡፡ እንዲህ አለች፡-

“እማዬ ሆይ! አንቺ እንዳልሽው አሁን ኸሊፋው የምንሰራውን ነገር አይመለከቱ ይሆናል፡፡ ሆኖም ግን የአላህስ ነገር፤ እርሱስ እንደማይመለከተን እርግጠኛ ነሽ? ይህን ድርጊት ከሰዎች መደበቅ እንችል ይሆናል፡፡ ግና ሁሉን ከሚያይ ጌታ መደበቅ እንችላለን?”

ኡመር (ረ.ዐ.) በዚህች ልጃገረድ አባባል ስሜታቸው ተናጠ፡፡ አላህን የምትፈራ በመሆኗ የተናገረቻቸው ቃላቶች ልባቸውን ሰርገው ገቡ፡፡ ከዚያም ለልጃቸው ሚስት ትሆን ዘንድ ሊድሩለት በልባቸው አጫት፡፡ እናም እንዳሰቡት አላህ አድርጐላቸው ልጃቸው ወጣቷን አገባ፡፡ ከሁለቱ ተጓዳኞች በኢስላም ታሪክ አንኳር ስፍራ ያለው ልጅ ተወለደ፡፡ እርሱም የዑመር (ረ.ዐ.) የልጅ ልጅ የሆነውና አምስተኛው በትክክል የመራ ኸሊፋ እንደሆነ የተመሰከረለት ዑመር ኢብኑ አብዱልአዚዝ ነው፡፡

ከዚህ ትረካ የምንቀስመው ዋነኛ ትምህርት ሁላችንም የትም ቦታ ብንሆን በምንም ጊዜ አላህን መፍራትና መጠንቀቅ ያለብን መሆኑን ነው፡፡ ይህን አስመልክቶ በቁርአን እንዲህ ተብሎ ተጽፏል፡-

﴿ وَهُوَ مَعَكُمْ أَيْنَ مَا كُنتُمْ ﴿٤﴾ ﴾ الحديد: ٤

“...የትም ብትሆኑ ከእናንተ ጋር ነው፡፡” (አል-ሐዲድ፡4)

ኃያሉ አላህ ሁሉንም የፍጡራኑን ሁኔታ በሚገባ ያውቃል፡፡ ይህንን ጠንቅቆ አለመገንዘብ የእርሱን ታላቅነት ማሳነስና በባህሪው ድክመት እንዳለበት ወደማመን ያስጠጋል፡፡ ይህ ደግሞ አደገኛ ወደሆኑ ወንጀሎች (ኃጢአቶች) ሊመራን ይችላል፡፡ ቁርአን የሚነግረን አላህ የሰዎችን ብቻ

ሳይሆን በሰማያትና በምድር እንዲሁም በመካከላቸው የሚገኙ ፍጡራንን ሁኔታ ሁሉ ልቅም አድርጎ የሚያውቅ መሆኑን ነው፡-

﴿ وَعِندَهُۥ مَفَاتِحُ ٱلۡغَيۡبِ لَا يَعۡلَمُهَآ إِلَّا هُوَۚ وَيَعۡلَمُ مَا فِي ٱلۡبَرِّ وَٱلۡبَحۡرِۚ وَمَا تَسۡقُطُ مِن وَرَقَةٍ إِلَّا يَعۡلَمُهَا وَلَا حَبَّةٖ فِي ظُلُمَٰتِ ٱلۡأَرۡضِ وَلَا رَطۡبٖ وَلَا يَابِسٍ إِلَّا فِي كِتَٰبٖ مُّبِينٖ ٥٩ ﴾ الأنعام: ٥٩

"የሩቅ ነገር መክፈቻዎች ከእርሱ ዘንድ ናቸው። ከእርሱ በቀር ማንም አያውቃቸውም። በየብስና በባሕር ያለውንም ሁሉ ያውቃል። ከቅጠልም አንዲትም አትረግፍም የሚያውቃት ቢሆን እንጂ። ከቅንጣትም በመሬት ጨለማዎች ውስጥ የለም፣ ከእርጥብም ከደረቅም አንድም የለም ግልጽ በሆነው መጽሐፍ ውስጥ (የተመዘገበ) ቢሆን እንጅ።" (አል-አንዓም፡59)

አንድ የአላህ ወዳጅ እንዲህ ይላሉ፡- "በባቡር ለመጓዝ ያሰበ ሰው በባቡር ጣቢያው ውስጥ ገብቶ ከተኛ ባቡሩ ያመልጠዋል። ይህ ዓለም ወደሚቀጥለው ዓለም እንደምንሸጋገርበት የባቡር ጣቢያ ማለት ነው። ማንም ተጓዥ የሚፈልገውን ባቡር ለመያዝና ጉዞውን ለመቀጠል ነቅቶ መጠበቅ አለበት።"

አላህ በማንኛውም ሁኔታ ላይ ብንሆን የእኛን ሁኔታ እንደሚከታተልና ንግግራችንን እንደሚሰማ ለመገንዘብ የሚቀጥለውን የቁርአን አንቀጽ እንመልከት፡-

﴿ أَلَمۡ تَرَ أَنَّ ٱللَّهَ يَعۡلَمُ مَا فِي ٱلسَّمَٰوَٰتِ وَمَا فِي ٱلۡأَرۡضِۖ مَا يَكُونُ مِن نَّجۡوَىٰ ثَلَٰثَةٍ إِلَّا هُوَ رَابِعُهُمۡ وَلَا خَمۡسَةٍ إِلَّا هُوَ سَادِسُهُمۡ وَلَآ أَدۡنَىٰ مِن ذَٰلِكَ وَلَآ أَكۡثَرَ إِلَّا هُوَ مَعَهُمۡ أَيۡنَ مَا كَانُواْۖ ثُمَّ يُنَبِّئُهُم بِمَا عَمِلُواْ يَوۡمَ ٱلۡقِيَٰمَةِۚ إِنَّ ٱللَّهَ بِكُلِّ شَيۡءٍ عَلِيمٌ ٧ ﴾ المجادلة: ٧

"አላህ በሰማያት ውስጥ ያለውን በምድርም ውስጥ ያለውን ሁሉ የሚያውቅ መሆኑን አታይምን? ከሦስት ሰዎች መንሾካሾክ አይኖርም እርሱ አራተኛው ቢሆን እንጅ። ከአምስትም (አይኖርም) እርሱ

ስድስተኛቸው ቢሆን እንጅ፡፡ ከዚያ ያነሰም የበዛም (አይኖርም) እርሱ የትም ቢሆኑ አብሮአቸው ቢሆን እንጂ፡፡ ከዚያም በትንሣኤ ቀን የሰሩትን ሁሉ ይነግራቸዋል፡፡ አላህ ነገሩን ሁሉ ዓዋቂ ነው፡፡" (አል-ሙጃደላህ፡7)

እንደገናም የገናናውን ኸሊፋ የዑመር ኢብን አልኸጣብን (ረ.ዐ.) ዘመን ልንመለስበት ነው፡፡ ዑመር (ረ.ዐ.) ሙዓዝን (ረ.ዐ.) በኑ ኪላብ ወደ ተባሉ ጐሣዎች አንዳች ጉዳይ ይፈጽምላቸው ዘንድ ይልኩታል፡፡ የተልእኮው ዓላማ አስፈላጊ የሆኑ ክፍያዎችን ለሚመለከታቸው ክፍሎች መፈፀም፣ የተለያዩ የፍጆታ እቃዎችን ማጓጓዝ፣ ከሃብታሞች ተወስዶ ለድሆች የሚከፋፈል የሆነን ዘካ (የግዴታ ምጽዋት) ሰብስቦ ማከፋፈል ነበር፡፡

ሙዓዝ (ረ.ዐ.) ይህን ታላቅ የሆነ ተልእኮ የፈፀመው በታላቅ ጥንቃቄ ሲሆን ሲመለስም የሰዎቹን ልብ ለማግኘት የተጠቀመባቸውን ዘዴዎች አስመልክቶ የሚያስደስቱ ትረካዎችን ይዞ ነበር፡፡ ከፀሀይና ከአቢራው የሚከላከልበትን ጨርቅ ብቻ አንጠልጥሎ ነበር ወደ ቤቱ የገባው፡፡

አንድ እለት ባለቤቱ እንዲህ በማለት ጠየቀችው፡-

"አንተ የፈፀምከውን ዓይነት ተልእኮ የፈፀሙ ሰዎች ክፍያ (ኮሚሽን) የሚያገኙ ሲሆን ለቤተሰባቸውም የሚሆን ስጦታን ይዘው ነው የሚመለሱት፡፡ ታዲያ ለእኛ ያመጣህልን ነገር ምንድን ነው?"

ሙአዝ (ረ.ዐ.) እንዲህ በማለት መልስ ሰጣት፡- "እኔ ሁልጊዜ አብሮኝ የሚሆንና እያንዳንዷን ድርጊቴን የሚተሳሰበኝ የሆነ ተቆጣጣሪ ነበረኝ፡፡"

በዚህ ጊዜ ባለቤቱ በንግግሩ ተናደደች፡፡ እናም እንዲህ አለች፡- "ነብዩ (ሰ.ዐ.ወ.) ያምኑህ ነበር፡፡ አቡበከርም እንዲሁ፡፡ አሁን ደግሞ የዑመር ጊዜ ነው፡፡ እናም ተቆጣጣሪ እንዴት ያሰማሩብሃል? አያምኑህም ማለት ነው?"

ሙዓዝ (ረ.ዐ.) ለባለቤቱ ሌላ የሰጣት መልስ መኖሩ ባይገለጽም ይህ የእርሷ ንግግር እንደዘበት ከዑመር (ረ.ዐ.) ባለቤት ጆሮ ውስጥ በመግባቱ

ብዙም ሳይቆይ ዑመር ሰሙት፡፡ ከዚያም ሙዓዝን አስጠርተው እንዲህ በማለት ጠየቁት፡-

“የተባለው ነገር ምንድን ነው? ከአንተ ጋር ተቆጣጣሪን በማድረግ ሰድጃለሁን? እንደማላምንህ ነው የምታስበው?”

ሙዓዝ (ረ.ዐ.) ግን በምሳሌነት የሚጠቀስ ምላሹን እንዲህ በማለት አቀረበ፡-

“የምእመናን አዛዥ ሆይ! ለባለቤቴ ከዚህ ሌላ ልነግራት የምችለው ነገር አልነበረኝም፡፡ እርግጥ ነው ተቆጣጣሪ ነበረኝ ያልኳት እርስዎን ሳይሆን አላህን ማለቴ ነበር፡፡ ይህንንም ስል ለሰጠሁት አገልግሎት ምላሽ ለራሴ ምንም ነገር መውሰድ አልፈልግም ማለቴ ነው…”

ዑመር (ረ.ዐ.) የሙዓዝን አባባል በሚገባ ተገነዘቡ፡፡ በእርግጥም ለዚህ ዓለም ሃብት ደንታ እንደሌለው ያውቃሉ፡፡ እናም ከራሳቸው ገንዘብ ላይ አንስተው ስጦታ ካበረከቱለት በኋላ እንዲህ አሉት፡- “ ይህን ይዘህ ሂድና ለባለቤትህ ካበረከትክላት በኋላ አባብላት!”

ሙአዝን (ረ.ዐ.) የመሰሉ ሰዎች የመጪው ዓለም መከራ እጅግ የሚያሳስባቸውና ነፍሳቸውንም በየጊዜው የሚመረምሩ ናቸው፡፡ አላህንም በመጠንቀቅ (ሙራቀባህ) ሕይወታቸውን አገባድደዋል፡፡ አላህ ሥራቸውን ይውደድላቸው፡፡ በእዝነቱም ውስጥ ያስገባቸው፡፡ ኡመር (ረ.ዐ.) እንዲህ ይሉ ነበር፡-

“ከአላህ ፊት ቆማችሁ ሳይተሳሰባችሁ በፊት ከነፍሳችሁ ጋር ተሳሰቡ፡፡“

አቡ ሰኢድ አል-ኹድሪ (ረ.ዐ.) ባስተላለፉትና ሙስሊም በዘገቡት ሐዲስ ነብዩ (ሰ.ዐ.ወ.) እንዲህ ብለዋል፡-

“ዓለም (ዱንያ) አረንጓዴና ጣፋጭ ናት፡፡ አላህ በዚህች ዓለም ላይ ተጠሪው (ኸሊፋው) አድርጓችኋል፡፡ የምትሰሩትን ያያል፡፡ በዓለማዊ

መጠቀሚያ (ዱንያ) ውስጥ ተዘፍቃችሁ ከመማረክና ከሴቶች ጋር በሚኖራችሁ ግንኙነት ከሚፈጠረው እኩይ ተግባር ተጠንቀቁ፡፡ አላህን ፍሩ፡፡ የእስራኤል ልጆች የመጀመሪያ መፈተኛ ሴቶችን የሚመለከት ነበርና፡፡"

ስለሆነም ሁልጊዜም ቢሆን ጠንቃቃዎች ሆነን መገኘት ነው ያለብን፡፡ በቀንም ሆነ በማታ የአላህን ውዴታ በሚያስገኙ መልካም ሥራዎች ራሳችንን ማስጠመድ ይኖርብናል፡፡ ኸይር (መልካም) ሥራዎችን ሰርተን መጥገብ የለብንም፡፡ እንደምናውቀው ሃያ አራት ሰዓት ሙሉ ኸይር (መልካም) ሥራን ለመሥራት ወቅቱ ክፍት ሆኖ ይጠብቃል፡፡ መልካም ሥራ ማለት ገንዘብ ለተቸገሩ መመጽወት ወይም ምግብ ማብላት ብቻ የሚመስላቸው አይጠፉም፡፡ የሚከተለውን ሐዲስ ስናነብ የመልካም ሥራ ዘርፎች ብዙ መሆናቸውንና የግድ የገንዘብ አቅም እንዲኖረን የሚጠይቁን አለመሆናቸውን እንገነዘባለን፡፡

አቡ ሁረይራ (ረ.ዐ.) ባወሩትና ቡኻሪና ሙስሊም በዘገቡት ሐዲስ የአላህ መልክተኛ (ሰ.ዐ.ወ.) እንደሚከተለው ብለዋል፡-

"ፀሐይ በወጣችበት ቀን ሁሉ የማንኛውም ሰው መገጣጠሚያዎች ሰደቃ (ምጽዋት) ማቅረብ አለባቸው፡፡ በሁለት ሰዎች መካከል በትክክል ብትፈርድ ሰደቃ ነው፡፡ አንድን ሰው ከመጓጓዣው ላይ ብታወጣው ወይም እቃውን ብትጭንለት ሰደቃ ነው፡፡ መልካም ንግግርም ሰደቃ ነው፡፡ እያንዳንዷ ወደ ሶላት የምታመራ እርምጃ ሰደቃ ናት፡፡ ከመንገድ ላይ ጐጂ ነገሮችን ማስወገድም ሰደቃ ነው፡፡"

እውነተኛ የአላህ ባሪያዎች የሰይጣን ተግዳሮት የማይበግራቸውና ምንጊዜም የጌታቸውን ውዴታ ለማግኘት ብቻ የሚሰሩ ናቸው፡፡ ለእንዲህ አይነት ሰዎች አላህ ቀጥተኛ የሆነ መመራትንና እውቀትን ይሰጣቸዋል። በመንፈስም ያፀናቸዋል፡፡ በዚህ እውቀታቸው እየተጠቀሙም የአጽናፈ ዓለሙን ሚስጥራት ይመረምራሉ፡፡ ሁሉም ነገር የተፈጠረው ለከንቱ እንዳልሆነም ያረጋግጣሉ፡-

﴿ إِنَّ فِي خَلۡقِ ٱلسَّمَٰوَٰتِ وَٱلۡأَرۡضِ وَٱخۡتِلَٰفِ ٱلَّيۡلِ وَٱلنَّهَارِ لَأٓيَٰتٖ لِّأُوْلِي ٱلۡأَلۡبَٰبِ ١٩٠ ٱلَّذِينَ يَذۡكُرُونَ ٱللَّهَ قِيَٰمٗا وَقُعُودٗا وَعَلَىٰ جُنُوبِهِمۡ وَيَتَفَكَّرُونَ فِي خَلۡقِ ٱلسَّمَٰوَٰتِ وَٱلۡأَرۡضِ رَبَّنَا مَا خَلَقۡتَ هَٰذَا بَٰطِلٗا سُبۡحَٰنَكَ فَقِنَا عَذَابَ ٱلنَّارِ ١٩١ ﴾ آل عمران: ١٩٠ - ١٩١

"ሰማያትንና ምድርን በመፍጠር ሌሊትና ቀንንም በመተካካት ለባለ አእምሮዎች ምልክቶች አሉ። (እነርሱም) እነዚያ ቆመው፣ ተቀምጠው፣ በጐኖቻቸውም ተጋድመውም አላህን የሚያወሱ በሰማያትና በምድር አፈጣጠርም የሚያስተነትኑ "ጌታችን ሆይ! ይህን በከንቱ አልፈጠርከውም ጥራት ይገባህ። ከእሳትም ቅጣት ጠብቀን የሚሉ ናቸው።" (አሊ-ዒምራን፡ 189)

ነቢዩላህ ዩሱፍን (ዐ.ሰ.) ከዝሙት (ፋህሻእ) አደጋ የጠበቃቸው ይህ ጥንቁቅነታቸው እንጂ ሌላ አልነበረም። በዚያ የጭንቅ ሰዓታቸው አላህ የሚሰሩትንና ጠቅላላ ሁኔታቸውን እንደሚያይ የማመንን ፀጋ (አል-ኢህሳን) ባይሰጣቸው ኖሮ ታላቅ ከሆነ ኃጢአት ላይ በወደቁ ነበር። ምክንያቱም ነፍስ ሁሉ ወደ መጥፎና የሚጠላ ነገር ጐትጓች ናትና። ነቢዩላህ ዩሱፍ (ዐ.ሰ.) በዚያ የፈተናቸው ሰዓት የተናገሩትን አባባል በቁርአን እንደሚከተለው እናነበዋለን፡-

﴿ وَمَآ أُبَرِّئُ نَفۡسِيٓۚ إِنَّ ٱلنَّفۡسَ لَأَمَّارَةُۢ بِٱلسُّوٓءِ إِلَّا مَا رَحِمَ رَبِّيٓۚ إِنَّ رَبِّي غَفُورٞ رَّحِيمٞ ٥٣ ﴾ يوسف: ٥٣

"ነፍሴንም (ከስሕተት) አላጠራም። ነፍስ ሁሉ ጌታዬ የጠበቃት ካልሆነች በስተቀር በመጥፎ ነገር በእርግጥ አዛዥ ናትና። ጌታዬ በጣም መሐሪ አዛኝ ነው (አለ)።" (ዩሱፍ፡53)

ወደ ባሕር የሚፈስ ወንዝ ከዓለቶችና ከሸለቆዎች ጋር ሲጋጭ ድምጽ ማሰማቱ አይቀርም። ድምጽ ማሰማት ካቆመ ከባሕር ጋር ተቀላቅሏል ማለት ነው፡ ስለዚህም ከዚያ በኋላ ወንዝ ተብሎ አይጠራም። "ኢሕሳን"

አንድ ሰው ሁለንተናው በፈጣሪው ቁጥጥር ስር መሆኑን የሚያምንበትና ከመለኮታዊ ፈቃድና ይሁንታ ውጭ ምንም ነገር ያለማድረግ የመጨረሻው ጫፍ ነው፡፡

ተቅዋ (አላህን መፍራት) የእምነት ዋና ፍሬ ነገር ነው፡፡ ሃቀኝነት በሶላት ላይ ኹሹዕ ማግኘት፣ ዱዓ (አላህን መለመን) ና ሌሎች መልካም ምግባራት የሚገሩት በአንድ ሰው ልብ ውስጥ ተቅዋ ካለ ብቻ ነው፡፡ ተቅዋን በተመለከተ ኃያሉ አላህ በቁርአን እንዲህ ይላል፡-

﴿ يَٰٓأَيُّهَا ٱلَّذِينَ ءَامَنُواْ ٱتَّقُواْ ٱللَّهَ حَقَّ تُقَاتِهِۦ وَلَا تَمُوتُنَّ إِلَّا وَأَنتُم مُّسۡلِمُونَ ١٠٢ ﴾ آل عمران: ١٠٢

“እናንተ ያመናችሁ ሆይ! አላህን ተገቢውን መጠንቀቅ ተጠንቀቁ...” (አሊ-ዒምራን፡102)

﴿ فَٱتَّقُواْ ٱللَّهَ مَا ٱسۡتَطَعۡتُمۡ ١٦ ﴾ التغابن: ١٦

“አላህንም የቻላችሁትን ያህል ፍሩት...” (አት-ተጋቡን፡16)

﴿ وَمَن يَتَّقِ ٱللَّهَ يَجۡعَل لَّهُۥ مَخۡرَجٗا ٢ وَيَرۡزُقۡهُ مِنۡ حَيۡثُ لَا يَحۡتَسِبُۚ ٣ ﴾ الطلاق: ٢ - ٣

“አላህን የሚፈራ ሰው ለእርሱ መውጫን ያደርግለታል፡፡ ከማያስበውም በኩል ሲሳይን ይሰጠዋል...” (አጥ-ጦላቅ፡2-3)

በአንድ ወቅት ኡወይስ አል-ቀረኒን እናቱ እንዲህ በማለት ጠየቀችው፡-

“ልጄ ሆይ! ሌሊቱን በሙሉ ስትሰግድ ማደር የምትችለው እንዴት ነው?”

ቀረኒ ሲመልስ እንዲህ አለ፡-

“የምወድሽ እናቴ! እኔ አላህን የማመልከው በታላቅ ጥንቃቄ ነው፡፡ ልቤ በአላህ ፍራቻ የተሞላ ስለሆነ ድካምም ሆነ በሰውነቴ ላይ የሚደርስ ነገር አያሳስበኝም፡፡ ስለሆነም ሌሊቱ ረዥም አይሆንብኝም፡፡”

“ኹሹዕ የሚባለው ነገርስ ምንድን ነው?” የእናቱ ጥያቄ ነበር፡፡ እርሱም እንዲህ አለ፡-

“አንድ ሰው በአምልኮት (ኢባዳ) ላይ እያለ በቀስት ፍላፃ ቢወጋ የማይሰማው መሆኑ ነው፡፡”

ቀጥሎ ደግሞ በኢስላም ታሪክ ታዋቂ የሆነን አንድ ገጠመኝ እንመልከት። በአንድ ጦርነት ላይ ዓሊ (ረ.ዐ.) በቀስት ፍላፃ እግራቸውን ይወጋሉ፡፡ በዙሪያቸው ያሉ ሰዎች ያንን ፍላፃ ሊነቅሉላቸው ሙከራ ቢያደርጉም ያንን ማድረግ አልቻሉም፡፡ ምክንያቱም በጣም ሕመም ስለተሰማቸው ነበር፡፡ ከዚያም ዓሊ (ረ.ዐ.) እንዲህ አሉ፡-

“ሶላት ላይ ስቆም ያኔ ከእግሬ ላይ ነቅላችሁ አውጡ!”

ሰዎቹም ልክ ዓሊ (ረ.ዐ.) በነገሯቸው መሠረት ሶላት ላይ ሲቆሙ ጠብቀው ነቅለውላቸዋል፡፡ ሶላታቸውን እንደጨረሱም ዓሊ (ረ.ዐ.) እንዲህ በማለት ጠየቋቸው፡-

“ምንድን ነው ያደረጋችሁት?”

“የቀስቱን ፍላጻ ነቅለን አወጣንልዎት!” በማለት መለሱላቸው፡፡

ይህን ታሪክ ስናነብ (ከዚህ በፊት አንብበነውም ይሆናል) መደነቃችን አይቀርም፡፡ እውነት ይህ በእውኑ የተፈፀመ ታሪክ ነው? ከሆነ አሁን በዚህ ዘመን የምንገኝ ሰዎች የምንሰግደው ሶላት ምን ዓይነት እጣ ይሆን የሚጠብቀው?

ዓሊ (ረ.ዐ.) የብረቱ ቁራጭ ከሰውነታቸው ተመዝዞ ሲወጣ በሶላታቸው እጅግ ተመስጠው የነበሩ ከመሆናቸው የተነሣ ምንም ዓይነት ህመም አልተሰማቸውም፡፡ ይህም ሊሆን የቻለው ዓሊ (ረ.ዐ.) ለአላህ የነበራቸው ፍራቻ ታላቅ ስለነበረ ነው፡፡

ማንም ቢሆን በሶላት ላይ እያለ መደሰትና ድካም የማይሰማው ቢሆን ይወዳል፡፡ ሆኖም ግን ይህን ደረጃ ለመጐናፀፍ የሚከፈለውን

መስዋእትነት ብዙዎቻችን እንፈራዋለን፡፡ ይህም በልባችን ውስጥ ለአላህ ያለንን ፍራቻ መጨመር ነው፡፡ አላህ እንዲህ ይላል፡-

﴿ قَدۡ أَفۡلَحَ ٱلۡمُؤۡمِنُونَ ١ ٱلَّذِينَ هُمۡ فِي صَلَاتِهِمۡ خَٰشِعُونَ ٢ ﴾ المؤمنون: ١ - ٢

"ምእመናን ፍላጐታቸውን ሁሉ በእርግጥ አገኙ (ዳኑ) እነዚያ እነርሱ በስግደታቸው ውስጥ (አላህን) ፈሪዎች፡፡" (አል-ሙእሚኑን፡1-2)

ሰዎች በኢህሣንና ሙራቀባህ ራሳቸውን ለማሰልጠን ከፈለጉ አላህን ማውሳት (ዚክር) ማብዛት አለባቸው፡፡ አላህን ማውሳት አእምሮንና ልብን (ቀልብን) ከአላህ ጋር ያገናኛል፡፡ ቀልብን እርካታ ያላብሳታል፡፡ የጥበብና የማስተዋል ባለቤት የሆነው አላህ እንዲህ ይላል፡-

﴿ ٱلَّذِينَ ءَامَنُواْ وَتَطۡمَئِنُّ قُلُوبُهُم بِذِكۡرِ ٱللَّهِۗ أَلَا بِذِكۡرِ ٱللَّهِ تَطۡمَئِنُّ ٱلۡقُلُوبُ ٢٨ ﴾ الرعد: ٢٨

"(እነርሱም) እነዚያ ያመኑ ልቦቻቸውም አላህን በማውሳት የሚረኩ ናቸው፡፡ ንቁ! አላህን በማውሳት ልቦች ይረካሉ፡፡"(አር-ራዕድ፣ 28)

አላህን ማውሳት ሰዎችን ጥበበኛና አስተዋይ ያደርጋቸዋል፡፡ ለዚህም ነው አላህ ሙሳን (ዐ.ሰ.) እና ወንድማቸውን ሃሩንን (ዐ.ሰ.) ወደ ፈርዖን ሲልካቸው እንደሚከተለው ያለው፡-

﴿ ٱذۡهَبۡ أَنتَ وَأَخُوكَ بِـَٔايَٰتِي وَلَا تَنِيَا فِي ذِكۡرِي ٤٢ ﴾ طه: ٤٢

"አንተም ወንድምህም በታምራቶቼ ሂዱ፡፡ እኔንም ከማውሳት አትቦዝኑ፡፡" (ጣሃ፡42)

አላህን በብዛት የምታወሳ ቀልብ እርሱን ለመፍራት የተገባች ነች፡፡ ይህን መሳዩዋ ቀልብ በሚቀጥለው የቁርአን አንቀጽ የተገለፀውን ምስጢር በሚገባ ትገነዘባለች፡-

﴿ يَوۡمَ لَا يَنفَعُ مَالٞ وَلَا بَنُونَ ٨٨ إِلَّا مَنۡ أَتَى ٱللَّهَ بِقَلۡبٖ سَلِيمٖ ٨٩ ﴾ الشعراء: ٨٨ - ٨٩

"ገንዘብም ልጆችም በማይጠቅሙበት ቀን፣ ወደ አላህ በንጹህ ልብ የመጣ ሰው ቢሆን እንጂ፡፡" (አሽ-ሹዐራ፡88-89)

እዚህ ደረጃ ላይ ለመድረስ አንድ ሰው የነፍስን ጣጣና የምትጋርጣቸውን መሰናክሎች መቋቋምና ማለፍ ይጠበቅበታል፡፡ ይህንንም ለማድረግ አላህን በማስታወስ (በዚክር)፣ በትእግስትና በሌሎች መልካም ምግባራት መበርታት አለበት፡፡

ኃይማኖትን (ዲንን) በሁለት ገጽታዎች ከፍለን ማየት እንችላለን፡፡ ይኸውም ሰዎች በየጊዜው በሚፈጽሟቸው የአምልኮት ተግባራት (ኢባዳዎች) ላይ የሚንፀባረቁ ላእላይ ክንውኖችና በልብ ውስጥ የሚፈፀሙና ከመለኮታዊው አካል ውጭ ማንም በማይቆጣጠራቸው ውስጣዊ ክንውኖቹ፡፡ የመጀመሪያውን በህንፃ ላይ እንደሚገኙና ህንፃውን ደግፈው እንደያዙት አምዶች (ምሶሶዎች) ብንቆጥረው ሁለተኛውን ደግሞ በምሰሶዎቹ ላይ እንደሚገኙትና የምሶሶዎቹን ውበት እንዳላበሱ የተለያዩ ጌጦችና ዲዛይኖች ልንቆጥረው እንችላለን፡፡ የኢስላም ምሁራን ውስጥንና ውጭን የማቀናጀቱን ይህን ሒደት ሁሉም ሰው ትኩረት እንዲሰጠው ይሻሉ፡፡

ለምሳሌ አንድ ሰው ሶላት ለመስገድ ቢፈልግ ከሁሉም በፊት የሰውየው አካል ከተለያዩ ቆሻሻዎች (ነጃሳዎች) ንጹህ መሆኑ ግድ ነው፡፡ ከዚያም አልባሳቱና የሚሰግድበት ቦታም እንዲሁ ንጽህናቸው የተጠበቀ መሆን አለበት፡፡ ይሁን እንጂ ይህ ሰው ሶላቱ ከአላህ ዘንድ ተቀባይነት እንዲኖረው የሚሻ ከሆነ ኹሹዕ (የአላህ ፍራቻና ሙሉ ትኩረት) ሊኖረው ይገባል፡፡ አላህ በቁርአን እንዲህ ይላል፡-

﴿ فَوَيۡلٞ لِّلۡمُصَلِّينَ ٤ ٱلَّذِينَ هُمۡ عَن صَلَاتِهِمۡ سَاهُونَ ٥ ﴾ الماعون: ٤ - ٥

"ወዮላቸው ለሰጋጆች፤ ለእነዚያ እነርሱ ከስግደታቸው ዘንጊዎች ለሆኑት (ሰጋጆች)፡፡" (አል-ማዑን፡ 4-5)

በሌላ የቁርአን አንቀጽም ኃያሉ አላህ እንዲህ በማለት በሶላት ውስጥ ተመስጦ (ኹሹዕ) ወሳኝ መሆኑን ይገልፃል፡-

﴿ قَدۡ أَفۡلَحَ ٱلۡمُؤۡمِنُونَ ١ ٱلَّذِينَ هُمۡ فِي صَلَاتِهِمۡ خَٰشِعُونَ ٢ ﴾ المؤمنون: ١ - ٢

"ምእመናን ፍላጐታቸውን ሁሉ በእርግጥ አገኙ (ዳኑ)፡፡ እነዚያ እነርሱ በስግደታቸው ውስጥ (አላህን) ፈሪዎች፡፡" (አል-ሙእሚኑን፡1-2)

የአላህ መልክተኛ (ሰ.ዐ.ወ.) ሃያ ሶስት አመታት በፈጀው ተጋድሏቸው ብዙ ፍዳና ቁም ስቅል አይተዋል፡፡ ክብራቸው ተደፍሯል፡፡ ንብረታቸው ወድሟል፣ ፈርስ ተደፍቶባቸዋል፣ ተርበዋል፣ ተጠምተዋል፣ ተሰድደዋል፡፡ ከቤተሰቦቻቸው መካከልም ባለቤታቸው እመት ከዲጃ በዚሁ ተደራራቢ የመከራ ዘመን በመጐዳታቸው ምክንያት (ረ.ዐ.) ሞተውባቸዋል፡፡ ከሃዲያኑ ባደረሱባቸው ግፍ ባለመርካታቸው ጦርነት የከፈቱባቸው በመሆኑ ከስጋ ዘመዶቻቸው መካከል ሃምዛ አሰዱላህን (ረ.ዐ.) እና ጃዕፈሩል ጦያርን (ረ.ዐ.) የመሳሰሉ የአይናቸውን ማረፊያዎችን አጥተዋል፡፡ ሆኖም ግን ይህ ሁሉ ግፍ ቢደርስባቸውም እንኳን በሱራ ሁድ ላይ የሰፈረውና የሚከተለው አንቀጽ ያሳደረባቸውን ተጽእኖ ያህል አላሳደረባቸውም፡፡

﴿ فَٱسۡتَقِمۡ كَمَآ أُمِرۡتَ وَمَن تَابَ مَعَكَ ١١٢ ﴾ هود: ١١٢

"እንደታዘዝከውም ቀጥ በል፡፡ ከአንተ ጋር ያመኑትም (ቀጥ ይበሉ፡፡)..." (ሁድ፡112)

ይህ አንቀጽና ሌሎች ተጓዳኞቹ ከወረዱ በኋላ የአላህ መልእክተኛ በጭንቅላታቸው ላይ የተወሰኑ የፀጉር ዘለላዎች ሸብተዋል፡፡ "ሱረቱል ሁድ አሸበተኝ" ሲሉም ተደምጠዋል፡፡

የአላህን ሕግጋትን አክብሮ መገኘት እንዲህ ቀላል ጉዳይ ተደርጐ መታየት የለበትም፡፡ ምክንያቱም የነፍስን ዝንባሌ ማሸነፍና በእርሷ ላይ መንገስን ይጠይቃልና፡፡

﴿ فَأَمَّا مَن طَغَىٰ ﴿٣٧﴾ وَءَاثَرَ ٱلۡحَيَوٰةَ ٱلدُّنۡيَا ﴿٣٨﴾ فَإِنَّ ٱلۡجَحِيمَ هِيَ ٱلۡمَأۡوَىٰ ﴿٣٩﴾ وَأَمَّا مَنۡ خَافَ مَقَامَ رَبِّهِۦ وَنَهَى ٱلنَّفۡسَ عَنِ ٱلۡهَوَىٰ ﴿٤٠﴾ ﴾ النازعات: ٣٧ - ٤٠

"የካደ ሰውማ ቅርቢቱንም ሕይወት የመረጠ ገሃነም እርሷ በእርግጥ መኖሪያው ናት፡፡ በጌታው ፊት መቆምን የፈራ ሰውማ ነፍሱንም ከዝንባሌዋ የከለከለ ገነት እርሷ በእርግጥ መኖሪያው ናት፡፡" (አን-ናዚዓት፡37-40)

እንግዲህ የአል-ኢህሳንና ሙራቀባህ ደረጃዎች ላይ ለመድረስ ልባችንን ማዘጋጀትና ነፍሳችንንም ከዝንባልዋ ትጠራ ዘንድ ማለማመድ ይጠይቀናል፡፡ በቁርአን ሁኔታቸው እንደሚከተለው ተብሎ ከተወሳ ሰዎች መሆን ይገባናል፡-

﴿ وَنَفۡسٖ وَمَا سَوَّىٰهَا ﴿٧﴾ فَأَلۡهَمَهَا فُجُورَهَا وَتَقۡوَىٰهَا ﴿٨﴾ قَدۡ أَفۡلَحَ مَن زَكَّىٰهَا ﴿٩﴾ وَقَدۡ خَابَ مَن دَسَّىٰهَا ﴿١٠﴾ ﴾ الشمس: ٧ - ١٠

"በነፍስም ባስተካከላትም፣ አመጽዋንና ፍርሃቷንም ባሳወቃት (እምላለሁ)፡፡ (ከኃጢአት) ያጸዳት ሰው ዳነ፡፡ (በሐጢአት) የሸፈናትም ሰው በእውነት አፈረ፡፡" (አስ-ሽምስ ፡7-10)

የሚከተሉትን ነጥቦች በጥንቃቄ ማጤን ከምንፈልገው ደረጃ ላይ ሊያደርሰን ይችላል፡-

- ሐላል (የተፈቀደ) በሆነ የገቢ ምንጭ መተዳደር ላይ ትኩረት ማድረግ ያስፈልጋል፡፡
- የሰው ልጆችንና ሌሎች የአላህ ፍጡራንን ተገቢ መብቶች መጠበቅ፡፡
- ከጐህ መቅደድ በፊት ያሉትን ጊዜያት (አስሃር) አላህን ይቅርታ በመጠየቅና ወደ እርሱም በመመለስ ማሳለፍ፡፡
- አላህ የፈቀደውን መስራትና የከለከለውን መከልከል፡፡

- በተለያዩ ማኅበራዊ እንቅስቃሴዎች ውስጥ ኃላፊነትን መውሰድና መንቀሳቀስ፡፡
- ለአላህ ብሎ ሶደቃ (ምጽዋትን) ለተቸገሩ መስጠት፡፡
- አላህን ከልብ መለመንና መማፀን፡፡
- ኢሞራላዊ ድርጊቶችን እንደ ሃሜት፣ ራስወዳድነት፣ ስግብግብነት፣ አባካኝነት፣ ምቀኝነት፣ ምኞት ማብዛት፣ መናፍቅነት የመሳሰሉትን ባሕሪያት ማስወገድ፡፡
- ሞትን በተደጋጋሚ ማስታወስ እንዲሁም ሞት እስኪመጣ ድረስ አላህን መፍራት፡፡

የአላህ መልእክተኛ (ሰ.ዐ.ወ.) ለኢህሳንና ለሙራቀባህ ምርጥ የሆነ ተምሳሌታዊ ሕይወት መርተዋል፡፡ በዚህ ረገድ ታላቅ ሞዴል ሆነው ይገኛሉ፡፡

﴿ لَّقَدۡ كَانَ لَكُمۡ فِي رَسُولِ ٱللَّهِ أُسۡوَةٌ حَسَنَةٞ لِّمَن كَانَ يَرۡجُواْ ٱللَّهَ وَٱلۡيَوۡمَ ٱلۡأٓخِرَ وَذَكَرَ ٱللَّهَ كَثِيرٗا ٢١ ﴾ الأحزاب: ٢١

“ለእናንተ አላህንና የመጨረሻውን ቀን የሚከጅል ለሆነ ሰው አላህንም በብዙ ለሚያወሳ በአላህ መልእክተኛ መልካም መከተል አልላችሁ፡፡” (አል-አሕዛብ፡21)

ምዕራፍ አሥራ ሁለት

የሰውን ልጅ የሚመለከቱ እውነታዎች

የዓለማት ሁሉ ጌታ የሆነው ኃያሉ አላህ በዚህች ምድር ላይ ያለውን ነገር ሁሉ የሰውን ልጅ እንዲያገለግል ፈጠረው፡፡ ይህንንም ሃቅ በሚከተለው የቁርአን አንቀጽ በግልጽ ተጽፎ እናገኘዋለን፡-

﴿ وَسَخَّرَ لَكُم مَّا فِي ٱلسَّمَٰوَٰتِ وَمَا فِي ٱلۡأَرۡضِ جَمِيعٗا مِّنۡهُۚ إِنَّ فِي ذَٰلِكَ لَأٓيَٰتٖ لِّقَوۡمٖ يَتَفَكَّرُونَ ١٣ ﴾ الجاثية: ١٣

"ለእናንተም በሰማያት ያለውንና በምድርም ያለውን ሁሉ በመላ ከርሱ ሲሆን የገራላችሁ ነው፡፡ በዚህ ለሚያስተነትኑ ሕዝቦች ተዓምራት አለበት፡፡" (አል-ጃሲያህ፡13)

ይሁን እንጂ የሰው ልጅ ኃላፊነቶች እንደተጣሉበት አላህ ሲገልጽ እንዲህ ይላል፡-

﴿ أَيَحۡسَبُ ٱلۡإِنسَٰنُ أَن يُتۡرَكَ سُدًى ٣٦ أَلَمۡ يَكُ نُطۡفَةٗ مِّن مَّنِيّٖ يُمۡنَىٰ ٣٧ ﴾ القيامة: ٣٦ - ٣٧

"ሰው ስድ ሆኖ መትተውን ይጠረጥራልን? የሚፈስ ከሆነ የፍትወት ጠብታ አልነበረምን? " (አል-ቂያማህ፡36-37)

የጥበብና የማስተዋል ባለቤት የሆነው አላህ መለኮታዊውን ሕጉን ሲያወጣ በነፃነትና ኃላፊነትን በመሸከም መካከል ሚዛናዊነትን ጠብቆ ነው፡፡ ይህንንም ደንብ ለሰው ዘር ብቻ ሳይሆን ለመላው አጽናፈ ዓለም ጭምር እንዲሰራ አድርጐ ነው ያረቀቀው፡፡ ይህንንም በሚከተለው የቁርአን አንቀጽ በግልጽ ሲያስቀምጠው እናስተውላለን፡-

﴿ وَٱلسَّمَآءَ رَفَعَهَا وَوَضَعَ ٱلۡمِيزَانَ ٧ أَلَّا تَطۡغَوۡاْ فِي ٱلۡمِيزَانِ ٨ ﴾ الرحمن:٧ - ٨

“ሰማይንም ከፍ አደረገ፡፡ ሚዛንንም አኖረ፡፡ በሚዛን (ስትመዝኑ) እንዳታጐድሉ፡፡” (አር-ራሕማን፡ 7-8)

የተፈጠሩበትን ምስጢር ያልተገነዘቡ ከመለኮታዊው ድንጋጌ ጋር ተጣጥመው መጓዝ አይችሉም፡፡ ምክንያቱም እነርሱ ከመንፈሳዊው ዓለም ወዲህ ካለችው የቅርቢቱ ዓለም (ዱንያ) ጋር በጽኑ የተሳሰሩ ናቸውና፡፡ በሚያሳዝን ሁኔታም እንዲህ ዓይነት ሕዝቦች የሕይወታቸውን ኮንትራት የሚያገባድዱት በድንቁርናና በግዴለሽነት ተውጠው ነው፡፡

የእኛን የሰውን ልጆች ሕይወት ካስተዋልን በሁለት ተቃራኒ ዝንባሌዎች የተዋጥን መሆናችንን እንገነዘባለን፡፡ እነዚህም ተቃራኒ ዝንባሌዎች መልካምና እኩይ ይሰኛሉ፡፡ እነዚህን ዝንባሌዎች ይዘን እንድንፈጠርና እንድንኖር መጀመሪያውኑ የወሰነው ጌታችን አላህ ሲሆን ይህም ለፈተና ነው፡፡ የዓለማት ጌታ አላህ እንዲህ ይላል፡-

﴿ ٱلَّذِى خَلَقَ ٱلْمَوْتَ وَٱلْحَيَوٰةَ لِيَبْلُوَكُمْ أَيُّكُمْ أَحْسَنُ عَمَلًا ۚ وَهُوَ ٱلْعَزِيزُ ٱلْغَفُورُ ﴿٢﴾ ﴾ الملك: ٢

“ያ የትኛችሁ ሥራው ይበልጥ ያማረ መሆኑን ሊሞክራችሁ ሞትንና ሕይወትን የፈጠረ ነው፡፡ እርሱም አሸናፊው መሀሪው ነው፡፡” (አል-ሙልክ፡2)

በእርግጥ የሰው ልጅ ሥውሩም ሆነ ውጫዊው የአካል ክፍሎቹ በቀላሉ ለጥሩም ሆነ ለእኩይ ምግባር የሚውሉበት ጥንተ-ባሕሪ እንዳላቸው መገንዘብ ይቻላል፡፡ ለምሳሌ አእምሮን ብንወስድ ልክ በሁለቱም ጠርዞቹ እንደሚቆርጥ የተሳለ ሰይፍ ማለት ነው፡፡ ምክንያቱም ለኃጢአት ድርጊቶች የተገራ የመሆኑን ያክል ሰናይ ምግባራትንም ለመፈፀም እንደዚያው ዝግጁ ሆኖ የሚገኝ በመሆኑ ነው፡፡ ባማረ አቋም (አህሰኑ ተቅዊም) ተብሎ በአላህ የተገለፀውን ደረጃውን ለማንፀባረቅ የሰው ልጅ የማሰብ (ምክንያታዊ የመሆን) ችሎታውን ማሳየት ወይም መጠቀም ይኖርበታል፡፡ ያንን ማድረግ ካልቻለ ግን ከእንስሳትም (ከዱር አራዊት) በታች የተዋረደ ይሆናል፡፡

እናም የሰው ልጅ አስተሳሰቡን መግራትን መማር አለበት፡፡ ምክንያታዊ በመሆንና መለከታዊውን ሕግ በመተግበር ሕይወቱን ማሳመር የሚችል ሲሆን በውጤቱም የመልእክተኛውን (ሰ.ዐ.ወ.) የሕይወት ዘይቤ (ሱና) ሙሉ በሙሉ የሚተገብር አዲስ ፍጡር ወደመሆን ይሸጋገራል፡፡

ከታሪክ እንደምንገነዘበው ብዙ ኩራተኞችና ማን አለብኝ የሚሉ ሕዝቦች ሌሎች ሕዝቦችን ለመጨቆንና ለማንገላታት አእምሯቸውን ተጠቅመውበታል፡፡ ይህንንም ሲያደርጉ ይፈጽሟቸው የነበሩ እኩይ ድርጊቶቻቸውን ከሁሉም በላይ አሳማኝና ምክንያታዊ ድርጊቶች እንደሆኑ በመጥቀስ ይከራከሩ ነበር፡፡ ለምሳሌ ከማእከላዊ ኢሲያ የሞንጐሊያ የግጦሽ መሬቶች የተነሱት ጀንጊዝ ኻንና ተከታዮቹ እንደ አንበጣ መንጋ የሙስሊሙን ዓለም ሲወርሩት በእጃቸው ብዙ ደም ፈሶ ነበር፡፡ የጀንጊዝ ኻን ልጅ ሁላጉ ኻን የያኔዋን የአባሲዮች መናገሻ ከተማ ባግዳድን ሲወር አራት መቶ ሺህ የሚሆኑ የከተማዋን ነዋሪዎች ገድሏል፡፡ ከነሕይወታቸውም በኤፍራጦስ ወንዝ ውስጥ ጨምሯቸዋል፡፡ ይህንን ሲያደርግም የሕሊናው ድምጽ ምንም አልረበሸውም ነበር፡፡

የኢስላም ብርሃን ከመፈንጠቁ በፊት በአረቢያ ምድረ በዳና በዙሪያው የነበሩ ሕዝቦች ሴት ልጆቻቸውን ከነሕይወታቸው ሲቀብሩና የልባቸው ምት እስኪቆም ድረስ አፈር ሲመልሱባቸው ሕሊናቸውን ትንሽ እንኳን ቆንጠጥ አያደርጋቸውም ነበር፡፡

እነዚህ ሁሉ ሰዎች በሕዝቦች ላይ ያንን የመሰለ መከራ ሲያመጡ አእምሮና ስሜት ሳይኖራቸው ቀርቶ አልነበረም፡፡ ሆኖም ግን ወደ ተቃራኒ አቅጣጫ እንደሚሸከረከር መንኮራኩር (ማሽን) ወደ ተሳሳተ አቅጣጫ መጓዙን ስለመረጡ ብቻ ነው፡፡ ይህ ምሳሌ የሚያሳየን ሰዎች ስንባል ሁልጊዜም መለኮታዊ አመራር ሊለየን የማይገባና በስብእናችን ውስጥ መልካምና እኩይ ባሕሪያትን ቀላቅለን የምንኖር መሆኑን ነው፡፡ በየጊዜው የሚነሱ ነቢያት መለኮታዊ አመራርን ለሰው ልጆች ባያስተምሩና ራሳቸውም ምሳሌ በመሆን ባያሳዩ ኖሮ በምድር ላይ ንቅዘትና ብዙ ምስቅልቅል በተከሰተ ነበር፡፡ ያለመለኮታዊ አመራር

የሚባዝን ሰው ዝናብ አዘል ዳመና ሙሉ በሙሉ እንደጋረዳት ጀንበር የአእምሮውንና የሕሊናውን ብርሃን የተነጠቀ በመሆኑ ስሜት አልባ፣ የደነዘዘና ርህራሄ የሌለው ይሆናል፡፡

መለኮታዊ አመራር በሃቅ ሲሰፍን ተዓምር የሚፈጠር ለመሆኑ እንደምሳሌ የሚወስደው የነቢዩ (ሰ.ዐ.ወ.) በአረቢያ ምድር መነሳት ነበር። በዚያ የአረቢያ ምድር ይኖሩ የነበሩ ሕዝቦች ከአውሬ የማይሻሉ፣ ስብእናቸው የዘቀጠና የተዋረዱ ነበሩ፡፡ የአላህ መልእክተኛ (ሰ.ዐ.ወ.) መጡና በታሪክ አቻ ያልተገኘለትን ሰብአዊ ስልጣኔ መሠረቱ፡፡ ሴት ልጆቻቸውን የመጥፎ ገድ ምልክቶች ናቸው በማለት ከነሕይወታቸው ይቀብሩ የነበሩ ሕዝቦች ምናልባትም ከየትኛውም ሕዝብ እጅግ በላቀ ደረጃ የሴትን ልጅ መብት የሚያከብሩ ሩህሩሆች ለመሆን በቁ፡፡

ሌላው አስደናቂ ነገር ደግሞ ከነቢያቱ ቀጥሎ ልዩ የሆነ የአላህ ፍራቻና ሌሎች ብቃቶችን የተላበሱ የሆኑ ሰዎችን አላህ በየጊዜው መፍጠሩ ነው። እነዚህ ሲዲቅ (እውነተኞች) በመባል የሚታወቁ በሥነ-ምግባራቸውና ለአላህ ባላቸው ቀረቤታ የታወቁ ሰዎች ከነቢያቱ ሕልፈት በኋላ ሕዝቡ እንዳይጠምና ከቀናው ጐዳና እንዳይወጣ ታላቅ ተጋድሎ አድርገዋል፡፡ የሰውን ልጅ አላህ ሲፈጥረው ዝቅተኛ የሆነ የነፍሱን ዝንባሌና ቅንነቷን አንድ ላይ አድርጐ ነው፡፡ ይህ ለፈተና መሆኑ ይታወቃል፡፡ እንደሚታወቀው ደመነፍሳቸውን ብቻ ሁልጊዜም በመከተል የሚታወቁት እንስሳት ሲሆኑ፤ ቅን በመሆን ወለም ዘለም ሳይሉ ፈጣሪያቸውን የሚገዙት ደግሞ መላእክት ናቸው፡፡ የሰው ልጅ ግን የሁለቱንም ባሕሪያት አጣምሮ በመያዝ እስከ እለተ ሞቱ ድረስ ወዲያና ወዲህ ሲላጋ ይኖራል፡፡ ስለዚህም የሰው ልጅ ነፍስ ተከታታይ የሆነ መንጽሔ (ተዝኪያህ) እና ስልጠና (ተርቢያህ) ያስፈልጋታል፡፡

መልካም ሥነ-ምግባር የሌለውና ውስጡም ያልፀዳ የሆነ ሰው ልክ እንደ እንስሳ፤ እንዲያውም ከዚያም የባሰ እንደሆነ አላህ በቁርአን ነግሮናል፡፡

﴿ وَلَقَدۡ ذَرَأۡنَا لِجَهَنَّمَ كَثِيرٗا مِّنَ ٱلۡجِنِّ وَٱلۡإِنسِۖ لَهُمۡ قُلُوبٞ لَّا يَفۡقَهُونَ بِهَا وَلَهُمۡ أَعۡيُنٞ لَّا يُبۡصِرُونَ بِهَا وَلَهُمۡ ءَاذَانٞ لَّا يَسۡمَعُونَ بِهَآۚ أُوْلَٰٓئِكَ كَٱلۡأَنۡعَٰمِ بَلۡ هُمۡ أَضَلُّۚ أُوْلَٰٓئِكَ هُمُ ٱلۡغَٰفِلُونَ ١٧٩ ﴾ الأعراف: ١٧٩

"ከጋኔንም ከሰዎችም ብዙዎችን ለገሃነም በእርግጥ ፈጠርን፡፡ ለእነርሱ የማያውቁባቸው ልቦች አሏቸው፡፡ ለእነርሱም የማያዩባቸው አይኖች አሏቸው፡፡ ለእነርሱም የማይሰሙባቸው ጆሮዎች አሏቸው፡፡ እነዚያ እንደ እንስሳዎች ናቸው፡፡ ይልቁንም እነርሱ በጣም የተሳሳቱ ናቸው፡፡ እነዚያ ዘንጊዎቹ እነርሱ ናቸው፡፡" (አል-አዕራፍ፡179)

ተራሮች ሊሸከሙት እንደሚከብዳቸው በመናገር የተውትን አማና (ዲን) የሰው ልጅ ሊሸከመው በመፍቀድ ተረክቧል፡፡ ይህንንም ሲያደርግ የተሰራበት ድርና ማግ ከሁለት ተቃርኖ ባሕሪያት የተዋቀረ መሆኑን እያወቀ ነው፡፡ በአንድ በኩል ሰናይ ምግባራትን በመፈጸም የአላህን ሞገስ ለማግኘትና በደረጃዎች ከፍ ለማለት የሚያስችለው ተሰጥኦ አለው፡፡ በሌላ በኩል የስሜቱን ነበልባል ማዳፈን ተስኖት በወላፈኑ እየተገፋ ሄዶ በሚፈጽማቸው እኩይ ተግባራት ከእንስሳትም በታች የሚዋረድበት ባህሪ አለው፡፡

ሰዎች በኢስላማዊ ሥነ-ምግባራት የማይታነፁ ከሆኑ ውስጣቸው የጠለሸና ሰላም የራቃቸው በመሆን የአውሬነትን ፀባይ ይላበሳሉ፡፡ በመሆኑም የተወሰኑት እንደቀበሮ ተንኮለኞች ሲሆኑ ሌሎቹ ደግም እንደ ጅብ ሆዳሞች ይሆናሉ፡፡ ጥቂቶቹ እንደ ጉንዳን ሰርተው የማይጠግቡ የሥራ ሱሰኞች ሲሆኑ የተወሰኑት እንደ እባብ መርዘኞች ይሆናሉ፡፡ አንዳንዶቹ በሰው ላይ ተጣብቀው እንደ መዥገር ወይም አልቅት ደም ይመጥጣሉ፡፡ ሌሎቹ ደግሞ ለማስመሰል ፈገግ እያሉ ከጀርባ ጓደኛቸውን በጨቤ ይወጋሉ፡፡ ሰዎች የኃይማኖትን ሕግጋት ችላ ብለው በራሳቸው መንገድ የሕይወትን አቀበት መግፋታቸውን እስከቀጠሉ ድረስ ባንዱ ወይም በሌላው ባሕሪያቸው የአውሬነት ፀባይ እንደማይለቃቸው የታወቀ ነው፡፡ በእንዲህ አይነቱ ሁኔታ ላይ ከሚገኙ ሰዎች የተወሰኑት

አንድ ዓይነት የእንስሳ ባህሪ ብቻ ይኖራቸው ይሆናል። ሌሎቹ ደግም ብዙ ዓይነት።

እንግዲህ ሰናይ ምግባር ያለውም ሆነ የመጥፎ ምግባር ባለቤት በዚህች ዓለም ላይ ጐን ለጐን ሆነው ይኖራሉ። ይህን ሁኔታ ከአንድ ጨካኝና አይምሬ የሆነ አውሬ ጋር በአንድ አካባቢ ከምትኖር ሚዳቋ ጋር ማነጻጸር ይቻላል። አንዳንድ ጊዜ መጥፎ የሆነ ሰው ቸርና ለጋስ ከሆነው ሰው ጋር ጐን ለጎን ይኖራል። የመልአክ የመሰለ ያማረ ፀባይ ያለው የሰይጣን ቡችላ ከሆነው የለየለት አረመኔ ጋር አብሮ ይሰራል።

በተቃርኖዎች የተሞላው ይህ ዓለም ለሰው ልጆች የፈተና ቦታ መሆኑ ግልጽ ነው። እንደዚያም ቢሆን ይህን ፈተና አልፈን የፈጣሪያችንን ሞገስ እንድናገኝ ይፈለጋል።

የሰው አካል የተፈጠረው ምድር ከያዘቻቸው የተለያዩ ንጥረ ነገሮች ነው፡ ፡ የዚህ ዓለም ሩጫውን ሲጨርስም ወደ አፈር ይመለሳል። ነፍሳችንን ከክፋትና እኩይ ዝንባሌዋ በማንጻት (ተዝኪያህ) ደረጃዋን ከፍ ካላደረግነው የመጪውን ዓለም ታላላቅ ፈተናዎች ማለፋ ያጠራጥራል። አላህ እንዲህ ይላል፡-

﴿ وَنَفۡسٖ وَمَا سَوَّىٰهَا ٧ فَأَلۡهَمَهَا فُجُورَهَا وَتَقۡوَىٰهَا ٨ قَدۡ أَفۡلَحَ مَن زَكَّىٰهَا ٩ وَقَدۡ خَابَ مَن دَسَّىٰهَا ١٠ ﴾ الشمس: ٧ - ١٠

"በነፍስም ባስተካከላትም አመጽዋንና ፍርሃቷንም ባሳወቃት (አምላክ እምላለሁ)። (ከኃጢአት) ያጠራት ሰው ፍላጐቱን በእርግጥ አገኘ። (በኃጢአት) የሸፈናትም ሰው በእውነት አፈረ።" (አሽ-ሸምስ፡7-10)

ምዕራፍ አሥራ ሦስት

ከራስ ይልቅ ሌሎችን ማስቀደም

(አል-ኢዛር)

አብደላህ ኢብን ጃዕፈር (ረ.ዐ.) በጉዞ ላይ እያለ ከአንድ የቴምር ማሳ አጠገብ አረፍ አለ፡፡ የዚያ የቴምር አዝመራ ተንከባካቢ ደግሞ ጥቁር ባሪያ ነበር፡፡ ይህ በእንዲህ እያለም የሆነ ሰው ለዚያ ጥቁር ባሪያ ሶስት ቂጣዎችን ሰጠው፡፡ በዚያው ሰዓት የተራበ መሆኑ የሚያስታወቅ ውሻ ወደ ባሪያው መጣ፡፡ ከዚያም ሰውየው አንዷን ቂጣ ሰጠው፡፡ ውሻውም በፍጥነት ዋጥ አደረጋት፡፡ እንደገና ሁለተኛዋን ደገመለት፡፡ ውሻው አሁንም በፍጥንት አጠናቀቃት፡፡ አሁንም የቀረችውን አንዷን ሰጠው፡፡ ውሻው ይህችንም ዋጥ ሲያደርጋት አልዘገየም፡፡ አብደላህ ይህን ሁሉ ሲያስተውል ከቆየ በኋላ ለዚያ ምስኪን የሚከተለውን ጥያቄ አቀረበለት፡-

“ለመሆኑ ምን ያህል ነው የሚከፈልህ?”

“ያየሃቸውን ሶስት ቂጣዎች በቀን አገኛለሁ፡፡”

አብደላህ መደነቁን አላቆመም፡፡ ከዚያም እንዲህ አለው፡- “ታዲያ ሁሉንም ለውሻው ለምን ሰጠኸው?”

“ብዙውን ጊዜ በዚህ አካባቢ ውሻ አይታይም፡፡ ይህ ውሻ ከሩቅ ሥፍራ መሆን አለበት የመጣው፡፡ እናም እንዲህ እንደተራበ እንዲሄድ አልፈለግሁም፡፡”

አብደላህ ጥቃቄውን ቀጠለ፡-

“ለመሆኑ ዛሬ ምን ልትመገብ አስበሃል?”

“እታገሳለሁ፡፡ ምክንያቱም የዛሬውን ቀለቤን እንዳየኸው ለውሻው አሳልፌ ሰጥቼዋለሁ፤ ለዚያ የተራበ የአላህ ፍጡር፡፡”

አብደላህ እንዲህ አለ፡-

“ሱብሃነሏህ! ሰዎች እኔን ቸር ነው ይላሉ፡፡ ሆኖም ግን ይህ ባሪያ ከእኔ በጣም የሚበልጥ ለጋስ ነው፡፡”

አብደላህ የቴምሩን ማሣ ከነባሪያው ገዛው፡፡ ለባሪያውም ነጻነቱን አጐናጸፈው፡፡ ማሳውንም ይተዳደርበት ዘንድ አበረከተለት፡፡ (ይህን ታሪክ ኢማም ገዛሊ “ኪሚያ ሰዓዳህ” በተባለው ድርሳናቸው ዘግበውታል፡፡)

ይህን የመሰሉ የፀአዳ ነፍስ ባለቤቶችንና ሩህሩህ ግለሰቦችን በብዛት ያፈለቀው ኢስላም ዘካን (የግዴታ ምጽዋትን) በሃብታሞች ላይ ደንግጓል፡ ፡ ይህም በመሆኑ ሃብታሞች ያላቸውን ነገር ከድሆች ጋር ተካፍለው እንዲበሉና እንዲተዛዘኑ መንገድ ጠርጓል፡፡ በዚህ ፍትሃዊ ሥርአት ውስጥ የሚኖሩ ድሆችም ድህነታቸው ሳያሳቅቃቸውና ፈጣሪያቸውንም ሳያማርሩ እንዲኖሩ ሆኗል፡፡ እንዲህ መሆኑ ደግሞ ብዙ ሃብት ጨብጠው በሚገኙ ጥቂት ሃብታሞችና ብዙሃን ድሆች መካከል የጐሪጥ መተያየት፣ ቅናት፣ ብሎም አመጽና ወንጀልን በእጅጉ በመቀነስ ሰላም የሰፈነበት ውሎና አዳርን አስገኝቷል፡፡

ፍቅርንና መተዛዘንን የተላበሱ ቀደምት የኢስላም ትውልድ አባላት ይህን ተረት የሚመስል ሕይወት በገሃዱ ዓለም ኖረውት አልፈዋል፡፡ በምድር ላይ የነበረው የሰዎች መተሳሰብ ጫፍ የደረሰ ስለነበርም በአምስተኛው ኸሊፋ ዑመር ኢብን አብዱልአዚዝ ዘመን ሰዎች ዘካ ይዘው የሚቀበላቸው እስከማጣት ደርሰዋል፡፡ ይህ የሚያሳየው ሰዎች የፈጣሪያቸውን መንገድ ወለም ዘለም ሳይሉ ከያዙ የሰማያትና የምድር በረከቶች ሁሉ እንደሚከፈቱላቸው ነው፡- ሃያሉ አላህ እንዲህ ይላል፡-

﴿ وَلَوۡ أَنَّ أَهۡلَ ٱلۡقُرَىٰٓ ءَامَنُواْ وَٱتَّقَوۡاْ لَفَتَحۡنَا عَلَيۡهِم بَرَكَٰتٖ مِّنَ ٱلسَّمَآءِ وَٱلۡأَرۡضِ وَلَٰكِن كَذَّبُواْ فَأَخَذۡنَٰهُم بِمَا كَانُواْ يَكۡسِبُونَ ٩٦ ﴾ الأعراف: ٩٦

“የከተማዋም ሰዎች ባመኑና በተጠነቀቁ ኖሮ በእነርሱ ላይ ከሰማይም ከምድርም በረከቶችን በከፈትንላቸው ነበር፡፡ …” (አል-አዕራፍ፡96)

ኢስላም የገንዘብ አቅም ባላቸው ተከታዮቹ ላይ ለድሆቻቸው የምትሰጥ የሆነችን ዘካ ግዴታ ሲያደርግ በፈቃደኝነትና የአላህን ውዴታ ፈልገው ገንዘባቸውን ለመልካም ሥራዎች ወጪ የሚያደርጉ ሰዎችንም በተለያዩ አጋጣሚዎች ማነሳሳቱን ገፋበት፡፡ ምክንያቱም ሰዎች የአላህን አንድነት በልባቸው አምነው በምላሳቸው ካወጁ በኋላ የኃይማኖቱ ዋነኛ ግብ የሰው ልጅ ምድራዊ ሕይወት በተቻለ አቅም ሰላም የሰፈነባት እንዲሆን ማድረግ ነው፡፡ እውነተኛ ሰላምና ፀጥታ የሚገኘው ደግሞ ከስግብግብነት የፀዱና የሌሎች ሰዎችን ምቾትና ደህንነት ከራሳቸው አስበልጠው የሚመኙ ሰዎች ሲፈልቁ ነው፡፡ ይህም የአል-ኢህሳን ጽንሰሃሳብ እንጂ ሌላ አይደለም፡፡

እዝነት ማለት በአንድ እውነተኛ ሙስሊም ልብ ውስጥ ምንጊዜም የሚነድ የፍቅር ነበልባል ነው፡፡ አማኝ የሆነ ሰው ቸር፣ ትሁትና ሌሎችን የሚያገለግል ቅንነት የተሞላ ፍጡር ነው፡፡ አማኝ የሆነ ሰው በሌሎች ሰዎች ልብ ውስጥ ደስታና ሰላም እስከበራ ድረስ ማንኛውንም መስዋእትነት ለመክፈል የሚሰለፈው በፊት ለፊት ነው፡፡ በሌላ በኩል ደግሞ አማኞች በማንኛውም አሳዛኝ ነገር፣ ችግርና መከራ ወቅት ገንቢ የሆነ ሚናን በጎብረተሰቡ ውስጥ ይጫወታሉ፡፡ ምንጊዜም የሚቆሙት ከግፉአኑ፣ በሃዘን ከተደቆሱት፣ ከተጣሉትና ከተረሱት፣ ተስፋም ካጡት ጐን ነው፡፡

የሰው ልጅ ሞራላዊ ብቃቶች የተሟሉ የሚሆኑት የቁርአንን አስተምህሮት ወደ ተግባር ሲቀይር ነው፡፡ ለዚህም ነው የቁርአንን የመጀመሪያ ገጽ ስንገልጥ “እጅግ በጣም ሩህሩህ፤ በጣም አዛኝ” የሚሉ ቃላትን የምናነበው፡፡ የእኛ ጌታ አላህ ከሁሉም በላይ ሩህሩህና ከአዛኞች ሁሉ የበለጠ አዛኝ እንደሆነ ሲገልጽልን፤ ይህን አዛኝ የመሆንን ባሕሪ እስከመጨረሻው ጥግ ድረስ ልናጐለብተው ይገባናል ማለት ነው፡፡ አላህን ከልብ የማፍቀር ውጤት የሚንፀባረቀው ለፍጡራኑ ሩህሩህና አዛኝ በመሆን ነው፡፡ የአላህ ወዳጅ የሆነ ሰው መስዋእት መክፈልን እንደ ዋነኛ የደስታ ምንጭ ይወስደዋል፡፡

ስለሆነም ሶደቃ (ምጽዋት) ለአላህ ፍጡራን መስጠት እርሱን የማፍቀር መገለጫ ነው ማለት ነው፡፡ እርግጥ ነው ብዙ የሶደቃ (ምጽዋት) አይነቶች አሉ፡፡ ብዙውን ጊዜ እኛ ሰዎች ስለ ምጽዋት ስናስብ ትዝ የሚለን ገንዘብ ወይም ምግብ ለተቸገሩት መስጠት ነው፡፡ ሆኖም ግን የአላህ መልእክተኛ (ሰ.ዐ.ወ.) እንዲህ ብለዋል፡-

“ፀሐይ በወጣችበት ቀን ሁሉ የማንኛውም ሰው መገጣጠሚያዎች ሶደቃ (ምጽዋት) ማቅረብ አለባቸው፡፡ በሁለት ሰዎች መካከል በትክክል ብትፈርድ ሰደቃ ነው፡፡ አንድን ሰው በመጓጓዣው ላይ ብታወጣው ወይም እቃውን ብትጭንለት ሰደቃ ነው፡፡ መልካም ንግግር ሰደቃ ነው፡፡ እያንዳንዷ ወደ ሶላት የምትመራ እርምጃ ሰደቃ ናት፡፡ ከመንገድ ላይ ጐጂ ነገሮችን ማስወገድም ሰደቃ ነው፡፡”

የሰደቃ (ምጽዋት) የመጨረሻው ደረጃ ከራስ ይልቅ ለሌሎች ቅድሚያ የመስጠት ጽንሰ ሃሳብ የሚንፀባረቅበት አል-ኢእሳር ነው፡፡ አል-ኢእሳርን ተግባራዊ የሚያደርጉት በእምነታቸው የበሰሉና ታላቅ ደረጃ ላይ የደረሱ ናቸው፡፡ ስለሆነም እንዲህ ዓይነት ባሕሪን ለማንፀባረቅ የሚቻለው ጥሩ በሆነ ልብና ነፍስ ሲሆን እውነተኛ ኢእሣር ድህነትን አያስፈራም፡፡

የአል-ኢሣር (ከራስ ይልቅ ሌሎችን ማስቀደም) በነብዩና በተከታዮቻቸው ዘመኖች ፈክቶ ነበር ማለት ይቻላል፡፡ እርግጥ ነው ሁሉም በዚያ ዘመን የነበረ ሰው እንዲህ ዓይነቱን ባሕሪ ተላብሶ ነበር ማለት ትክክል ላይሆን ይችላል፡፡ ሆኖም ግን ይህ ባህሪ በብዛትና በስፋት ይንፀባረቅ የነበረው በዚያ ወርቃማ ትውልድ ዘመናት መሆኑ እውነት ነው፡፡

አቡ ሁረይራ (ረ.ዐ.) ባወሩት ሐዲስ አንድን ሰው የአላህ መልእክተኛ (ሰ.ዐ.ወ.) ከባለቤቶቻቸው ወደ አንዷ ምግብ ይኖራት እንደሆነ ጠይቆ እንዲመጣ ላኩት፡፡ ሆኖም ግን ባለቤታቸው “እርስዎን በላከዎት አላህ እምላለሁ፤ ከውሃ በስተቀር ምንም የለኝም፡፡” በማለት ገለፀች፡፡ በዚህ ዓይነት ወደሌሎቹ ባለቤቶቻቸው ቢልኩም ሁሉም ተመሳሳይ መልስ ሰጧቸው፡፡ ከዚያም ወደባልደረቦቻቸው ሄዱና “ከእናንተ ማንኛችሁ ነው ይህን እንግዳየን የሚያስተናግድልኝ?” በማለት ጠየቁ፡፡ ከአንሷር

(የመዲና) ሰዎች አንዱ “የአላህ ነቢይ ሆይ! የእኔ እንግዳ ይሆናል፡፡” በማለት ያንን ድሃ ሰው ይዞት ወደቤቱ ሄደ፡፡ ቤት እንደደረሱም ሰውየው ባለቤቱን “አንዳች የሚበላ ነገር የለሽምን?” በማለት ጠየቃት፡፡ “የለኝም፤ ያለው ለልጆቹ ብቻ የሚሆን ምግብ ነው” በማለት መልስ ሰጠችው፡፡ ሰውየው ባለቤቱን “ልጆቹ ምግቡን እንዲረሱ አድርጊያቸው፡፡ እንቅልፋቸው ሲመጣም አስተኚያቸው” በማለት አዘዛት፡፡ ቀጠለና “ምግቡን እንዳቀረብሽ በድንገት እንደሆነ አስመስለሽ መብራቱን አጥፊው። እኛም አብረነው እየበላን ስለሚመስለው እንግዳው ረሃቡን ያስታግሳልና፡፡” አላት፡፡ ባልና ሚስቱ በተመካከሩት መሠረት እንግዳው ሰው ምግብ ወደሚበላበት ቦታ እንደደረሰ ሁለቱም ልክ አብረው እንደሚመገቡ በመምሰል ከእርሱ ጋር ተቀመጡ፡፡ መብራቱ የጠፋ በመሆኑ እንግዳው ሰው እነርሱም አብረውት እየተመገቡ መሆኑን በማመን እስከሚጠግብ ድረስ በላ፡፡ እነርሱ ግን ባዶ አንጀታቸውን ረሃብ እያኝካቸው ወደመኝታቸው ሄዱ፡፡ ሲነጋም ሰውየውና እንግዳው ወደመስጊድ ሄዱ፡፡ ነብዩ (ሰ.ዐ.ወ.) ባልደረባቸውን እንዳዩት አንዲህ አሉት፡- “ባለፈው ምሽት እንግዳችሁን ለማስተናገድ ያደረጋችሁትን ነገር አላህ ወዶላችኋል፡፡” (ቡኻሪና ሙስሊም)

ከራስ ይልቅ ሌሎችን ማስቀደም (አል-ኢእሣርን) ተግባራዊ ለማድረግ ሁል ጊዜም ታላላቅና ብዙ ወጪ የሚጠይቁ ነገሮችን ብቻ ማሰብ አይኖርብንም፡፡ እቤታችን ውስጥ እንደቀልድ ለዲኮሬሽን የምናወጣውን፣ ጫማችንን የምናስቀባበትን፣ አለያም ደግሞ ለጋዜጣና ለመጽሄት መግዣ የመደብነውን ወጪ የራሳችንን ፍላጐት ገድበን ለባለበት ወንድማችን መስጠት ነው፡፡

ከራስ ይልቅ ሌሎችን ማስቀደም (አል-ኢእሣር) ቸር ከመሆንም ዘለል ያለ ነው፡፡ ምክንያቱም ቸር መሆን ማለት ከራስ አስፈልጐት የሚተርፍን ሃብት ለሌሎች መስጠት ነውና፡፡ ሌሎች ሰዎችን ከራሳችን ይበልጥ ስናስቀድም ግን ለእኛ የሚያስፈልገንን ነገር ይቅርብን ብለን በመሆኑ ከዚያኛው ይልቃል፡፡ ኢሣር ብለን ለምንጠራው ቅዱስ ተግባር

እጅግ ከፍተኛ መስዋእትነት በመሆኑ ምንዳውም የዚያኑ ያክል ታላቅ ነው ማለት ይሆናል፡፡

የአንሷሮች (የመዲና) ሰዎች ሙሃጂሮችን በመልካም ሁኔታ የተቀበሏቸው ሲሆን ከራሳቸው ፍላጐት ይበልጥ ለእነርሱ ሲጨነቁ አላህ አየ፡፡ ይህን የሰብአዊነት የመጨረሻ እርከን ተግባራዊ ያደረጉትን ሰዎች እንደሌሎች ተራ ክስተቶች በቀላሉ ሊያልፈው አልፈለገም፡፡ የሚከተለውን የቁርአን አንቀጽ አወረደ፡-

﴿ وَٱلَّذِينَ تَبَوَّءُو ٱلدَّارَ وَٱلۡإِيمَٰنَ مِن قَبۡلِهِمۡ يُحِبُّونَ مَنۡ هَاجَرَ إِلَيۡهِمۡ وَلَا يَجِدُونَ فِي صُدُورِهِمۡ حَاجَةً مِّمَّآ أُوتُواْ وَيُؤۡثِرُونَ عَلَىٰٓ أَنفُسِهِمۡ وَلَوۡ كَانَ بِهِمۡ خَصَاصَةٞۚ وَمَن يُوقَ شُحَّ نَفۡسِهِۦ فَأُوْلَٰٓئِكَ هُمُ ٱلۡمُفۡلِحُونَ ٩ ﴾ الحشر: ٩

“እነዚያም ከበፊታቸው አገሪቱን መኖሪያ ያደረጉት እምነትንም የለመዱት ወደነርሱ የተሰደዱትን ሰዎች ይወዳሉ፡፡ (ስደተኞቹ) ከተሰጡትም ነገር በልቦቻቸው ውስጥ ቅሬታን አያገኙም፡፡ በእነርሱ ላይ ችግር ቢኖርባቸውም በነፍሶቻቸው ላይ ሌላውን ይመርጣሉ፡፡ የነፍሱንም ንፍገት የሚጠብቅ ሰው እነዚያ እነርሱ ምኞታቸውን አግኚዎች ናቸው፡፡” (አል-ሐሽር፡9)

በአንድ ወቅት ገናናው ኡመር ኢብን አል-ኸጣብ (ረ.ዐ.) ታሪካዊውን የእየሩሳሌም (ቁድስ) ጉዞ አድርገው ነበር፡፡ በዚያን ጊዜም አንድን ግመል ከአገልጋያቸው ጋር በየተራ እየጋለቡ ነበር የሚጓዙት፡፡ እንደአጋጣሚ ሆኖ ከከተማዋ መግቢያ አካባቢ ሲደርሱ ተራው የአገልጋያቸው ሆነ፡፡ እናም አገልጋያቸው ከግመሏ ላይ ሆኖ እርሳቸው ደግሞ በእግር ይጓዙ ነበር፡፡ ይህ ዓይነተኛ የአል-ኢእሣር ተምሳሌት ነው፡፡ ሁኔታው የሚያሳየው ሰደቃ (ምጽዋት) ሁልጊዜም ቢሆን ገንዘብን መቸር አለመሆኑን ነው፡፡ ይህ ከላይ ያየነው የኸሊፋው ተግባር ራሱ የሰደቃ (ምጽዋት) ክፍል ነውና፡፡

በነፍስ ላይ ሌላውን መምረጥ (አል-ኢሣር) ማለት የሰደቃ (ምጽዋት) የመጨረሻው ደረጃ ሲሆን ራስን ከአንድ ነገር ሙሉ በሙሉ አቅቦ ወንድሙን ማስቀደም ማለት ነው፡፡ ይህም ልዩ የሆነ ባህሪ ሲሆን የነቢያት፣ የተከታዮቻቸው፣ የአላህ ወዳጆችና የሳሊሆች መንገድ ነው፡፡

የሚከተለው ክስተት ደግሞ አሊን (ረ.ዐ.) እና ተወዳጅዋን ባለቤታቸውን ፋጢማ ቢንት ሙሐመድን (ረ.ዐ.) የሚመለከት ነው፡፡ ኢብን አባስ (ረ.ዐ.) እንዳወሩት ሃሰንና ሁሴን የተባሉት ልጆቻቸው ታመው በመዳናቸው ምክንያት አላህ ካዳናቸው ሶስት ቀናትን ለመጾም ነዝር (ስለት) አደረጉ፡፡ ያንን ለመሙላት ሁለቱም ጾሙ፡፡ የመጀመሪያውን ቀናቸውን ጾም ለማፍጠር ፋጢማ (ረ.ዐ.) ከገብስ የተሰራ ምግብ አቀረበች፡፡ በዚያው ቅጽበት ሊመገቡ እንደተዘጋጁ በሩ ተንኳኳ፡፡ በሩን ያንኳኳው በጣም የተራበ ድሃ ሰው ነበር፡፡ ቤተሰቡ ለዚህ ለተራበ ሰው ያንን የማፍጠሪያ ምግብ ለአላህ ብለው በመስጠት እነርሱ ግን በውሃ አፈጠሩ፡፡ በቀጣዩ ቀንም እንዲሁ ለማፍጠር ሲዘጋጁ አንድ የቲም (ወላጅ አልባ) ልጅ ከቤታቸው አጠገብ በመቆም እርዳታቸውን እንደሚሻ ገለፀ፡፡ እነርሱም ታላቅ የሆነን ትእግስት በመታገሥና እርሱን ከነፍሳቸው በማስቀደም ምግባቸውን አሳልፈው ሰጡት፡፡

ይህ አምሳያና ብጤ የሌለው ደግነት አላህ እንዲህ በማለት ካሞገሰው መልካም ተግባር ጋር ይመሳሰላል፡-

﴿ وَيُطْعِمُونَ ٱلطَّعَامَ عَلَىٰ حُبِّهِۦ مِسْكِينًا وَيَتِيمًا وَأَسِيرًا ﴿٨﴾ إِنَّمَا نُطْعِمُكُمْ لِوَجْهِ ٱللَّهِ لَا نُرِيدُ مِنكُمْ جَزَآءً وَلَا شُكُورًا ﴿٩﴾ إِنَّا نَخَافُ مِن رَّبِّنَا يَوْمًا عَبُوسًا قَمْطَرِيرًا ﴿١٠﴾ فَوَقَىٰهُمُ ٱللَّهُ شَرَّ ذَٰلِكَ ٱلْيَوْمِ وَلَقَّىٰهُمْ نَضْرَةً وَسُرُورًا ﴿١١﴾ ﴾ الإنسان: ٨ - ١١

“ምግብንም ከመውደዳቸው ጋር ለድሃ፣ ለየቲምም፣ ለምርኮኛም፣ ለእስረኛም ያበላሉ፡፡ የምናበላችሁ ለአላህ ውዴታ ብለን ብቻ ነው፡፡ ከእናንተ ዋጋንም ማመስገንንም አንፈልግም፡፡ እኛ (ፊትን) የሚያጨፈግግን ብርቱ ቀን ከጌታችን እንፈራለንና (ይላሉ)፡፡ አላህም

የዚያን ቀን ክፉት ጠበቃቸው፡፡ (ፊታቸው) ማማርንና መደሰትንም ገጠማቸው፡፡" (አድ-ደህር፡ 8-11)

ቸር በመሆን፣ ስጦታን ያለልክ በመስጠትና ከራስ ይልቅ ሌላውን በማስቀደም ነብዩን (ሰ.ዐ.ወ.) የሚስተካከላቸው አንድም አይገኝም፡፡ ቸርነታቸው ያለቅጥ ታላቅ ከመሆኑ የተነሣ ለማመን ይከብድ ነበር፡፡ በእርግጥም እርሳቸው በእውቀታቸው፣ በኃብታቸው፣ በነፍሳቸው፣ በአላህ መንገድ ራሳቸውን በመሰዋት፣ ሰዎችን ወደቀናው መንገድ በማመላከት፣ የተራቡትን በማብላት፣ መሃይማንን በመምከር፣ የተቸገሩትን በመርዳትና ሸክማቸውን ከጫንቃቸው ላይ በማንሳት ያደረጉት ቸርነት ድካ አልነበረውም፡፡

ሱፍያን ኢብን ኡመያ በጣም የታወቀ፣ ቀንደኛ ከሆኑት የቁረይሽ ከሃዲያን አንዱና ግንባር ቀደም የነብዩ (ሰ.ዐ.ወ.) ጠላት ነበር፡፡ በሁነይን ዘመቻ ወቅት ላይላዩን የሰለመ መስሎ ከነብዩ (ሰ.ዐ.ወ.) ጋር ዘመቻ ወጣ፡፡ ውስጡ ግን እንዳኮረፈና በቀድሞው እምነቱ ላይ እንደጸና ነበር፡፡ ጂራና በተባለው አካባቢ ከጦርነቱ የተሰበሰበ የተወሰነ ምርኮ ተቀምጦ ሳለ ሰፍዋን በመደነቅ ያስተውል ጀመር፡፡ በዚህ ጊዜ ነብዩ (ሰ.ዐ.ወ.) ሰፍዋንን እንዲህ አሉት፡-

"ይህን ነገር ትፈልገዋለህን?"

መልሱ "አዎን" መሆኑን የተገነዘቡት ነቢይ ለአፍታም ሳያቅማሙ "ውሰደው፤ ሁሉም ያንተ ነው፡፡" አሉት፡፡ በዚህ ጊዜ ሰፍዋን ሸሃዳ በማለት ሙስሊም ሆነ፡፡ ከዚያም እንዲህ አለ፡-

"ይህን አይነት ችሮታ የምታደርግ ልብ የነቢይ ልብ እንጂ ሌላ አይደለችም፡፡" (ኢስላም ታሪኺ፡174)

ከራስ ይልቅ ሌላውን ማስቀደም (ኢሣር) የቸርነት አንፀባራቂ ገጽታ ነው። ልብንና መንፈስን በሚያጥለቀልቅ እንዲህ ዓይነት የፍቅር መገለጫ ድርጊት እጅጉን ደምቀው ይታዩበት የነበሩት የነብዩ (ሰ.ዐ.ወ.) ባልደረቦችና ከእነርሱም በኋላ የመጡት ደጋግ ሰለፍ አባቶች ነበሩ፡፡

በዚህ ድርጊታቸው የተነሳ ሌላው ቀርቶ በክህደታቸው ፀንተው የቆዩና እንደ አለት የጠጠረ ልብ የነበራቸው ሰዎች ወደ ኢስላም መግባት ችለዋል፡፡ በተመሳሳይ ሁኔታ ከራስ ይልቅ የወንድምን ጉዳይ ማስቀደምን በአንክሮ ያስተዋሉ ጠላቶች ወዳጅ ሆነዋል፡፡ የአላህ መልእክተኛ (ሰ.ዐ.ወ.) አንድን ነገር ተጠይቀው ከእርሳቸው ዘንድ እስካለ ድረስ አይሆንም ብለው አያውቁም፡፡ በአንድ ወቅት ዘጠና ሺህ የሚሆን ዲርሃም ከእጃቸው ገብቶ ነበር፡፡ ከምንጣፍ ላይ አደረጉትና የቸገረውና ገንዘብ ያስፈለገው ሁሉ እያነሳ እንዲወስድ አደረጉ፡፡

የመልካም ሥራ (ቢር) ደረጃ የት ድረስ

በቁርአን “ቢር” ተብሎ የሚጠራው በጐ ሥራ ልክ እንደ አል-ኢእሣር ሁሉ የምጡቅ ባህሪ መገለጫ ነው፡፡ የሁሉም ምርጥ ባህሪያት ተምሳሌት የሆኑት ነብዩ (ሰ.ዐ.ወ.) በዚህም ቢሆን አምሳያ አልነበራቸውም፡፡ የሚከተለው ትረካ የሚያሳየን የአላህ መልእክተኛ በጣም ትንሽ በምትባል ነገር እንኳን ሳይቀር አንድም ቀን ከሌላው ይልቅ ነፍሳቸውን ከሌሎች አስቀድመው እንደማያውቁ ነው፡፡

አንድ እለት ነብዩ (ሰ.ዐ.ወ.) ሁለት ሲዋኮችን (መፋቂያ) አዘጋጁ፡፡ አንደኛው የተስተካከለና እንከን የማይወጣለት ሲሆን ሌላኛው ደግም አባጣ ጐባጣ የሆነ ነበር፡፡ ከዚያም የሚያምረውን ለአንዱ ባልደረባቸው በመስጠት እንደነገሩ የሆነውን ለራሳቸው አስቀሩ፡፡ ባልደረባቸውም ሁኔታውን ካየ በኋላ “ይኸኛው ይሻልዎታል፤ የአላህ መልእክተኛ (ሰ.ዐ.ወ.)” በማለት የሚያምረውን ሲዋክ እንዲወስዱ ጋበዛቸው፡፡ የአላህ መልእክተኛ (ሰ.ዐ.ወ.) በዚህ ጊዜ እንዲህ አሉ፡- “አንድ ሰው ለአንድ ሰዓት እንኳን አብሮት ለቆየው ሰው የጓደኝነት ሃቁን ካጓደለበት መጠየቁ አይቀርም፡፡ “ (ኢህያእ ኡሉሙዲን ፡435)

የሚከተለው ትረካም ሌላው የዚህ ባህሪ መገለጫ ነው፡፡ አንድ እለት የነብዩ (ሰ.ዐ.ወ.) ባልደረቦች በመስጊድ ውስጥ ተሰባስበው የእርሳቸውን ኹጥባ (ዲስኩር) ያዳምጡ ነበር፡፡ ከዚያም ነብዩ (ሰ.ዐ.ወ.) የሚከተለውን የቁርአን አንቀጽ አነበቡ፡-

﴿لَن تَنَالُواْ ٱلۡبِرَّ حَتَّىٰ تُنفِقُواْ مِمَّا تُحِبُّونَۚ وَمَا تُنفِقُواْ مِن شَيۡءٖ فَإِنَّ ٱللَّهَ بِهِۦ عَلِيمٞ ٩٢﴾ آل عمران: ٩٢

"የምትወዱትን እስከምትለግሱ ድረስ በጐን ሥራ (ዋጋውን) አታገኙም። ከምንም ነገር ብትለግሱ አላህ ያውቀዋል።" (አሊ-ዒምራን፡ 92)

ባልደረቦቻቸው ነብዩ (ሰ.ዐ.ወ.) ያነበቡትን የቁርአን አንቀጽ አዳምጠው የልባቸውን ሥር እስኪነዝራቸው ድረስ በጥልቀት እያስተነተኑና ስሜታቸው ተነክቶ ነበር። ከሚወዱት ነገር ውስጥ ምን ቢሰጡ ለዚህ የቁርአን አንቀጽ ምላሽ እንደሚሆንላቸው በማሰብ ፀጥ ብለዋል። ከዚያም በድንገት አንዱ ባልደረባቸው ተነሳ። ይህ ሰው የእምነት ለዛ ውስጡን የቀየረው አቡ ጦልሃ (ረ.ዐ.) ነበር። ስድስት መቶ የሚሆኑ የቴምር ዛፎችን ያቀፈና ለነብዩ (ሰ.ዐ.ወ.) መስጊድ ቅርብ የሆነ ትልቅ የአትክልት ቦታ ነበረው። ብዙ ጊዜ ነብዩ (ሰ.ዐ.ወ.) ወደዚያ የአትክልት ሥፍራ እንዲመጡ ይጋብዛቸውና ዱአቸውን ያገኝ ነበር።

ከዚያም አቡ ጦልሃ እንዲህ አለ፡- "የአላህ መልእክተኛ ሆይ፤ ካሉኝ ንብረቶች ሁሉ በጣም የምወደው ያን የሚያውቁትን የአትክልት ማሳየን ነው። ከእንግዲህ እኔ ለአላህ ብዬ ለእርስዎ ሰጥቼዎታለሁ። እርስዎ ለመሰለዎት ጉዳይ ሊያውሉት ይችላሉ።" ይህን ካለ በኋላ ውሳኔውን ተግባራዊ ለማድረግ ወደ አትክልት ሥፍራው ገሰገሰ። እዚያ እንደደረሰም ባለቤቱ በዛፎቹ ጥላ ሥር ተቀምጣ አገኛት። አቡ ጦልሃ (ረ.ዐ.) ወደ አትክልቱ ሥፍራ አልገባም። በዚህ ጊዜ ባለቤቱ "አቡ ጠልሃ ሆይ! ለምን ከማሳው ውጭ ቆየህ? ና ወደዚህ" አለችው። አቡ ጠልሃ (ረ.ዐ.) እንዲህ አለ፡- "ከእንግዲህ ወደ ውስጥ አልገባም። አንቺም ብትሆኚ ንብረቶችሽን ያዥና ውጪ።" በዚህ ያልተጠበቀ አነጋገር የተደነቀችው ባለቤቱ "ለምን አቡ ጦልሃ? ይህ የአትክልት ሥፍራ የእኛ አይደለምን?" በማለት ጠየቀችው። "አይደለም። ከእንግዲህ ይህ የአትክልት ሥፍራ ለመዲና ምስኪን ነዋሪዎች ይሆን ዘንድ

ተሰጥቷል።›› በማለት መለሰላት፡፡ ከዚያም ነብዩ (ሰ.ዐ.ወ.) የተናገሩትንና ያነበቡላቸውን የቁርአን አንቀጽ፣ የሰዎችን ሁኔታና እርሱ የወሰደውን እርምጃ አንድ በአንድ ተረከላት፡፡ ባለቤቱ እንዲህ በማለት ጠየቀችው፡- “የሆነስ ሆነና ለራስህ ብቻ ነው ወይስ በሁለታችንም ስም ሰደቃ የሰጠኸው” “አይ በሁለታችንም ስም” በማለት መለሰላት፡፡ ይህን ከሰማች በኋላ ባለቤቱ ቀስ እያለች የሚከተለውን ስትናገር ሰማት፡- “በሰራኸው ሥራ አላህ ይደሰትብህ አቡ ጠልሃ! እኔ ሁልጊዜም የመዲናን ምስኪኖች ባየሁ ቁጥር ይህን ነገር አስብ ነበር፡፡ ሆኖም ደፍሬ ልነግርህ ወኔ አጣሁ፡፡ አላህ ምጽዋታችንን ይቀበለን፡፡ እኔም ከእንግዲህ ቦታውን ለቅቄ ወደ አንተ እየመጣሁ ነው፡፡”

እስኪ ልብ እንበል! ይህን የመሰለ ጥልቅ እምነትና የአላህን ውዴታ ለማግኘት ተብሎ የሚደረግ ልግስና በዘመናችን ቢኖር አለም ምን ልትመስል ትችል ነበር? የብዙዎቹ የደስታ ፀሐይ ከአድማሱ ላይ ትፈስ ነበር፡፡ ነፍሳቸውም በሐሴት ትፍነከነክ ነበር! አቡ ጠልሃ (ረ.ዐ.) ያን የመሰለ ድህነትን የማያስፈራ መስዋእትነት እንዲከፍል ያደረገው ይህ ስሜት እንጂ ሌላ አልነበረም፡፡

የአላህ መልእክተኛ (ሰ.ዐ.ወ.) ከባልደረቦቻቸው ውስጥ በጣም አነስተኛ ሃብት የነበራቸውን እንኳን ሳይቀር በአቅማቸው ለጋስ እንዲሆኑ ያበረታቷቸው ነበር፡፡ ለምሳሌ አቡ ዘር (ረ.ዐ.) ከባልደረቦቻቸው ውስጥ ድሃ ከሚባሉት መካከል አንዱ ነው፡፡ እንደዚያም ቢሆን ባለው ነገር ቸር እንዲሆን እንዲህ በማለት መክረውታል፡- “አቡ ዘር ሆይ! ስጋ ስታበስል ውሃ አብዛበት፡፡ ከዚያም ሌላ ነገር ካጣህ ውሃውንም ቢሆን ለጐረቤቶችህ አዳርስ፡፡ (ሙስሊም)

አማኝ የሆነ ሰው ድቅድቅ በሆነ ጨለማ በተዋጠ አድማስ ላይ ብቅ እንደምትል ጨረቃ መሆን አለበት፡፡ ብዙዎች የሕይወት ክርን አድቅቋቸው፡ ኑሮ ጐምዝዟቸው፣ ድህነት በድዱ ሲስቅባቸው እያየ አይቶ እንዳላየ መሆን ከእርሱ አይጠበቅም፡፡ የግፉአንን እንባ ማበስ፣ የሌሎችን

ስሜት መጋራት፣ ህመማቸውን መታመም፣ ችግራቸውን መቸገርና በማንኛውም ጊዜ ከጐናቸው ሆኖ አለሁላችሁ ማለት ይጠበቅበታል፡፡

ምዕራፍ አሥራ አራት

ኢስላም ለሰው ልጆች ሕይወት ይለግሳል

የአላህ መልእክተኛ (ሰ.ዐ.ወ.) የተሰጡትን የእምነት ችቦ ገና ሲለኩሱ የአረቢያ ባህረ ገብ መሬትና በዙሪያው ያሉ ማኅበረሰቦች በድቅድቅ ጨለማ በሚመሰል ሕይወት ውስጥ ይገኙ ነበር፡፡ ከዚያም በእርሳቸው እዝነትና ፍቅርን በሚረጭ ስብእና ቀስ በቀስ ሰዎች እየተማረኩ ይሄዱ ጀመር፡፡ በዚህ ዓይነት ሂደት የእለት ተእለት ሕይወቱ በሁከትና ብጥብጥ ይታመስ የነበረው ያ ማኅበረሰብ ጠንቃቃና ድንቅ ሆነ፡፡ ለሰብአዊ ትውልድ ሁሉ አርአያ የሚያደርገውን የሥነ ምግባር ምጥቀት ተቆናጠጠ፡፡

ከእርሳቸው መምጣት በፊት ሰዎች እንደ ዱር አውሬ እርስ በርስ የሚፋጁ፣ ጉልበተኛው አቅመ ደካማውን እንደፈለገ የሚያደርግበትና ፍትህ ይሉት ነገር የማይታወቅበት ሥርአት በዚያ ምድር ላይ ክፉኛ ተንሰራፍቶ ነበር፡፡ ከዚያም የነብዩ (ሰ.ዐ.ወ.) ማራኪ ስብእና በሰዎች ልብ ውስጥ ደድሮ የኖረውንና እንደ አለት የጠነከረውን የጭካኔ፣ የርክሰትና የጃሂሊያ ዝንባሌ ቀስ በቀስ እንደበረዶ እያቀለጠው ይሄድ ጀመር፡፡ እናም ሰዎች ውድና መተኪያ የሌላቸው የሚመስሏቸውን ወጐችና ልማዶች እንደ አሮጌ በርኖስ እያወለቁ መጣል ጀመሩ፡፡ ይህንን ሲያደርጉም ከቶም ቁጭት የሚባል ነገር አይሰማቸውም ነበር፡፡ በየጊዜው ስብእናቸው እያማረና የሚያሳዩት ለውጥም እጅግ የሚያስደንቅ እየሆነ መጣ፡፡ ከእንዲህ ዓይነት ስብእናዎች የተዋቀረው ማኅበረሰብ በጥቁሩ ሰማይ ላይ ፈክተው እንደሚታዩ ከዋክብት የኢስላምን ውበት ያንፀባርቅ ያዘ፡፡ የሚቀጥለው የሙስዓብ ኢብኑ ኡመይር (ረ.ዐ.) ታሪክ ከብዙ ምሳሌዎች አንዱ ነው፡፡

ሙስአብ መዲና እንደደረሰ ከአስአድ ቢን ዙራራህ ዘንድ አረፈ። ሁለቱ አማኞች በየስራብ ሰዎች መካከል ኢስላምን በከፍተኛ ስሜትና በቁም ነገር ማሰራጨት ጀመሩ። ሙስአብ «የቁርአን መምህር»

በሚል ቅጽል ይታወቅ ነበር። ከሚጠቀሱት አስደናቂ የዳእዋ (የሰበካ) ስኬቶቻቸው መካከል አስዓድ ቢን ዙራራህ አንድ ቀን ወደ በኒ አብድል አሽሐልና ወደ በኒ ዙፍር መኖሪያዎች ይዞት ሄደ። ከበኒ ዙፍር ክልል በመግባት «ቢእር ሙሩቅ» ከሚባል ጉድጓድ አጠገብ ተቀመጡ። ሌሎች ሙስሊሞችም አብረዋቸው ተቀመጡ። የየጎሳቸው አለቃዎች የሆኑት ሰእድ ቢን ሙዓዝና ኡሰይድ ቢን ሁደይር ያኔ ከጣኦት አምልኮ ውስጥ ነበሩ። የነ ሙስአብን መምጣት በሰሙ ጊዜ ሰእድ ለኡሰይድ፡- «ደካሞቻችንን ሊያቄሉ ወደመጡት ወደነዚህ ሰዎች ሂድና ገስጻቸው። ወደ ክልላችንም ዳግም እንዳይመጡ ንገራቸው። ሰእድ ቢን ዙራራህ የአክስቴ ልጅ ባይሆን ኖሮ እኔው ራሴ እገስጻቸው ነበር።» አለው። ኡሰይድ ጦሩን ይዞ ወደነርሱ አመራ። አስዓድ ሲያየው ለሙስአብ፡- «ይህ የወገኖቹ አለቃ ነው። ወደእኛ እየመጣ በመሆኑ ለአላህ በእውነት ጽና» አለው። «ከተቀመጠ እናገረዋለሁ።» አለ። ኡሰይድ ከአጠገባቸው ደርሶ ቆመ። ፊቱን አቀጭሟል። «ለምን ወደኛ መጣችሁ? ደካሞቻችንን ለማቄል ነውን? ሕይወታችሁን የምትፈልጉት ከሆነ ከአካባቢያችን ራቁ» አላቸው። ሙስአብም፡- «ተቀምጠህ የምንለውን ለመስማት አትፈቅድምን? ከወደድከው ትቀበለዋለህ። ከጠላኸውም፣ የምትጠላውን ከመፈጸም እንታቀባለን።» አለው። «ጥሩ ብለሐል» በማለት ጦሩን ከመሬት ተክሎ ተቀመጠ። ሙስአብ ስለ እስልምና ነገረው። ከቁርአን መልእክትም ጥቂት አነበበለት። «ገና ከመናገሩ በፊት በፊቱ ብሩህነትና ፈገግታ እንደሚሰልም አወቅን።» ሲሉ ተናግረዋል። የሙስአብን ገለጻ እና የቁርአን ንባብ ካደመጠ በኋላ «እንዴት ውብና ማራኪ ነው? ወደዚህ ሐይማኖት ልትገቡ ስትሉ ምንድን ነው የምታደርጉት?» አላቸው። «ታጠብ። ልብስህንም አጽዳ። ከዚያም የእውነትን ምስክርነት መስክር። ሁለት ረከዓዎችንም ስገድ።» አሉት። ተነስቶ ሄደ። ታጥቦ እና ልብሶቹን አጽድቶ ተመለሰ። ሸሃዳ (ምስክርነት) ፈጸመ። ሁለት ረከዓዎችንም ሰገደ። ከዚያም፡- «ከኋላየ አንድ ሰው አለ። እርሱ ከተከተላችሁ ከወገኖቹ ተነጥሎ የሚቀር አንድም ሰው አይኖርም። ወደናንተ እልከዋለሁ። ሰውየው ሰእድ ቢን ሙዓዝ ነው።» አላቸውና ጦሩን ይዞ ወደ ሰእድ ተመለሰ። ሰእድ ከወገኖቹ መሐል ነበር። ተሰባስበው ተቀምጠዋል። ሰእድ፡- «በአላህ

እምላለሁ፣ የኡሰይድ የአሁኑ ገጽታ ሲሄድ ከነበረው የተለየ ነው»አለ።

ኡሰይድ ከስብስቡ አጠገብ ሲደርስ፦ «ምን አደረግክ?» ሲል ሰእድ ጠየቀው። «ሁለቱን ሰዎች አናግሬያቸዋለሁ። መጥፎ ነገር አያደርሱም። ከልክያቸዋለሁ። የፈቃድህን እንፈጽማለን ብለውኛልም። ባይሆን የበኒ ሐሪሳህ ሰዎች የአጎትህ ልጅ መሆኑን በማወቃቸው አንተን ለመጉዳት ሲሉ ሊገድሉት ወጥተዋል መባልን ሰምቻለሁ» አለ። ሰእድ በሰማው ነገር ተቆጥቶ ተነሳ። ጠሩን ያዘና ወደነሙስአብ ገሰገሰ። ተረጋግተው ሲያያቸው ጊዜ ኡሰይድ ትምህርታቸውን ይሰማ ዘንድ እንደላከው አወቀ። ፊቱን አቀጭሞ ከአጠገባቸው ቆመ። ለአስዓድ ቢን ዙራራህም፦ «በአላህ እምላለሁ፣ በመካከላችን ያለውን ዝምድና ባትተማመን ኖሮ ይህን ነገር አትፈጽምም ነበር። የምንጠላውን ነገር ወደ ክልላችን ታመጣለህን» ሲል ወቀሰው። አስዓድ ለሙስአብ፦ «ከኋላው ብዙ ሰዎችን ያሰለፈ የወገኖቹ አለቃ እየመጣ ነው። እርሱ ከተከተለህ ከወገኖቹ መካከል ተነጥሎ የሚቀር አንድም የለም» ብሎት ኖሯል። ሙስአብ፦ «ፈቃደኛ ከሆንክ ተቀመጥና የምንለውን ስማን። ከወደድከው ትቀበለዋለህ። ካልወደድከውም የምትጠላውን ነገር አንፈጽምም» አለው። «ጥሩ ብለሃል» በማለት ጠሩን ተክሎ ተቀመጠ። እስልምናን አብራራለት። ከቁርአን መልእክትም ጥቂት አነበበለት። «በአላህ እምላለሁ፣ ከመናገሩ በፊት በገጽታው ብሩህነት እና ፈገግታ እንደሚሰልም አውቀን ነበር።» ሲሉ አውግተዋል። «ስትሰልሙ ምንድን ነው የምታደርጉት?» አላቸው። «ታጠብ፣ ልብስህንም አጽዳ። ከዚያም የእውነትን ምስክርነት መስክር። ሁለት ረከዓዎችንም ስገድ።» አሉት። ያዘዙትን ሁሉ ፈጸመ።

ጠሩን ይዞም ወደተሰበሰቡት ወገኖቹ ሄደ። ሲያዩት፦ «በአላህ እንምላለን፣ የተመለሰው ሲሄድ በነበረው ገጽታ አይደለም።» አሉ። ከአጠገባቸው ቆመና፦ «የአብድል አስህም ልጆች ሆይ፣ በናንተ ውስጥ የኔን ባህሪ እንዴት ትገልጹታላችሁ?» ሲል ጠየቃቸው። «አለቃችን፣ በአስተሳሰብ ከሁላችን የላቅክ፣ ቅን መሪያችን ነህ» አሉት። «በአላህና በመልእክተኛው ﷺ እስክታምኑ ድረስ ሴት

ወንዳችሁን ማናገር ለኔ እርም ነው» አለ። የዚያን ቀን ሴት ወንዳቸው ሁሉ ሰልመው አመሹ።

እንግዲህ የአረብ ዋና ዋና ሰዎች ጠንካራና ሻካራ የሆነን ስብእናና ልብ ይዘው ኢስላምን ቢቀርቡም በመጨረሻ ልባቸው በጣፋጭ መልእክቱ እንደሰም እየቀለጠ የሄደበት ሂደት ይህን ይመስል ነበር። ለዚህ ሁሉ ታላቅ የሆነ ስብእና ምጥቀት ዋነኛው ምንጭ የነብዩ (ሰ.ዐ.ወ.) ስብእና ማማር ነው፡-

﴿ فَبِمَا رَحۡمَةٖ مِّنَ ٱللَّهِ لِنتَ لَهُمۡۖ وَلَوۡ كُنتَ فَظًّا غَلِيظَ ٱلۡقَلۡبِ لَٱنفَضُّواْ مِنۡ حَوۡلِكَ ﴾ آل عمران: ١٥٩

“ከአላህም በሆነች ችሮታ ለዘብክላቸው። ዐመለ መጥፎ፣ ልበ ደረቅም በሆንክ ኖሮ ከዙሪያህ በተበተኑ ነበር።” (አሊ-ዒምራን፡159)

የአላህ መልእክተኛ (ሰ.ዐ.ወ.)ሊገደሉ ለሚገባቸው ብዙ ወንጀለኞች የምህረት እጃቸውን ዘርግተውላቸዋል። ሌላው ቀርቶ ተወዳጁን አጐታቸውንና የጥቢ ወንድማቸውን ሐምዛን (ረ.ዐ.) የገደለባቸውን ዋህሺን እንኳ ምህረት አድርገውለታል። የአላህ ነብይ (ሰ.ዐ.ወ.) ምንጊዜም ቢሆን ምህረታቸው ከቁጣቸው ይቀድማል። ብዙ ጨካኝና ርህራሄን የማያውቁ ሰዎች ልቦች ከእርሳቸው ጋር ጥቂት ጊዜ ከቆዩ በኋላ የእዝነት አበባዎች የፈኩባቸው ማሳዎች ሆነዋል።

አንድ ቱርካዊ ባለቅኔ ቅድመ ኢስላም የአረቦችን ሥነምግባርና የነበሩበትን ሁኔታ ሲገልጽ እንዲህ ብሏል፡- “የሰው ልጅ ጥርስ ባይኖረው ኖሮ የገዛ ወንድሞቹ ስጋውን ዘልዝለው ይሰለቅጡት ነበር።”

ይህ የሚያሳየው በአካል የሰው ስጋ ይበላሉ ለማለት ሳይሆን የጭካኔያቸው ደረጃ ያን ያክል ርቆ ሊሄድ የሚችል መሆኑን ነው። እንግዲህ ይህን ከመሰለው ድንቁርናና ከፊል አውሬነት ባሕሪ ነው ኢስላም መንጭቆ ያወጣቸውና ሰብአዊነትን ያላበሳቸው።

እነዚያን ከመሰሉ ከአውሬ የማይሻሉ ሕዝቦች ነው የሚከተለውና በየርሙክ ጦርነት የተከሰተ የሰብአዊ ስልጣኔና እዝነት የተስተዋለው፡፡ ጉዳዩ እንዲህ ነው፡፡ በየርሙክ ጦርነት ከሙስሊም ተዋጊዎች ውስጥ የተወሰኑት ቁስለት አግኝቷቸውና በአደገኛ ሁኔታ ላይ ጊዜ ሞታቸውን እየተጠባበቁ ነበር፡፡ ከእነዚያ መካከል ኢክሪማ ኢብን አቡ ጃህል አንዱ ነበር፡፡ አንድ ዘመዱ መቁሰሉን ሰምቶ ሲፈልገው ከጥቂት ሰዎች ጋር ቆስሎ ሽሂድነቱን እየተጠባበቀ አገኘው፡፡ ከዚያም ውሃ ሲሰጠው በዚያው ቅጽበት ሌላ ቁስለኛ ውሃ እንደሚያስፈልገው ገለጸ፡፡ ኢክሪማህም ያ ቁስለኛ ሰው በመጀመሪያ ሳይጠጣ እርሱ እንደማይቀምስ ተናገረ፡፡ ውሃውን የያዘው ሰው ወደ ሰውየው ሲሄድ ሌላው ቁስለኛ ድምጹን በማሰማቱ ውሃውን ለእርሱ እንዲሰጠው ነገረው፡፡ እንዲህ እንዲህ እያለ አሥር የሚሆኑ ቁስለኞችን አዳርሶ ሰውየው ወደ ኢክሪማህ ሲመለስ ሽሂድ (ሰማእት) ሆኖ አገኘው፡፡ ወደ ሁለተኛውም ሲሄድ እንደዚያው ሽሂድ ሆኗል፡፡ በዚህ አይነት ሁሉም ሽሂድ ሆነው አገኛቸው፡፡

የአላህ መልክተኛ (ሰ.ዐ.ወ.) የፍቅርንና የእዝነትን ቅፍለት ከፊት ለፊት ሆነው ያለመታከት እየመሩ ተከታዮቻቸውን ታላቅ ወደሆነ የሰብአዊነት ሰገነት ላይ አውጥተዋቸዋል፡፡ በመጨረሻም ወዳጆቻቸውና ጠላቶቻው አንድ ላይ ሆነው ምርጥ የሆነውን የእርሳቸውን ፈለገ ሕይወት (ሱና) ለመከተል በቁ፡፡

﴿ وَإِنَّكَ لَعَلَىٰ خُلُقٍ عَظِيمٍ ٤ ﴾ القلم: ٤

“አንተም በታላቅ ጠባይ ላይ ነህ፡፡” (አል-ቀለም፡4)

የነብዩ (ሰ.ዐ.ወ.) ባልደረቦች ከነበሩት የሶሃባ ትውልድ አባላት መካከል ከዘጠና በመቶ በላይ የሚሆኑት ኢስላምን የተቀበሉት በሚያስተምሯቸው የሞራል ምጥቀት ተስበው ነበር፡፡ ጥቂቶቹ ለነቢዩ (ሰ.ዐ.ወ.) ግልጽ የሆነ የጠላትነት ስሜትን ያንፀባርቁ የነበሩ ቢሆንም ውሸታም፣ አምባገነን ወዘተ በማለት አይከሷቸውም ነበር፡፡ እንዲያውም ከዚያ

በተቃራኒ በሁሉም ባህሪያቶቻቸው አድናቆታቸውን ሊቸሯቸው ተገደዋል፡፡

ለኢስላም ልባቸውን ሙሉ በሙሉ ያስረከቡና ኃይማኖቱን ለማሳደግ ደፋ ቀና የሚሉ ሰዎች ማወቅ ያለባቸው ጉዳይ ኢስላም ከሁሉም በላይ የሚሻው ስነምግባርን ከፍ ማድረግ መሆኑን ነው፡፡

የአላህ መልእክተኛ (ሰ.ዐ.ወ.) እንዲህ ብለዋል፡-

‹‹እኔ የተላክኩት መልካም ስነምግባራትን ለማሟላት ነው፡፡››

ይህ አባባል የሚያሳየን የኢስላም ዋነኛ ተልእኮ በምድር ላይ የአላህ ኸሊፋ (ምትክ) ሆኖ የተቀመጠውን የሰው ልጅ በሁሉም መልኩ የተሟላ ስብእና ያለው ማድረግ ነው፡፡

በዚህም የተነሣ ኢስላም በዋነኛነት አጽንኦት የሚሰጠው መንፈሳዊ ለሆነው ስልጠና ሲሆን በዚህ ስልጠና ሥር ያለፉና ከታላላቅ የስብእና እርከን ላይ የደረሱ ሰዎችንም አፍርቷል፡፡ እነዚህ ሰዎች ያንፀባረቋቸውን የሞራል የበላይነቶችና ያሳዩዋቸውን የአመራር ብቃቶች ሙስሊሞች ብቻ ሳይሆኑ በየዘመናቸው የነበሩ የሌላ ኃይማኖት ተከታዮችም መስክረውላቸዋል፡፡ ይህም ዝም ብሎ የተገኘ ሳይሆን መለኮታዊ ችሮታ ነው፡፡ ነብዩ (ሰ.ዐ.ወ.) አዛኝና ሩህሩህ ሆነው መላካቸውን አላህ (ሱ.ወ.) በሚከተሉት የቁርአን አንቀጽ ገልጿል፡-

﴿ وَمَآ أَرۡسَلۡنَٰكَ إِلَّا رَحۡمَةٗ لِّلۡعَٰلَمِينَ ١٠٧ ﴾ الأنبياء: ١٠٧

“(ሙሐመድ ሆይ!) ለዓለማቱም እዝነት አድርገን እንጂ አልላክንህም፡፡” (አል-አንቢያ፡ 107)

ይህ እዝነት ሙሉ በሙሉ ከሰረጻቸው ሰዎች መካከል ገናናው ኡመር ኢብን አል-ኸጣብ (ረ.ዐ.) ይገኙበታል፡፡ ኡመር (ረ.ዐ.) በጃሂልያ ዘመን ሴት ልጃቸውን በቁሟ ከነሕይወቷ የቀበሩ ሲሆን በኋለኛው ዘመን ሕይወታቸው ግን ሌላው ቀርቶ ጉንዳንን እንኳን ላለመጉዳት ከፍተኛ ጥንቃቄ ያደርጉ ነበር፡፡

ኦቶማን ቱርኮች በቁጥጥራቸው ስር ለነበሩ ምርኮኞች በሚያሳዩት ርህራሄ የታወቁ ነበሩ፡፡ በአንድ ወቅት በእነርሱ ቁጥጥር ስር የነበረ አንድ የጦር መኮንን "አንቺ እዝነት ሆይ! ምን ዓይነት ግፈኛ ነሽ! ጠላቴን እንዳፈቅር አደረግሺኝ ኮ!" ብሏል፡፡

አሁን በምንገኝበት ዘመን የምናየውና የምንሰማው ግን የሚያሳዝን ነው፡፡ በአሁኑ ጊዜ ብዙ ቁስአካላውያንና እምነት የለሽ የሆኑ የምዕራቡ ዓለም ሕዝቦች ኢስላምንና አሸባሪነትን እያቀላቀሏቸው ይገኛሉ፡፡ ይህ የሰው ልጅ በታሪኩ አጋጥሞት የማያውቅ የሆነ መከራ ነው፡፡ አሸባሪነትን የወለደው ለሰው ልጆችና በአጠቃላይ ለሰብአዊው ስልጣኔ የማያዝን ልብና ይህን ታላቅ ስሜት ያልተሸከመ መንፈስ ነው፡፡ አሸባሪነትን የሚተውኑ ሰዎች ለኢስላም ሁለንተናዊ ጽንሰ ሃሳቦች ግድ የሌላቸው፣ ነገሮችን ከራሳቸው ስሜቶች ጋር ብቻ የሚያያይዙ ግልቦች ናቸው፡፡ እነዚህ ሰዎች እንከተለዋለን የሚሉት ኃይማኖት ለእዝነትና ለርህራሄ የሰጠውን አትኩሮት የማያውቁ ወይም ቢያውቁም ግድ የሌላቸው፣ እንደ ዓለት የደደረ ልብ ያላቸው ናቸው፡፡ ኢስላም ከመሰረቱም ቢሆን አሸባሪነትንና ሥርአተ-አልበኝነትን አይቀበልም፡፡ ይህም የሚገለፀው በየጊዜው በታየውና ሙስሊምም ሆኑ ሙስሊም ያልሆኑ ሰዎችን መብት ያለምንም ልዩነት ሲያከብር የሚታይ በመሆኑ ነው፡፡

በአንድ ወቅት የአላህ መልእክተኛ (ሰ.ዐ.ወ.) ለተወሰኑ ጦሣዎች ቁርአንንና የኃይማኖታቸውን ጉዳይ ያስተምሯቸው ዘንድ ሰባ የሚሆኑ ምሁራንን (ሰባ ቁራኦችን) ወደዚያው ላኩ፡፡ "ቢር ማኡና" በተባለው ቦታ ከሃዲያኑ ግርግር ፈጥረው እነዚያን ሰዎች ከከበቧቸው በኋላ ጥቂት ሰዎች ሲቀሩ ሁሉንም ፈጅተዋቸዋል፡፡ ከዚህ አሳዛኝ የሆነ ክስተት በኋላ የአላህ መልእክተኛ (ሰ.ዐ.ወ.) የኃይማኖት አስተማሪዎችን ወደተለያዩ ሥፍራዎች ሲልኩ ከአደጋ የሚጠብቋቸውን ወታደሮች አብረው ይልኩ ነበር፡፡ እነዚያን ተዋጊዎችም ጦራቸውን መጠቀም የሚኖርባቸው የኃይማኖት ምሁራኑን አደጋ ከገጠማቸው ብቻ እንደሆነ በማስገንዘብ ያስጠነቅቋቸው ነበር፡፡

ይሁን እንጂ አንድ ጊዜ ኻሊድ ኢብን አልወሊድ (ረ.ዐ.) ይህን በመሰለ ተልእኮ ላይ ሳለ የተወሰኑ ሲቪሎችን የገደለ ሲሆን ንብረታቸውንም አወደመ፡፡ ይህን የሰሙት ነብዩ (ሰ.ዐ.ወ.) “አላህ ሆይ! ኻሊድ ከሰራው ነገር እኔ ንጹህ ነኝ፡፡ በሰራው ነገርም አልተደሰትኩም፡፡” ማለታቸው ተወስቷል፡፡ እነዚህን ቃላት ለሶስት ጊዜያት ያክል ከደጋገሟቸው በኋላ ዓሊን (ረ.ዐ.) ልከው ለጉዳተኞች የደም ካሣ ከፈሉ፡፡

የአላህን መልእክተኛ ጠባይና የሥነ-ምግባር ታላቅነት ዓለም በአንድ ድምጽ ይመሰክራል፡፡ ይህንንም ወዳጆቻቸው ብቻ ሳይሆኑ ጠላቶቻቸውም በተለያዩ ጊዜያት አረጋግጠውታል፡፡ ባለፈው ምዕተ ዓመት ለምሳሌ ሆላንድ አገር ሄግ በተባለ ሥፍራ የዓለም ምሁራንና ፈላስፎች በዓለም አቀፍ ደረጃ ተጽእኖ ያሳደሩና በሰው ዘር ላይ መልካም ነገርን ያመጡ ሰዎችን መርጠው በተራ ቁጥር አስቀምጠው ነበር፡፡ እነዚህ ሰዎች ያስቀመጧቸውን መስፈርቶች በሚገባ አሟልተው የአንደኝነቱን ሥፍራ የወሰዱት ነብዩ ሙሐመድ (ሰ.ዐ.ወ.) ናቸው፡፡ የዚህ ቡድን አባላት በሙሉ ክርስቲያኖች ነበሩ፡፡

አሁን ባለው ሙስሊም ዓለም የምንገኝ ሰዎች ይህንን ኢስላማዊ ባሕላችንን ባለመርሳት ሰዎችን ለፈጣሪያቸው ብለን መውደድ ይጠበቅብናል፡፡ ይህንንም ማድረግ ያለብን ለፖለቲካዊ ምክንያት ሳይሆን የአላህን ውዴታ ለማግኘት መሆን አለበት፡፡

አሁን ባለንበት ዘመን የሚገኙ ሕሊና ቢስ የሆኑ ኃይላት የሰውን ልጅ ሕይወት ክፉኛ ሰቆቃ ላይ ጥለውታል፡፡ ይህንንም ድርጊታቸውን በኃይማኖት ላይ ለማላከክ ይፈልጋሉ፡፡ በአጭሩ እንዲህ ዓይነት ሰዎች ነፍሰ ገዳዮች ናቸው፡፡ በእነርሱ ጦስ አእላፋት ሰዎች የሚወዱትን አጥተዋል፡፡ በቀያቸው ላይ ለፀሐይና ለቁር ተዳርገዋል፡፡ በልባቸው ውስጥ ያለው ፍቅር ያነሰባቸው እነዚህ ሰዎች በተለያዩ ኃይማኖቶች ውስጥ ይገኛሉ፡፡ በሰው ልጅ ታሪክ ላይ ከታዩት የሰብአዊው ፍጡር ጠላቶች ዋነኞቹ እነዚህ ሰዎች ናቸው፡፡ የአለማት ጌታ አላህ (ሱ.ወ.) እንዲህ ይላል፡-

﴿ وَإِذَا قِيلَ لَهُمۡ لَا تُفۡسِدُواْ فِي ٱلۡأَرۡضِ قَالُوٓاْ إِنَّمَا نَحۡنُ مُصۡلِحُونَ ١١ أَلَآ إِنَّهُمۡ هُمُ ٱلۡمُفۡسِدُونَ وَلَٰكِن لَّا يَشۡعُرُونَ ١٢ ﴾ البقرة: ١١ - ١٢

"ልእነርሱም በምድር ላይ አታበላሹ በተባለሉ ጊዜ እኛ አሳማሪዎች ብቻ ነን ይላሉ፡፡ ንቁ! እነርሱ አጥፊዎቹ እነርሱ ናቸው፤ ግን አያውቁም፡፡" (አል-በቀራህ፡11-12)

ሲቪሉችን መጨፍጨፍን ማንም ሰው ቢሆን ኃይማኖታዊ ክንዋኔ እንደሆነ አድርጐ ሊያቀርብ እንዲሁም በአላህ መንገድ ላይ ከመዋጋት (ጂሃድ) ጋርም ሊያምታታው አይገባል፡፡ ምክንያቱም ሁለቱ ለየቅል ናቸውና፡፡ ለሰይጣናዊ ድርጊታቸው ኃይማኖታዊ ሽፋን ለመስጠት የሚሞክሩ የአላህን ውዴታ ያጡ መሆናቸው ነው ሃቁ፡፡ ኃያሉ አላህ ይህ ታላቅ የሆነ እኩይ ምግባራቸው የሚያስከትልባቸውን አስከፊ ውጤት እንደሚከተለው ይገልጸዋል፡-

﴿ أَنَّهُۥ مَن قَتَلَ نَفۡسَۢا بِغَيۡرِ نَفۡسٍ أَوۡ فَسَادٖ فِي ٱلۡأَرۡضِ فَكَأَنَّمَا قَتَلَ ٱلنَّاسَ جَمِيعٗا وَمَنۡ أَحۡيَاهَا فَكَأَنَّمَآ أَحۡيَا ٱلنَّاسَ جَمِيعٗاۚ ٣٢ ﴾ المائدة: ٣٢

"...እነሆ ነፍስ (ያልገደለን) ወይም በምድር ላይ ያላጠፋን (ሰው) ነፍስ የገደለ ሰው ሰዎችን ሁሉ እንደገደለ ነው፡፡ ሕያው ያደረጋትም ሰው ሰዎችን ሁሉ ሕያው እንዳደረገ ነው ...." (አል ማኢዳህ፡32)

እናም ቅዱስ ቁርአን የአንድን ሰው ነፍስ በከንቱ ማጥፋትን የሰውን ዘር ነፍስ በከንቱ ከማጥፋት ጋር ነው የሚያመሳስለው፡፡ እንዲህ ዓይነቱን ከንቱ ግድያ የሚፈጽም ሰውም የሰውን ልጅ ክቡር ነፍስ የሚያረክስና የሕይወትን ዋጋ በሚገባ ያልተገነዘበ መደዴ ነው፡፡ አንድ ሰው በራሱ ስሜት ተገፋፍቶ የአንድን ሰው ነፍስ ካጠፋ የሰውን ዘር በሙሉ በራሱ ፍላጐት ተነሳስቶ እንዳጠፋ ነው የሚቆጠርበት፡፡ በዚህ ጋጠወጥ ድርጊቱ ሌሎች ሰዎችም ክቡር የሆነችውን ነፍስ በዘፈቀደ እንዲያጠፉና ደምንም እንደጐርፍ እንዲያፈሱ አርአያ ስለሚሆናቸው ይደፋፈራሉ፡፡ ለዚህም ነው ንጹህ የሆነን ሰው መግደል በኢስላም ከታላላቅ ኃጢአቶች አንዱ

ሊሆን የቻለው፡፡ ይህንን ድርጊት የሚፈጽሙም በፍርዱ ቀን የአላህን ቁጣ ያተርፋሉ፡፡ በተለይም ደግሞ የሚገደሉት ሰዎች ምእመናን ከሆኑ ኃጢአቱ የከፋ እንደሚሆን አላህ በቁርአን እንዲህ በማለት ይገልጻል፡-

﴿ وَلَا يَقۡتُلُونَ ٱلنَّفۡسَ ٱلَّتِي حَرَّمَ ٱللَّهُ إِلَّا بِٱلۡحَقِّ ﴾ الفرقان: ٦٨

“…..ያችንም አላህ እርም ያደረጋትን ነፍስ ያለ ሕግ የማይገድሉት ….” (አል-ፉርቃን፡68)

﴿ وَلَا تَقۡتُلُواْ ٱلنَّفۡسَ ٱلَّتِي حَرَّمَ ٱللَّهُ إِلَّا بِٱلۡحَقِّۚ ﴾ الأنعام: ١٥١

“…ያችንም አላህ እርም ያደረጋትን ነፍስ በሕግ ቢሆን እንጂ አትግደሉ….” (አል-አንዓም፡151)

﴿ لَئِنۢ بَسَطتَ إِلَيَّ يَدَكَ لِتَقۡتُلَنِي مَآ أَنَا۠ بِبَاسِطٖ يَدِيَ إِلَيۡكَ لِأَقۡتُلَكَۖ إِنِّيٓ أَخَافُ ٱللَّهَ رَبَّ ٱلۡعَٰلَمِينَ ٢٨ ﴾ المائدة: ٢٨

“ልትገድለኝ እጅህን ወደ እኔ ብትዘረጋ እኔ ልገድልህ እጄን ወዳንተ የምዘረጋ አይደለሁም፡፡ እኔ የዓለማትን ጌታ አላህ እፈራለሁና አለ፡፡” (አል-ማኢዳህ፡28)

﴿ وَمَا كَانَ لِمُؤۡمِنٍ أَن يَقۡتُلَ مُؤۡمِنًا إِلَّا خَطَـٔٗاۚ ﴾ النساء: ٩٢

“ለእምመንም በስህተት ካልሆነ በቀር ምእመንን መግደል አይገባውም….”(አን-ኒሳእ፡92)

﴿ وَمَن يَقۡتُلۡ مُؤۡمِنٗا مُّتَعَمِّدٗا فَجَزَآؤُهُۥ جَهَنَّمُ خَٰلِدٗا فِيهَا وَغَضِبَ ٱللَّهُ عَلَيۡهِ وَلَعَنَهُۥ وَأَعَدَّ لَهُۥ عَذَابًا عَظِيمٗا ٩٣ ﴾ النساء: ٩٣

“ምዕመንንም ሆነ ብሎ የሚገድል ሰው ቅጣቱ በውስጧ ዘውታሪ ሲሆን ገሃነም ናት፡፡ አላህም በእርሱ ላይ ተቆጣ፡፡ ረገመውም፡፡ ለእርሱም ከባድ ቅጣትን አዘጋጀ፡፡” (አን-ኒሳእ፡93)

ምዕራፍ አሥራ አምስት

የጸባይ ታላቅነትና ውስጥን ማጽዳት

ከነብዩ (ሰ.ዐ.ወ.) ባልደረባዎች አንዱ የነበረው አቡ ደርዳእ (ረ.ዐ.) የደማስቆ ቃዲ ሆኖ ነበር፡፡ በያዘው የዳኝነት ስልጣን ምክንያት በየጊዜው ብዙ ወንጀለኞች ወደ እርሱ ይመጡ ነበር፡፡ አንድ እለት የቀረበለትን ወንጀል ተመልክቶ ተገቢውን ፍርድ ከሰጠ በኋላ ጉዳዩ ተዘጋ፡፡ ይሁን እንጂ በዚያ የፍርድ ሂደት ላይ የነበሩ ሰዎች ጥፋተኛ ሆኖ በተገኘው ተከሳሽ ላይ እርግማናቸውን ያወርዱበት ጀመር፡፡ ይህንን የሰማው አቡ ደርዳእም (ረ.ዐ.) ሲራገሙ የነበሩትን ሰዎች እንዲህ በማለት ጠየቃቸው።

“በአንድ ጥልቅ ጉድጓድ ውስጥ ወድቆ የገባን ሰው ብታዩ ምን ታደርጉ ነበር?”

“ገመድ እንልክለትና ያንን ይዞ እንዲወጣ በማድረግ እናተርፈው ነበር” አሉ፡፡

“ታዲያ አሁን በኃጢአት ጉድጓድ ውስጥ የገባውን ይህን ሰው ልታድኑት ለምን አትሞክሩም?”

በዚህ የአቡ ደርዳእ (ረ.ዐ.) ንግግር የተገረሙት ሰዎች “ይህን ኃጢአተኛ ሰው አትጠላውምን” በማለት ጠየቁት፡፡

አቡ ደርዳእ (ረ.ዐ.) በዚህን ጊዜ ብልህነት የተንፀባረቀበት መልሱን እንዲህ በማለት ሰጣቸው፡-

“እኔ ያ ሰው የሰራውን ኃጢአት እንጂ እርሱን ራሱን አልጠላውም፡፡”

አቡደርዳእ (ረ.ዐ.) ያንፀባረቀው ይህ ውብ አገላለጽ ከመለኮታዊው የእውቀት ባሕር እየተቀዳ ይፈስላቸው ከነበሩት ታላቅ ነቢይ (ሰ.ዐ.ወ.) በቀጥታ የተወረሰ እንጂ ሌላ አልነበረም፡፡ እንዲህ ዓይነቱ ያማረ አቀራረብ ነው ኃጢአተኞችን ከተዘፈቁበት የኃጢአት ማጥ ውስጥ መንጭቆ የሚያወጣቸው፡፡ ይህን የመሰለው አቀራረብ ኃጢአተኞች

በፍቅር፣ በምህረትና በይቅር ባይነት ባሕር ውስጥ ገብተው እንዲጠመቁ ያደርጋቸዋል። የአላህ መልእክተኛ (ሰ.ዐ.ወ.) የኡመቴ ፊርዓውን በማለት ለጠሩት አቡ ጀህል እንኳ ሳይቀር ይህን የመሰለ ፍቅርና ርህራሄ ያሳዩት ነበር። ኃጢአተኛ መሆኑን እየጠቀሱ ለሰዎች መዛበቻ ከማድረግ ይልቅ የእዝነትን መንገድ ነበር የመረጡት።

﴿ وَمَآ أَرۡسَلۡنَٰكَ إِلَّا رَحۡمَةٗ لِّلۡعَٰلَمِينَ ١٠٧ ﴾ الأنبياء: ١٠٧

"(ሙሐመድ ሆይ!) ለዓለማት እዝነት አድርገን እንጂ አልላክንህም።" (አል-አንቢያ፡107)

ኃያሉ አላህ ወደእርሱ ተጸጽተው ለሚቀርቡት ጥልቅ የሆነ እዝነትና ፍቅር አለው። አንድ ባሪያ ከልቡ ተጸጽቶ ወደ አላህ እስከቀረበ ድረስ ያለፈውን ኃጢአቱን በሙሉ ይምረዋል። እንዲያውም አላህ እርሱ ለሻው ባሪያው ኃጢአቱን ሳይቀር ወደ ሃሰናት ይቀይርለታል። አላህ እንዲህ ይላል፡-

﴿ إِلَّا مَن تَابَ وَءَامَنَ وَعَمِلَ عَمَلٗا صَٰلِحٗا فَأُوْلَٰٓئِكَ يُبَدِّلُ ٱللَّهُ سَيِّـَٔاتِهِمۡ حَسَنَٰتٖۗ وَكَانَ ٱللَّهُ غَفُورٗا رَّحِيمٗا ٧٠ ﴾ الفرقان: ٧٠

"ተፀፅቶ የተመለሰና ያመነ፣ መልካምን ሥራ የሰራ ሰው ብቻ ሲቀር እነዚያም አላህ መጥፎ ሥራዎቻቸውን በመልካም ሥራዎች ይለውጣል፤ አላህም እጅግ መሐሪ አዛኝ ነው።" (አል-ፉርቃን ፡70)

አነስ ኢብኑ ማሊክ (ረ.ዐ.) ባስተላለፉትና ቡኻሪና ሙስሊም በዘገቡት ሐዲስ የአላህ መልእክተኛ (ሰ.ዐ.ወ.) እንዲህ ብለዋል፡-

"አላህ አንድ አገልጋዩ በኃጢአቱ ተፀፅቶ ይቅርታ ሲጠይቀው፤ አንዳችሁ ግመሉ በምድረበዳ በረሃ ውስጥ ከጠፋበት በኋላ በድንገት መልሶ ሲያገኘው ከሚሰማው ደስታ የበለጠ ይደሰታል።"

አንድ የአላህ ባሪያ በዚህ በኩል አርአያነት ያለው ተግባር ፈጽመዋል። እኒሁ ሸህ ሙሐመድ ሳሚ የተባሉ ሰው ኃጢአት የፈፀመን አንድ

ሙስሊም እንዴት እንደተቀበሉት እንመልከት፡፡ አንድ እለት ከተማሪዎቻቸው አንዱ ባደረበት የመንፈስ ጭንቀት የተነሣ መጠጥ ጠጥቶና ጥንብዝ ብሎ ወደቤታቸው በመምጣት ይከፍቱለት ዘንድ በራቸውን ይደበድባል፡፡ በሩን የከፈተለት ሰው በዚህ ወጣት ሁኔታ በጣም በመናደዱ ግንባሩን ቋጠረበት፡፡ ከዚያም እንዲህ አለው፡- “ምን ማድረግህ ነው? አሁን እየገባህ ያለኸው ወደማን ቤት እንደሆነ አስተውለሃለን?” ያ በስካር ላይ የነበረ ወጣት ግን እንዲህ አለ፡- “ይህ ቤት እንደሚቀበለኝ አድርጐ ሊቀበለኝ የሚችል ሌላ ቤት ያለ ይመስልሃልን?” ይህን የሁለቱን ሰዎች ምልልስ የሰሙት ሸይኽ ሙሐመድ ሳሚ ወደ በሩ በመምጣት ያን ወጣት ወደ ውስጥ ካስገቡት በኋላ እንዲረጋጋ አድርገው ችግሮቹን የሚፈታበትን መንገድ አመላከቱት፡፡ ሸይኹ የወጣቱን የተጎዳና የቆሰለ ልብ በእዝነትና ፍቅር አከሙት፡፡ ይህን የመሰለው ፍቱን ሕክምናም ተጐጂው ችግሮቹን በፍጥነት አስወግዶ ወደ ፈጣሪው በተውበት እንዲመለስ አደረገው፡፡ በኋላም አላህን ፈሪ (ተቅይ) ለመሆን በቃ፡፡

ይህን ዓይነት አቀራረብ የሚከተሉ የአላህ ባሮች የሰው ልጆችን በአዎንታዊና ወንድማዊ ስሜት ስለሚይዙ የሰዎችን መንፈስ በቀላሉ መግዛትና ማሸነፍ አይሳናቸውም፡፡ አላህ እንዲህ ይላል፡-

﴿ ٱدۡفَعۡ بِٱلَّتِي هِيَ أَحۡسَنُ ٱلسَّيِّئَةَۚ نَحۡنُ أَعۡلَمُ بِمَا يَصِفُونَ ٩٦ ﴾ المؤمنون: ٩٦

“በዚያች እርሷ መልካም በሆነችው (ጠባይ) መጥፎይቱን ገፍትር….” (አል-ሙእሚኑን፡ 96)

ኡመር ኢብን አል-ኸጣብ (ረ.ዐ.) ባስተላለፉትና ቡኻሪ በዘገቡት ሐዲስ ላይ እንዲህ የሚል ነገር እናገኛለን፡-

በነብዩ (ሰ.ዐ.ወ.) ዘመን አብደላህ የሚባልና በቅጽል ስሙም ሒማር (አህያው) ተብሎ የሚጠራ ሰው ነበር፡፡ ይህ ሰው ነብዩን (ሰ.ዐ.ወ.) በማሳቅ የተዋጣለት ነበር፡፡ ይሁን እንጂ በብዙ አጋጣሚዎች አስካሪ

መጠጥ እየጠጣ በመገኘቱ ነብዩ (ሰ.ዐ.ወ.) እንዲገረፍ አድርገዋል፡፡ አንድ እለትም እንዲሁ መጠጥ ተጐንጭቶ በመገኘቱ ተከስሶ ወደ ነብዩ (ሰ.ዐ.ወ.) ከተወሰደ በኋላ ተገረፈ፡፡ በዚህ ጊዜ ከሰዎች ውስጥ አንዱ እንዲህ አለ፡- “አላህ ሆይ! እርግማንህን አውርድበት፡፡ በዚህ ወንጀሉ ምክንያት ነብዩ (ሰ.ዐ.ወ.) ዘንድ እየተከሰሰ ስንት ጊዜ ቀረበ!” ይህን ንግግር ነብዩ (ሰ.ዐ.ወ.) እንደሰሙ እንዲህ አሉ፡- “አትርገመው፡፡ በአላህ ይሁንብኝ! እርሱ አላህንና መልእክተኛውን ይወዳል፡፡”

የሰው ልጆች ሰው በመሆናቸው ብቻ ከፍጥረታት ሁሉ የበለጠ ደረጃ አላቸው፡፡ መጥፎ ሥራዎቻቸውና ባህሪያቶቻቸው ይህን ልዩ የሆነ ደረጃቸውን እንዲያጡ አያደርጓቸውም፡፡ ምክንያቱም የሰው ዘር በሙሉ የመለኮታዊው እስትንፋስ ድርሻ በየነፍሱ ውስጥ ይገኛልና፡፡ ምንም አንኳን ብዙ ኃጢአተኞች ባይገነዘቡትም ቅሉ ይህ መለኮታዊ አስትንፋስ በየሰው ሁሉ ዘንድ አብሮት ይኖራል፡፡ ለዚህ አባባል ማሳያ የሚሆን ምሳሌን እንጠቀም፡፡ እንበልና ጥቁሩ ድንጋይ (ሐጀረል-አስወድ) ከጭቃ ላይ ወድቆ ሁሉም ሰው ተመለከተ፡፡ ለዚህ ተቆርቋሪነት የማያሳይና ያንን ድንጋይ ከወደቀበት ቦታ አንስቶ እቦታው ላይ ለመመለስ የማይሞከር አንድም ሙስሊም አይገኝም፡፡ ሙስሊሞች በእንባቸውና በጸማቸው ጭቃውን እየጠረጉ ከተቀደሰ ቦታው ላይ እንደሚያስቀምጡት አያጠያይቅም፡፡ ምንም እንኳን በጭቃ ተለውሶና ቆሻሻም ነክቶት ቢመለከቱ ሙስሊሞች ለዚያ ድነጋይ ፍቅርና ክብር መስጠታቸው አይቀርም፡፡ ያ ድንጋይ ከጀነት የወረደ እንደሆነ ስለሚያውቁ ትልቅ ግምት ይሰጡታል፡፡ የሰውም ልጅ ሁኔታ ከዚህ ጋር ተመሳሳይ ነው፡፡ ምንም እንኳን ከጀነት ቢባረርም (አባታችን አደምና እናታችን ሃዋ ከጀነት መባረራቸውን ልብ ይሏል፡፡) እና የፈለገውን ያህል በሐጢአት ቢጨቀይም ሲፈጠር ጀምሮ ከዘር ማንዘሮቹ የወረሰው መለኮታዊ እስትንፋስ አይለየውም፡፡

በተመሳሳይ ሁኔታ አንድ ጥሩ ዶክተር በበሽተኛው ድክመት አይበሳጭም፡፡ ታማሚው ምናልባት በሽታውን የሸመተው በመኃይምነቱ፣ በስንፍናው ወይም በሌሎች ድክመቶቹ ሊሆን ይችላል፡፡

ይሁን እንጂ አንድ መልካም ሥነ-ምግባር ያለው ዶክተር ትኩረት የሚሰጠው የሰሽተኛውን ስቃይና በሽታው የሚያሳድርበትን አሉታዊ ተጽእኖ እንጂ ከቶም ድክመቶቹን አይደለም፡፡ ስለዚህም ዶክተሩ በሽተኛውን ለማዳን ወዲያና ወዲህ ይሯሯጣል አንጂ በመናደድ ብቻ ቁጭ ብሎ ጊዜውን አያባክንም፡፡ በተመሳሳይ ሁኔታ የአላህ ወዳጆች ከእነርሱ ዘንድ አንድ በኃጢአት ስብእናው የጨቀየ የአላህ ባሪያ ቢያጋጥማቸው ኃጢአት መስራቱን እያነሱ በመውቀስ ጊዜያቸውን አያባክኑም፡፡ ከዚያ ይልቅ የቆሰለ መንፈሱን ለማከምና ልቡን ለማዳን ነው የሚረባረቡት፡፡ ስለዚህ እነዚህ ሰዎች በኃይለኛ ወጀብ በታጀበ ዝናብ እንደሚለበስ መልካም ጃኬት ሊመሰሉ ይችላሉ፡፡

ከኸይበር ዘመቻ በኋላ ነብዩ (ሰ.ዐ.ወ.) ዓሊን (ረ.ዐ.) እንዲህ አሏቸው፡- “አሊ ሆይ! ፀሐይ የወጣችበትን ነገር ሁሉ ከምታገኝ በአንተ ሰበብ አንድ ሰው ወደ ኢስላም ቢመራ ይበልጥልሃል፡፡”

ኃያሉ አላህም የሰውን ልጅ ከመንፈሳዊም ሆነ ከአካላዊ ሞት ይታደገው ዘንድ ቀደም ባሉት ምዕራፎች የተጠቀሰውን የቁርአን አንቀጽ እንደገና በመጥቀስ ያስታውሰናል፡-

﴿ أَنَّهُۥ مَن قَتَلَ نَفۡسَۢا بِغَيۡرِ نَفۡسٍ أَوۡ فَسَادٖ فِي ٱلۡأَرۡضِ فَكَأَنَّمَا قَتَلَ ٱلنَّاسَ جَمِيعٗا وَمَنۡ أَحۡيَاهَا فَكَأَنَّمَآ أَحۡيَا ٱلنَّاسَ ٣٢ ﴾ المائدة: ٣٢

“...እነሆ ነፍስ (ያልገደለን) ወይም በምድር ላይ ያላጠፋን (ሰው) ነፍስ የገደለ ሰዎችን ሁሉ እንደገደለ ነው፡፡ ሕያው ያደረጋትም ሰው ሰዎችን ሁሉ ሕያው እንዳደረገ ነው ...” (አል-ማኢዳህ፡32)

አንድ ሰው ከሚፈጽማቸው ኃጢአቶች ሁሉ በጣም የከፋው አላህን መካድና ከእርሱ ሌላ የሆነን ነገር አጋር አድርጐ መያዝ ነው፡፡ ለዚህም ታላቅ የሆነ ኃጢአት ቢሆን መድኃኒቱ መልካም የሆነ አቀራረብና ለስላሳ ምክር እንጂ ሌላ አይደለም፡፡ ኃያሉ አላህ ሙሣን (ዐ.ሰ.) እና ወንድማቸውን ወደ ፈርዖን ሲልካቸው ለስላሳ በሆነ አነጋገር (ቀውለን ለይን) እንዲያነጋግሩት ነበር ያዘዛቸው፡፡ ፈርዖን ራሱን እንደጌታ

የሚቆጥር ታላቅ የሆነ ኃጢአተኛ እንደነበር ይታወቃል፡፡ አንድን ሰው ወደ ቀናው መንገድ በተሳካ ሁኔታ መምራት ለአንድ አማኝ ታላቅ የሆነ ስኬት ሲሆን መድህን የማግኛ ድልድይ (ሰበብ) ሆኖም ያገለግላል፡፡ ኃያሉ አላህ ሙሣን (ዐ.ሰ.) እና ወንድማቸውን ወደ ፈርኦን ሄደው በለስላሳ ቃላት እንዲያናግሩት ሲልካቸው ፈርኦን ትእቢተኛና አምባገነን መሆኑን አጥቶት አይደለም፡፡ ይህን ያደረገው ለመጪ ትውልዶች የዳዕዋን ስልት ለማስተማርና ኢስላምን የምናስፋፋበትን ዘዴ እንድናውቅ ፈልጐ ነው፡፡

እኛ ወደ ኢስላም የምንጠራው ሰው ልክ እንደ ፈርኦን ሁሉ ጠንካራ ልብ ያለውና ለኢስላም ጠላት ቢሆንም ቅሉ እኛ ግን በለስላሳና ያማሩ ቃላት ነው ልናናግረው የሚገባን፡፡ አቀራረባችን ምንጊዜም ቢሆን ስሜታዊነት የተጫነውና ሸካራ መሆን የለበትም፡፡ ማስፈራራት፣ መራገምና መሰል ሸካራ ባሕሪያትን ማንፀባረቅ ኢስላምን ከሚያስፋፉ ሰው ፈጽሞ አይጠበቅም፡፡

የሚከተለው የቁርአን አንቀጽ የአላህን መልእክተኛ (ሰ.ዐ.ወ.) ትክክለኛ ባሕሪ የሚያንፀባርቅ ነው፡-

﴿ فَبِمَا رَحۡمَةٖ مِّنَ ٱللَّهِ لِنتَ لَهُمۡۖ وَلَوۡ كُنتَ فَظًّا غَلِيظَ ٱلۡقَلۡبِ لَٱنفَضُّواْ مِنۡ حَوۡلِكَۖ فَٱعۡفُ عَنۡهُمۡ وَٱسۡتَغۡفِرۡ لَهُمۡ وَشَاوِرۡهُمۡ فِي ٱلۡأَمۡرِۖ فَإِذَا عَزَمۡتَ فَتَوَكَّلۡ عَلَى ٱللَّهِۚ إِنَّ ٱللَّهَ يُحِبُّ ٱلۡمُتَوَكِّلِينَ ١٥٩ ﴾ آل عمران: ١٥٩

“ከአላህም ባሆነች ችሮታ ለዘብክላቸው፡፡ ዐመለ መጥፎ፣ ልበደረቅም በሆንክ ኖሮ ከዙሪያህ በተበተኑ ነበር፡፡ ከእነርሱም ይቅር በል፡፡ ለእነርሱም ምሕረትን ለምንላቸው፡፡ በነገሩም ሁሉ አማክራቸው፡፡ አላህ በእርሱ ላይ ተመኪዎችን ይወዳልና፡፡” (አሊ-ዒምራን፡ 159)

ኢስላምን ለሰዎች ማስተማርን በተመለከተ ከወረዱ የቁርአን አንቀጾች መካከል የሚከተለው አንቀጽ ጉልህ ሥፍራ ይይዛል፡-

﴿ ٱدۡعُ إِلَىٰ سَبِيلِ رَبِّكَ بِٱلۡحِكۡمَةِ وَٱلۡمَوۡعِظَةِ ٱلۡحَسَنَةِۖ وَجَٰدِلۡهُم بِٱلَّتِي هِيَ أَحۡسَنُۚ إِنَّ رَبَّكَ هُوَ أَعۡلَمُ بِمَن ضَلَّ عَن سَبِيلِهِۦۖ وَهُوَ أَعۡلَمُ بِٱلۡمُهۡتَدِينَ ١٢٥ ﴾ النحل: ١٢٥

"ወደ ጌታህ መንገድ በብልሃትና በመልካም ግሣጼ (በለዘብታ ቃል) ጥራ፡፡ በዚያችም እርሷ መልካም በሆነችው (ዘዴ) ተከራከራቸው፡፡ ጌታህ እርሱ ከመንገዱ የተሳሳተውን ሰው አዋቂ ነው፡፡ እርሱም ቅን የሆኑትን ሰዎች አዋቂ ነው፡፡" (አን-ነሕል፡ 125)

ዱዓት የሚያሳዩት መቻቻልና የጨዋነት ባሕሪ ለኃጢአተኞችና ኃይማኖቱን ለካዱ ብቻ ሳይሆን ለመልካም የአላህ ወዳጆችም ጭምር መሆን አለበት፡፡ እኛ ሁላችንም የሰው ልጆች ስንሆን ኢስላምን በምልአት የሚተገብሩ ቅን የአላህ ወዳጆች እንኳን ከስህተት እንደማይጸዱ ግልጽ ነው፡፡ ስለሆነም ከስህተት ላይ የወደቀን ሰው ለማረም የምንጠቀመው ዘዴ ሻካራ ከሆነ ሰውየውን ከማቃናት ይልቅ አሉታዊ ወደሆነ አቅጣጫ እንዲሄድ ያደርገዋል፡፡ ሰውየውን በመንፈስ ከማከም ይልቅ ወደባሰና መራር ወደሆነ የጥመት መንገድ ልናስገባው እንችላለን፡፡ የሰው ልጅ በተፈጥሮው ጠንካራ የሆነን ግሳጼ አይቀበልም፡፡ ሌላው ቀርቶ ልጆች እንኳ የወላጆቻቸውን ጠንካራ የሆነ ግሳጼ ከመቀበል ይልቅ ቀላል በሆነ ምክር የመመለስ አዝማሚያ አላቸው፡፡ ስለሆነም በሻካራ ቃላት የታጀበ ምክር በውስጡ የያዘውን ጠቀሜታ በሙሉ ያጣል ማለት ነው፡፡

የሰውን ልጅ በቀላሉ የሚጐዳ (ብስክስክ) ሥነ-ልቦናዊ ጐን በአንክሮ ማመን አለብን፡፡ ስለሆነም ምንም ያክል በኃጢአት ባህር ቢዘፈቅ ከዚያ ሁኔታ እንዲወጣ ከፈለግን አቀራረባችን ለስላሳና ማራኪ መሆን ይኖርበታል፡፡ እኛ የምናደርግላቸው ጥሪ በውስጣቸው አድፍጦና በኃጢአት ተከቦ የተቀመጠውን በራስ የመተማመንና መልካም ነገር የማድረግ መንፈስ ከማነቃቃት የዘለለ መሆን የለበትም፡፡ የአላህ መልእክተኛ (ሰ.ዐ.ወ.) አማኝ ሰውን መናቅና አክብሮት አለማሳየት ኃጢአት መሆኑን እንዲህ በማለት ተናግረዋል፡-

“ለአንድ አማኝ፣ ሙስሊም ወንድሙን አለማክበር ታላቅ ኃጢአት ነው፡፡” (አቡ ዳውድ፣ ሙስነድ አህመድ)

ኢስላምን እናስተምራለን ካልን ማራኪና ጨዋነትን የተላበሰ ስብዕና አንዲሁም በእዝነት የታጀበ አቀራረብን በመከተል ከትችትና ሰውን ዝቅ አድርጐ ከማየት መቆጠብ ይኖርብናል፡፡ ኃያሉ አላህ እንዲህ ይላል፡-

﴿ وَكَفَىٰ بِهِۦ بِذُنُوبِ عِبَادِهِۦ خَبِيرًا ﴿٥٨﴾ ﴾ الفرقان: ٥٨

“...በባሮቹ ኃጢአቶችም ውስጥ አዋቂ በርሱ በቃ፡፡” (አል-ፉርቃን፡58)

በሌላ የቁርአን አንቀጽ ደግሞ አላህ እንዲህ ይላል፡-

﴿ يَٰٓأَيُّهَا ٱلَّذِينَ ءَامَنُواْ ٱجۡتَنِبُواْ كَثِيرٗا مِّنَ ٱلظَّنِّ إِنَّ بَعۡضَ ٱلظَّنِّ إِثۡمٞۖ وَلَا تَجَسَّسُواْ وَلَا يَغۡتَب بَّعۡضُكُم بَعۡضًاۚ أَيُحِبُّ أَحَدُكُمۡ أَن يَأۡكُلَ لَحۡمَ أَخِيهِ مَيۡتٗا فَكَرِهۡتُمُوهُۚ وَٱتَّقُواْ ٱللَّهَۚ إِنَّ ٱللَّهَ تَوَّابٞ رَّحِيمٞ ﴿١٢﴾ ﴾ الحجرات: ١٢

“እናንተ ያመናችሁ ሆይ! ከጥርጣሬ ብዙውን ራቁ፡፡ ከጥርጣሬ ከፊሉ ኃጢአት ነውና፡፡ ነውርንም አትከታተሉ፡፡ ከፊላችሁም ከፊሉን አይማ፡፡ አንደኛችሁ የወንድሙን ስጋ የሞተ ሆኖ ሊበላው ይወዳልን? (መብላቱን) ጠላችሁትም፡፡ (ሀሜቱንም ጥሉት) አላህንም ፍሩ፤ አላህ ፀፀትን ተቀባይ አዛኝ ነውና፡፡” (አል-ሑጁራት፡12)

የአላህ መልእክተኛ (ሰ.ዐ.ወ.) አንድ ሰው ስህተት ሲሰራ ከተመለከቱ ሰውየውን በቀጥታ አይጋፈጡትም ነበር፡፡ ከዚያ ይልቅ ሁሉንም ሰዎች በመምከር ያም ሰው ጥፋቱን እንዲያርም እድል ይሰጡታል፡፡ ይህም ልዝብና የሰውን ክብር ሳይነኩ የማስተማሪያ ምርጥ ዘዴ ነው፡፡

በኃጢአትና በእኩይ ምግባር የተከበቡ ሙስሊሞችን ከገቡበት አዘቅት ለማውጣት መልካም ጠባይና ጥሩ አቀራረብን ማሳየት የአንድ ጥሩ ሙስሊም ባሕሪ ነው፡፡ አንድ ጥሩ ሙስሊም ከዚህ አልፎ ለኃጢአተኞችና በወንጀል ለተጨማለቁ ሙስሊሞች አላህ ይምራቸው

ዘንድ ዱዓ (ፀሎት) ያደርግላቸዋል። የአላህ ነብይ (ሰ.ዐ.ወ.) በዚህ ረገድ ታላቅ የሆነ ምሳሌ ትተውልን አልፈዋል። የጧኢፍ ሰዎች በድንጋይ ሲወግሯቸው አላህ እንዲቀጣቸው በመለመን ፈንታ ምህረትን ነበር የተመኙላቸው። እርሳቸውንም ሆነ ተከታዮቻቸውን ለጉዳት የዳረጉ ሕዝቦችን እንዲያጠፋላቸው አንድም ጊዜ አላህን ለምነው አያውቁም። የመካ ሰዎች ያን ያክል መከራቸውን ሲያበሏቸውና በመጨረሻም ሊገድሏቸው ሲሞክሩ እርሳቸው ግን አላህ እንዲምራቸው ይለምኑላቸው ነበር። በዚህ ልመናቸው ሰበብም ብዙ አምባገነኖችና ማን አለብኝ ባዮች ጥሩ ሙስሊም ለመሆን በቅተዋል።

﴿ وَلَا تَسۡتَوِي ٱلۡحَسَنَةُ وَلَا ٱلسَّيِّئَةُۚ ٱدۡفَعۡ بِٱلَّتِي هِيَ أَحۡسَنُ فَإِذَا ٱلَّذِي بَيۡنَكَ وَبَيۡنَهُۥ عَدَٰوَةٞ كَأَنَّهُۥ وَلِيٌّ حَمِيمٞ ٣٤ ﴾ فصلت: ٣٤

“መልካሚቱና ክፉይቱ (ጠባይ) አይስተካከሉም። በዚያች እርሷ መልካም በሆነችው ጠባይ (መጥፎይቱን) ገፍትር። ያን ጊዜ ያ በአንተና በርሱ መካከል ጠብ ያለው ሰው እርሱ ልክ እንደ አዛኝ ዘመድ ይሆናል። ” (ሐሚም አስ-ሰጅዳህ፡34)

ነብዩ (ሰ.ዐ.ወ.) ሲናገሩ “ጽድቅ ማለት መልካም ለሰራላችሁ በአፀፋው መልካም ማድረግ እንዲሁም መጥፎ ለሰራባችሁ መጥፎ ማድረግ ሳይሆን ለመጥፎ ሥራ መልካም ማድረግ ነው።” ብለዋል። (ቲርሚዚ)

በሌላ በኩል ግን አንድ መታወቅ ያለበት ጉዳይ ኃጢአተኞችን በግለሰብ ደረጃ ብቻ ነው መታገስ የሚቻለው። ሆኖም ግን ኃጢአታቸው ማህበረሰቡን የሚበክልና የቆመበትን ሥርአት የሚያፋልስ ሆኖ ሲገኝ በትእስግስት ሊታለፍ አይችልም።

በግለሰብ ደረጃ ኃጢአተኞችን በተመለከተ ግን ተደጋግሞ እንደተጠቀሰው መቻልና በመልካም ፀባይ መቅረብ ያስፈልጋል። የአላህ መልእክተኛም (ሰ.ዐ.ወ.) እንዲህ በማለት መክረዋል፡-

‹‹አግራሩ እንጅ አታጥብቁ። ብስራት ነጋሪዎች እንጅ በታኞች አትሁኑ።›› (ቡኻሪ)

ምዕራፍ አሥራ ስድስት

አላህንና መልእክተኛውን (ሰ.ዐ.ወ.) መውደድ

ፍቅር ማለት ደስታ፣ ፍስሃ፣ ሰላምና ፀጥታን በዚህች አላፊና ጠፊ ሕይወት ውስጥ ማጣጣም ማለት ነው፡፡ ፍቅር ማለት የሕልውናችን ማቆያ የሆነው ህብስት እንዲጣፍጥ የሚያደርገው እርሾ ነው፡፡ የማፍቀር ፀጋ ፈጣሪያችን አላህ ለሰው ልጆች ከሰጣቸው ፀጋዎች ሁሉ ታላቁ ነው። ለሰው ልጆችና ለሌሎች ፍጥረታት የሚኖረን ፍቅር አላህንና መልእክተኛውን ወደ ማፍቀር የሚወስደን የመጀመሪያ ደረጃ ፍቅር ነው። ሆኖም ግን እንዳለመታደል ሆኖ ብዙ ሰዎች ይህን የአምላክ ስጦታ የሆነ ፍቅር ለዝንባሌያቸውና አላፊና ጠፊ በሆነ ስሜታቸው ሲለውጡት ይታያሉ፡፡

ፍቅርን ተገቢ ላልሆነ አካል መስጠት በሕይወት ውስጥ አሳዛኙና ትልቁ ኪሣራ ነው፡፡ ርካሽ የሆኑ ዓለማዊ ፍላጐቶችን ማፍቀር በአውራ መንገድ መሃል ላይ እንደበቀለች የምታምር አበባ ይመሰላል፡፡ ይህች አበባ ዘግይታም ሆነ ፈጥና በሰዎች እግር መጨፍለቋ አይቀርምና፡፡ የከበረ ድንጋይ ወይም አልማዝ በጐዳና ላይ መውደቁ ምንኛ እድለ ቢስነት ነው! ይህ ውድ ነገርስ ከማይሆን ሰው እጅ መግባቱ ምንኛ ጥፋት ነው!

የፍቅር ሁሉ ምንጭ የሆነውን አላህን የመውደድ ፀጋ የታደለ ሰው የሌሎች ፍጡራንን ሃቅ በሚገባ ይጠብቃል፡፡ ምክንያቱም ያስገኛቸውንና የፈጠራቸውን ጌታ ፈቃድ መሙላቱ ያስደስተዋልና፡፡ በዚህ ዓይነት የአላህ ወዳጆች ልቦናቸውን ትርኪ ምርኪ ከሆኑ ነገሮች በማጽዳት ከሁሉም በላይ የአላህንና የመልእክተኛውን (ሰ.ዐ.ወ.) ፍቅር ያስገቡበታል፡፡ በሚከተለው ሐዲስ አል-ቁድስ የተጠቀሰውን ነገር እናንብብ፡፡ ከአቡ ሁረይራ (ረ.ዐ.) በተላለፈው መሠረት አላህ እንዲህ ማለቱን የአላህ መልእክተኛ (ሰ.ዐ.ወ.) ተናግረዋል፡-

“ለወዳጀ ጠላት በሆነ ሰው ላይ ጦርነት አውጀያለሁ፡፡ ለአንድ አገልጋዬ (ባሪያዬ) ወደ እኔ (ውዴታ) ለመቅረብ እኔ እንዲፈጽም ግዴታ

ያደረግሁበትን የመቅረቢያ ነገር (ኢባዳ) ከመፈፀም ይበልጥ ከእኔ ዘንድ የተወደደ ነገር የለም፡፡ ከግዴታው በኋላም ተጨማሪ (ነዋፊል) ኢባዳዎችን እያዘወተረ ሲመጣ ወደ እኔ ይበልጥ ይቀርባል፡፡ ለውዴታዬ ሲበቃም (ሸሪዓው እንዲሰማ የሚፈቅድለትን ነገር ብቻ የሚሰማበት) መስሚያ ጆሮ እሆንለታለሁ፡፡ (ሸሪዓው እንዲያይ የሚፈቅድለትን ነገር ብቻ የሚያይበት) ዓይን እሆንለታለሁ፡፡ (ሸሪዓው የሚፈቅድለትን ብቻ) የሚጨብጥበት እጅም እሆንለታለሁ፡፡ (ሸሪዓው ወደሚፈቅድለት ብቻ) የሚጓዝበት እግርም እሆንለታለሁ፡፡ ሲለምነኝ በእርግጥ እሰጠዋለሁ፡፡ (ከሚፈራው ነገር) እንድጠብቀው ሲጠይቀኝም በእርግጥ እጠብቀዋለሁ፡፡" (ቡኻሪ የዘገቡት)

እንግዲህ እዚህ መንፈሳዊ ደረጃ ላይ ለመድረስ ልክ እንደታላቅ ተራራ አናት አልፎ አልፎ ካልሆነ አይቻልም፡፡ እንዲህ ዓይነቱን ደረጃ የተቆናጠጡ ሰዎች ትክክለኛዎቹ የአላህ ወዳጆች ናቸው፡፡

ይህን አጽናፈ ዓለም በጥሞና ለሚያስተውሉ ሁሉም ፍጥረት አንደበትና የየራሱ ቋንቋ አለው፡፡ ይህንንም ማስተዋል በራሱ ታላቅ ተሰጥኦን ይጠይቃል፡፡ የምሽቱ ንፋስ ብዙ እጅግ ብዙ ነገሮችን ይነግረናል፡፡ የጧት ጤዛና ብርድስ ቢሆን ስንትና ስንት ታሪኮችንና የሕይወት ትዝታዎችን አዝሏል፡፡ እውነተኛ አማኞች በዚህች ዓለም ላይ ሲኖሩ ይህንና የመሰሉ የመለኮታዊው ትዕይንት አካል የሆኑ ነገሮችን እየመዘገቡ በልባቸውና በአእምሯቸው ማህደሮች ውስጥ ያኖራሉ፡፡

ማንኛውም ሙስሊም አላህንና መልእክተኛውን ከማንኛውም ነገር አብልጦ ማፍቀር ይጠበቅበታል፡፡ ይህንን ፍቅር በልባቸው ውስጥ ለማያሰርጹና ከዚህ ለሚያፈገፍጉ በቁርአን የተሰጠው ማስጠንቀቂያ የሚከተለው ነው፡-

﴿ قُلْ إِن كَانَ ءَابَآؤُكُمْ وَأَبْنَآؤُكُمْ وَإِخْوَٰنُكُمْ وَأَزْوَٰجُكُمْ وَعَشِيرَتُكُمْ وَأَمْوَٰلٌ ٱقْتَرَفْتُمُوهَا وَتِجَٰرَةٌ تَخْشَوْنَ كَسَادَهَا وَمَسَٰكِنُ تَرْضَوْنَهَآ أَحَبَّ إِلَيْكُم مِّنَ ٱللَّهِ وَرَسُولِهِۦ

وَجِهَادٍ فِي سَبِيلِهِۦ فَتَرَبَّصُواْ حَتَّىٰ يَأۡتِيَ ٱللَّهُ بِأَمۡرِهِۦۗ وَٱللَّهُ لَا يَهۡدِي ٱلۡقَوۡمَ ٱلۡفَٰسِقِينَ ﴿٢٤﴾ التوبة: ٢٤

"አባቶቻችሁና ወንዶች ልጆቻችሁ፣ ወንድሞቻችሁም፣ የሰበሰባችኋቸው ሃብቶችም፣ መክሰሩዋን የምትፈሩዋት ንግድም፣ የምትወዷቸው መኖሪያዎችም ከእናንተ ዘንድ ከአላህና ከመልእክተኛው፣ በርሱ መንገድም ከመታገል ይበልጥ የተወደዱ እንደሆኑ አላህ ትዕዛዙን እስከሚያመጣ ድረስ ተጠባበቁ በላቸው። አላህም አመፀኞች ሕዝቦችን አይመራም።" (አት-ተውባህ፡ 24)

አላህንና መልእክተኛውን መውደድ የሚገለፀው እነርሱን እወዳለሁ በማለት ብቻ አይደለም። ተግባራዊ እንቅስቃሴና ሙሉ መከተልን (ኢቲባዕ) ይጠይቃል። አላህም ይህንኑ በቁርአን ሲያረጋግጥ እንዲህ ይላል፡-

﴿ قُلۡ إِن كُنتُمۡ تُحِبُّونَ ٱللَّهَ فَٱتَّبِعُونِي يُحۡبِبۡكُمُ ٱللَّهُ وَيَغۡفِرۡ لَكُمۡ ذُنُوبَكُمۡۚ وَٱللَّهُ غَفُورٞ رَّحِيمٞ ﴾ آل عمران: ٣١

"በላቸው - አላህን የምትወዱ እንደሆናችሁ ተከተሉኝ። አላህ ይወዳችኋልና- ኃጢአቶቻችሁንም ይምርላችኋል። አላህም መሐሪ አዛኝ ነው።" (አሊ-ዒምራን፡ 31)

የማፍቀር ምልክቱ ለዚያ ላፈቀሩት ነገር ራስን ማስገዛትና መስዋእትነት መክፈል ነው። አላህንና መልእክተኛውን (ሰ.ዐ.ወ.) የሚወድ ሰው በልቡ ውስጥ ያለው ፍቅር ስራውን በቁርጠኛ ሐሳብ (ንያ) እና በሃቀኝነት እንዲከውን ያደርገዋል። የሰው ልጅ የሚሰራቸው ማናቸውንም የአምልኮ ተግባራት በፍቅርና እየወደደ ቢሰራቸው ጠቀሜታቸው ታላቅ ይሆንለታል። ከዚህ በተቃራኒ በልቡ ፍቅርና ውዴታ ሳይኖር እንዲሁ እየተሰላቸ የሚሰራቸው መልካም ተግባራት ጥንካሬ የሚጐድላቸው፣ ቁርጠኛ ሐሳብ (ንያ) የሚያንሳቸውና ያልተስተካከሉ ይሆናሉ።

ሌላው ይቅርና ትንሽ ብትሆን እንኳን በጥሩ ንያና በፍቅር የምትሰራ ሥራ ባልተስተካከለ ንያ ከሚሰራ እጅግ ብዛት ያለው ሥራ ትበልጣለች፡፡

አላህን የመውደድ ምልክትና ወደዚያው የሚያደርሰን መንገድ ግዴታ የተደረጉብንን የአምልኮ ተግባራት ከልብና በሙሉ ስሜት መከወን ነው፡፡ ከዚያ በኋላ ደግሞ ነዋፊል (ተጨማሪ) የሆኑ መልካም ሥራዎችን ስንፈጽም አላህ እየወደደንና ይበልጥ እያቀረበን ይመጣል፡፡

በአንድ ሰው ልብ ውስጥ የአላህ ፍቅር እየጨመረ ሲመጣ ለአላህ ብሎ የሚሰራቸው መልካም ምግባራትም እንዲሁ የሚጨምሩ መሆኑ ጥርጥር የለውም፡፡ ለዚህም ምክንያቱ በአላህ ፍቅር ልባቸው የነደደ ሰዎች ግዴታ የተደረጉባቸውን ነገሮች በመፈፀም ብቻ ስለማይረኩ ነው፡፡ ከዚያ ይልቅ በተመሳሳይ ፍላጐትና ደስተኛ ስሜት ተጨማሪ የሆኑ መልካም ምግባራትን ይፈጽማሉ፡፡ በውጤቱም ምድረበዳ የሆነ መሬት ውሃ እንደማይጠግበው ሁሉ እነርሱም በጐ ምግባራትን ሰርተው አይጠግቡም፡፡ በዚህ ሁኔታ ላይ ያሉ ሰዎችን ወደ አላህ መመለስ እንጂ ይበልጥ የሚያረካቸው ነገር የለም፡-

﴿ يَٰٓأَيَّتُهَا ٱلنَّفۡسُ ٱلۡمُطۡمَئِنَّةُ ٢٧ ٱرۡجِعِيٓ إِلَىٰ رَبِّكِ رَاضِيَةٗ مَّرۡضِيَّةٗ ٢٨ فَٱدۡخُلِي فِي عِبَٰدِي ٢٩ وَٱدۡخُلِي جَنَّتِي ٣٠ ﴾ الفجر: ٢٧ - ٣٠

"(ለአመነች ነፍስም) አንቺ የረካሽው ነፍስ ሆይ! ወዳጅ ተወዳጅ ሆነሽ ወደ ጌታሽ ተመለሽ፡፡ በባሮቼም ውስጥ ግቢ፡፡ ገነቴንም ግቢ (ትባላለች)፡፡" (አል-ፈጅር ፡27-30)

ደረጃቸው ከፍ ያለና በሁሉም ድርጊቶቻቸው አላህ እንደሚከታተላቸው የተገነዘቡ እውነተኛ ባሮቹ አጠቃላይ የሕይወት መርሃቸው በሚከተለው የቁርአን አንቀጽ ሊገለጽ ይችላል፡-

﴿ قُلۡ إِنَّ صَلَاتِي وَنُسُكِي وَمَحۡيَايَ وَمَمَاتِي لِلَّهِ رَبِّ ٱلۡعَٰلَمِينَ ١٦٢ ﴾ الأنعام: ١٦٢

“ስግደቴ፣ መገዛቴም፣ ሕይወቴም፣ ሞቴም ለአለማት ጌታ ለአላህ ነው በል፡፡” (አል-አንዓም፡ 162)

ይህ ደረጃ አል-ኢህሳን የሚሰኝ ሲሆን የዚህ ደረጃ ባለቤቶች አላህን እንደሚያዩት አድርገው ይገዙታል፡፡ ምክንያቱም እነርሱ ባያዩትም እርሱ እንደሚያያቸው ያውቃሉና፡፡ ስለዚህም ሰዎች ሳያዩዋቸው ገለልተኛ በሆነ ሥፍራ በጌታቸው ፊት ቆመው በአክብሮትና በፍቅር እየሰገዱ ያመልኩታል፡፡ ከሌሊቱም ክፍል ግማሹን ወይም የበለጠውን በዚህ ዓይነት ሁኔታ ያሳልፋሉ፡፡ አላህ እንዲህ ይላል፡-

﴿ وَٱلَّذِينَ يَبِيتُونَ لِرَبِّهِمْ سُجَّدًا وَقِيَٰمًا ﴿٦٤﴾ ﴾ الفرقان: ٦٤

“እነዚያም ለጌታቸው በግንባራቸው ተደፊዎችና ቋሚዎች ሆነው የሚያድሩት ናቸው፡፡” (አል-ፉርቃን፡ 64)

﴿ تَتَجَافَىٰ جُنُوبُهُمْ عَنِ ٱلْمَضَاجِعِ يَدْعُونَ رَبَّهُمْ خَوْفًا وَطَمَعًا وَمِمَّا رَزَقْنَٰهُمْ يُنفِقُونَ ﴿١٦﴾ ﴾ السجدة: ١٦

“ጌታቸውን ለመፍራትና ለመከጀል የሚጠሩት ሲሆኑ፣ ጐኖቻቸው ከመጋደሚያ ሥፍራዎች ይራራቃሉ፡፡ ከሰጠናቸውም (ፀጋ) ይለግሳሉ፡፡” (አስ-ሰጅዳህ፡16)

የሚከተለው አጋጣሚ በአማር ኢብኑ ያሲር (ረ.ዐ.) ሕይወት ዙሪያ የሚያጠነጥን ሲሆን ይህ ክቡር የሆነ የነብዩ (ሰ.ዐ.ወ.) ባልደረባ በአንድ ወቅት በኤፍራጥስ ወንዝ (ኢራቅ) ዳርቻ ላይ (ወደ ጦርነት ከመግባቱ በፊት) እየተራመደ የተናገረው እንደሚከተለው ቀርቧል፡-

“ጌታዬ ሆይ! ከታላቅ ተራራ አናት ላይ ተንከባልዬ መሞቴን የምትወድልኝ መሆኑን ባውቅ ኖሮ አሁኑኑ አደርገው ነበር፡፡ ራሴን በእሳት አቃጥዬ ማለፌ ይበልጥ የሚያስደስትህ መሆኑን ባውቅ ኖሮም ጊዜ ሳላጠፋ አደርገው ነበር፡፡ ጌታዬ ሆይ! ራሴን ወደ ባህር ውስጥ በመወርወር ሰጥሜ መሞቴ የአንተን ውዴታ የሚያስገኝልኝ መሆኑን

ባውቅ ሳላመነታ እፈጽመው ነበር፡፡ ጌታዬ ሆይ! እነሆ እኔ የአንተን ውዴታ ብቻ ፈልጌ ወደ ውጊያ ልገባ ነው፡፡ ይህንን ምኞቴን እንዳጣ አታድርገኝ፡፡ ውዴታህንም እንደማገኝ ተስፋ አለኝ፡፡" (ጦበቃት ኢብን ሰዓድ)

አላህንና መልእክተኛውን (ሰ.ዐ.ወ.) ከምንም ነገር በላይ መውደድ የኃይማኖታችን ዋነኛ ፍሬ ነገር፣ እንዲሁም ብሩክ የሆነው ወደ አላህ የሚያስጠጋን መንገድ ነው፡፡ ይሁን እንጂ መውደድ ማለት በልብ ውስጥ የሌለውንና በሥራ የማይገለፀውን ነገር በአፍ ብቻ ማውራት አይደለም፡፡

የነብዩ (ሰ.ዐ.ወ.) ባልደረባዎች የነበሩት ሶሃባዎች እውነተኛ የሆነውን አላህንና መልእክተኛውን (ሰ.ዐ.ወ.) የመውደድ ምስጢር በሚገባ ተገንዝበውት ነበር፡፡ በዚህም የተነሣ በእለታዊ አኗኗራቸው ይህን ታላቅ የሆነ ነገር ሲያንፀባርቁት ይታዩ ነበር፡፡ ከዚህ በታች የተወሰኑትን ለአብነት ያክል እንዳስሳለን፡-

በመዲና ዙሪያ ነዋሪ የነበሩ የተወሰኑ ጐሣዎችን ያስተምሩ ዘንድ ነብዩ (ሰ.ዐ.ወ.) የተወሰኑ አስተማሪዎችን ላኩ፡፡ አድልና ቃራ የተባሉት ጐሣዎች ከእነዚያ ጐሣዎች ውስጥ ይገኙ የነበረ ሲሆን ኃይማኖታቸውን እንዲያስተምሯቸው በመፈለግ መምህራን እንዲላኩላቸው ጠይቀው ነበር፡፡ ከዚያም የተወሰኑ መምህራን ወደዚያው አመሩ፡፡ ሆኖም ግን እነዚያ ጐሣዎች ከሃዲያን ስለነበሩ አስተማሪዎቹን መንገድ ላይ አድፍጠው በመጠበቅ ስምንቱን ገደሏቸው፡፡ የሁሉንም ሥራ ይውደድላቸውና - ተማርከው ወደ መካ ከተወሰዱ በኋላ ለመካ ከሃዲያን ተላልፈው ተሰጡ፡፡ የመካ ከሃዲያንም ሁለቱንም ወደ ሚገደሉበት ቦታ ከወሰዷቸው በኋላ በመጀመሪያ ዘይድን እንዲህ በማለት ጠየቁት፡- "በአንተ ቦታ ሙሐመድ ቢሆንና አንተ ነፍስህን ብታተርፍ ይህን ትቀበላለህን?" ዘይድ ይህን ጥያቄ ያቀረበለትን አቡ ሱፍያንን በሃዘኔታ ካስተዋለው በኋላ እንዲህ አለ፡- "ፈጽሞ፤ እንኳን በዚህ ቦታ ላይ እንዲሆኑ ይቅርና እኔ ከቤተሰቤና ከልጆቼ ጋር ሆኜ እርሳቸውን እሾህ እንዲወጋቸው አልፈልግም፡፡"

በዚያ አምሳያ የሌለው ፍቅር አቡ ሱፍያን ተደነቀ፡፡ እንዲህም አለ፡- “በጣም ይደንቃል! የሙሐመድን ተከታዮች እርሱን የሚወዱትን ያክል ሰዎች ሌላን ሰው ሲወዱ አላየሁም፡፡”

ከሃዲያኑ ወደ ሁበይብ (ረ.ዐ.) በመሄድም ከያዘው ኃይማኖት የሚመለስ ከሆነ ከመገደል እንደሚድን ነገሩት፡፡ እርሱም እንዲህ በማለት መልስ ሰጣቸው፡- “መላውን ዓለም ብትሰጡኝ እንኳን ኃይማኖቴን አልለቅም፡፡” ሁበይብ ሸሂድ (ሰማእት) ሆኖ ከመሞቱ በፊት አንድ ምኞት ነበረው፡፡ ይኸውም ለአላህ መልእክተኛው (ሰ.ዐ.ወ.) ሰላምታውን ማድረስ ነበር፡፡

ታዲያ ይህንን ሰላምታውን ማን ያደርስለት ይሆን? አቅመ- ቢስ መሆኑን በማመን ወደ ሰማይ አይኖቹን አቅንቶ ጌታውን እንዲህ በማለት ከልቡ ተማፀነ... ”ጌታዬ ሆይ! እዚህ ካሉት ሰዎች ውስጥ ይህን ሰላምታዬን ለመልእክተኛህ የሚያደርስልኝ አይገኝም፡፡ ሰላምታዬን አንተ አድርስልኝ፡፡”

እዚህ ላይ ነው እንግዲህ አስደናቂው ነገር የተከሰተው፡፡ የአላህ መልእክተኛ (ሰ.ዐ.ወ.) በመዲና ከባልደረቦቻቸው ጋር ሆነው “ወአለይሂ- ሰላም” የሚለውን መልሳቸውን የሰጡት፡፡ ይህን የሰሙት ባልደረቦቻቸው በሁኔታው በመገረም እንዲህ በማለት ጠየቁቸው፡- “የአላህ መልእክተኛ ሆይ! የማንን ሰላምታ ነበር አፀፋውን የመለሱት?” እርሳቸውም እንዲህ አሉ “የወንድማችሁን የሁበይብን ሰላምታ፡፡”

ሁለቱን ምርኮኞች የመካ ከሃዲያን ብዙ ካሰቃዩአቸው በኋላ ገደሏቸው፡፡ የታላቁ ሶሃባ የሁበይብ የመጨረሻ ቃል እንዲህ የሚል ነበር፡- “ሙስሊም ሰማእት (ሸሂድ) ሆኜ እስከተገደልኩ ድረስ በየትኛውም ዓይነት አኳኋን ብሞት ግድ የለኝም፡፡” (ቡኻሪ)

በተመሳሳይ ሁኔታ ለአላህ መልእክተኛ (ሰ.ዐ.ወ.) በነበራቸው ጥልቅ ፍቅር የተነሳ ብዙ ወጣቶች እርሳቸውን የሚያስደስቱ ተግባራት በየጊዜው ለመፈጸም ይረባረቡ ነበር፡፡ ከእነዚህ ወጣቶች ጥቂቶቹ ነብዩ (ሰ.ዐ.ወ.) ለተለያዩ ነገሥታትና የሃገር መሪዎች የጻፏቸውን ደብዳቤዎች

ለማድረስ ተራራ ዞረው፣ ሸለቆና ምድረበዳ አቋርጠው፣ ባህር ተሻግረው ሄደዋል፡፡ ከዚያም በአምባገነን ነገሥታት ፊት በነፍሰ ገዳዮች ተከበው በታላቅ ወኔ የደብዳቤውን ፍሬ ሐሳብ አንብበዋል፡፡

የነብዩ (ሰ.ዐ.ወ.) ባልደረቦች ለእርሳቸው ከነበራቸው ፍቅርና አክብሮት የተነሳ መልካቸውና አቋማቸው ምን ዳንደሚመስል እንዲያብራሩ ሲጠየቁ መልስ ለመስጠት ይቸገሩ ነበር፡፡

ኻሊድ ኢብን አል-ወሊድ (ረ.ዐ.) በአንድ ሙስሊም ጦሣ መኖሪያ አጠገብ ያልፍ ነበር፡፡ የጦሣው መሪ የነቢዩን ክብርና አጠቃላይ ሁኔታ እንዲገልጽለት ኻሊድን (ረ.ዐ.) ጠየቀው፡፡ ኻሊድ (ረ.ዐ.) ሲመልስ እንዲህ አለ፡- “እኔ በእውነቱ የእርሳቸውን ሁኔታ መግለጽ አልችልም፡፡” የጦሣው መሪ ጥያቄውን ገፋበት፡- “እባክህ የምታውቀውን ያክል አብራራልኝ፡፡” ኻሊድ (ረ.ዐ.) እንዲህ አለ፡- “ልነግርህ የምችለው ነገር የአላህ መልእክተኛ ደረጃ ከፍተኛነት በላካቸው አካል ከፍተኛነት የሚለካ መሆኑን ነው፡፡ እርሳቸውን የላካቸው የአጽናፈ ዓለሙ ፈጣሪ ነው፡፡ ስለዚህ የእርሳቸውን ደረጃ በዚህ መገመት ትችላለህ !”

ሌላው ታላቅ ሶሃባ አምር ኢብን አል-አስ (ረ.ዐ.) ተመሳሳይ ጥያቄ ቀርቦለት እንደሚከተለው በማለት መልሷል፡-

“እኔ ለእርሳቸዉ ካለኝ ክብር የተነሣ ቀና ብዬ በሙሉ ዓይኔ ተመልክቻቸው አላውቅም፡፡ ስለሆነም ስለእርሳቸው ሁኔታ ልገልጽልህ አልችልም፡፡”

የነብዩ (ሰ.ዐ.ወ.) ተከታዮች ለእርሳቸው የነበራቸውን ታላቅ ፍቅርና አክብሮት ከሚገልጹባቸው መንገዶች ዋነኛው እርሳቸው ያዘዙትን መፈጸምና የከለከሉትንም መከልከል ነው፡፡ ከዚህ ቀጥሎ የሚቀርበውና ከአቡ አብዱራህማን አል ጁበሊ የተወራው ገጠመኝ ለዚህ አባባል እንደማሳያ ሆኖ ሊያገለግል ይችላል፡-

“ከቤዛንታይን ወታደሮች ጋር በነበረን ጦርነት ከአቡ አዩብ አል-አንሷሪ (ረ.ዐ.) ጋር በመሆን በመርከብ እንጓዝ ነበር፡፡ መሪያችን አብደላህ ኢብን

ቀይስ ነበር፡፡ አቡ አዩብ አል-አንሷሪ (ረ.ዐ.) ምርኮ የማከፋፈል ኃላፊነት ወደተሰጠው ሰው ሲመጡ አንድ የምታለቅስ ሴት ተመለከቱ፡፡ ሴትዮዋ በጦርነቱ ጊዜ የተማረከች ነበረች፡፡ አቡ አዩብ (ረ.ዐ.) ሴትዮዋ ለምን እንደምታለቅስ ሲጠይቁ፣ ልጅ እንደነበራትና ልጅዋን ለይተው ለሌላ ሰው ድርሻ በማድረግ ስለሰጡባት መሆኑ ተነገራቸው፡፡

አቡ አዩብ (ረ.ዐ.) ወዲያው ልጁን ፈልገው በማግኘት ለእናቱ መለሱላት፡፡ ከዚያ በኂላ እናቱ ማልቀሷን አቆመች፡፡ የምርኮ ክፍፍሉን ኃላፊነት የወሰደው ሰው በዚህ ጊዜ ወደ ጦሩ መሪ ወደ አብደላህ ኢብን ቀይስ (ረ.ዐ.) በመሄድ አቡ አዩብ (ረ.ዐ.) ያደረጉትን ነገር ነገረው፡፡ አብደላህ፣ ለምን እንደዚያ እንዳደረጉ እንዲያስረዱት አቡ አዩብን ሲጠይቃቸው እንዲህ አሉ፡- “የአላህ መልእክተኛ (ሰ.ዐ.ወ.) እናትና ልጅን የሚለያዩ ሰዎች አላህ በፍርዱ ቀን ከሚወዷቸው ሁሉ ይለያያቸዋል፤ በማለት ሲናገሩ ሰምቻለሁ፡፡” (ሙስነድ አህመድ፣ቲርሚዚ)

ከዚህ ቀጥሎ ያለው ትረካ ደግሞ የሚገልጽልን ለሰዎች እዝነትንና ፍቅርን ማሳየት የሚያስገኘውን ጥቅም ነው፡፡

ነብዩ (ሰ.ዐ.ወ.) በሕይወት በነበሩባቸው የደስታ ዘመናት (አስር አስ-ሰዓዳህ) ሐኪም ኢብን ሂዛም የሚባል ሰው ነበር፡፡ ይህ ሰው የእመት ኸዲጃ (ረ.ዐ.) የቅርብ ዘመድ ነበር፡፡ ሐኪም በጣም ለጋስ፣ ሩህሩህና ደግ ነበር፡፡ በዚህ ፀባዩም በዘመነ ጃሂሊያ አረቦች ሴት ልጆች እንዲኖራቸው ስለማይፈልጉ ሊገድሏቸው ያሰቧቸውን ልጆች በገንዘቡ እየገዛ ከሞት ያተርፋቸው ነበር፡፡ ኢስላምን ከተቀበለ በኂላ በቀድሞ ጊዜ ይሰራቸው የነበሩ ይህን የመሰሉ መልካም ሥራዎቹ አሁን ይጠቅሙት እንደሆነ ለማወቅ ነብዩን (ሰ.ዐ.ወ.) ጠየቃቸው፡፡ እርሳቸውም፡፡ በእነዚያ መልካም ሥራዎቹ ምክንያት ኢስላምን ሊቀበል እንደበቃ ገለጹለት፡፡

---------- ተፈጸመ ------